ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

የግብርና ዘርፍ የ5 ዓመት የልማት ዕቅድ

□□□ **2012**

□□□□ □□□□□

ይዘት

ክፍል I: የዘርፉ ስትራቴጅክ ሁኔታዎች 1

1.1 መግቢያ 1

1.2 ዘርፉ ያለበት ሁኔታ 1

1.3 የእቅዱ መነሻዎች 11

1.4 ስትራቴጅክ አቅጣጫዎች 11

1.5 የዕቅድ ዝግጅት አካሄድ 13

ክፍል II የዕቅዱ ዓላማዎች 13

2.1 ስትራቴጅክ ዓላማ I፡ ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ 14

2.1.1. የአነስተኛ ይዞታ ያደገ የተሻሻሉ የሰብል ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች አጠቃቀም 15

2.1.1.1 በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የሰብል ቴክኖሎጅ ማቅረብ 15

2.1.1.2 በሰብል ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር 18

2.1.1.3 የሰብል ጥበቃ 22

2.1.1.4 የተሻሻለ የሰብል ግብዓት አቅርቦት 23

2.1.1.5 የሰብል ግብዓት ጥራትና ቁጥጥር 32

2.1.2 የተስፋፋ የመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት ሰብል ልማት 41

2.1.2.1 ያደገ የመካከለኛ እና ሰፋፊ ሰብል ልማት ኢንቨስትመንት 41

2.1.2.2 ውጤታማ የመካከለኛ እና ሰፋፊ ሰብል ልማት ኢንቨስትመንት 42

2.1.3 ሰብል ምርት ግብይት 46

2.1.4 የሰብል ምርቶች ጥራትና ደህንነት 51

2.2 ስትራቴጅክ ዓላማ II ፡ ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት 51

2.2.1 ያደገ የተሸሻሉ የአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር እንስሳትና ዓሳ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች አጠቃቀም 54

2.2.1.1 በእንስሳትና ዓሳ ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር 55

2.2.1.2 እንስሳትና ዓሳ ሀብት ዝርያ ማሻሻል 59

2.2.1.3 የእንስሳትና ዓሳ መኖ ልማት 60

2.2.1.4 የእንስሳትና ዓሳ ጤና አገልግሎት 63
2.2.1.5 የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ቴክኖሎጂ አቅርቦት 69
2.2.1.6 የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ግብዓት አቅርቦት ስርዓት 71
2.2.1.7 የእንስሳትና ዓሳ ግብዓት ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ 74
2.2.2 የተስፋፋ የባለሀብት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት 76
2.2.2.1 ያደገ የግል ባለሀብት የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ኢንቨስትመንት 76
2.2.2.2 ውጤታማ የባለሀብት እንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት 78
2.2.3 የእንስሳትና ዓሳ ምርት ግብይት 79
2.2.4 የእንስሳትና ዓሳ ምርት ጥራትና ደህንነት 85
ስትራቴጂክ ዓላማ III፡ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም 89
3.1 የተሻሻሉ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች አጠቃቀም 90
3.1.1 ዘላቂ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት 90
3.1.2 በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት የቴክኖሎጂ አቅርቦት 95
3.1.3 በተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ አሠራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/አርብቶ አደር 97
3.3.1.4 የተሻሻለ የተፈጥሮ ሀብት ግብዓት አቅርቦት 105
3.2 ያደገ የመስኖ ሽፋንና አጠቃቀም 106
3.2.1 የተስፋፋ የመስኖ መሰረተ ልማት 106
3.2.2 የተሻሻለ የመስኖ አውታር አስተዳደርና ውሀ አጠቃቀም 107
3.3 የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ማስፈፀሚያ ስልቶች 108
ክፍል III፡ ቁልፍ የስኬት መስኮች 111
3.1 የግብርና ኤክስቴንሽን 111
3.2 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና 115
3.3 የግብርና ምርምር 119
3.4 የግብርና ሜካናይዜሽ አገልግሎት 122
3.5 የህብረት ስራ ማህበራት 127
ክፍል IV፡ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች 131
4.1 ምግብ ዋትስና 131
4.2 ስርዓተ ምግብ ዋስትና 133
4.3 ስርዓተ ፆታ 134
4.4 አካባቢና አየር ንብረት ለውጥ 134
4.5 ስራ ዕድል ፈጠራ 135
ክፍል V: የማስፈፀሚያ ስልቶች 139

5..1 ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን 140
5.2. የግብርና ልማትን ዲጅታላይዝ ማድረግ 140
5.3. የፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች 140
5.4 የገጠር ከተማ ትስስር 140
5.5 የክትትልና ግምገማ ስርዓት 141
ክፍል VI: የሰው ኃይልና የፋይናንስ ፍላጎት 142
6.1 የሰው ኃይል ፍላጎት 142
6.2 የፋይናስ ፍላጎት 142
7.2 አባሪ2፡ የሰው ኃይል ፍላጎት 149
7.3 ፡ የፋይናንስ ፍላጎት 150
ክፍል ሰባት፡ አባሪ
7.1 የውጤት ማዕቀፍ
7.2 የሰው ኃይል ፍላጎት
7.3 የፋይናንስ ፍላጎት
7.4 ከ 30 ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር በላይ በጀት ያላቸው የግብርና ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች
7.5 ከሌሎች ዘርፎች/ተቋማት እንዲቀርቡ የሚጠበቁ ግብዓቶች

ክፍል I: የዘርፉ ስትራቴጅክ ሁኔታዎች

1.1 መግቢያ

የግብርና ዘርፍ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ዘርፍ መሆኑ ይታወቃል። ዘርፉ የሚጠበቅበትን ውጤት ለማሳካት የተነደፉ ሀገራዊ ፖሊስዎችና ስትራቴጂዎች በየአምስት ዓመቱ ተከታታይ የልማት ፕሮግራሞችን እየነደፈ ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። የዚሁ አካልና ከዕድገት ባሻገር ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ ታቅዶ ሲተገበር የቆየው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ሁለት የዚሁ መገለጫ ነው። ዕቅዱ በተተገበረው ልክ ዉጤት ያረጋገጠ፣ በርካታ ልምዶች የተገኙበትና በዚሁ ላይ በመመስረት ትራንስፎርሜሽን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቀጣይ ሥራ መስራት እንደሚጠይቅ ግንዛቤ የተያዘበትም ነው። በመሆኑም በሁለተኛው የዕትዕ ትግበራ በተገኙ ውጤቶች ላይ በመመስረትና ሀገር በቀል የኢኮኖሚክ ፖሊሲ ማሻሻያንና እንዲሁም የግብርና ዘርፍ ማሻሻያ (ሪፎርም) እርምጃዎች መሰረት በማድረግ የግብርና ዘርፍ የ5 ዓመት መሪ ዕቅድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። መሪ ዕቅዱም ዓላማዎች፣ በየዓላማው ዒላማዎች፣ ዒላማዎችን ለማሳካት ለማሳካት ሊፈፀሙ የሚገባቸው ተግባራት፣ ለዕቅዱ ማስፈፀሚያ የሚያስፈልገውን የኢንቨስትመንት መጠን፣ የሰው ኃይል፣ የማስፈፀሚያ ስልቶችንና ከሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የግብርና ዘርፍ የሚፈልጋቸው ግብዓቶችን በዝርዝር እንዲያካትት ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

1.2 ዘርፉ ያለበት ሁኔታ

የግብርና ሴክስተር ለአጠቃላይ አገራዊ ልማት ያደረገው አስተዋፅኦ

በሁለተኛው የአድገትና ትራንስፎርሜሽን አመታት ዋናዎቹ ግቦቻችን የነበሩት ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን ማረጋገጥ፣ መዋቅራዊ ሽግግር ማምጣት እንዲሁም በየደረጃው ከሚኖረው ልማት የህዝቡን የላቀ ደረጃ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ነበር። ፈጣን እድገት ከማረጋገጥ አንፃር የአገራችን ኢኮኖሚ ባለፉት 5 ዓመታት በአመት በአማካይ 8.7 በመቶ ያደገ ሲሆን ለዚህም የግብርና ዘርፍ አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ ይታወሳል። የግብርናውን ዘርፍ ስንመለከት ደግሞ ዋና ዋና ግቦች የነበሩት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን ማረጋገጥ፣ በዘርፉ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው እድገት ማምጣት፣ የህዝቡን ተጠቃሚነት በየደረጃው ማረጋገጥ፣ በአጠቃላይ ኢኮኖሚ በዘርፍ ደረጃ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲመጣ ማስቻል የሚሉት ነበሩ።

የግብርና ዘርፍ ባለፉት ዓመታት በአማካይ በዓመት 4.1 በመቶ አድገት አስመዝግቧል (ምስል 1) ። ይህም አፈፃፀም በእቅድ ከታየዘው 8 በመቶ ጋር ሲነፃፀር አጥጋቢ አይደለም። የሰብል ዘርፍን እድገት ስንመለከት አማካይ አመታዊ አፈፃፀም 5.3 በመቶ፣ የእንስሳት ዘርፍ ደግሞ 3.5 በመቶ ደርሷል። ለዚህም አነስተኛ አፈፃፀም ሲተነትን የአየር ንብረት ለውጥ ያስከተለው ተጽዕኖ፣ የሰው ሀይል የማሰፈጸም አቅም፤ የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲሁም የኢንቨስትመንት ውስንነትና በሀገር ደረጃ የነበረው የፖለቲካ አለመረጋጋትም እንደሆነ ይታወቃል። ይህም የግብርና እድገት የህዝቡን ተጠቃሚነት እያረጋገጠ የመጣ ሲሆን ባለፉት አመታት በዘርፉ የተመዘገበው እድገት የገጠር የድህነት ምጣኔ በ1998 ዓ.ም ከነበረበት 39.3 በመቶ በ2008 ዓም ወደ 25.6 በመቶ በመቀነስ የተሻለ ኑሮ ሁኔታ እና ድህነትን በማጥፋትና ማህበራዊ ዋስትናዎችን ለማረጋገጥ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል። እንዲሁም የብሄራዊ የድህነት ምጣኔ በ1998 ከነበረበት 38.7 በመቶ በ2008 ወደ 23.5 በመቶ ዝቅ ብሏል። ይሁን እንጂ ዘርፉ በሚፈለገው ባለማደጉ ለሃገራችን በቂ ምግብ ማቅረብ ተስኖት አስከ 25 ሚሊዮን ያህል ዜጎች በቂ ምግብ ማግኘት ያልቻሉበትና ከነዚሁም 18 ሚሊዮን የማያንሱ በእለት ደራሽ እርዳታና በልማታዊ ሴፍቲኔት ታቅፈው ይገኛሉ።

ግብርና ከአጠቃላይ ኢኮኖሚ ያለው ድርሻ 2004 በጀት ዓመት ከነበረበት 43 በመቶ በ2011 ወደ 33 በመቶ እና የአግልግሎት ዘርፉም ከ45.5 በመቶ ወደ 39.1 በመቶ ዝቅ ያለበት በአንፃሩ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ ከ11.5 በመቶ ወደ 26 በመቶ ከፍ ያለበት ሁኔታ ታይቷል (ምስል 1)። በአጠቃላይ ኢኮኖሚ ውስጥ የተመዘገበው የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር አዝጋሚ ቢሆንም የግብርናው ዘርፍ አስተዋፅዖ ከፍተኛ ነበር። ሆኖም ግን የዘርፉ የሰው ሃይል ምርታማነት እድገት እንዲሁም የምርቶች

ምርታማነት ወደ ከፍተኛ ምርታማነት ወዳላቸው ምርቶች የመሸጋገር ሂደቱ ደካማ በመሆኑ አሁንም የዘርፉን መዋቅራዊ ለውጥ (ግብርና ትራንስፎርሜሽን) ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ይጠይቃል።

ምስል 1 የግብርና ዘርፍ አጠቃላይ ምርት ድርሻና የእድገት ምጣኔ





የግብርና ዘርፍ አስተዋፅኦ የታየበት መስክ የውጪ ምንዛሬ ግኝት ነው። ባለፉት 5 ዓመታት ከአጠቃላይ የወጪ ምንዛሬ ግኝት 80 በመቶ የሚሆነው የተገኘው በግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ነው። ይህ የሚያሳየው የወጪ ንግድ አሁንም ድረስ በግብርና ምርቶች ላይ የተመሰረት ነው። ማለትም በ2012 የግብርና ኤክስፖርት ከጠቅላላ ኤክስፖርት 57 በመቶ እንዲደርስ የታቀደ ቢሆንም አፈፃፀሙ በሌሎች ዘርፎች የውጪ ንግድ እድገት አለመኖር የተነሳ በግብርናው ላይ የተንጠለጠለ መሆኑ ያሳያል። የግብርና ምርቶች የወጪ ንግድ ገቢ የግብርና ምርቶች የውጪ ንግድ እንዲሻሻል ምርታማነትን የሚጨምሩ፣ ጥራትን የሚያሻሽሉ፣ የግብይት ሰንሰለትን የሚያቀላጥፉ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል። በተጨማሪም ህብረት ስራ ማህበራት የእሴት ጭመራና የውጪ ገበያ ተሳትፎአቸውን ለማሳደግ የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የመሬት አቅርቦትና ሌሎች አገልግሎቶች ድጋፍ ሲደረግላቸው ቆይቷል።

ለገጠሩ ህብረተሰብ የሚፈጠር የስራ እድል በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 1 ሚሊዮን በእቅዱ ዘመን መጨረሻ 4.32 ሚሊዮን ለማድረስ ታቅዶ 6.5 ሚሊዮን ማድረስ ተችሏል። በከተማ አከባቢዎችም ወጣቱን ወደ ግብርና ዘርፍ በመሳብ የስራ እድል ከመፍጠር በተጨማሪ ለከተሞች በቂ የግብርና ምርት ለማቅረብ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል። ወጣቱን ወደ ግብርና ዘርፍ ለመሳብና ተሳትፎ እየጨመረ እንዲሄድ ለማድረግ የግብርና ማዘመን ስራዎች ከፍተኛ ድርሻ ይኖራቸዋል። ይህንንም በመረዳት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በእሴት ጭመራ እንዲሁም በግብይት ሰንሰለት ልማት ላይ ሰፋፊ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ የግብርና ልማትን ከማምጣት አንፃር የተለዩ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ ቴክኖጂዎችን በመደበኛ የልማት እቅድ ውስጥ በማካተት እንዲተገበሩ ተደርጓል። በአጠቃላይ በዕ.ት.እ 2 መጨራሻ ከተቋሙ 78.1 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ተቅዶ 36.8 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለማግለል/ለመቀነስ የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ አፈፃጸሙ 47.1 በመቶ ነው። አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት አመራሩ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስራዎች በቂ ትኩረት ያለመስጠትና በየደረጃው ያሉ ሙያተኞች እውቀት ውስንነት ነዉ

የዘርፎች አፈፃፀም ዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች የሰብልና የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም መጨመር፣ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ማስፋፋት፣ የግብይት ስርዓትን ማሻሻል፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ መጨመርና የመስኖ ልማትን ማስፋት ዋና ዋና ትግባሮች ናቸው

የዘርፎች አፈፃፀም ዘርፉ የትኩረት አቅጣጫዎች የሰብልና የእንስሳት ምርትና ምርታማነት ማሳደግ፣ የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አጠቃቀም መጨመር፣ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ማስፋፋት፣ የግብይት ስርዓትን ማሻሻል፣ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ መጨመርና የመስኖ ልማትን ማስፋት ዋና ዋና ተግባሮች ናቸው።

የሰብል ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል

በዕትዕ መጨረሻ በ2011/12 የመኸር ምርት ዘመን የአነስተኛ ይዞታ እርሻ 335 ሚ/ን ኩ/ል የእህል ሰብሎች ምርት ተገኝቷል። ይህም ከእቅዳችን አንፃር 80 በመቶ እንደደረስን ያሳያል። ይህም በዕትዕ መነሻ ዓመት የ2007 ምርት ዘመን ከነበረው 270 ሚሊዮን ኩንታል ምርት በየአመቱ በአማካይ በ5 በመቶ የምርት ዕድገት አሳይቷል። ዋና ዋና የእህል ሰብሎች አገዳና ብርዕ፣ ጥራጥሬና ቅባት እህሎች ናቸው። በአገዳና ብርዕ ሰብል አጠቃላይ ምርቱን በመነሻዉ ዓመት (2006/7) ከነበረበት 236 ሚሊየን ኩ/ል በ2011/12 ወደ 297 ሚሊየን ኩ/ል፣ በጥራጥሬ ሰብል 26.7 ሚሊየን ኩ/ል ወደ 30 ሚሊየን ኩ/ል፤ ቅባት ሰብል 7.6 ሚሊየን ኩ/ል ወደ 8.4 ሚሊየን ኩ/ል እንደደረሰ ያሳያል። ይህም ምርት እድገት የተመዘገበው በአብዛኛው በአገዳና ብርዕ ሰብሎች ምርታማነት ጭማሪ ሲሆን ለመሳያነትም የስንዴ ምርታማነት 30 ኩንታል የደረሰ ሲሆን ከባለፉት 5 ዓመታት የ17 በመቶ ፣ የበቆሎ ምርታማነት 42.4 ኩንታል የደረሰ ሲሆን የ24 በመቶ እንዲሁም የጤፍ ምርታማነት 18.5 ኩንታል የደረሰ ሲሆን የ17.5 በመቶ እድገት ታይቷል።

የእንስሳት ምርትና ምርታማነት

በዕትዕ መጨረሻ በ2012 አመታዊ የወተት ምርት 6.6 ቢሊየን ሊትር የደረሰ ሲሆን ይህም ከመነሻ ዓመት (2007) ከነበረው 5.3 ቢሊየን ሊትር ወተት ምርት የ25 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። የሥጋ ምርት 1.7 ሚሊየን ቶን የደረሰ ሲሆን በ2007 ከተመረተው 1.2 ሚሊየን ቶን ጋር ሲነፃፀር 42 በመቶ እድገት አሳይቷል። የእንቁላል ምርት 1.85 ቢሊየን የደረሰ ሲሆን በ2007 ከተመረተው 0.16 ቢሊየን ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ እድገት አሳይቷል። የዶሮ ሥጋ ምርት አቅርቦት 63 ሺህ ቶን የደረሰ ሲሆን በ2007 ዓ.ም ከተመረተው 49 ሺህ ቶን ጋር ሲነፃፀር 29በመቶ እድገት አሳይቷል። የቆዳና ሌጦ ምርትን 23 የደረሰ ሲሆን በ2007 ከተመረተው 22.4 ሚሊየን ጋር ሲነፃፀር መጠነኛ እድገት አሳይቷል፡ ፡ የማር ምርትን 110 ሺህ ቶን የደረሰ ሲሆን በ2007 ከተመረተው 60.7 ሺህ ቶን ጋር ሲነፃፀር የ80 በመቶ እድገት አሳይቷል። የዓሳ ምርትን 55 ሺህ ቶን የደረሰ ሲሆን በ2007 ከተመረተው 50.1 ሺህ ቶን ጋር ሲነፃፀር የ10 በመቶ እድገት አሳይቷል።

የወተት ምርታማነትን በተመለከተ ከአንድ ሀገር በቀል እንስሳት ዝርያ የአካባቢ ዝርያ የወተት ላም የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት 2.6 ሊትር የደረሰ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 1.51 ምርታመነት ጋር ሲነፃፀር 72 በመቶ እድገት አሳይቷል። ከአንድ ዲቃላ የወተት ላም የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት 12 ሊትር የደረሰ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 8 ሊትር በቀን ምርታመነት ጋር ሲነፃፀር 50 በመቶ እድገት አሳይቷል። ከአንድ ግመል የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት 5.4 ሊትር የደረሰ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 3.75 ምርታመነት ጋር ሲነፃፀር 12 በመቶ አድጓል። ከአንድ የወተት ፍየል የሚገኝ አማካይ የቀን የወተት ምርት 0.4 ሊትር የደረሰ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 0.3 ሊትር ጋር ሲነፃፀር 33 በመቶ አድጓል። የስጋ ምርታማነትን ከአንድ ዳልጋ ከብት የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት (carcas weight) 110 ኪሎ ግራም የደረሰ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 107 ኪሎ ግራም ጋር ሲነፃፀር 3 በመቶ እድገት አሳይቷል። ከአንድ በግ የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት 11 ኪሎ ግራም የደረሰ ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 9 ኪሎ ግራም ጋር ሲነፃፀር 2 በመቶ እድገት አሳይቷል። ከአንድ ፍየል የሚገኝ አማካይ የሥጋ ክብደት 8 ኪሎ ግራም ሲሆን ከ2007 ዓ.ም ከነበረው 8 ኪሎ ግራም ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ያሳያል።

የእንስሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት አፈፃፀም ግምገማ የግብርና ሚኒስቴር አስተዳደራዊ መረጃ መሰረት ያደረገ ሲሆን በተመረጡ የምርት አይነቶች የ10 አመቱ መሪ እቅድ መነሻ የተወሰደው ከማዕከላዊ ስታስቲስቲክስ ባለስልጣን የ2012 አመታዊ መረጃ ምንጭ መሰረት በማድረግ ነው። በመሆኑም ወተት ፣ ቀይ ስጋ፣ እንቁላል፣ የዶሮ ስጋ እና ማር ምርት መነሻ የተወሰደው የ2012 የተደረሰብት አስተዳደራዊ መረጃ እንዳልሆነ መረዳቱ እንዲኖር ያስፈልጋል።

የተፈጥሮ ሃብት ልማት

የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በዕትዕ መጨረሻ 97,240 የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት የተካሄደ ሲሆን ይህም ከመነሻ ዓመት (2007) መጨረሻ ላይ ከተደረሰበት 60,460 አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር የ61 በመቶ እድገት አሳይቷል። ተከልሎ እንዲያገግም የተደረገ መሬት ሽፋን በ2007 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 12 ሚሊዮን ሄ/ር ወደ 7 ሚሊየን ሄ/ር የተጎዳ መሬት ተከልሎ እንዲያገግም በማድረግ በድምሩ 19 ሚሊየን ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህም የ58 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። ይህም 1 ሚሊዮን በላይ ወጣቶችና ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል። የተለያዩ የፊዚካል አፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ተግባራዊ የተደረገበትን መሬት በ2007 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 20.2 ሚሊዮን ሄ/ር የማህበረሰብ ተፋሰሶች በ11.3 ሚሊየን ሄ/ር ላይ ተግባራዊ በማድረግ ወደ 31.5 ሚሊየን ሄ/ር የደረሰ ሲሆን የ55 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል። በስነ-ህይወታዊ ዘዴዎች የተሸፈነ የማህበረሰብ ተፋሰስ በ2007 ከተደረሰበት 17 ሚሊዮን ሄ/ር በማሳደግ በእቅድ ዘመኑ 21 ሚሊዮን ሄ/ር ማድረስ የተቻለ ሲሆን ይህም የ18 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። በስነ ህይወታዊ ዘዴዎች ከተሸፈኑ የማህበረሰብ ተፋሰሶች 31.59 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ለማግለል ታቅዶ 17.55 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን (49.31በመቶ) የሙቀት አማቂ ጋዞች ለማግለል የተቻለ ሲሆን በዚህም አገራችን ለዓለም አቀፍ ህብረተሰብ በ 2030 ያስቀመጠችውን ዒላማ 250 ሚሊየን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ የመቀነስ ድርሻ ይኖረዋል። የአጻጸም ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ከስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ ጋር ሲነጻጸር ለስነ-

ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ የተሰጠው ትኩረት አነስተኛ በመሆኑና የተሟላ መረጃ ማግኘት ባለመቻሉ ነው፡፡

የገጠር መሬት ይዞታ ማረጋገጫ በ2007 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 1.2 ሚሊዮን መነሻ በማድረግ ለ28.6 ሚሊዮን ማሳዎች ሰርተፍኬት በመስጠት ወደ 29.8 ሚሊየን ለማድረስ ታቅዶ ለ11.64 ሚሊዮን (40.7በመቶ) ማሳዎች የይዞታ ማረጋገጫ በመስጠት የዞታ ማረጋገጫ የተሰጣቸውን ማሳዎች 12.84 ሚሊየን ማድረስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት መክንያት ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓትን ለመዘርጋት የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ግኝር ለመፈጸም፣ በሁሉም ደረጃ የሠው ኃይል ለማሰልጠን እንዲሁም በቂ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት ከፍተኛ ሀብት ምንጭ አስፈላጊ ስለነበር ከልማት ድጋፍ ሠጪ አካላትና ከመንግስት የተገኘው በጀት ከዕቅዱ ጋር መመጣጠን ባለመቻሉ ዕቅዳችንን ማሳካት አልተቻለም፡፡ በዚህም የሁለተኛ ደረጃ የገጠር መሬት የይዞታ ማረጋገጫ በ2007 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 0.33 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች በ7.2 ሚሊዮን በማሳደግ ወደ 7.53 ሚሊየን (1.44 ሚሊየን እማወራ) ለማድረስ ታቅዶ 3.4 ሚሊየን (47.2በመቶ) (1.04 ሚሊዮን እማወራ) በማከናወን ባጠቃላይ ለ3.73 ሚሊየን ተጠቃሚዎች መስጠት ተችሏል፡፡ የዕቅድ አፈፃፀሙ ዝቅ ያለበት ምክንያት ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓትን ለመዘርጋት የተለያዩ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ግኝር ለመፈጸም፣ በሁሉም ደረጃ የሠው ኃይል ለማሰልጠን እንዲሁም በቂ የቅየሳ መሰረተ ልማት ለመዘርጋት ከፍተኛ የበጀት ምንጭ አስፈላጊ ስለነበር ከልማት ድጋፍ ሠጪ አካላትና ከመንግስት የተገኘው በጀት ከዕቅዱ ጋር መመጣጠን ባለመቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም በ 359 ወረዳዎች የመሬት አስተዳደር መረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት ታቅዶ በ56 ወረዳዎች (15.6በመቶ) ብቻ ተከናውኗል፡፡ የዕቅድ አፈፃፀሙ በጣም ዝቅተኛ የሆነው የግዢ ሂደት መራዘም እና የሽግግር መረጃ ስርዓት ፕሮግራሙ በ111 ወረዳዎች በማስፋትና የሙከራ ሥራው ጊዜ በመውሰዱ ዘመናዊውን የመረጃ ሥርዓት አፈጻጸም ዝቅ ሊያደርገው ችሏል፡፡

አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሰነድ ለ6521 ቀበሌዎች ለማዘጋጀት ታቅዶ ለ3417 ቀበሌዎች (52.4በመቶ) ተዘጋጅቷል፡፡ በተጨማሪም በ 3970 ቀበሌዎች አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ለመተግበር ታቅዶ ለ 2125 ቀበሌዎች (53.53በመቶ) ተከናውኗል፡፡ የዕቅዱ አፈፃፀም ዝቅ ያለበት ዋናው ምክንያት ዕቅዱ በሚታቀድበት ጊዜ በጀት ሙሉ በሙሉ ወረዳዎች ሸፍነው ይሰራሉ የሚል ታሳቢ ተወስዶ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በየደረጃ ያለው አስፈፃሚ አካል ለአሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ትኩረት ባለመስጠቱ ለባለሙያዎች ስልጠናና ስራ ማስኬጃ በቂ በጀት ባለመመደቡ አፈጻጸሙን ዝቅ አድርጎታል፡፡ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ለመዘርጋት በተደረገው ጥረት አርሶ/አርብቶ አደሩ በተለይ ሴቶችና ወጣቶች እንዲበረታቱ፣ በይዞታቸው የመጠቀም መብታቸው እንዲጎለብትና የተፈጥሮ ሀብቱንም በዘላቂነት እንዲንከባከቡ አድርጓል፡፡

የመስኖ ልማትን በማስፋፋት በ2007 መጨረሻ ላይ የተደረሰበትን 2.34 ሚሊዮን ሄ/ር በ2012 በጀት ዓመት ወደ 4.14 ሚሊዮን ሄ/ር መሬት ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም በተደጋጋሚ ጊዜ በተደረገው ግምገማ በመረጃ አያያዝ ላይ ከፍተኛ ክፍተት መኖሩ ተረጋግጦ የመረጃ ስርዓት ለማሻሻል በተደረገው ጥረት በጂፒኤስ በመለካትና ሌሎች የመረጃ ቴክኒኮችን በመጠቀም አጠቃላይ የመስኖ መሬት ሽፋኑ እስከ 2012 በጀት አመት መጨረሻ በተገኘው መረጃ መሰረት 790 ሺህ ሄ/ር ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በእቅድ ዘመኑ ቢያንስ አንድ የውሃ ምንጭ አማራጭ ያላቸው አርሶ/አርብቶ አደሮች ቁጥር 4.3 ሚሊዮን ደርሷል፡፡

የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የኮትቻ አፈር ለማልማት በ2007 መነሻ ዓመት ከተደረሰበት 0.73 ሚሊዮን ሄ/ር መነሻ በማድረግ በዕ.ት.ዕ. ዘመን 8.5 ሚሊዮን ሄ/ር የኮትቻ አፈርን በማልማት 9.23 ሚሊየን ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 6.26 ሚሊዮን ሄ/ር (73.65በመቶ) በማልማት ወደ 6.99 ሚሊየን /ር ማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም አርሶ አደሩ ከአንድ መሬት ላይ በዓመት ሁለትና ጊዜና ከዚያም በላይ እንዲያመርት በማድረግ ገቢውን እንዲያሳድግ ረድቶታል፡፡ አሲዳማ አፈርን በኖራ በማከም ለማልማት በ2007 መነሻ 5,100 ሄ/ር ከደረሰበት በ226,000 ሄ/ር መሬት በማልማት ወደ 231,000 ለማድረስ ታቅዶ 142,000 ሄ/ር(62.83በመቶ) በማልማት 147,100 ሄ/ር ማድረስ ተችሏል፡፡ ለዚህም 6.78 ሚሊየን ኩ/ል ኖራ ለማሰራጨት ታቅዶ 2.44 ሚሊየን ኩ/ል (36በመቶ) ሲሆን በዚህም በአሲዳማነት

ችግር ምክንያት ሙሉ በሙሉ እና በከፊል ከምርት ውጪ የሆኑ የእርሻ መሬቶችን በኖራ በማከም ከ50-300በመቶ የምርት ጭማሪ እንዲመጣ አድርጓል:: አፈጻጸሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት ለአሲዳማ አፈር ልማት የሚውለው የኖራ ለማሰራጨት ከፍተኛ በጀት የሚጠይቅ በመሆኑ የተፈለገውን ኖራ ለአ/አደሩ ማቅረብ ባለመቻሉ፣ የኖራ አምራች ፋብሪካዎችም በሀይል እጥረትና መቆራረጥ እንዲሁም በማሽኖቹ አቅም ውሱንነት የተፈለገውን ያህል ኖራ ማምረት ባለመቻሉ ነው። ጨዋማ አፈር ባለባቸው አካባቢዎች አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም 128,000 ሄ/ር መሬት ለማከም የታቀደ ቢሆንም ጨዋማነትን የሚቋቋሙ የሰብልና የመኖ ዝርያዎችን በ658 ሰርቶ ማሳያዎች ከመሞከር በስተቀር የማስፋት ስራ አልተከናወነም። ምክንያቱም ደግሞ ጨዋማ አፈርን ለማልማት ጨዋማነትን የሚቋቋሙ የመኖ እና የሰብል ዝርያዎች በምርምር ማእከላት እስካሁን በሙከራ ላይ በመሆናቸው፣ ከምርምር ማዕከላቱ የሚለቁ ዝርያዎች የዘር ለቀቃ አጽዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ የሚፈልጉ በመሆናቸው የተነሳ ነው።

የህያው ማዳበሪያ ልማትን በተመለከተ በመጀመሪያው ዕ.ት.ዕ ዘመን በህያው ማዳበሪያ የለማውን 11,963 ሄ/ር የጥራጥሬ ሰብል በእቅድ ዘመኑ ዘመን ወደ 260,000 ሄ/ር ለማድረስ ታቅዶ 262,000 ሄ/ር መሬት (122.4በመቶ) በማልማት 273,963 ሄ/ር ማድረስ ተችሏል። በዚህም የጥራጥሬ ሰብሎችን ምርታማነት በአማካይ በሄ/ር ከ8--12በመቶ ለማሳደግ ተችሏል።

የአፈር ናሙና ማሰባሰብ በ2007 መጨረሻ ላይ ከተደረሰበት 400 ወረዳዎች በተጨማሪ በ2ኛው ዕ.ት.ዕ. ከ250 ወረዳዎች የአፈር ናሙና ለመበሰብ የታቀደ ሲሆን በ 348 ወረዳዎች ተጠናቋል። በአጠቃላይ ከ748 ወረዳዎች የተሰበሰቡ ከ80,000 በላይ የአፈር ናሙና እንዲሁም የሳተላይት ምስል መረጃዎችን በማቀናጀትና በመተንተን በወረዳ ደረጃ ለሁሉም ክልሎች እንዲሁም ለድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የአፈር ለምነት ሁኔታና የማዳበሪያ ዓይነት ምክረ-ሐሳብ ካርታ ለማዘጋጀት ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት (100በመቶ) ተከናውኗል። በዚህም የአፈር ንጥረ-ነገር እጥረት እንዲሁም የአሲዳማ አፈር ደረጃንና ስርጭት የሚገልጽ ካርታ ጥቅም ላይ በመዋሉ የማዳበሪያና የኖራ አቅርቦትና አጠቃቀም በእጅጉ እንዲያድግና በምርትና ምርታማነት ላይ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በገጠር የሚኖሩ ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸውን ቤተሰቦች የምግብ ዋስትናቸውን ለማሻሻል በሰባት ክልሎች (ከጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉምዝ በስተቀር) እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ 382 ወረዳዎች 8.3 ሚሊዮን (50 በመቶ ሴቶች) ለሚሆኑ ተጠቃሚዎች በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እንዲገነቡ ለማስቻል ታቅዶ 7.9 ሚሊዮን (95.2በመቶ) ተጠቃሚ ሆነዋል (52 በመቶ ሴቶች) ። የሴፍቲኔት ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ 1.223 ሚሊየን የቤተሰብ ኃላፊዎች (58,704 እማወራዎች) ለማስመረቅ ታቅዶ 103,916 (47,750 እማወራዎች) (8.5በመቶ) ማስመረቅ ተችሏል። ለዚህ ዝቅተኛ አፈፃፀም ዋነኛ ምክንያት መረጃን መሰረት ያደረገ እና ተጠያቂነት ያለው የምረቃ ስርዓት አለመኖር፣ በኤልኒኖ ክስተት በተፈጠረው ድርቅ በቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ የስራ ዘርፍ የታቀፉ ተጠቃሚዎች በአብዛኛው ድርቁን መቋቋም በሚያስችላቸው ተግባራት ላይ ትኩረት በማድረጋቸው እንዲሁም ለጥሪት ግንባታ አገልግሎት የሚውል በቂ የብድር ገንዘብ በክልሎች ባለመመደቡ ነው። የሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን ቀዳሚ የብድር ተጠቃሚ በማድረግ በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እዲፈጥሩ ለማድረግ በ2007 በጀት ዓመት ከነበረበት 233,400 በእቅድ ዘመኑ ማብቂያ ወደ 628,850 (282,980 እማወራ) የቤተሰብ ኃላፊዎች ለማድረስ ታቅዶ 551,157 (248,021 እማወራ) የሚሆኑ ተጠቃሚዎች (87.65በመቶ) በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እንዲፈጥሩ ተደርጓል።

በምግብ ዋስትና ፕሮገራም እ.አ.አ በ2018 በተካሄደው የፕሮግራሙ ውጤታማነት ጥናት ውጤት መሰረት አማካይ ዓመታዊ የምግብ ክፍተት፡- ወራት በደጋማ ክልሎች በ2016 ከነበረበት 2.5 ወራት ወደ 1.9 ወራት (በ24 በመቶ) በቆለማ አርብቶ አደር አካባቢዎች ደግሞ በ2016 ከነበረበት 2.4 ወራት ወደ 1.28 ወራት (47 በመቶ) ቀንሷል። የአመጋገብ /የማዕድ አይነት ብዛት (Household Dietary Diversity):- በደጋማ ክልሎች በ2016 ከነበረበት 3.8 አይነት ወደ 4.33 የምግብ ዓይነት ወይም 12 በመቶ ዕድገት አሳይቷል። የቤት እንስሳት ይዞታ (TLU)፡- በ2016 ከነበረበት 1.93 ወደ 2.9 (50 በመቶ) እድገት አሳይቷል። ችግርን ለመቋቋም ያፈሩትን እንስሳት ሃብት ለመሸጥ ይገደዱ የነበሩ

ቤተሰቦች (distress livestock sales) በመቶኛ በ 2016 ከነበረበት 17 በመቶ ወደ 13.22 በመቶ ማለትም በ 22 በመቶ ቀንሷል፡፡

በአጠቃላይ የዘርፉን እድገት እያሻሸልን ለመሄድ የተለያዩ ስትራቴጂ፣ ፖሊሲና አመቺ የህግ ማእቀፎች በማውጣት፣ በማጥራትና በማሻሻል የግብርና ዘርፍ በዘር፣ በማዳበሪያ፣ በውል ግብርና በኤክስቴንሽን፣ በግብይት ዙሪያ ከፍ ያለ ትኩረት ተስጥቶት ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ከዚህም አኳያ አርሶ/አርብቶ አደሩን ተጥቃሚ ለማድረግ የተለያዩ ፕሮግራሞች፣ ፕሮጀክቶችና ችግር ፈቺ የመፍትሄ ሃሳቦች ተግብራዊ ተደርገዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የግብርና እድገት ፕሮግራም (AGP)፣ የእንስሳትና ዓሳ ዘርፍ ልማት ማስተር ፕላን(LFSDP)፣ ልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም (PSNP) ፣ የድርቅ መቋቋምና ቀጣይነት ያለው መተዳደሪያ ፕሮግራም (DRLSP) ሲተገበሩ ቆይተዋል፡፡ የእነዚህ ፕሮግራሞች ትግበራ ግልፅ በሆነ መልኩ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ኑሮ እንዲሁም ገቢው የተሻለ እንዲሆን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የአርሶ/አርብቶ አደሩን ኑሮ ለመቀየር፣ ገቢውን ለማሳደግ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የትራንስፖርት፣ የመብራትና የውሃ መሰረተ ልማቶችን ከማሟላት በተጨማሪ የኤክስቴንሽን ስርዓቱን ለማሳደግ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትንና የአርሶ/አርብቶ አደሮች ስልጠና ማእከላትን ማጠናከር፣ የምርምር ተቋማትን አቅም መገንባት፣ መጋዘንና የግብይት ማዕከላትን ማስፋፋትና ያሉትንም ጥራታቸውን ማሳደግ፣ የጥራትና ጤና ቁጥጥር ተቋማትን ማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ኢንቨስትመንቶችን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተጨማሪም የመስኖ አውታርን ለማስፋፋትና አማራጭ የወሃ ምንጮችንና አጠቃቅምን ለማሻሻል በርካታ ኢንቨስመንቶች ሲደረጉ ቆይቷል፡፡

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ በመገንባት በ2017 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ ግብ በማስቀመጥ ወደ ተግባር መግባቷ ይታወቃል ይህንን ግብ ለማሳካት የግብርና አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ በሆኑ በስልቱ ውስጥ ተገልጾዋል፡፡ ግብርናችን በተለመደው የአሰራር ስርአት የሚቀጥል ከሆነ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ከሌሎች ተግዳሮት ጋር ተዳምሮ በፍጥነት እያደገ ያለውን ህዝብ የምግብ ዋስትና መረጋገጥና ቀጣይነት ያለውን እድገት ለማረጋገጥ ፈታኝ ይሆናል፡፡ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣመ ግብርና በመገንባት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዘው የሚያገጥሙ ተፅእኖዎችን በመቀነስ የዘርፉን የመቋቋ አቅም በማጎልበት የሚከሰቱትን አደጋዎች መቀነስ ያስፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት በተቋሙ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችሉ በስልቱ የተለዩ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ ቴክኖጂዎችን በመደበኛ የልማት እቅድ ውስጥ በማካተት እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በእርሻ ልማት ዘርፍ የተለያዩ ዝቅተኛ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ያላቸውና የተሻለ ምርት የሚሰጡ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመተግበር 28.15 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ታቅዶ 7.23 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ተችሏል፡፡ በእንስሳት ልማት ዘርፍ አነስተኛ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ያለቸውን የእንስሳት ዝርያዎችን በማስፋፋት 18.4 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ታቅዶ የዶሮ ልማት በማስፋፋት 12.06 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ተችሏል፡፡ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ ተፋሰስን መሰረት የደረገ ስነ-ህይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመተግበር 31.59 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ታቅዶ 17.55 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለማግለል ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በዕ.ት.እ 2 መጨረሻ ከዘርፉ 78.14 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለመቀነስ ተቅዶ 36.84 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ለማግለል/ለመቀነስ የተቻለ ሲሆን አጠቃላይ አፈፃጸሙ 47.15 በመቶ ነው፡፡ አፈፃፀሙ ዝቅተኛ የሆነበት ምክንያት በሜካናይዜሽንና የግጦሽ መሬት ለማሻሻል የተሰሩ ስራዎች መረጃ መግኘት ስላልተቻለ ሪፖርቱ ውስጥ መካተት አልተቻለም በተጨማሪም አመራሩ ለአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስራዎች በቂ ትኩረት ያለመስጠትና በያደረጃው ያለ ሙያተኛ በዚህ ዙርያ ያለው ግንዛቤ አነስተኛ መሆኑ ለአፈጻጸሙ መነስ ምክንያት ሆኗል፡፡

ተቋማዊ አቅምንና እስከ አርሶ አደር ድረስ ያለ ክህሎትን ከማሳደግ አንፃር የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ የቆዩ ሲሆን ከእነዚህም መካከል ሁሉቱን ሚኒስትር መ/ቤቶች ማቀናጀቱ፣ ከክልሎች ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከራችን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በፌደራል ደረጃ ካሉ 12 ተጠሪ

ተቋማት ጋር ያለውን የግንኙነትና የአሰራር ስርዓት በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ርቀት ተጉዘናል። ክህሎትን ከማሻሻል አንፃር በዋነኛነት ከልማታ አጋሮች ጋር በመተባበር ለፌደራልና የክልል ባለሙያዎች የተለያዩ ስልጠናዎችን ስንሰጥ ቆይተናል። ከዚህም በተጨማሪ ባለሙያዎቻችንን ወደ ውጪ ሀገር በመላክ የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን እንዲያገኙ በማድረግ የሰው ሃይል ሀብታችንን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት አድርገናል። የአርሶ/አርብቶ አደሮችን ክህሎት ከማሳደግ አኳያ አሳታፊ የምርምርና ኤክስቴንሽን ስራዎችን ጨምሮ የተለያዩ የእሴት ሰንሰለት ስልጠናዎችን ስንሰጥ ቆይተናል።

ያጋጠሙ ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች፦ የግብርና ዘርፍ እድገት በሚፈለገው ደረጃ ፈጣን እድገትና መዋቅራዊ ለውጥ (ግብርና ትራንስፎርሜሽን) እንዳያመጣ ብሎም የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ለማስተካከል ተገቢውን ሚና እንዳይጫወት ያዳረጉት ስትራቴጂካዊ ማነቆዎች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል። የ 5 ዓመት የመካከለኛ ጊዜ እቅዱም እነዚህ ማነቆዎችን ለመፍታት ትኩረት አድርጎ ይንቀሳቀሳል።

የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ሁኔታዎች፦ እንደሚታወቀው ባለፉት 4 ዓመታት የሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ከፍተኛ አለመረጋጋቶች ሲታዩበት ቆይቷል። ይህም በዋነኛነት ለአርሶ አደሮች እንደ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ ያሉ ግብዓቶች ወቅቱን ጠብቀው እንዳይደርሱ ማነቆ ሆኗል። ለአብነት ያህል በምዕራብ ኢትዮጵያ በተከሰተው አለመረጋጋት ምክኒያት ያጋጠመው የምርጥ ዘር እጥረት ተጠቃሽ ነው። በተጨማሪም ምርትን ወደ ገበያ በማቅረብ ሂደት ውስጥ የነበረው የሰላምና ፀጥታ እጦት ከፍተና ችግር ሆኖ ቆይቷል። ይህ ሁኔታ ለኤክስፖርት የሚቀርቡ እንደ ቁም እንስሳት፣ ቡና፣ ሰሊጥና ሌሎች ምርቶች ላይ ታይቷል።

የአየር ንብረት ለውጥ፦ የግብርናው ዘርፍ በዝናብ ላይ የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም የአየር ንብረት ለውጥ አርሶ/አርብቶ አደሮች ህይወት ላይ የጎላ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። የአየርን ንብረት ለውጥ ዋነኛው የአርሶ/አርብቶ አደሮቻችን ማነቆ መሆኑ ይታወቃል። በተለይም በ2007/8 የተከሰተው የኤልኒኖ ድርቅ ጋር ተያይዞ የግብርና ምርት እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ተከስቷል።

ግብዓትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ስርዓት ኋላቀርነት፦ ቀጣይነት ያለው የቴክኖሎጅ ማመንጨት፣ ብዜትና ስርፀት ስርዓት አለመዳበርና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ አነስተኛ መሆን አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚያስፈልገውን ግብዓቶችና የቴክኖሎጂ ውጤቶች በተገቢው ጊዜ፣ በሚፈለገው ጥራትና መጠን እንዳያገኝ ማነቆ ሆኖ ቆይቷል። በተለይም ለሁሉም ስነ ምህዳርና የግብርና ምርቶች የሚያግዝ እንዲሁም በአየር ንብረት ለውጥ ምክኒያት ለሚከሰቱ አዳዲስ በሽታዎች፤ ነፍሳቶችና አረሞች የሚቋቋም በቂ ቴክኖሎጂ ማቅረብ አልተቻለም። ከምርምር የሚለቀቁ ቴክኖሎጂዎች ማባዛት ዋናው ማነቆ ሆኖ ቆይቷል። ይህም ሁኔታ በተለያየ መልክ በመንግስት ፕሮግራሞች ውስጥ የተካተተ ቢሆንምና ተስፋ ሰጪ ውጤቶች የተገኙ ቢሆንም ጥሩ ተሞክሮዎችን በሚፈለገው መጠን ማስፋት አልተቻለም። የግብርና ሜካናይዜሽን አጠቃቀማችን ከዓለምአቀፍ ዕድገት ጋር ሲነጻጸር እጅጉን አነስተኛ ነው። በዋናነት የችግሩ መንስኤ መካናይዜሽንን ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችል የፖሊሲ ድጋፍ እጅጉን አነስተኛ ሆኖ መቆየቱ ነው። ምክንያቱም አገራዊ የማቅረብ አቅማችን አነስተኛ ሆኖ በመቆየቱ በአገር ውስጥ የማምረት አቅማችን ያላደገ መሆኑ ብዙውን የሜካናይዜሽን መሳሪያዎችን ከውጭ እናቀርባለን። በሜካናይዜሽን መሳሪያዎች አቅርቦት የሚታዩት ማነቆዎች ምርምር ረገድ የአቅም ክፍተት መኖሩ፣ በአገር በቀል መሳሪያ አምራችና አቅራቢዎች አቅም /የማስተዋወቅ፣ የፋይናስ እና የሰው ኃይል/ ያላደገ መሆን፣ የመሳሪያዎች የጥራት ስታንዳርድ በተሟላ ሁኔታ ያለመኖር፣ ከውጭ ለሚገቡ መሳሪያዎች የጉምሩክ ታሪፍ እና ሌሎች ግብር ክፍያዎች ከፍተኛ መሆን እና ከአቅርቦትና ከአጠቃቀም በኋላ የመለዋወጫ እጥረት መኖር የሚጠቀሱ ማነቆዎች ናቸው።

ለግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በአብዛኛው በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ላይ የተመረኮዘ ነው። እነዚህ የአርሶ/አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት በአብዛኛው ግብዓት ያልተሟላላቸው በመሆናቸው፣ ለአርሶና/አርብቶ አደሩ ችግር ፈቺ እንዲሁም በገበያ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን ለማምረት የሚያስችል የምክር አገልግሎት መስጠት አልቻሉም። ለውጤቱ አነስተኛ መሆን የሚጠቀሱ መንስኤዎች በዋናነት የኤክስቴሽን ተግባራት መንግስትን ብቻ የሚጠብቁ መሆንናቸውና የግል ዘርፉን፣ ማህበራትን እና ሌሎች ተቋማትን በተደራጀ መልኩ ያላሳተፈ፣ ተወዳዳሪነት የጎደለውና ገቢ በሚያስገኝ መልኩ የተቃኘ

አለመሆኑ ሲሆን የልማት ሰራተኞችም ሥራቸውን ወደውት አንዲሰሩ የሚያደረግ አመቺ የስራ ከባቢ አልተፈጠረላቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልማት ሰራተኞቹ ከአርሶአደሩ ተሸለው እንዲገኙና በማማከር ወቅት በተጠቃሚው ዘንድ አዳዲስ የቴክኖሎጂ እውቀት እንዲኖራቸው የሚያስችል የምርምር ኤክስቴሽን ትስስር ባለመጠናከሩ እና በኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የዘመነ የኤክስቴሽን ስርዓት አለመኖሩም ለአገልግለሎቱ መዳከም አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

የፋይናንስ ተደራሽነት፦ የፋይናንስ ተቋማት ለግብርና ግብዓት እና ምርት ግብይት የሚያሰፈልገውን ፋይናንስ በበቂ ሁኔታ እያቀረቡ አይደሉም፡፡ አርሶና አርብቶ አደሩ ለብድሩ የሚውል ማሰያዣ የማቅረብ አቅም ውስን መሆን በሚፈለገው መጠን ከብድር አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም፡፡ እንዲሁም አበዳሪ ተቋማት ያስቀመጡት የብድር መስፈርት የአርሶና አርብቶ አደሩ የማያሟሉት መሆኑና የብድር መጠኑም የተገደበ በመሆኑ በፈለጉበት ስራ መጠቀም እንዳይችሉ አድርጎቸዋል፡፡ በተመሳሳይ በዘርፉ ለተሰማሩ ሰፋፊ አልሚዎች፣ እሴት ጨማሪዎች እና አግልግሎት ሰጪዎችን ልማት የሚገድብ ሆኖ ይገኛል፡፡ በአጠቃላይ ዘርፉ ከአገር አቀፍ የባንኮች የብድር ስርጭት ባላፉት ተከታታይ 5 ዓመታት በከፍተኛ ሁኔታ እየቀነሰ መጥቶ ከ10በመቶ የማይበልጥ ሆኗል፡፡ ከብድር በተጨማሪ ያሉት የፋይናንስ አማራጮች በየጊዜው የሚታየውን የግብርና ምርት የዋጋ መዋዠቅ እና በማምርት ሂደት የሚፈጠሩ ልዩ ልዩ አደጋዎችን በመቀልበስ አስተማማማኝ የማምረት ሂደት መፍጠር፣ የገበያ ትስስር ካላቸው ፋይዳ አንፃር አልተስፋፉም፡፡ በተለይም የኮንትራት እርሻ፣ የግብርና ምርት ማከማቻ ደረሰኝ፣ የፎርዋርድ /forward/ ግብይት እና የሰብል እና እንስሳት መድህን የአሰራር ሥርዓትና የህግ ማእቀፍ በተሟላ ሁኔታ ባለመዘርጋቱ በበቂ ሁኔታ አልተስፋፉም፡፡ በዚህ የተነሳ በአርሶና አርብቶ አደሩ እና የግል ባለሃብቱንና የግብርና ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ሆኖ ይታያል፡፡

ያልዘመነ የምርት ገበያ፦ የግብርና ምርትና ምርታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም ዘመናዊ ግብይት ስርዓት ባለመዘርጋቱ አምራቹ ላመረተው ምርት ተመጣጣኝ የገበያ ዋጋ እያገኘ አይደለም፡፡ የገበያ ስርዓቱ እንዳይዘምን ያደረገው አርሶና አርብቶ አደሮችን የሚያመርቷቸው ምርቶች በአመዛኙ ገበያን ታሳቢ ያላደረገ ፣ እሴት ጨምሮ (በተለይም በመጀመሪያ ደረጃ ሊተገበሩ የሚችሉትን በጥራት መውቃት፣ ማበጠርና ደረጃ ማዘጋጀት፣ ማሸግ፣ ማከማቸት) መሸጥን ያላገናዘበ እና የገበያ ትስስር ያልተፈጠረላቸው መሆኑ ናቸው፡፡ በግብይት ስርዓቱ ውስጥ የሚሳተፉ ተዋናዮች መካከል ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር ፍላጎት፣ ቅንነትና ተአማኒነት አለመኖሩ ፣ በግብይት ሰንሰለት ውስጥ እሴት የማይጨምሩና በአቋራጭ ተጠቃሚ ለመሆን የሚፈልጉ ብዙ አካላት በመኖራቸው ምክንያት የግብይት ሰንሰለቱ የተንዛዛ በመሆኑ አምራቹ እና ሸማቹ በቀጥታ እንዳይገናኙ በማድረግ ሁለቱምን ተጠቃሚ ማድረግ አልተቻለም፡፡ አምራቹን በተሻለ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ የወጪ ንግድ እና የኢንዱስትሪ ምርት አቀነባባሪዎችን ጋር በቀጥታ እንዲገበያዩ የሚያግዝ ስርዓትም በበቂ አልተዘረጋም፡፡ በተጨማሪም በገጠር ከግብርና ውጪ ያሉ የልማት እንቅስቃሴች የገጠር ከተማ ልማት አለመጎልበቱ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

በቂ ያልሆነ መሰረተ ልማትና ኢንቨስትመንት፦ መንግስት በመሰረት ልማትና ሎጂስቲክ ረገድ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ከፍተኛ የሆኑ ተግባራት የተከናወኑ ቢሆንም ዘርፉ ከደረሰበት ዕድገት አንጻር አሁንም ብዙ ያልተሟሉ መሰረተ ልማቶች አንዳሉ ይታወቃል፡፡ በመንግስት ከ1996 እስክ 2003 በጀት አመታት ለግብርናና ገጠር ልማት ከፍተኛ መዋለ-ንዋይ ያፈሰሰና ይህም የአፍሪካ ሀገራቶች ከጠቅላላ የመንግስት አመታዊ በጀት ውስጥ ለግብርና ዘርፍ መመደብ አለበት ተብሎ ከተቀመጠው የ10 በመቶ ዝቅተኛ መስፈት በከፍተኛ ደረጃ አሟልተዋ ተብለው ከተለዩት 10 ሀገራት ተርታ ውስጥ እንዳደረገ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኑም ግን ይህ የበጀት ምደባ ከ2004 ጀምሮ በጣም እያሽቆለቆለ አመታዊ አማካይ 5.2 ደሷል፡፡ ከዚህ ውስጥ ለግብርና መሰረተ ልማት የተመደበው በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ከፍተኛ (11 ሚሊየን ሄክታር) ቢሆንም እስካሁን ማልማት የተቻለው ከአንድ ሚሊዮን ሄክታር ማለትም ከ10 በመቶ በታች ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው እስካሁን ለንዑስ ዘርፉ የተደረገው ኢንቨስትመንት ዝቅተኛ መሆኑና ለወደፊቱም ልዩ ትኩረት ካልተሰጠው ዘርፉን ማሳደግና ከሱም የሚገኘውን ጥቅም አሟጦ መጠቀም የማይቻል መሆኑን ነው፡፡ ከመንግስት በተጨማሪ ለመሰረተ ልማትና ኢንቨስትመንት ምንጭ የሆነው የግል ባለሃብትም ድርሻ ዝቅተኛ ነው፡፡

ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም፦ የግብርና ዘርፍ በበቂ ጥናት የተደገፈ፣ ተናባቢና ተደጋጋፊ የሆነ አደረጃጀት ያለመኖር፣ የህግና አሰራር ስርዓት ክፍተት፣ ተቋማዊና ሙያዊ አቅም ውስንነት እንዲሁም የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም አለመዳበር ተልዕኮውን በሚገባ እንዳይወጣ ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ነው። ዘርፉ የሚመራበት ፖሊሲና ስትራቴጂዎች የተዘጋጁ ቢሆንም የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር ክፍተት በመኖራችው ምክንያት የዘርፉ የማስፈፀም አቅም እንዲሁም ለግብርናው ዕድገት እንዳይፋጠን የራሱ አሉታዊ ሚና ነበረው። በተጨማሪም በፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ከክልል ግብርና ቢሮዎች ያልተናበበና ተጠያቂነት ያልተዘረጋለት የሰራ ግንኙነት መሆኑ ሀገራዊ ግቦችን ለማሳካት ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል።

የዘርፉም የሰው ሃይል አደረጃጀት ዘርፉ በሚያስፈልግው ብቃት ባለመደራጀቱ የዕውቀት፣ ክህሎትና ተነሳሽነት/ቁርጠኝነት ክፍተት ተጋርጦበታል። ይህም የሰው ሃይል ትምህርትና ስልጠና ፣ ቅጥር ፣ ደመወዝና ማበረታቻ እና ግምገማና ምዘና ስርዓት ለዘርፍ የተለየ ባህሪ ያልተቃኘ በመሆኑ ፍተሻ ይፈልጋል። ለምሳሌ ግብርና ምርምር፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ኤክስቴንሽን ግንኙነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ቢሆንም ግንኙነቱ በባለቤትነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ ባለመዘርጋቱ ዘርፉ የሚያስፈልገው ምሩቋን ማቅረብ ፣ የአርሶና አርብቶ አደራችንን ችግር የሚፈቱ የተሻሻለ ቴክኖሎጂ ማፈለቅና ጥቅም ላይ ማዋል ጉድለት ይታይበታል። በተመሳሳይ የመካከለኛ ደረጃ የግብርና ባለሙያዎችን የሚያፈልቁት ቴክኒክና ሙያ ሰልጠና ተቋማትም ጥራት ያለው ሠልጣኞች ለማቀረብ የአሰራርና ብቃት ክፍተቶች ይስተዋልባቸዋል። በስራ ላይ የተሰማራውም ባለሙያና አመራር አግባብ ያለው ተጠያቂነትና የዘርፉን የስራ ባህሪ መሰረት ያደረገ ማትጊያ ስርዓት ባለመኖሩ ዘርፉን በእውቅት ለመምራትና የሚጠበቅበት አካታቸና ዘላቂ አስተዋፆ ለማበርከት ተግዳሮት ሆኖበታል። በተጨማሪም የስራ ግብዓትና ሃብት አቅርቦትና አጠቃቀም እጥረቶች በመኖራቸው ከዘርፉ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል።

1.3 የእቅዱ መነሻዎች

የ 10 ዓመት የረጅም ጊዜ ዕቅዱ

የ 5 ዓመት የመካከለኛ ጊዜ ዕቅድ ለማዘጋጀት የ10 ዓመት መሪ ዕቅዱ እንደ መነሻ በመውሰድ በሚከተሉት ጉዳየች ላይ ዕቅዱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ የሰብል፣ እንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል፣ የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂነት እንዲለማና እንዲጠበቅ እና ጥምር ግብርና ማስፋፋት፣ የግብርና ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ስርጭት ስርዓትን ማሻሻል፣የግብርና ምርት ጥራት ቁጥጥር፣ የገበያ ትስስር፣ የምግብ ዋስትናና የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ያካትታል፡፡

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ክስተት

የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ (COVID-19) በሀገር ኢኮኖሚ በአጠቃላይ በግብርናው ሴክተር በተለይ የሚያደርሰዉን ተፅእኖ ለመቀነስ በተቋም ደረጃ የተዘጋጀው የኮሮና ቫይረስ ምላሽ እቅድ (COVID-19 response plan) የበጀት ዓመቱ እቅድ አካል ተደርጎ ተግባራዊ የሚደገረግ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ባለፈው ምርት ዘመን ወደ ልማት የገባውን መሬት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከተያዘው ዕቅድ በተጨማሪ በአነስተኛ አርሶ አደሩና በግል ባለሀብቱ ተጨማሪ መሬቶችን ወደ ምርት የማስገባት እንዲሁም ይህንኑ ለማሳካት የሚያችሉ የኤክስቴንሽን ምክር አገልግሎት ተግባራት በተጠናከረ ሁኔታ የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

1.4 ስትራቴጅክ አቅጣጫዎች

የመስኖ አቅምን በማጎልበት የግብርናን ዘርፍ ከዝናብ ጥገኝነት ማላቀቅ፡- የሀገራችን ምርት በዝናብ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ምክንያት ለምርታማነት ዝቅተኛነት የተጋለጠ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከዓመት ዓመት የምርት መጠን ከዝናብ መጠን መለያየት ጋር ታያይዞ ከፍተኛ ልዩነቶች ይታዩበታል፡፡ ይህ አካሄድ የሚጠበቀውን የግብርና ትራንፎርሜሽን ለማምጣት በቂ ስላልሆነ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት የመስኖ ልማት ላይ ኢንቨስትመንት ማድረግ አለበት፡፡ ይህም ያሉንን የምርት ወቅቶች ከ3 እና 4 ጊዜ በማድረስ የምግብ ዋስትናን ከማረጋግጥ በላይ ለኢንዱስትሪና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ከማቅረብ አኳያ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያመጣል፡፡ የምንከተለው የመስኖ ልማት አካሄድ በሁለት ይከፈላል፤ ይህም የአነስተኛ መስኖ ልማትና መካከለኛና ትላልቅ መስኖ ልማት ሲሆን የምንተገብረውም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ይሆናል፡፡ የመስኖ ልማት ስራችን በተለያዩ ተዋንያኖች የሚፈፀምበትን ሁኔታ በማመቻቸት ለምሳሌ በመንግስት፣ በልማት አጋሮች፣ በግሉ ዘርፍ እንደዚሁም በማህበረሰብ ተሳትፎ የሚሰራ መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ የመስኖ ኢንቨስትመንት ቅደም ተከትል በሚሰጡት ጥቅምና በመረጃ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በመስኖ ስራ ላይ ትኩረት መስጠት በቤተሰብ ደረጃ የውሃን ተደራሽነት ከማረጋገጥ ባሻገር ተያያዥ ለሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች መነልበት የራሱን አስተዋኦ ያደርጋል፡፡

የሜካናይዜሽን አገልግሎትን ማስፋፋት ፦ የሜካናይዜሽን አግልግሎት ማስፋፋት ግብርናን ለማዘመንና የምርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ለሀገራችን መልከዓ ምድርና አግሮ ኢኮሎጂ ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በመጠቀምና ተደራሽነትን ለአርሶ/አርብቶ አደር በማረጋገጥና አጠቃቀም ላይ የተመሰረተና የአርሶአደሩን አቅም ያገናዘበ ሀገር-በቀል የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ፈጠራ፣ ማኑፋክቸሪንግና ስርጭት ስርዓት በማስፋፋት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የአርሶአደሩን ገቢ ትርጉም ባለው መልኩ ማሳደግ ይቻላል፡፡

ዘርፉ የሚጠቀማቸውን ማናቸውም የቴክኖሎጂ ግብዓትና ማሽነሪዎች ከግብር ነጻ በማድረግና የሊዝ ፋይናንሲንግ የብድር ስርዓት በመገንባት ግብርናን ለማዘመን ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ በዚህም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለመቋቋም ከፍተኛ ዕገዛ ይኖረዋል፡፡ ምርታማነትና የምርት ጥራት በማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ የስራ እድል በመፍጠር ወጣቱን ትውልድ ወደ ግብርና መሳብ ያስችላል፡፡ የሜካናይዜሽን አገልግሎት ዋና ምሶሶ የግሉ ዘርፍ መሆኑ ቢታወቅም የግብርና ዘርፍ ከአጋሮቹ ጋር በመሆን የቁጥጥርና ፍተሻ እንዲሁም ክትትል ስራዎችን ይሰራል፡፡ የግሉን ዘርፍ ለማሳተፍ በሚደረገው ሽግግር መንግስት የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶች ይጠቀማል፡፡

በከፍተኛ ምርታማነታቸው የሚታወቁ አነስተኛ አርሶ አደሮች የተሻለ የመሬት ይዞታ እንዲኖራቸው ማገና ቀስ በቀስ ወደ ኢንቨስተርነት ማሳደግ፡

እንስሳት ሃብት ልማት፤ መኖ ልማትና ጤና ማሻሻል፦ የእንስሳት ሃብት ልማትን መደገፍ የአረባብ ስርዓትን ከማሻሻልና ገበያ መር ከማድረግ ይጀምራል። በተጨማሪም በእንስሳት ጤና አገልግሎት ውስጥ የግሉን ዘርፍ ሚና ማሳደግ፣ የመኖ ምርትን ማስፋፋትና የግብይት ማዕከላትን ማጠናከር ዋና ዋና ተኩርት የሚደርግባቸው ጉዳዮች ናቸው። የወጪ ንግድ አፈፃፀምን ከማሻሻል አኳያ የኳረንቲን ማዕከላትን አጠናክሮ ወደ ስራ ማስገባትና ሌሎች ከግብይት ጋር የተያያዙ መሰረተ ልማቶችን በመንግስት-ግል ዘርፍ ሽርክና ማሟላት ትኩርት ሊደረግባቸው ይገባል። የወጪ ንግዳችንን የሚያነቃቁና ወደ አዳዲስ ገበያዎች እንድንገባ የሚያደርጉ ዘመናዊ የምርት ዱካ ስርዓት መተግበር ፣ የፋይናንስና ኢንሹራንስ ስርዓቶችን ማሻሻል፣ የአርብቶ አደር አከባቢዎችን እንደ FMD ካሉ ከበሽታዎች የፀዱ ማድረግና ህገወጥ ንግድን ትርጉም ባለው መልኩ መቆጣጠር በስፊው ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የእሴት ጭመራን ለማቀላጠፍ በኤክሽፖርት ቁራዎችና በአርቢዎች መካከል ቀጥታ የምርት-ግብዓት ግንኙነቶችን ማዳበር ትኩረት ሊደረግበት ይገባል።

ሆርቲካልቸር ልማት ፦ የሆርቲካልቸር ልማት ዋና ምሶሶዎች የሚሆኑት በክላስተር የተደራጁ አነስተኛ አርሶ አደሮችና ትላልቅ የግል አምራቾች ይሆናሉ ተብለው ይጠበቃል። በዘርፉ የምርት ስፔሺያላዝሽን ቢበረታታም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን መሰረተ ያደረገና የዋጋ ግሽበትን የሚያረጋጋ ስትራቴጂ የምንከተል ይሆናል። (ለምሳሌ የአቮካዶ የወጪ ንግድ፣ የፍራፍሬ ምርቶች ወደ አግሮ ኢንዱስትሪን፣ አበባ ምርት ኤክስፖርት ማስፋት)

የሆርቲካልቸር ዋና ስትራቴጂ የሚሆነው ግብዓት አቅርቦት ስርዓቱን ማዘመን ነው፤ ይህም ማለት ገበያ ተኮር የሆነና የገበያውን ፍላጎት የሚያሟሉና ከፍተኛ ምርታማነት ያላቸው ዝርያዎችን ማፍለቅና ማሰራጨት፣ የግሉ ዘርፍ ተሳታፊነቱን አሁን ካለበት ማስፋፋትና ተመሳሳይ ስራዎችን ያጠቃልላል። የዘመናዊ ነርሰሪ ልማት ስትራቴጂያዊ በሆኑ ቦታዎች ላይ ማጠናከር፣ የግብይት ማዕከላትን ለአርሶ አደሩ ቅርበት ባለባቸው አከባቢዎች ማደራጀት፣ የኮልድ ቼይን መሰረተ ልማት ከግሉ ዘርፍ ጋር በመሆን ማመቻቸት ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

የገበያ ትስስርን በተመለከተ በትላልቅ የሆርቲካልቸር ምርት ሰብሳቢዎችና በአርሶአደሮች መካከል ቅርበት ፈጥሮ የሀገር ውስጥ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል የሚያመቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ በሌላ በኩል የኤክስፖርት ገበያዎች ወስጥ ያለንን ድርሻ ማጠናከር በሰፊው ይሰራባቸዋል።

በግብርና ልማት የባለሀብቱን ተሳትፎ ማሳደግ፦ ባለሃብቱ በዘርፉ ላይ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ይህም በምርምር፣ በኤክስቴንሽን፣ በፋይናንስና ኢንሹራንስ አቅርቦት፣ በግብዓት አቅርቦት፣ በግብርና ምርት ፣ በግብይት መሰረተ ልማት ላይ የተሻሉ ድጋፍና ማበረታቻዎችን በመስጠት ዘርፉ ውስጥ መሰረታዊ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንግስት ከሀገር በቀልና አለማቀፍ ባለሃብቶች ጋር በጥምረት የሚሰራ ይሆናል።

በተጨማሪም ባለሃብቱን የእሴት ጭመራ ስራዎች ላይ ለማሳተፍ በተለይም አግሮ ኢንዱስትሪዎችን መሰረት ያደረገ የእሴት ሰንሰለት ማጠናከር ስራ የሚሰራ ይሆናል።

ተቋማዊ የማስፈፀም አቅምን መገንባት፦ የ 10 ዓምቱን እቅድ ለማሳካት ዋናው መሰረት የዘርፉን የማስፈፀም አቅምና ክህሎት ማሳደግ ግድ ይላል። በዚህም ረገድ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር ደረጃ ስር- ነቀል የሰው ሃብት ሪፎርም እየተሰራ ይገኛል። ይህ ስራ የአገልግሎት ጥራትና ጊዜን የሚያፋጥን ሲሆን የወሳኔ አሰጣጥን የሚያቀላጥፍ ነው።

በክልል፤ በዞንና በወረዳ የኤች አይቪ ኤድስ ባለሙያ እንዲመድቡ ማድረግ በ2030 ሀገራችን የያዘችውን አዲስ በኤች አይቪ መያዝ ዜሮ የማድረግ እቅድ ለማሳካት ይረዳል ።

ይህ ጅማሮ በክልል በዞንና በወረዳ መውረድ እንዳለበት ሲታመን፣ የተቋማዊ መሰተጋብር ጎን ለጎን መቀናጀት አለበት። እነዚህም የቅንጅት ስራዎች አብሮ በማቀድ፣ አብሮ ችግሮችን በመፍታት፣

ተደጋጋሚ ግንኙነቶችን በማድረግ፣ ሀገራዊ የሆነ የስራ ድግግሞሽን ፣ የሃብት አጠቃቀም ጉድለትን የሚቀንስ ሲሆን እንደዚሁም ያለውን የቴክኒክ አቅም በሀገር ደረጃ እንድንጠቀምበት ያደርጋል።

የሥራ ዕድል መፍጠር

በገጠር የሚኖሩ ስራ ፈላጊ ዜጎች ፍትሃዊ፣ ዘላቂና ውጤታማ የስራ እድል ተፈጥሮላቸው የልማቱ ተሳታፊ እና ተጠቃሚ በመሆን ለሃገር እድገት እና ትራንስፎርሜሽን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ዘላቂ ግብርና ልማት ማካሄድ፦

የግብርና ምርት በአማካይ በዓመት 5.6 በመቶ እያደገ የኤክስፖርት ምርቶችን በበቂ በማቅረብ የግብርና ምርት የወጪና ገቢ ምርት ሚዛን ያሻሽላል፣ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ግብዓት ያሟላል፤ ሀገራዊ የምግብ ፍጆታን ክፍተትን ያሟላል። የምርት ስበስጥር ደረጃ በማሻሻል አርሶ/አርበቶ አደሮች አነስተኛ መጠን የተሰባጠረ የምግብ ምድቦችን መመገብ እንዲችሉ ያደርጋል። የግብርና ልማትን ዘላቂነት በማረጋገጥ ከግብርና ልማት የሚወጣውን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን መቀነስ ይሆናል።

1.5 የዕቅድ ዝግጅት አካሄድ

የዕቅድ ዝግጅቱ የሚመራበት ማዕቀፍ ማዘጋጀት

የግብርና ዘርፍ የ5 ዓመት መሪ ዕቅድ ስትራቴጅክ የዕቅድ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ኣላዎች አካቶ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። የግብርና ርዕይ፣ የዘርፉን መሰረታዊ ማነቆዎች ሊፈቱ የሚችሉ ስትራቴጅክ ዓላማዎች፣ ለስትራቴጅክ ዓላማዎች ቁልፍ የስኬት መሰረት የሆኑ ውጤቶችን መለየት፣ በየደረጃው የተቀመጡትን ውጤቶች መለካት የሚያስችሉ ቁልፍ አሀዛዊና ገላጭ አመልካቾች ተቀምጠዋል፤ ውጤቶችን ለማሳካት ወሳኝ የሆኑ ትራንስፎርሜሽናል የትግበራ መስኮች ተለይተዋል። የእቅድ ዝግጅት ማዕቀፉ ላይ የተቀመጡ ቁልፍ የውጤት መስኮችና ውጤቶችን ለማሳካት የሚረዱ የትግበራ መስኮች መሰረት በማድረግ በትንተና የተደገፈ የተሟላ የዕቅድ ሰነድ እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

ክፍል II የዕቅዱ ዓላማዎች

የግብርና ዘርፍ ርዕይ

በ2022 የተሸጋገረ ግብርና በመፍጠር **በውስጣዊ ሸግግር** ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግና ከድህነት ማላቀቅ፤ ***ለሀጋራዊ ኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር*** ደግሞ ሀገሪዊ ምግብና ስርዓተ ምግብ ፍልጎት ያሟላ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትና ለወጪ ንግድ በቂ ምርት ያቀረብ ፣ ወደ እሴት ጭመራ የተራመደ እና በገጠር በቂ ስራ እድል የፈጠረ ዘርፍ ማድረግ ይሆናል።

ግብ

የግብርና ዘርፍ ዕቅድ ግብ ከሀገራዊ ኢኮኖሚው አስተዋፅኦ ማበርከት ሲሆን በሚቀጥሉት 5 ዓመታ ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢ ማሳደግ፣ የምግብና ስርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እና ለመዋቅራዊ ሽግግር አስተዋፅ ማድረግ ሲሆን ለሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ ትራንስፎርሜሽን በሚከተሉት መስኮች ላይ የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል። ግብርና ለጠቅላላ ምርት ያለው አስተዋፅ፣ አነስተኛ መጠን የተሰባጠረ የምግብ ምድቦችን መመገብ የቻሉ የአርሶ/አርበቶ አደሮች ቁጥር ማሳደግ፣ የምርት ስበስጥር ደረጃ ማሻሻል፣ የግብርና ምርት የወጪና ገቢ ምርት ሚዛን ማሻሻል፣ የግብርና-ኢንዱስትሪ ትስስር ማጠናከር፣ በግብርና የሚተዳደር የህብረተሰብ ክፍል እየቀነሰ እንዲሄድ ማስጫል፣ ከግብርና ልማት የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን መቀነስ ናቸው።

2.1 ስትራቴጅክ ዓላማ ፡ ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

የሰብል ምርትና ምርታማትን ለማሳደግ የምንከተለው የአመራረት ስርዓት በአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች እና በመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎች ሲሆን የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች ሶስት የምርት ወቅት (መኸር፣ በልግና መስኖ) እና የመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት እርሻዎች መሰረት አድርጎ የሚለማ ይሆናል። በዕቅዱ የተካተቱ ሰብሎች ሆርቲካልቸር፣ አዝርዕት፣ ቡና ሻይና ቅመማ ቅመምን ይይዛል።

በሁሉም የአመራት ስርዓቶች እና የሰብል ዓይነቶች የሰብል ምርትን ከ543 ወደ 707 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ዕቅድ የተያዘ ሲሆን የአዝርዕት ምርትን ከ362 ወደ 490 ሚሊየን ኩንታል፣ የሆርቲካልቸር ምርትን ከ181 ወደ 217 ሚሊየን ኩንታል፣ የቡና ምርትን ከ6 ወደ 8.9 ሚሊየን ኩንታል ፣ የሻይ ምርትን ከ0.8 ወደ 1 ሚሊየን ኩንታል፣ የምርት መጠን ለማድረስ ዕቅድ ተይሏል።

የሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ምርት አቅርቦት በተመለከተ የአበባ ምርት ከነበረበት 94556 ቶን ወደ 208196 ቶን፤ አትክልት, ስራስርና እጸ ጣዕም (ቨርብስ) ምርትን ከነበረበት 149,191 ቶን ወደ 765,916 ቶን፤ የፍራፍሬ ምርትን ከነበረበት 28,441 ቶን ወደ 72,298 ቶን ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል።

ከአጠቃላይ አነስተኛ ይዞታ የአዝርዕት ምርት ውሰጥ በመኽር ከ335.9 ወደ 425 ሚሊየን ኩንታል፣ በበልግ ከ21 ወደ 28 ሚሊየን ኩንታል፣ በመስኖ ከ7.6 ወደ 9.8 ሚሊየን ኩንታል የምርት ድርሻ የሚይዙ ሲሆን ትልቁ ድርሻ 92 በመቶ ከመኽር የሚገኝ ይሆናል። ከመስኖ የሚገኘው የአዝርዕት ምርትም ከፍተኛ ዕድገት እንዳለው ያሳያል።

ከአጠቃላይ የአነስተኛ ይዞታ ሆርቲካልቸር በመኽር ከ68 ወደ 86 ሚሊየን ኩንታል፣ በበልግ ከ47 ወደ 51 ሚሊየን ኩንታል ፣ በመስኖ ከ65 ወደ 68 ሚሊየን ኩንታል የምርት ድርሻ የሚይዙ ሲሆን በ5 ዓመቱ መጨረሻ ከመኽር፣ መስኖ እና በልግ ምርት በቅደም ተከተል 42 ፣ 25 እና 33 በመቶ ድርሻ ይኖራቸዋል።

የቅድመና ድህረ ምርት ብክነት መቀነስ

የተቀናጀ ተባይ መከላከል ዘዴን አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ በማሳደግ በ10 የተመረጡ ሰብሎችና ተባዮች ላይ መከላከል እንዲካሄድ በማድረግ ሊባክን የሚችለው የምርት መጠን በ1% ዝቅ እንዲል ይደረጋል፤ የድህረ ምርት ብክነት ዒላማ በዝርዝር ሰብሎች የተቀመጠ ሲሆን ለማሳያነት የስንዴ ምርት ብክነት ከ 14 በመቶ ወደ 5 በመቶ፤ ሽንኩርት ከ22 በመቶ ወደ 13 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ታቅዷል።

ጥራቱ ጤንነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ለገበያ የቀረበ ምርት መጠን

ለገበያ የሚቀርብ የሰብል ምርት መጠን በዝርዝር ሰብሎች የተቀመጠ ሲሆን ለማሳያነት ስንዴ አሁን ካለበት 9 ወደ 87 ሚሊየን ኩንታል፤በቆሎ ከ13 ወደ 163 ሚሊየን ኩንታል፤ቲማቲም ከ1 ወደ 8 ሚሊየን ኩንታል፤ አቮካዶ ከ290 ሺ ኩንታል ወደ 5 ሚሊየን ኩንታል ለማቅረብ በዕቅድ ተይሏል።

የኢንስፔክሽንና የምርመራ ውጤት ጥራትና ደህንነት በማሻሻል ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶች ተቀባይነት ያጡ የነበሩትን በአንድ በመቶ ዝቅ እንዲል ይደረጋል።

2.1.1. የአነስተኛ ይዞታ ያደገ የተሻሻሉ የሰብል ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች አጠቃቀም

የአርሶ አደሩን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን መጠቀም ያስፈልጋል። የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም ደግሞ በተጠቃሚዎች ዘንድ ተቀባነት ያላቸው ቴክኖሎጅዎች በምርምር እንዲፈልቁ ወይም እንዲላመዱ ማድረግ፤ አርሶና አርብቶ አደሩ በቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣አመለካከቱና ክህሎቱ እንዲጎለብት ማድረግ፤ የቴክኖሎጅ ግብዓት በሚፈለገው መጠን፣ወቅት፤ቦታ እና ተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ወሳኝነት ይኖረዋል። የሰብል ቴክኖሎጅዎች መጠቀም ስንል ከተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎች፣ማዳበሪያ፣ አግሮ-ኬሚካልና ሜካናይዜሽን በተጨማሪ የእርሻ መሬት በአግባቡ ለመጠቀም የአፈርና ውሃ እቀባ ተግባራት፤ የአሲዳማ አፈር ማከም ወይም የእርሻ መሬት የሚኖረውን የአፈር ለምነት እንዳይለቅ መንከባከብ፤ አርሶ አደሩ ከገበያ ተጠቃሚ የሚሆንበት የግብይት የምክር አገልግሎትና ስርዓት መዘርጋትን ያካትታል።

2.1.1.1 በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የሰብል ቴክኖሎጅ ማቅረብ

የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ሁሉንም የእሴት ሰንሰለት ተከትሎ ማፍለቅ ተግባር በምርምር ተቋማት የሚካሄድ ሲሆን በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ምርት የሚሰጡና ተባይን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን ወይም ምርታማነትን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂን በመኮረጅ እና የአግሮ-ኢኮሎጂ ተስማሚነታቸውን በማጥናት የኤክስቴንሽን ተግባራትን በማጠናከር የማስፋት ስራ የሚሰራበት ሲሆን ከመካከለኛና ረጅም ጊዜ ለየአግሮ-ኢኮሎጂው የሚሆኑ ዝርያዎችን ማፍለቅና ለተጠቃሚ ማቅረብ ከምርምርና ከፍተኛ ት/ት ተቋማት ይጠበቃሉ።

ለዚህም እንዲረዳ የምርምር ሥርዓቱ በተጠቃሚው ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸውን ቴክኖሎጂዎችና መረጃዎች (በቂ ዝናብ ላላቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ምርት የሚሰጡ ዝርያዎችን፣ የዕፅዋት በሽታና ተባይ ችግር በጎላባቸው አካባቢዎች ችግሩን የሚቋቋሙ ዝርያዎችን፣ የዝናብ እጥረት ላለባቸው አካባቢዎች ደግሞ ድርቅን ሊቋቋሙ የሚችሉ ዝርያዎችን በገበያ ተፈላጊ የጥራትና ሌሎች ባህሪያት ያላቸው) በማቅረብ ፍላጎት እንዲፈጠር መሥራት ያስፈልጋል።

በሀገራችን የአርሶ አደር አመራረት ደረጃ የተደረሰበት በምርምር ማሳ ከተገኘው የሚስተዋለው ሰፊ የምርታማነት ክፍተት (yield gap) የመነጨው በዋናነት በሰብል አያያዝ ልዩነት ምክንያት ነው። ስለሆነም የሰብል ምርታማነቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ ከተመረጠው የሰብል ዝርያ በተጓዳኝ የተሻሻሉ የአመራረት ዘዴዎች ማለትም አግሮኖሚውና የሰብል ጥበቃው በወጡ ምክረ-ሃሳቦች መሠረት ተሟልቶ ሊተገበር ይገባል።

በሂደቱም የግብርና አመራረቱ እንዲሻሻል አስፈላጊ ግብዓቶች ተሟልተው በአግባቡ ማከናወን የሚያስችል የዕውቀት ሽግግር እንዲኖር የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለተጠቃሚ ማህበረሰቡ ማካሄድ ይጠይቃል።የወረዳ ግብርና ልማት ባለሙያው በመጀመሪያ ደረጃ በቂ ሥልጠና አግኝቶ እውቀቱና ክህሎቱ እንዲያድግ በማድረግ ያላየውንና የማያቀውን የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ እንዲያሸጋግር መጠበቅ ሳይሆን አስቀድሞ እራሱ በሚገባ የሚያቀውን ለአርሶ አደሩ ማሳየትና መከታተል እንዲችል በሥልጠና ማረጋገጥ ይገባል። የዕውቀት ሽግግሩ ሥራም የአርሶ አደሩን አመለካከት በመቀየር የአመራረቱ ተግባር ላይ ለውጥ አምጥቶ ከገበያ ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ማስቻል ይፈልጋል። ይህም ሥራ የግብርና ምርምርና የኤክስቴንሽን ክንፉ ከመቼውም ጊዜ በላይ ጠንክራ ትስስር ፈጥረው በጋራ መንቀሳቀስ ይኖርባቸዋል። ለዚህም በሁለቱም በኩል የሚገኘው የአመራርና ፈፃሚ አካል ብቃት ኖሮት ለሥራው ሙሉ ተነሳሽነትና በቁርጠኝነት ለመሥራት ከላይ እስከ ታች ያለው ባለሙያ ሥራውን ያመነበትና ለማስፈፀምየ ተዘጋጀ ሊሆን ይገባል።

በግብርና ልማቱ ላይ የግል ሴክተሩ በስፋት እንዲሳተፉ ማበረታታትና መደገፍ የተቀመጠውን ሀገራዊ ግብ ለማሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ተገንዝቦ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ይጠይቃል። በግብርና ሙያ የተማሩትን እና በአግሪቢዝነስ ልማት ለመሰማራት የሚፈልጉትንም በልዩ ድጋፍ እንዲታቀፉ ዕድል መፍጠሩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደቱን እንደሚያጠናክረው ይታመናል።

ለቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርምር ልዩ ትኩረት በመስጠት እራሱን ችሎ በኢንስቲቲዩ ደረጃ እንዲደራጅ በማድረግ የዘረ-መል ጥበቃና አዳዲስ ዝሪያዎች የማፍለቅ፤ የተሻሻሉ የአመራረት ዘዴዎችና ሰብል ጥበቃ የምርምር ፕሮግራሞችን በመቅረጽ አዳዲስ ግኝቶችን እና ምክረ-ሃሳቦችን የማቅረብ፣ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ መቋቋም የሚያስችል ምርምር የማካሄድ፣ በእሴት ጭመራና ጥራት ማሻሻያ የምርምር ፕሮግራም በመቅረጽ ምክረ-ሃሳቦችን የማቅረብ፣ በአፈርና ውሃ ጥበቃ እና በግብዓትና መስኖ አጠቃቀም ላይ ያተኮረ የምርምር ፕሮግራም በመቅረጽ ምክረ-ሃሳቦችን የማቅረብ፤ የምርምር እና ኤክስቴንሽን ትስስር የሚያጠናክሩ ምክረ-ሃሳቦች የማመንጨት፣ የባዮ-ቴክኖሎጂ ምርምር አቅም የማሳደግ፣ ስነ-ምህዳርን ማዕከል ያደረገ ምርምር የማካሄድ እና አጠቃላይ የምርምር ተቋማዊ አቅምን በማጎልበት በዓለም ገበያ በተወዳዳሪነት መገዘለቅ የሚያስችል የንዑስ ዘርፉን ምርትና ምርታማነት የማሳደግ ሥራ ይሠራል።

ሀ)የሰብል ቴክኖሎጅ ማመንጨት

የሰብል ቴክኖሎጂና የአሰራር ማሻሻያ መረጃ አቅርቦት

የሰብል የአዝርዕት፣ ሆርቲካልቸር፣ ቡናና ሻይ ቅ/ቅመም ሰብሎች ዝርያን በማዳቀል፣ በመረጣና በባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎች በመታገዝ ወይም በማላመድ ዘዴ ለከፍተኛ ምርታማነት፣ ለተፈላጊ ጥራት ማሻሻል፤ የአፈር ንጥረ-ነገርና በውሃ አጠቃቀም ውጤታማ (nutrient and water use efficient) የሆኑ ዝርያዎች ለማውጣት ምርምር ማካሄድ፤ የሰብል ዕደገትን የሚገቱ እንደ የዝናብ ዕጥረት፣ የአፈር ኮምጣጣነት፣ የአፈር ጨዋማነት እና የመሳሰሉትን ተዕዕኖ ለመቋቋም እንዲችሉ ዝርያዎችን ማሻሻል፤ በአሁኑ ጊዜ ለሰብል ልማት ስጋት እየፈጠሩ ያሉ የእፅዋት በሽታዎችና ተባዮችን እንዲቋቋሙ ዝርያዎችን ማሻሻል፤ ለግብርና ሜካናይዜሽን አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲያስችል በተለይም በጤፍ ላይ የሚገጥሙን የመውደቅ ችግር (lodging problem) የሚቋቋሙ ዝርያዎችን እንዲሁም በሰሊጥ ላይ ደግሞ ዘራቸው የማይበተን ዝርያዎችን (shattering resistant varities) ለማውጣት ምርምር ማካሄድ፤

በእፅዋት ባዮቴክኖሎጂ በመታገዝ ለተመረጡ የሰብል ዓይነቶች በቲሹ ካልቸር ንፁህ ዘር በብዛት ለማባዛት የሚያስችል ፕሮቶኮል ማዘጋጀት፤ የዝርያ ማሻሻያ ሂደቱን ለማፋጠን የሚያግዙ የባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎች ማውጣት፤ በባዮቴክኖሎጂ ዘዴ ታግዞ የተመረጡ ሰብሎችን የምግብ ንጥረ-ነገር ይዘት የጨመረ (biofortification) እና ረዘም ላለ ጊዜ ሳይበላሹ የሚቆዩ ዝርያዎችን ለማውጣት ማሻሻል፤ ዘረመላቸው የተለወጠ (genetically modified organisms) የአካባቢን ለውጥ ተዕዕኖ እንደ እፅዋት በሽታ እና የመሳሰሉትን መቋቋም የሚችሉ ዝርያዎችን በማላመድ በሂደትም ተፈላጊውን ዘረመል በመለየትና ወደ ተመረጠ የሰብል ዝርያ ባባዮቴክኖሎጂ ዘዴ በማስገባት (introgression) ማሻሻል፤

የሰብል ዝርያ ባለው የጀኔቲክ አቅም ድረስ ምርታማነቱን ጠብቆ እንዲሰጥ የሚያግዘውን የተሻሻሉ ወቅታዊ የሰብል አግሮኖሚ ምክረ-ሃሳቦች ለማቅረብ በሰብል እና በአመራረት ዓይነቶች ላይ ተመርኩዞ ምርምር ማካሄድ፤ የሰብል ጤንነት በተጠበቀ ሁኔታ ማምረት የሚያስችል የተቀናጀ የሰብል ጥበቃ ምክረ-ሃሳብ ለማቅረብ የሚረዳ የምርምር አቅም መገንባትና የተጠናከረ የሰብል ጥበቃ ምርምር ማካሄድ፤ የሰብል ድህረ-ምርት ብክነትን ለመቀነስ የሚያስፈልጉ የአያያዝ ማሻሻያ ምክረ-ሃሳቦች ለማቅረብ ምርምር ማካሄድ።

ለምግብነት የሚውሉ የግብርና ምርቶችን የምግብ ንጥረ-ነገር ይዘት የማዳበር ዘዴ (food formulation) ፣ በምግብ የማቀነባበሪያ ሂደት ወይም በማብሰል ወቅት የሚባክኑ ንጥረ-ነገሮችን ለመቀነስ የሚያስችል የአሰራር ዘዴ እና ምግብን ለረዥም ጊዜ ሳይበላሽ የማቆያ ዘዴን (preservation) ማቅረብ፤

የግብርና ምርት ዕሴት ሰንሰለት ዙሪያ የሚገጥሙ ተግዳሮቶችን በመለየት ወቅታዊ የመፍትሄ ምክረ-ሃሳቦችን ማውጣት፤ ለተለያዩ የግብርና ኮሞዲቲዎች አመራረት፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እና የግብርና ሜካናይዜሽንን የተመለከተ የቴክኖሎጂ አዋጭነት ጥናት በማካሄድ ውጤታማነትን የሚያሳድግ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ፤ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ሥርፀትና ፋይዳ (technology adoption and impact) ጥናት በማካሄድ መረጃ ማቅረብ፤

ለአትክልት ሰብሎች ዘር ብዜት ተስማሚ የሆነ የአየር ሁኔታ ያላቸውን አካባቢዎች በመምረጥ ለተወሰኑ የአትክልት ዓይነቶች የማባዛት ሥራን ማስጀመር፤

የሰብል ዘር ጥራትን እና ምርታማነትን የሚያስጠብቁ የተሟላ የዘር አመራረት፣ የድህረ ምርት አያያዝ እና የዘር ግብይት ሂደትን በአግባቡ ለማከናወን የሚረዱ የግብርና አሠራር መረጃዎችን ማቅረብ፤ በአገሪቱ የዘር ሥርዓት ውስጥ የዘር ጥራት ስታንዳርድን ለመከለስ የሚያስችሉ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ መረጃዎችን ማቅረብ፤

የሰብል አመራረትን ለአነስተኛና መካከለኛ የሰብል አመራረት ደረጃዎች የሚስማሙ የሜካናይዜሽን ዓይነቶች ከመሬት ዝግጅት አንስቶ ለዘር መዝሪያ፣ ለማዳበሪያ መስጫ፣ ለአረም ማረሚያ፣ ለመድኃኒት መርጫ፣ ለማጨጃ እና ለመውቂያ የሚውሉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ለተለያዩ ሰብሎችና የአፈር ዓይነቶች በማላመድ ወይም በመስራት ለማቅረብ ምርምር ማካሄድ፤ የዕቀባና የእቅጩ እርሻ (conservation agriculture and precision farming technologies) መሣሪያዎችን ማላመድና የማሻሻል ሥራን መሥራት

የሰብል ምርትን ለማንቀዝ፣ ዘር ለማበጠር፣ በዘር ጥራት ደረጃው ለመለየት እና ለማከማቸት ሚያስፈልጉ የሜካናይዜሽን መሣሪያዎችን ለተለያዩ የሰብል ዓይነቶች በማላመድ ወይም በመሥራት ማሻሻል፤ የተለያዩ የፍራፍሬ ዓይነቶችን ጭማቂ (jam, juice, nectar) ማዘጋጃና ማሸጊያ ተስማሚ መሣሪያዎችን ማላመድ ወይም መሥራት፤

ለሆርቲካልቸር ልማት ተስማሚና ደረጃቸውን የጠበቁ ቴክኖሎጂዎች ማቅረብ፣

በሀገር ውስጥ በቀላሉ ሊመረቱ የሚችሉ የሆርቲካልቸር ልማት ቴክኖሎጂዎች (ኔት ሀውስ፣ ግሪን ሀውስ እና ተነል እንዲሁም የከተባ ቢላዋ እና መቀሶች) እንዲመረቱ እንዲሁም የምርት ማሸጊያ ማቴሪያል/ቴክኖሎጂ/ ጥራትን እንዲሻሻል በሀገር ውስጥ ለሚያመርቱ ድርጅቶች የጥራት ደረጃ ማውጣትና እንዲመረት በማድረግ የውጭ ምንዛሪን የማዳን ስራ ይሰራል፡፡

ለ)የሰብል መነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

የሰብል ዝርያን መነሻ ዘር (early generation seed) በበቂ መጠንና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለማቅረብ እንዲቻል መስኖን በመጠቀም በዓመት ሁለት ጊዜ የማምረት ስልቶችን እና ሌሎች ተግባራዊ አማራጮችን መከተል፤ለዘር ብዜት ቀዝቃዛ ሥፍራን (chilling temperature) ለሚፈልጉ የአትክልት ሰብሎች ተስማሚ የአየር ሁኔታ ያላቸውን አካባቢዎች በመምረጥ ለተወሰኑ የአትክልት ዓይነቶች የማባዛት ሥራን ማስጀመር፤

የመነሻ ዘር ጥራቱን እና ምርታማነቱን የሚያስጠብቅ የተሟላ የሰብል አያያዝ (አግሮኖሚ እና ሰብል ጥበቃ) አሰራርን በመከተል የብዜት ሥራን እስከ ማከማቸት ሂደት (eg. seed processing, seed treatment, drying, packaging) ድረስ ያለውን በአግባቡ ማከናወን፤

የሰብል መነሻ ዘር ብዜት ሥራውን እና የዘር ጥራቱን ስታንዳርድ ለማስጠበቅ የአሰራር ሥርዓቱን ማጠናከር፤

ሐ)የሰብል ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ቅድመ-ማስፋፋት

አዳዲስ የሚወጡ የሰብል ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ ወጣቶችና ሴቶችን ያማከለ አዋጭ ቴክኖሎጂ በመለየት ማሸጋገር፤

በቅርቡ እየተቋቋሙ ላሉት የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች የሆርቲካልቸር፣ አዝርዕት እና የቡና የሰብል ምርት አቅርቦትን ለማሳደግ በተመረጡ ሰብሎች አመራረት ላይ የቅድመ-ማስፋት ሥራ ማካሄድ፤

መ)በሰብል ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ሥልጠና መስጠት

የግብርና ልማት ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴዎችን መከተል እንዲችል የሚያግዝ ዕውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ የሰብል ምርት ተኮር የሆነ ተከታታይ ሥልጠና ለኤክስቴንሽን የግብርና ባለሙያ እና ለተጠቃሚው አካል መስጠት፤

የምርምር የሰው ኃይልን ለማጎልበት በድህረ-ምረቃ ደረጃ በተለያዩ ስፔሻላዜሽኖች ተመራማሪዎችን በማሰልጠን የዕውቀትና የክህሎት ደረጃቸውን ማሳደግ፤

ምርምርን በጥልቀት ለማካሄድና አስተማማኝ ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስፈልጉ የምርምር መሠረተ-ልማቶች በተለይም ያሉትን ላቦራቶሪዎች ዘመኑ ባፈራው ሳይንሳዊ መሣሪያዎች እና የኢኮቴ አገልግሎት ከዳታ መሰብሰብ አንስቶ

2.1.1.2 በሰብል ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር

በአጭር ጊዜ ከሚጠበቀው ውጤት አንዱ በአዝርዕት፣ ሆርቲካልቸርና ቡና ሻይና ቅ/ቅመም ተገቢ የሆነ የኤክስቴንሽን አደረጃጀትና አሰራርና ስልቶች በመንደፍ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር በቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ማሳደግ ነው፡፡ የዕውቀት ሽግግሩ አርሶ አደሮች ተወዳዳሪ እና ጥራቱን የጠበቀ ቴክኖሎጂዎች ግብዓት መጠቀም የሚችልበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ሀ) የአዝርዕት ሰብል ልማት ምክርና ስልጠና

የአዝርዕት ሰብሎች ልማት የእህልና የምርጥ ዘር ማምረትን ያጠቃልላል፡፡የአዝርዕት ሰብል ምርትና ምርታማነት ዕድገት የሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ዕድገት ውጤት ነው፡፡እነዚህም የለማ ማሳ መጠን እና የሰብል ምርታማነት እድገት በሄ/ር ናቸው፡፡ዓለም አቀፍ ልምዶች እንደሚያሳዩት በምርታማነት ዕድገት የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎች ድርሻ ከ50-60 በመቶ እንዲሁም የተሻሻሉ አሰራሮችና ሌሎች ግብዓቶች በምክረ-ሃሳቡ መጠቀም ከ40-50 በመቶ ድርሻ እንደሚኖራቸው ይተነብያሉ፡፡

በሌሎች ሀገራት በ2017 በአማካይ የስንዴ ምርታማነት ከ101 ኩ/ል በሄ/ር በላይ፣ ሩዝ 93 ኩ/ል በሄ/ር በላይ እና በቆሎ ከ257 ኩ/ል በሄ/ር በላይ ድረስ ተመርቷል፡፡በአገራችን በተመሳሳይ ወቅት በአማካይ ስንዴ 28 ኩ/ል በሄ/ር፣ ሩዝ 29 ኩ/ል በሄ/ር እና በቆሎ 37 ኩ/ል በሄ/ር የተመዘገበ ሲሆን ከ4 እስከ 7 እጥፍ ዝቅ ያለ ምርታማነት ደረጃ ላይ እንዳለን ለመረዳት ተችሏል፡፡ለዚህም ዝቅተኛ ምርታማት ምክንያት በአነስተኛ አርሶ አደሮች ማሳ የሚከናወንና እና ዝናብ ጠባቂ ልማት በመሆኑ ውጤታማነቱ የአገሪቱን ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች ማለትም የምግብ እና ሥነምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ የአግሮኢንዱስትሪ ፍላጎትን ማሟላትን፣ የኤክስፖርት ግብን ማሳካትንና ከውጭ የሚገባውን የሰብል ውጤቶችን ማስቀረት ያልቻለ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከዚህም የተነሳ በ2017 ከእህል ሰብሎች በስንዴ ብቻ 10.7 ሚሊየን ኩንታል ምርት እንዲሁም የሌሎች ሰብሎችን ጨምሮ 17.4 ሚሊየን ኩንታል ምርት በ 640 ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር ወጪ ለማድረግ ተገደናል፡፡

ይህን ሁኔታ ለመቀየር ለማሳያነት ስንዴን ብንወስድ ምርታማነት ከ 30 ወደ 38 ኩንታል በሄ/ር ለማድረስ በዕቅድ ተይዟል፡፡ ይህም ማለት በአማካይ 18 በመቶ ዓመታዊ ዕድገት ይኖራዋል፡፡ አብዛኛው የምርታማነት ዕድገት አማጭ የሆኑ ቴክኖሎጅዎችን(ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ አግሮ-ኬሚካል፣ ሜካይዜሽን) በመጠቀም፣ እድገትን የሚያፋጥኑ ሆርሞኖች፣ ማይክሮ ንጥረ-ነገሮችን /Mn, Cu, Mg, B, Zn/ በቅጠሉ ላይ መርጨት፣የአርሶ አደሩን ዕውቀት፣አመለካከትና ክህሎት በማሳደግና የተፈጥሮ ሀብትን (የአፈር ለምነትና ጤንነት፣ ተፋሰስ ልማት፣ መስኖ፣የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲ ማሻሻል) መሰረት ያደረገ ነው፡፡

የአዝርዕት ሰብሎች/አገዳ፣ብርዕና ጥራጥሬ ሰብሎች/ የምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተነደፉትን ግቦች ለማሳካት ይቻል ዘንድ በቀጣይ አምስት ዓመታት በአዝርዕት ሰብል ልማት ምክርና ስልጠና አገልግሎት የሚከተሉት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የአዝርዕት ልማት ፓኬጅ ዝግጅት

የአዝርዕት ሰብል ምክር አገልግሎት ለመስጠት የቴክኖሎጅ ፓኬጅ የሚዘጋጅ ሲሆን ፓኬጁ በመሬት ዝግጅት፣ዝግጅት፣አዘራርና ግብዓት አጠቃቀም፣ሰብል አያያዝና ጥበቃ፣ሰብል ስብሰባና ድህረምርት አያያዝ ላይ ከምርምር የወጡ/የሚወጡ ቴክኖሎጅና የመረጃ አቅርቦትን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

በተንቀሳቃሽ ላቦራቶሪ የአፈር ንጥረ-ነገር ምርመራ መሠረት ያደረገ የማዳበሪያ ምክረ-ሃሳብ አገልግሎት ማስፋፋት፡-አፈርና ሰብልን መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ አጠቃቀም እውን ለማድረግ በስፋት ይዘረጋል፤ የህያው ማዳበሪያ አጠቃቀምን ማሳደግ፡- እስከ 2011 ምርት ዘመን በነበረው ጊዜ ውስጥ የጥራጥሬ ሰብሎች ልማትን ለማሳደግ የህያው ማዳበሪያ አጠቃቀምን በ172,000 ሄ/ር ደረጃ ማሳደግ እንደተቻለ የአቅራቢዎችና የተጠቃሚ ክልሎች ሪፖርት ያመለክታል፡፡ በቀጣይ ዓመታትም ይህን በማስፋት ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ በትኩረት ይሰራል፡፡፤

የአሰልጣኞችና የአርሶ አደር ስልጠና

የተዘጋጀውን ፓኬጅ ወደ አርሶ/አርብቶ አደሩ ለማድረስ በየደረጃው የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል በተለይም የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በተግባር የተደገፈ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓኬጅ ስልጠናውን በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ለአርሶ አደሩ እንዲያደርሱ ይደርጋል፡፡

የመስክ ድጋፍና ክትትል

የአሰልጣኖች ስልጠናንና የአርሶ/አርብቶ አደር ስልጠናዎች ከተሰጡ በኃላ የፓኬጆችን ትግበራና የአፈፃፀም ደረጃ መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የድጋፍና ክትትል ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ የድጋፍና ክትትል አሰጣጥ የድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ በማዘጋጀት ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

በሰርቶ ማሳያ ማስተዋወቅ

በምክርና ስልጠና አገልግሎት አሰጠጥ ሌላው ተግባር የተሻለ አፈፃፀም ባላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ ቀን በማዘጋጀት በአቅራቢያው ያሉ አርሶ አደሮች ትምህርትና ልምድ እንዲወስዱ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ተግባር በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በየደረጃው የሚከናወን ሲሆን አገር አቀፍ የመስክ ቀን ዝግጅት ግን ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

በመስክ ድጋፍና ክትትልና ከምናካሂዳው ሰርቶ ማሳያዎች የሚገኙ የአዝርዕት ልማት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ አብዛኛው አርሶ አደር ማስፋት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ይሆናል፡፡

ለ) ሆርቲካልቸር ሰብል ልማት ምክርና ስልጠና

የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርትና ምርታማነት ዕድገት የሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ዕድገት ውጤት ነው፡፡ እነዚህም የለማ ማሳ መጠን እና የሰብል ምርታማነት እድገት በሄ/ር ናቸው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሆርቲካልቸር ሰብሎች የምርታማነት እድገት ከፍተኛ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በቲማቲም 687ኩ/ል በሄ/ር፣ በድንች 448 ኩ/ል በሄ/ር፣ በአቮካዶ 164 ኩ/ል በሄ/ር፣ በማንጎ 266 ኩ/ል በሄ/ር እንዲሁም በሙዝ 658 ኩ/ል በሄ/ር አማካይ ምርታማነት የሚያገኙ ሲሆን በሀገራችን በቲማቲም 52 ኩ/ል በሄ/ር፣ በድንች 137 ኩ/ል በሄ/ር፣ በአቮካዶ 33 ኩ/ል በሄ/ር፣ በማንጎ 75 ኩ/ል በሄ/ር እንዲሁም በሙዝ 88 ኩ/ል በሄ/ር አማካይ ምርታማነት የምናገኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለዚህም ዋናኛው ምክንያት ንዑስ ዘርፉ ባብዛኛው በአነስተኛ አርሶ አደሮች ማሳ የሚከናወንና እና ዝናብ ጠባቂ ልማት በመሆኑ ውጤታማነቱ

የአገራቱን ስትራቴጂክ አቅጣጫዎች ማለትም የምግብ እና ሥነምግብን ዋስትና ማረጋገጥ፣ የአግሮኢንዱስትሪ ፍላጎትን ማሟላትን፣ የኤክስፖርት ግብን ማሳካትንና ከውጭ የሚገባውን የሰብል ውጤቶችን ማስቀረት ያልቻለ ነው። ከዚህም የተነሳ ከሆርቲካልቸር የአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ስራስር፣ ቡና፣ ሻይና ቅ/ቅመምን ጨምሮ 1,310,110 ኩ/ል ከውጭ ገበያ እንዲቀርብ በማድረግ 89,497,000 የአሜሪካን ዶላር ወጪ ለማድረግ ተገደናል። ይህ ደግሞ የዘርፉን ውጤታማነት ማነስ ያመላክታል። የዘርፉ ዋና አቅጣጫ የሚሆነው የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

የሆርቲካልቸር ሰብሎች እጅግ በጣም ጥንቃቄ የሚሹና አሰራሩም ከፍተኛ ዕውቀትና በክህሎት የሚሹ ናቸው። በመሆኑም ዘመናዊ የአሰራር ስርዓትን በመከተልና ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉና በአፈፃፀም ወቅት ክፍተት የነበረባቸውን (missing elements) ተግባራት ማለትም ወቅቱን ጠብቆ ማሳን ማዘጋጀት፣ የዘር መጠንን ጠብቆ መዝራትን፣ በአንድ ዩኒት ማሳ ስፋት ውስጥ መኖር የሚገባውን የቡቃያ/ተክል ቁጥር እንዲኖር ማድረግን፣ ተገቢው አግሮኬሚካል ምክረ-ሀሳቡን በሚያዘው መጠን መጠቀምንና ተገቢ የማሳ አንክብካቤን፣ ምርትን በወቅቱ ማሰባሰብን እና የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስን በማረጋገጥ ተግባራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል። እስካሁን ያለው የልማት ሰራተኞች በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ለአምራቹ አካል ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል ዕውቀትና ክህሎት ጨብጠው ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማይወጡ በመሆናቸው ያለውን ክፍተት የሚሞላ የአቅም ግንባታ ተግባር በአጭር ጊዜ መፈፀም ያስፈልጋል። በመካከለኛና በረጅም ጊዜ ደግሞ በ2011 ዓ.ም. የተቀረፀውን የሆርቲካልቸር ካሪኩለም አምቅ አቅም ላላቸው አካባቢዎች በቂ የልማት ሰራተኞችን በሆርቲካልቸር ሳይንስ በማሰልጠን ወደ ስራ እንዲገቡ ይደረጋል። ከዚህም ባሻገር በሆርቲካልቸር ልማት ዘርፍ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላትና ምሩቅ ወጣቶችና ሴቶችን የስፔሻላይዜሽን ስልጠና እና ተገቢውን ዕገዛ እንዲያገኙ በማድረግ ለዘርፉ ዕድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ በትኩረት ይሰራል።

በቀጣይ አምስት ዓመታት የሆርቲካልቸር ሰብሎች/አትክልት፣ፍራፍሬና ስራ ስር ሰብሎች/ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና ገበያ ተኮር እንዲሆን ለማድረግ የተቀመጡ ዒላማዎችን ለማሳካት ይቻል ዘንድ በሆርቲካልቸር ልማት ምክርና ስልጠና አገልግሎት የሚከተሉት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

አነስተኛ ሆርቲካልቸር ልማት ፓኬጅ ዝግጅት

የሆርቲካልቸር ሰብል ምክር አገልግሎት ለመስጠት የቴክኖሎጅ ፓኬጅ የሚዘጋጅ ሲሆን ፓኬጁ በመሬት ዝግጅት፣ አዘራርና ግብዓት አጠቃቀም፣ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም፣ ሰብል አያያዝና ጥበቃ፣ ሰብል ስብሰባና ድህረምርት አያያዝ ላይ እንዲሁም በፍራፍሬ ከቲሹ ከልቸር ማዕከላት የሚወጡ ችግኞች አተካከልና እንክብካቤ፣ የፍራፍሬ ችግኝ ማባዛትና አተካከል፣ የመልካም እርሻ አተገባበር ስርዓትን ከማስፈን አኳያ ከምርምር የወጡ/የሚወጡ ቴክኖሎጅና የመረጃ አቅርቦትን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ ይሆናል።

የአሰልጣኞች እና የአርሶ አደር ስልጠና

የተዘጋጀውን ፓኬጅ ወደ አርሶ/አርብቶ አደሩ ለማድረስ በየደረጃው የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል በተለይም የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በተግባር የተደገፈ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓኬጅ ስልጠናውን በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ለአርሶ አደሩ እንዲያደርሱ ይደረጋል።

የመስክ ድጋፍና ክትትል

የአሰልጣኖች ስልጠናንና የአርሶ/አርብቶ አደር ስልጠናዎች ከተሰጡ በኃላ የፓኬጆችን ትግበራና የአፈፃፀም ደረጃ መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የድጋፍና ክትትል ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል። የድጋፍና ክትትል አሰጣጥ የድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ በማዘጋጀት ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል።

ሰርቶ ማሳያ ማካሄድ

በምክርና ስልጠና አገልግሎት አሰጠጥ ሌላው ተግባር የተሻለ አፈፃፀም ባላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ ቀን በማዘጋጀት በአቅራቢያው ያሉ አርሶ አደሮች ትምህርትና ልምድ እንዲወስዱ ማድረግ ነው። ይህ ተግባር በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በየደረጃው የሚከናወን ሲሆን አገር አቀፍ የመስክ ቀን ዝግጅች ግን ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፌደራል አስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል።

በመስክ ድጋፍና ክትትልና ከምናካሂዳው ሰርቶ ማሳያዎች የሚገኙ የሆርቲካልቸር ልማት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ አብዛኛው አርሶ አደር ማስፋት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ይሆናል።

ሐ) የቡናና ቅመማ ቅመም ሰብል ልማት ምክርና ስልጠና

የቡና ሻይ ቅመማ ቅመም ኤክስቴንሽን አገልግሎት እና ስርዓት

ለቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት ተስማሚ ስነ-ምህዳር እና ከ5.6 ሚሊዮን በላይ አምራች አርሶ አደሮች ቢኖሩትም በንዑስ ዘርፉ ላይ ያተኮረ የተጠናከረ የኤክስቴንሽን ሥርዓት ባለመመዘርጋቱ፣ የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ምርታማነትን ማሳደግ ሳይቻል ቆይቷል።

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርቶች በሚመረቱባቸው አካባቢዎች ዘመናዊ የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ አደረጃጀቶችንና የግንኙነት አሰራሮችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል። የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ጣቢያዎችን፣ ሠርቶ ማሳያ ቦታዎችን፣ዘመናዊ ቴክኖሎጂና ግብዓት አጠቃቀም ፓኬጆችን፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ስርጭት ዘመናዊ የኮሙኒኬሽን ሚዲያዎችን እና በሙያው የሰለጠነ የኤክስቴንሽን ሰራተኛ የማደራጀት የማስፋፋትና የማጠናከር ሥራ ይሰራል።

ስለሆነም በቀጣይ የዕቅድ ዘመን የተሻሻሉ የግብርና አሰራር ዘዴዎችን አጠቃቀም በማሳደግ፣ በዘርፉ ዘመናዊ የኤክስቴንሽን ስርዓት በመዘርጋትና ተደራሽ በማድረግ የአምራቹን አመለካከት ዕውቀትና ክህሎትን በማሻሻል፣ምርጥ ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋት፣ ያረጁ በማደስ በማደስ፣ የግብዓት አቅርቦትና አጠቃቀም በማሳደግ፣ የድህረ-ምርት አያያዝና ጥራት በማሻሻል እና በዘርፉ የወጣቶችና ሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት በማሳደግ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች እና በሰፋፊ እርሻዎች ልማት የሚገኝ የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ይሰራል።

የቡና ሻይ ቅመማ ቅመም ልማት ፓኬጅ ዝግጅት

የቡናና ቅመማ ቅመም ሰብል ምክር አገልግሎት ለመስጠት የቴክኖሎጅ ፓኬጅ የሚዘጋጅ ሲሆን ፓኬጁ በመሬት ዝግጅት፣አዘራርና ግብዓት አጠቃቀም፣ሰብል አያያዝና ጥበቃ፣ሰብል ስብሰባና ድህረምርት አያያዝ፣ ያረጀ ቡና ዕደሳ ላይ ከምርምር የወጡ/የሚወጡ ቴክኖሎጅና የመረጃ አቅርቦትን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ ይሆናል።

በእርጅና ምክንያት ምርታማነቱ የቀነሰ ከ650,000 ሄ/ር በላይ የቡና ማሳ የሚገኝ ሲሆን በየመቱ 130,000 ሄ/ር (20%) በጉንደላ እና በነቅሎ ተከላ ዘዴ በማደስና ተገቢውን እንክብካቤ በማድረግ ምርታማነትን በላቀ ደረጃ ማሳደግ ይቻላል። ስለሆነም በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን የቡና አምራች አርሶ አደሩ እና ባለሃብቱ በቡና ዕደሳ ያላቸውን ዕውቀትና ክህሎት በተከታታይ ስልጠናና ሰርቶ ማሳያ በማሳደግ፣ ለዕደሳ ሥራ የሚያገለግሉ ግብዓቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በየወቅቱ እንዲቀርብ በማድረግ፣በቡና ዕደሳ ወቅት የሚያጋጥመውን የገቢ ጉድለት ለመደጎም ደባል ሰብል ልማት በተጓዳኝነት በማልማት ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ይሰራል።

የአሰልጣኞች እና አርሶ አደር ስልጠና

የተዘጋጀውን ፓኬጅ ወደ አርሶ/አርብቶ አደሩ ለማድረስ በየደረጃው የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል በተለይም የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በተግባር የተደገፈ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓኬጅ ስልጠናውን በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ለአርሶ አደሩ እንዲያደርሱ ይደርጋል።

የመስክ ድጋፍና ክትትል

የአሰልጣኖች ስልጠናንና የአርሶ/አርብቶ አደር ስልጠናዎች ከተሰጡ በኃላ የፓኬጆችን ትግበራና የአፈፃፀም ደረጃ መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የድጋፍና ክትትል ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ የድጋፍና ክትትል አሰጣጥ የድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ በማዘጋጀት ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፊዴራል አስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

ሰርቶ ማሳያ

በምክርና ስልጠና አገልግሎት አሰጠጥ ሌላው ተግባር የተሻለ አፈፃፀም ባላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ ቀን በማዘጋጀት በአቅራቢያው ያሉ አርሶ አደሮች ትምህርትና ልምድ እንዲወስዱ ማድረግ ነው፡፡ ይህ ተግባር በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በየደረጃው የሚከናወን ሲሆን አገር አቀፍ የመስክ ቀን ዝግጅት ግን ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፊዴራል አስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

በመስክ ድጋፍና ክትትልና ከምናካሂዳው ሰርቶ ማሳያዎች የሚገኙ የቡና ሻይ ቅመማ ቅመም ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ አብዛኛው አርሶ አደር ማስፋት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ይሆናል፡፡

በቡና ሻይና ቅመማቅመም ምርቶች ስራ ላይ ለተሰማሩ የቀን ሰራተኞችን የኤች አይቪ/ኤድስ መከላከል ተግባራትን እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ማከናወን

2.1.1.3 የሰብል ጥበቃ

መጤ ተምችና የመደበኛ ተባዮችን መከላከል

የተዛማች ተባዮችን ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውለው የፀረ ተባይ መጠን በ2011/12 ከተደረሰበት 360533 ሊትር ወደ2 ሚሊየን ሊትር ከፍ በማድረግ የተባዮቹ ጉዳት ከ3% በታች እንዲሆን ማድረግ፤ የመደበኛ ተባዮችን ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውለው የፀረ ተባይ መጠን ወደ 2.5 ሚሊየን ሊትር ከፍ በማድረግ የተባዮቹ ጉዳት ከ5 በመቶ በታች እንዲሆን ማስቻል፤የተቀናጀ ተባይ መከላከል ዘዴን አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ በማሳደግ በ10 የተመረጡ ሰብሎችና ተባዮች ላይ መከላከል እንዲካሄድ በማድረግ ሊባክን ከሚችለው የምርት መጠን በ1% ዝቅ እንዲል ይደረጋል፤

በአገራችን እየተስፋፉ የሚገኙትን ዋና ዋና ተባዮች ለአብነት የአሜሪካን መጤ ተምች፣የበቆሎ ገዳይ የቫይረስ በሽታ፣ የማንጎ ነጭ ስኬል፣የቡና ድንችና ዝንጅብል አጠውላጊ የባክቴሪያ በሽታዎች፤የስንዴ ዋግ፣መጤ ወራሪ አረሞችና ሌሎች ተባዮች ከምርምር በሚገኙ አዳዲስና ነባር የተቀናጀ ተባይ መከላከል ቴክኖለጂዎች በመጠቀም የመደበኛ ተባዮችን መከላከል ሥራ እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

የተዛማች ተባዮች ክስተት ቅድሚያ በማስጠንቀቅ መከላከል

የተባይ ክስተት ትንበያና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አሠራር ሥርዓት በመዘርጋት በስንዴ ዋግ፣ በበረሃ አንበጣ፣ በአፍሪካ ተምችና በግሪሳ ወፍ መከላከል የሚሳተፉ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከወረርሺኝ መከሰት ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው ይደረጋል፤

የተባይ መከላከል አገልግሎት (የፀረተባይ ርጭትና ማጠንት..) የሚሰጡ 50 ቡድን እንዲቋቋሙ በማድረግ 350 ወጣት ወንዶችና 150 ሴቶች እንዲደራጁ ከሚመለከታቸው አካላት በትብብር ይሠራል፣ የተደራጁት የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የተዛማች ተባዮች ክስተት ቀድሞ በመተንበይና አርሶ/አርብቶ አደሩን በቅድሚያ በማስጠንቀቅ ለመከላከል እንቅስቃሴው እንዲዘጋጅ ማድረግ፡፡ መንግሥትም አስፈላጊውን ፀረ ተባይ፣ የመከላከያ ትጥቅ፣ የመርጫ መሣሪያና ሌሎች የሎጂስቲክስ አቅርቦት ቀድመው እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ ተባዮቹ ሲከሰቱም እንደ አግባቡ በአውሮፕላን (፣በመኪና በሚጠመድና በጀርባ በሚታዘል መርጫ መሣሪያ በመጠቀም በፊዴራል መንግሥት ወጪ መከላከል እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ በዚሁም በተባዮቹ ሊባክን ይችል የነበረውን መጠን እንዲቀንስ አስተዋፅዖ ያደርጋል::

የተቀናጀ የሰብል ጥበቃ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ

ምክንያቱም ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ተባዮች ምርቱን በጥራት፣ በደህንነትና በመጠን ብክነት አንዳያደርሱ በብቃት በመከላከል ለምርትና ምርታማነት ማደግ አስተዋፅዖ ማድረግ የሚያስችሉ ተግባራት ማከናወን ነው፡፡ ለዚሁም የተዛማች ተባዮችና የመደበኛ ተባዮች (የጎተራ ተባዮችን ጨምሮ) ክስተት ከማጋጠሙ በፊት በትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመታገዝ፣ የተባይ ክስተት ሲያጋጥም ደግሞ ተገቢውን የመከላከያ ዘዴ በመጠቀም ወቅቱን ጠብቆ ጉዳት ሳያስከትሉ መከላከል ሲቻል ነው፡፡ ይሀንን በዋናነት ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ ከምርምር በሚገኙ በዋናነት የተቀናጀ ተባይ መከላከያ ዘዴ በመተግበር፤ፀረ ተባይና የሥነ ሕይወታዊ የተባይ መከላከያ ዘዴ፣ባህላዊ የመከላከያ ዘዴ በመጠቀም፣በአይሲቲ የተደገፈ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ሥርዓት በመዘርጋትና የተባይ ልየታና የአግሮኬሚካል ጥራትና ይዘት ለመመርመር አንድ ዘመናዊ ላቦራቶሪ ገንብቶ ወደ ሥራ በማስገባት ነው፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ዝርዝር ተግባራት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ፀረ ተባይ ርጭት አገልግሎት አሰጣጥን ማጠናከር

የፀረ ተባይ አጠቃቀምና አያያዝ ከጤናና ከአከባቢ የተያያዙ ችግሮችን ማቃለል እንዲያግዝ የፀረ ተባይ ርጭት አገልግሎት ዕውቀትና ብቃት ባላቸው ሰዎች እንዲከናወን የሰለጠኑ የግሉ ሴክተር አባላት በተለይም ወጣት ሴቶችና ወጣት ወንዶች ተደራጅተው ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል አገልግሎቱ (Pest Management Support Service Providers) እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ ፀረተባይ ከአከባቢው የእርሻ አገልግሎት ማዕከል (Farm Service Center) ወይም ከፀረተባይ አስመጪዎች በመግዛት እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡ ይህ ዓይነት አሠራር ብዙ ዕውቀት የሌለውን አርሶ/አርብቶ አደር ከፀረ ተባይ ጉዳት ይታደገዋል፤ የፀረተባይ ውጤታማነትም ይጨምራል፡፡ ከዚህ ሌላ የሥራ ዕድል በመፍጠርም ትልቅ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

የሰብል ጥበቃ አገልግሎት በሜካናይዜሽን እንዲደገፍ በማድረግ እና የታችኛው መዋቅር በጸረ-ተባይ መከላከል አገልግሎት የተሰማሩትን አገልግሎት ሰጪዎችን በማዘመን የሰብል ልማቱን ምርትና ምርታማነት እንዲደግፉ ማድረግ ይቻላል፡፡

የሆርቲካልቸር ምርቶች በገበያ ላይ ተፈላጊነት እንዲኖራቸው በአቅርቦት፤ በጥራትና በዋጋ ደረጃ ያሉትን ክፍተቶች ከማሻሻል ጎን ለጎን በገበያ ውስጥ ለመግባት የአለምአቀፍ የአመራረት፤ የአካባቢና ህብረተሰብ ጥበቃ መስፈርቶችን ማሟላትና ዕውቅና (certification) ለማግኘት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ረገድ ያሉ ፕሮጀክቶች፤ ድጋፍ ሰጪ ተቋማትና ባለሙያዎች ስለ መልካም እርሻ (GAP-Good Agricutural Practices) አተገባበር፣ የተለያዩ የአለም አቀፍ የገበያ ጥራት መስፈርት ሰርተፍኬቶች (Global GAP, BRC, BSI, ETI, TESCO እና የምርት ሀገር ስሪት የHs code) ገበያው የሚፈልጋቸው ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የግንዛቤ ማሳደግ ስራ በቀጣይ አምስት ዓመታት በተከታታይ የሚከናወን ተግባር ይሆናል፡፡

በአትክልትና ፍራፍሬ ለሚከሰቱ ተባዮች እና በአገሪቱ የተስፋፉትን ወራሪ መጤ አረሞችን ለመከላከል የሥነ-ሕይወታዊ የተባይ መከላከያ ዘዴን (Biological Control) ትኩረት ሰጥቶ ማስፋትና ሌሎች የተባይ መከላከያ ዘዴዎችን በመጠቀም በተባዮቹ የሚደርሰውን የምርት ብክነት ለመቀነስ በስፋት ይሰራል፡፡

2.1.1.4 የተሻሻለ የሰብል ግብዓት አቅርቦት

የሰብል ግብዓት የተሻሻሉ ዝርያዎች **(አዝርዕት፣አትክልት፣ ፍራፍሬ እና እና ስራስር ሰብሎች፣ ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም)**፣ማዳበሪያ፣አግሮ-ኬሚካል እና የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጅን ያጠቃልላል፡፡በዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ትንተና መሰረት የተሻሻሉ የሰብል ዝርያዎች ከ50-60 በመቶ እንዲሁም የተሻሻሉ አሰራሮችና ሌሎች ግብዓቶች በምክረ-ሃሳቡ መጠቀም ከ40-50 በመቶ ድረስ ለምርታማት ድርሻ እንደሚኖራቸው ይተነብያሉ፡፡ የሰብል ግብዓት በሚፈለገው መጠን፣ወቅት፣ጥራትና በተመጣጣኝ ዋጋ ሊቀርብ የሚገባ ሲሆን ይህን ማሳካት ሲቻል አርሶ አደሩ የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎች የመጠቀም ዕድሉ በማስፋት የሚጠበቀውን ምርትና ምርታማት ማሳካት ይቻላል፡፡

የሰብል ዝርያ አጠቃቀምን ለማሳደግ አነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሩ ወዶና ፈቅዶ ሊጠቀማቸው የሚችሉ አካባቢ ተኮር፣ ምርታማና ሌሎች ጠቃሚ ባህርያትን የተላበሱ የሰብል ዝርያዎች እንዲቀርቡለት የሚያስችል የአገር ውስጥና የውጭ አገር የግል ዘርፉን ተሳትፎ የሚያበረታታ ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ይህን በማድረግም በአገር ውስጥ አርሶአደሩ ከፍተኛ ዋጋ ከፍሎ የሚጠቀማቸውን በምርታማነታቸው የላቀ ውጤት ያሳዩትን ዓይነት ዝርያዎች በብዛትና በመጠን እንዲቀርብለት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ በምግብ ንጥረ-ነገር ተፈላጊነታቸው የተነሳ የተለየ ትኩረት የሚሹ የሰብል ዝርያዎች ልማትን ለማሳደግ ልዩ የሆነ የድጋፍ ሥርዓት ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

በቀጣይ አምስት ዓመታት የተቀናጀ የግብዓት አቅርቦት መርሃ ግብር በመከተል የተሻሻሉ ዝርያዎችና የመስኖ አጠቃቀም ማዕከል ያደረገ የግብዓት አቅርቦት አካሄድ በመከተል ምርትና ምርታማትን ከፍ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡

የተሻሻሉ ግብዓቶች ከማምረት እስከ ተጠቃሚው የማድረስ ተግባራት ላይ የግል ዘርፉን ተሳትፎ በማጠናከር ባለፉት ጥቂት ዓመታት በግል ዘርፉ በግብዓት አቅርቦት የታዩ ጠንካራ ልምዶችን የማስፋት ሥራ ከተሰራ ተወዳዳሪ የግብዓት ግብይት ሥርዓት በመዘርጋት ግብዓቶች በአርሶ አደሮች ፍላጎት መሰረት እንዲቀርቡ የሚያስችል ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ያስችላል፡፡ ለአብነት ያህል በበቆሎ የፓዮኒር ዝርያዎች በአርሶ አደሮች ያላቸውን ተመራጭነት እንዲያድግ ከማድረግ ጎን ለጎን በሀገር ውስጥ ምርምር ተቋማት የተለቀቁ ምርጥ ዝርያዎች የፓዮኒር ዝርያዎች በተዋወቁበት መንገድ አንዲተዋወቁ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡

በተጨማሪም ፓይነርን ሊወዳደሩ የሚችሉ ሌሎች ዝርያዎች ማቅረብ የሚችሉ አገራዊና የውጭ አዳቃይ ኩባያዎች አንዲመሰረቱና እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡ የተመሰከረላቸው ዝርያዎች እንዲለቀቁ የሚያደርግ የዝርያ ማጎልበት አና ለቀቃ እና ዘር ጥራት ቁጥጥር ተወዳዳሪ ሥርዓት በመዘርጋት ለግሉና ለመንግስት ምርምር ዘርፍ እኩል አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የፖሊሲ ምህዳር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በማዳበሪያ በኩል አፈርን እና የዕጽዋት ፍላጎት መሰረት ያደረገ እና የታዘዘውን ምክረ ሃሳብ ማሳካት የሚያስችል የአጠቃቀም ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ አሁን ያለውን ከ50 ኪ/ግ በሄ/ር በታች የሆነውን የማዳበሪያ አጠቃቀም በማሳደግ በቀጣይ 5 ዓመታት ዓመታት ማዳበሪያ በምክረ-ሃሳቡ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የጸረ ተባይና አረም ኬሚካል አጠቃቀምም ጥራቱ ተጠብቆ ጥቅም ላይ እንዲውል ሥራ ይሰራል፡፡

በአጠቃላይ በእህል፣ ሆርቲካልቸርና የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ግብዓትን በአገር ውስጥ የማምረቱ ሥራ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ በተለይ የምርጥ ዘር ብዜት በዓይነትና በሚፈልግ መጠን እንዲቀርብ ታማኝ አርሶ አደሮች መሰረት ያደረገ የመነሻ ዘር እና የተመሰከረለት ዘር ብዜት ሥራ በስፋት ይከናወናል፡፡ የኮንትራት ዘር ብዜትን ከማጠናከር ጎን ለጎን ክፍተኛ አስተዋጽኦ ለሚያበርክቱ እና የራሳቸውን ዝርያ ያላቸው ዘራቸውን የሚያባዙበት ማሳ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የውጭ እና የግል ዘርፉ በዘርና በሌሎች ግብዓቶች የምርምር ድርሻቸው አንዲያድግ ድጋፍ ለግብዓት አቅርቦት መቀላጠፍ በዋናነት ትኩረት የሚሰጠው የግብርና ግብዓት መረጃን በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል በበይነ መረብ የማስተሳሰር ሥራ ይሰራል፡፡ የሚቀርበው ግብዓት ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የክልል እና የፌደራል ዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካላት እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

በሚቀጥሉት አስር ዓመታ የአዝርዕት ግብዓት አጠቃቀም ኤን.ፒ.ኤስ/ዳፕ አሁን ካለበት 11 ወደ 14 ሚሊየን ኩንታል፣ ዩሪያ አሁን ካለበት 5 ወደ 8.7 ሚሊየን፣ ምርጥ ዘር አሁን ካለበት 970 ሺ ኩንታል ወደ 1.5 ሚሊየን ኩንታል፣ፀረ ተባይ ኬሚካል አሁን ካለበት 3 ወደ 5.7 ሚሊየን ሊትር ለማቅረብ በዕቅድ ተይዟል፡፡

2.1.1.4.1 የሰብል ግብዓት አቅርቦት

ሀ) የማዳበሪያ ግዢ

የማዳበሪያ የአቅርቦት ሰንሰለትን ማሻሻልና ዘመናዊና ቀልጣፋ እንዲሆን ለማስቻል በማዳበሪያ አቅርቦት ሰንሰለት ማሻሻያ ጥናት የተቀመጡ ምክር ሃሳቦች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡ እነዚህን የውሳኔ አቅጣጫዎች

ተግባራዊ በማድረግ ማዳበሪያን ለአርሶ አደሩ በሚፈለገው ወቅት፣ መጠን፣ ጥራት፣ ዓይነት፣ ቦታ እና በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ አስቻይ ሁኔታዎችን ይመቻቻሉ። በዚህም መሠረት በየዓመቱ የሚደረገውን የማዳበሪያ ግዢ አሠራር ወደ ተራዘመ ጊዜ አሰራር በመቀየር /ከ2-3 ዓመት/ የሚቆይ የግዢ ውል ከተለያዩ አምራቾች ወይም ከተመረጡ አቅራቢዎች ጋር ይፈጸማል።

ለ) የኬሚካል እና የህያው ማዳበሪያ ማምረት

የውጭ ምንዛሬ እጥረት እየፈጠረ ያለውን የአቅርቦት ክፍተት ጫና ለመቀነስ አገራዊ የማምረት አቅም እንደሚያድግ ታሳቢ ተደርጓል። በተለይ የኬሚካል ማዳበሪያ አቅርቦቱ የአርሶ አደሩን ተጠቃሚነት ለማሳደግ በአነስተኛ ከረጢት/መያዣ እንደቀርብለት ይደረጋል። የግሉን ዘርፍ ከማምረት እስከ ግብይት ተሳታፊነት ማሳደግና የአግሮ ዲለር ፕሮግራሞችን በስፋት እንዲካሄዱ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡

ሐ) የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ምርጥ ዘር ማምረት/ማባዛት

1. በመንግስት ባለቤትነት ሥር ያሉ የሰብል ዝርያዎች በስፋት ጥቅም አንዲውሉ ማድረግ፡-

ከተለቀቁት 1,264 በላይ የሰብል ዝርያዎች የሆርቲካቸር ዝርያዎች ከሆኑት 296 ያህሉ የአትክልት፣ ፍራፍሬና ስራስር ሰብሎች ዝርያ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ዝርያዎች ከውጭ የመጡና በማላመድና በሙከራ ውጤታማነታቸው የተረጋገጡ ናቸው። በውጭ ኩባንያዎች ከተመዘገቡት ዝርያዎች አብዛኞቹ ሳይባዙ የቀሩ ናቸው። ከተመዘገቡት ውጭም ሳይመዘገቡ የሚሰራጩና በአርሶአደሩ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያያደሩ ያሉም የአትክልት ዝርያዎች አሉ። ይህን ችግርም ለመቅረፍ በአርሶአደሩ ተፈላጊ ሆኑት ዝርያዎች ከፍተኛ ምርት የሚሰጡትን እንደየ አግሮኢኮሎጂው ሁኔታ ለአርሶአደሮች እና ሌሎች አልሚዎች እንዲዳረሱ ማድረግ የሚያስችል አሰራር እንዲዘረጋ ይደረጋል። በዋናነት የመንግስት ምርምር ተቋማት ይህን ኃላፊነት በመውሰድ ይመሩታል። ይህንም እውን ለማድረግ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ። ይህንም እውን ለማድረግ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ።

የአዝርዕትና የሆርቲካልቸር ዝርያ ዝርዝር ቆጠራ ማካሄድ፡ በህዝብ ሃብት የተያዙ ዝርያዎች መኖራቸውን የሚያረጋግጥ የዝርያ ዝርዝር ቆጠራ ማካሔድና መለየት፤ የመለየቱ ሥራ በዋናነት በየክልሉ እና በፌደራል ደረጃ የተዋቀሩ የምርምር ተቋማት እንዲከናወን ይደረጋል። የመለየት ሥራው ሲከናወን የዝርያው ጠባቂ ማዕከል፤ ዝርያው የተለቀቀበት ዓላማ፣ አግሮኖሚክ ምክረ-ሃሳብ እና ሌሎች ዝርዝር መግለጫዎች ይዘጋጃል። በዋናነትም ልዩ የምግብ ንጥረ-ነገር ፋይዳ ያላቸውን፣ ለመስኖ፣ ለዝናብ አጥር ግብርና፣ ለውጭ ገበያ ዋጋ ወዘተ... ተለይተው መዘርዘር አለባቸው።

የማስተዋወቅ ሥራን በሰፊው መስራት፡- የአዝርዕትም ሆነ የሆርቲካልቸር ዝርያዎች እንዳሉ የማረጋገጥ ሥራ ከተሰራ በኋላ ዝርያዎችን በማሳ እና በመገኛኛ ብዙሃን የማስተዋቅ /ዝርዝራቸውን በጋዜጣ እንዲታተም በማደረግ፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን/ ሥራ ይሰራል። በወጣው የዘር ግብይት መመሪያም መሰረት የግል ዘርፉ ለሚጠቀማቸው የህዝብ ሃብት የሆኑ ዝርያዎች የማስተዋወቅ ግዴታውን እየተወጣ ስለመሆኑ ክትትል ሥራዎች ይሰራሉ፤ የመንግስት ኤክስቴንሽን ስርዓትም እነዚህን ተግባራት እንዲያከናወንና ዓመታዊ እቅዱ ውስጥ እንዲያካትታቸው ይደረጋል።

የተለዩትንና መነሻ ዘራቸው በዋናነትም አራቢ ዘር ያላቸውን በመለየት የመነሻ ዘር ማባዛት ሥራ መስራት፡- የአዝርዕት ዝርያዎችን ማባዛት የሚችሉ አቅም ያላቸው ከ50 ያላነሱ የመንግስት፣ የግል እና የዩኒየን ዘር አምራቾች ይገኛሉ። እነዚህን በመጠቀም የመነሻ ዘር ማባዛት ተግባራት እንዲከናወን ይደረጋል።

ጥራት ያላቸው አዝርዕት ሰብል ዝርያዎች ብዜት ማካሄድ፡- ስነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ ለዘር ብዜት የሚውል መሬት በማዘጋጀት ከፍተኛ ምርት የሚሰጡና በገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ ዝርያዎችን የሚያመርቱ አቅም ያላቸው ባለሃብቶችን እና በተማሩ ወጣቶችና ሴቶችን በማደራጀት የማባዛት፣ የማቅረብ እና አጠቃቀም ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት ላይ ተሳትፏቸውን እንዲጨምር ይደረጋል። ከውጪ ሀገር የሚገቡ አትክልት ዝርያዎች የቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል። **የሆርቲካልቸር ሰብሎች ዝርያን ከማባዛትና ከማሰራጨት አኳያ** በመንግስትም ሆነ በግል አሳቹ ድርጅቶች ከፍተኛ ውስንነት ያለ በመሆኑ በቀጣይ አምስት ዓመት በዘር ማባዛት ለመሳተፍ የሚፈልጉ

የግል አባኸር አካላት ምቹ ሁኔታ መፍጠርን፣ የግሉ ዘርፍ ለማባዛት የማይፈልጋቸውንና በአርሶ አደሩ ተፈላጊ የሆኑ ዝርያዎችን በመንግስት የማባዛትና የማሰራጨት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ በተጨማሪም መንግስት በግልም ይሁን በመንግስት ደረጃ የሚባዙ ዘሮችን የመቆጣጠርና ዕውቅና የመስጠት ተግባር ያከናውናል፡፡ **ጥራት ያላቸው የሆርቲካልቸር ዝርያዎች ብዜት ማካሄድ፡-** ስነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ ለዘር ብዜት የሚውል መሬት በማዘጋጀት ከፍተኛ ምርት የሚሰጡና በገበያ ላይ ተፈላጊ የሆኑ ዝርያዎችን የሚያመርቱ አቅም ያላቸው ባለሃብቶችን እና በተማሩ ወጣቶችና ሴቶችን በማደራጀት የማባዛት፣ የማቅረብ እና አጠቃቀም ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት ላይ ተሳትፏቸውን እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ ከውጪ ሀገር የሚገቡ አትክልት ዝርያዎች የቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የማበረታቻ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

አንዳንድ ውጤታማና በመንግስት እጅ የሚገኙ የአዝርዕትና የሆርቲካልቸር ሰብል ዝርያዎች አቅም ላላቸው ዘር አምራቾች በባለቤትነት ማስተላለፍ፡ ከዚህ አኳያ ልዩ የህግ ማዕቀፍ በመዘርጋት በመንግስት ሥር የተያዙ ዝርያዎች ለኩባንያዎች ማስተላለፍ የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፤ እንዲተላለፍም ይደረጋል፡፡

2)የአገር ውስጥ የግል፣ የዩኒየንና የመንግስት ዘር አምራቾች ውጤታማነት እና ቁጥራቸውንም ማሳደግ

የመንግስት ዝርያዎች በስፋት እንዲተዋወቁ እና የግል ዘርፉም ባለቤት እንዲሆን በማድረግና በዕትዕ ወቅት የታየውን ውጤታማ የግል ዘርፉን ስኬት በማስፋት አርሶ አደሩ የሚወዳቸውን ዝርያዎች በስፋት እንዲያመረቱ የማድረግ ተግባር ይከናወናል፡፡ከዚህም ባሻገር በመንግስት ባለቤትነት ሥር የተያዙ ውጤታማ የእህል ሰብል ዝርያዎች በስፋት እንዲባዙ የሚደረግ ሲሆን **በአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ስራስር** ከዚህ በፊት ትኩረት የተነፈጋቸው በመሆኑ በቀጣይ አስር አመት በዓይነትም ሆነ በመጠን የሚፈለገውን የዘር/ችግኝ አቅርቦት እንዲካሄድ እና አጠቃቀሙን ከፍ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በሚቀጥሉት ስትራቴጂክ ዓመታት የሚከተሉትን እቅጣጫዎች መሰረት ያደረገ ሥራ ይሰራል፡፡

አገራዊ የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዝርያ አዳቃይ ኩባንያዎች በአገር ልጆች እንዲስፋፉ የሚያደርግ የማበረታቻ ሥርዓት መዘርጋት፤ የውጭ አገር ኩባያዎችን አሉታዊ ተጽእኖ ለመቀነስ አንዲቻል አገር በቀል ኩባያዎች በስፋት እንዲፈጠሩ የሚያስችል እና ውጤታማ አዳቃዮችን የሚያበረታታ አሰራር ይዘረጋል፡፡ ለዚህም መንግስት ልዩ ፋይናንስና የመሬት ድጋፍ ስርዓት ይዘረጋል፤ ማህበርም እንዲኖራቸው የማስተባበር ሥራ ይሰራል፡፡

የመንግስት የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዘር አምራች ኩባያዎች በአክስዮን ከግል ድርጅቶች እና ከአርሶአደሮች ጋር አንዲሰሩ ማድረግ፤ በሌሎች አገሮች እንደሚደረገው መንግስት የንዑስ ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተዕዕኖ እንዳያደርስ እና የመንግስት ኩባንያዎች የመሬት ተደራሽነታቸው እንዲጠናከር ከግል ኩባንያዎች እና አርሶአደሮች ጋር በአክስዮን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

በክልል ተወስነው የሚሰሩትን የክልል ኩባንያዎች አገራዊ ኩባንያዎች አንዲሆኑ መስራት፡ በክልል ተወስነው የኖሩትን የክልል መንግስት ኩባያዎች በክልል ከተወሰነው አስተሳሰባቸው እንዲወጡ አገራዊ እና ተወዳዳሪ ኩባንያዎች አንዲሆኑ የማደርግ ሥራ ይሰራል፡፡ ለዚህም እያንዳንዳቸው በየክልሉ ቅርጫፍ የማባዣ እና የግብይት ማዕከላት ይኖራቸዋል፡፡

ለአገር በቀል የግልና የመንግስት የምርጥ ዘር ኩባምያዎች በተዘዋዋሪ ፈንድ አሰራር ውጤታማ የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት በመፍጠር፡-ይህ ተግባር የምርጥ ዘር ኩባንያዎች በአርሶአደር ዘር ብዜት ፕሮግራም የሚያባዙትን ምርጥዘር አርሶአደሮች ምርጥ ዘሩን ሰብስበው ቤት ከማስገባታቸው መሬት በመድረስ የጥሬ ዘር ለመግዛት የሚያስላቸው ነው፡፡ እስከ አሁን ባለው ተሞክሮ ፋይናንስ በወቅቱ ስለማያገኙ አርሶአደሮች በውላቸው መሰረት ጥሬ ምርጥ ዘር ለኩባንያዎች እያቀረቡ አይደለም፡፡ ይን በተዘዋዋሪ ፈንድ አማካይነት በመፍታ ድርጅቶች ብዙ ምርጥ ዘር እንዲገዙ በማድረግ ለአርሶአደሮች ምርጥ ዘር በተፈለገው መጠን፣ዓይነትና ጥራት እንዲያቀርቡ ያስችላል፡፡

በተዘዋዋሪ ፈንድ አሰራር መሰረት ለሶስቱም የክልል መንግስት ዘር ኩባያዎች በከፍተኛ መጠን ዘር የማበጠር አቅም ያላቸውን ማበጠሪያ መሸኖችን መግዛትን እና የዘር ማከማቻ መጋዝኖች መገንባት፡ የክልል ዘር አምራች ድርጅቶች ዘር የማበጠር አቅም እንዲያሳድጉ በማድረግ ምርጥ ዘር በወቅቱ ተበጥሮ እንዲቀርብ የማድረግ አቅም አንዲያድግ ይደረጋል፡፡ ይህን በማድረግ አርሶ-አደሮች ምርጥ ዘር በወቅቱ እንዲደርሳቸው የሚደረገውን ጥረት የመደገፍ ሥራ ይሰራል፡፡

የአነስተኛ የግል ምርጥ ዘር አምራቾችን የጋራ የውስጥ ዘር ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ አገልግሎት፣ መጋዝንና ዘመናዊ የዘር ማበጠሪያ ተደራሽነት እንዲኖራቸው በማድረግ አቅማቸውን ማሳደግ፡ ይህ ተግባር የሚከናወነው በጋራ ማህበራቸው አማካይነት ሲሆን ዘር አምራቾቹ የእነዚህ ቁሳቁሶች እና አገልግሎቶች በጋራ እንዲያገኙ በማድረግ ምርጥ ዘር በወቅቱ፣ በበቂ መጠን እና በተፈላጊው ቦታ፣ መጠንና ዓይነት አንዲቀርብ የሚደረገውን ጥረት መደገፍ ይቻላል፡፡

አገር በቀል የመነሻ ዘር አምራቾችን የማምረት አቅም ለማሳደግ የመስኖ አውታር፣ የኤልክትሪክ ኃይል እና የመሬት ተደራሽነት አቅማቸውን ማሳደግ፡-የመነሻ ዘር አቅርቦት አቅማቸውን ለማሳደግ በአመት ሁለት ጊዜ እና ከዚያ በላይ የማምረትንና ዘር የማዘጋጀት አቅማቸውን በማሳደግ ለአርሶአደሮች በወቅቱ እንዲያቀርቡ ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡

የኮንትራት ግብርናን መሰረት ያደረገ የእህልና ምርጥ ዘር ማምረት ሥርዓትን ማጠናከር የተጣጣመ አገራዊ ህግ በማውጣትና በክልሎች እሰከአሁን የነበረውን በውል የተመሰረተው የአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዘርና የእህል ማባዛት ሥራ ማነቆዎች በመቀነስ ከውል ተቀባይ ዘር አምራቾችም ሆነ ውል ሰጪ ኩባንያዎች የተነሳ ይባክን የነበረውን በማሰቀረት በውሉ መሰረት እንዲሰበሰብ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የቲሹ ካልቸር ላቦራቶሪዎችን በማስፋፋት፤ የኳራንቲን አሰራር በማጠናከር፤ የምርመራ፣ የእውቅና አሰጣጥ ስርዓት በመዘርጋትና የግብይት መሰረተ ልማት በማመቻቸት ረገድ በዘርፉ ሊከናወኑ የሚገቡ የተለያዩ የድጋፍ ስራዎች ይጠበቃሉ፡፡

3) ውጤታማ የሆኑ የውጭ አገር አዝርዕትና ሆርቲካልቸር ዝርያዎች አገር ውስጥ በስፋት እንዲመረቱ ማድረግ፡-

በውጭ አገር የበለጸጉ ዝርያዎች ከአገር ውስጥ ይልቅ በአገራችን አርሶ አደሮች ዘንድ ተቀባይነት እንዳላቸው በተወሰኑ ድቃይ ዝርያዎች የታየው ሰብል ልማት ሽፋን በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር በተካሄደ አንድ ዳሰሳዊ ጥናት የፓየኒር የበቆሎ ዝርያዎች አገራዊ ሽፋን በ2009/10 ምርት ዘመን 31 በመቶ ሲሆን ዝርያዎቹ በስፋት በሚቀርብበት እንደ ኦሮሚያ ክልል 54 በመቶ ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር በአትክልትና ፍራፍሬ አብዛኛዎቹ ዝርያዎች የውጭ መሆናቸው እና ዘራቸው ከውጭ የሚገባ በመሆኑ በሀገር ውስጥ የሚባዛበት ስርዓት ይመቻቻል፡፡በአገር አቀፍ ያለው ልምድ የሚያሳየው የምርጥ ዘር ዝርያዎች ምርታማነት አሳማኝ እስከሆነ ድረስ ዝርያዎቹ ዋጋ ሳይበግራቸው ምግዛት የሚችሉ አርሰአደሮች በብዛት እየተፈጠሩ መሆኑ በፓኒር ዝርያዎች የታው አርሶደሮች የመግዛት ፈቃደኝነት አመላካች ነው፡፡

ስለዚህ የገበያ ተወዳዳሪነትን በማሳደግ ለአርሶ አደሩ የሚቀርቡ ዝርያዎች የላቀ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው እና ተጠቃሚነቱን በመጠንና በዓይነት ለማስፋት የውጭ አገር ኩባንያዎች አገር ውስጥ ገብተው የማምረት ተግባር እንዲያከናውኑ የሚከተሉት ተግባራት ላይ ትኩረት በመስጠት ይሰራል፡፡

በውጭ አገር የበለጸጉ ዝርያዎች ከአገር ውስጥ ይልቅ በአገራችን አርሶአደሮች ዘንድ ተቀባይነት እንዳላቸው በተወሰኑ ድቃይ ዝርያዎች የታየው ሰብል ልማት ሽፋን በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ለአብነት ያህል በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር በተካሄደ አንድ ዳሰሳዊ ጥናት የፓየኒር የበቆሎ ዝርያዎች አገራዊ ሽፋን በ2009/10 ምርት ዘመን በቆሎ 31 በመቶ ሲሆን ዝርያዎቹ በስፋት በሚቀርብበት እንደ ኦሮሚያ ክልል 54 በመቶ ነበር፡፡ ከዚህም ባሻገር በአትክልትና ፍራፍሬ አብዛኛዎቹ ዝርያዎች የውጭ መሆናቸው እና ዘራቸው ከውጭ የሚገባ በመሆኑ በሀገር ውስጥ የሚባዛበት ስርዓት ይመቻቻል፡፡ በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ያለው ልምድ የሚያሳየው የምርጥ ዘር ዝርያዎች ምርታማነት አሳማኝ እስከሆነ ድረስ ዝርዝዝርያዎቹ ዋጋ ሳይበግራቸው ምመግዛት የሚችሉ አርሰአደሮች በብዛት እየተፈጠሩ መሆኑ በፓዮኒር ዝርያዎች የታየው አርሶደሮች የመግዛት ፈቃደኝነት አመላካች ነው፡፡

ዓለምአቀፍ ኩባንያዎች አገር ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ ዓለም አቀፍ የማስተዋወቅ ሥራዎችን መስራት፡ - በዕጽዋት ዘር ንዑስ ዘርፉ ዓለምአቀፍ ኩባንያዎች አገር ውስጥ ገብተው እንዲሳተፉ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቲክ ሚሽኖችን የመጠቀም ሥራ ይሰራል፡፡ እነዚህ ኩባንያዎች አገር ውስጥ ገብተው እንዳይሰሩ ሊከለክላቸው የሚችለውን የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትና አጠቃቀም ማነቆዎች ከብሄራዊ ባንክ ጋር በመስራት እንዲፈቱ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዝርያዎቻቸውን በአገር ውስጥ ማባዛት አንዲችሉና ለመሰረተ-ልማት ግንባታ የሚያስፈልግ የመሬት አቅርቦትና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችንም የማመቻቸት ሥራ ይሰራል፡፡

የአዳቃዮች መብት ጥበቃ ሥርዓትን መተግበር፡- የውጭ ባለሃብቶች በስፋት በአገር ውስጥ እንዲንቀሳቀሱና ውጤታማ የሰብል ዝርያዎቻቸው በአርሶአደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ ዘንድ በስፋት እንዲመረቱ የሚያደረግ የአዳቃዮች መብት ጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ ለመድረግ ሥርዓቱን የሚደግፍ ምቹ የህግ ምህዳር መዘርጋት፣የየአህጉር እና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መተግበር እና ይህን በጤናማ መልኩ መጠቀም የሚያስችለን አቅም የገነባ ተቋም ይደራጃል፡፡

በምግብ ንጥረ-ነገር የበለጸጉ ዝርያዎችን በስፋት ለማምረት ልዩ ድጋፍ መስጠት፡ በተለይ የጥራጥሬ እና የቅባት ሰብሎች ምርታማነታቸው ከአገዳና ብርዕ ሰብሎች ጋር ሲነፃፀር አናሳ መሆናቸው በምግብ ስርዓት ውስጥ ያለውን የንጥረ-ነገር ተደራሽነት ውስን አድርጎታል፡፡ ከዚህም ባሻገር የአትክልት፣ ስራስር እና ፍራፍሬ ትኩረት ተሰጥቷቸው ባለመሰራቱና የዘር ግብዓት አቅርቦት ውስንነት በመኖሩ በምግብና ስርዓተ-ምግብና የሚጠበቀውን ያህል አስተዋጽኦ አላደረጉም፡፡ በመሆኑም የሆርቲካልቸር ምርቶች፣ ጥራጥሬ እና ቅባት ሰብሎች ምርት በአመጋገብ ስርዓት ውስጥ በበቂ ሁኔታ እንዲኖር ለማድረግ ከመኸር እርሻ መሬት በተጨማሪ በመስኖ ልማት እና እንደ ስነ ምህዳሩ ተጨባጭ ሁኔታ በቀሪ እርጥበት እንዲመረቱ ይደረጋል፤ በንጥረ-ነገር ለበለፀጉ ሰብሎች ልዩ የድጋፍ ማዕቀፍ ማዘጋጀት እና የሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ መተግበር፣ በምርት መጠናቸው ከሌሎች ዝርያዎች ጋር ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉና ልዩ ንጥረ-ነገር ያላቸውን ዝርያዎችን ዘር ብዜት ስርዓት በመዘርጋት በስፋት ማባዛት፤ የተባዛው ዘር ለአርሶአደሩ እንዲዳረስ በስፋት ማስተዋወቅና ለማልማት ትኩረት ይደረጋል፡፡

4)የመጠባበቂያ ዘር ክምችት ሥርዓት መዘርጋት

የውጭና የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ያለምንም መከልከል በአገር ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ ሲፈቀድ የምግብ ዋስትና አጀንዳችን ጥያቄ ውስጥ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ እስከአሁንም ከታየው ልምድ ተተባይ ባልሆነ ሁኔታ አርሶ አደሩ የዘር ማምረት ወቅቱ ካለፈ በኋላ በሚያሳየው የዝርያ ፍላጎት ለውጥ የተነሳ ከሚመረተው እና ከሚሰበሰበው ዘር እስከ 30 በመቶ በአርሶአደሩ ጥቅም ላይ ሳይወል ያድራል፡፡ ብዙ ወጪ ወጥቶበት የተመረተውም ዘር ለእህልነት ይሸጣል ወይም ባደረበት መጋዝን ተበላሽቶ ይቀራል፡፡ አርሶአደሩ በሌላ ዓመት አልፈልገውም ያለውና ለእህልነት የተሸጠውን ዝርያ መልሶ ሲፈልገው ይታያል፡፡ ከዚህም ባሻገር በአየር ንብረት ተለዋዋጭነት የተነሳ አንዳንድ ዝርያዎች ለምሳሌ በአጭር ጊዜ የሚደርሱ በመጠባበቂያ መልኩ መያዙ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ በተለይም ያላደገው የሰብል ልማት ዘርፉ እስኪያደግ ድረስ ይህ በስፋት መሰራት ይገባል፡፡ይህን ተግባር የልማት አጋሮቻችን አንዲደግፉት መጠበቅ አይኖርብንም፡፡ ይህ ተግባር ሙሉበሙሉ የመንግስት ኃላፊነት ሊሆን ይገባል፡፡

2.1.1.4.2 የሰብል ግብዓት ስርጭት ስርዓት መዘርጋት

የምርጥ ዘር አቅርቦት በ2012 ከነበረው 1,086,000 ኩንታል 2022 በማሳደግ 2.3 ሚሊዮን ኩንታል ይደርሳል ተብሎ ታቅዷል፡፡ በኢትዮጵያ የአፈር ማዳበሪያና ሥርጭት ከዓመታ ዓመት እየጨመረ መጥቶ በ2011ዓም 15.8 ሚሊየን ኩንታል የነበረው የስርጭት መጠን በ2022 የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ሥርጭት 31.5 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ታቅዷል፡፡ 79.2 ሚሊየን ኩንታል ኖራ 3 ሚሊየን ሄ/ር አሲዳማ አፈርን ለማከም ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

የሰብል ዘር አቅርቦት ሥርዓት ማሻሻል

የአርሶአደር ለአርሶአደር ይደረግ የነበረውን የምርጥ ዘር አጠቃቀም አካቶ ሪፖርት ይደረግ ስለነበር ከ2008 እስከ 2011 ድረስ የነበረው የምርጥ ዘር አቅርቦት በየዓመቱ እየቀነሰ እንደመጣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ አሰተዳደራዊ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ከ2009 ምርት ዘመን ጀምሮ ግን አርሶአደር ለአርሶደር የምርጥ ዘር ልውውጥ አፊሳሊያዊ በሆነ መንገድ ሪፖት አንዳይደረግ ከክልሎች ጋር ስምምምት በተደረሰው መሰረት ሪፖርት ስለማይደረግ ከዕትእ አንጻር የምርጥ ዘር አቅርቦትና አጠቃቀም እየቀነሳ የመጣ እንደሚስል በተቃራኒው ግን ከ1ኛው ዕትዕ አንጻር ሲታይ በዘር ጥራት ተቆጣጣሪ አካላት ጥረቱ ተረጋግጦ የሚሰራጨው የምርጥ ዘር መጠን እጅግ የጨመረ ሲሆን በአንደኛው ዕትዕ መጨረሻ ከነበረው 500 ሺህ ኩ/ል ያልዘለለ የነበረው የተመሰከረለት ዘር እቀርቦት ወደ አንድ ሚሊዮን ከፍ ሊል ችሏል፡፡ መንግሥት ለግብርናው ዘርፍ እየሰጠ ያለው ትኩረትና ድጋፍ እንዲሁም ግብርና በኢኮኖሚው ውስጥ ያለው ከፍተኛ ሚናና ቴክኖሎጂ የመጠቀም አቅም ይቀጥላል ተብሎ ስሊሚታሰብ የዘር ፍላጎትም በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ስለሆነም በገበያ ተፈላጊ የሆኑ የግብርና ምርቶችን በማባዛትና ገበያው በሚፈልገው የጥራት ደረጃ በማምረት የዘርፉን ተዋንያን ከሀገር ውስጥና ከውጭ ገበያ ተጠቃሚ ለማድረግ የምርጥ ዘር አቅርቦትን በተቀናጀ የሥርጭትና ቁጥጥር ሥርዓት በመምራት በ2022 ሊደረስበት የታቀደውን ምርትና ምርታማነት ለማሳካት ይሠራል፡፡

የምርጥ ዘር አቅርቦት ከተማከለ የመረጃ ልውውጥ ፣ የተሻለ አቅም፣ የተቀናጀ የማምረትና ሥርጭት ሥርዓት፣ በመዘርጋትና ከጥራት ጉድለት እና ከፍትሃዊ አጠቃቀም አንጻር የሚታዩ ችግሮች በመፍታት እና አገር አቀፍ የሆነ የዘር አቅርቦት ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የቀጥታ ዘር (ግብዓት) ግብይት ሥርዓት (Direct Input Marketing) በስፋት ተግባራዊ ይደረጋል፡ ሥርዓቱ እስካሁን ያስገኛቸውን ጠቃሚ ተሞክሮዎች በመቀመር የምርጥ ዘር ግብይት ተወዳዳሪነት የሰፈነበት እና ገበያ ተኮር እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የቀጥታ ዘር ግብይት ሥርዓት የዘር አምራች ድርጅቶች ያመረቱትን ዘር ተጠያቂነት ባለው መልኩ በራሳቸው የሽያጭ ወኪል በቀጥታ ለተጠቃሚው በመሸጥ የዕጽዋት ዘርን ከአማራጭ ምንጮች በወቅቱ፣ በሚፈለገው ዓይነት፣ በጥራት፣ በቦታ እና በመጠን እንዲያገኝ በማድረግ የሚያድርን የዘር መጠን ወሳኝ በሚባል መልኩ ቀንሷል፡፡ ስለሆነም በጥናት ላይ በመመስረት እንዲሁም አስፈላጊውን የተጠናከረ ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ ሥርዓቱ በሚ/ር መ/ቤቱ በጸደቀው የዘር ግብይት አስተዳደር መመሪያ እና ሌሎች የህግ ማአእቀፎች መሰረት በአዳዲስ አካባቢዎች በማስፋፋት አርሶና አርብቶ አደሮች የተሻለ የግብኣት አቅርቦት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማእከላትን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ያስገኙትን ውጤታማነት ከግምት በማስገባት ማዕከላቱን ለማስፋትና የግብዓት ተደራሽነት ለማሳደግ በተለይ በዘርና ኬሚካል አቅርቦት ሚናቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ አሁን ያለውን የማእከልት ቁጥር በ2022 ወደ 500 በማሳደግ በሂደትም መንግሥት የማእከላቱን ቁጥር በመጨመርና የአሠራራቸውን በማቀላጠፍ ቀስ በቀስ ሥራውን ለግሉ ዘርፍ ለማስተላለፍ ያስችለዋል፡፡ በዚህም መሠረት ማዕከላቱን ለማቋቋም የሚሳተፉ ባለሃብቶችን የሚያበረታታ አመቺ ሁኔታ በመፍጠርም የግብዓት የተጠቃሚውን ተደራሽነት በጉልህ ለማሳደግ ያስችላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በውሱን የግብርና ግብዓቶች ማለትም ዘርና ኬሚካሎች ላይ ተወስነው የሚንቀሳቀሱ ሲሆን በሂደትም ማዳቢያን ለማከፋፈል የነሚያስችላቸው አሠራር በመዘርጋት የግብዓቱን ተደራሽነትና የሥርጭቱን ቀልጣፋነት ማረጋገጥ ያስፈልጋለ ፡፡ ይህንንም ለማስፈጸም የተዘጋጀውን የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ ተግባራዊ የማድረግ ሥራ ይሠራል፡፡ አዲስ ወደ ሥራ በሚገቡት ማእከላትም እስከ 10 000 የሚደርስ የስራ እድል ይፈጠራል፡፡

የግብዓት አቅርቦትና ሥርጭት ክትትል ሥርዓት (Input Tracking System) በተመረጡ ግብዓቶችና አካባቢዎች ተግባራዊ ይደረጋል፣ በሂደትም እንደአስፈላጊነቱ በስፋት ሥራ ላይ ውላል፡፡ የግል ዘርፉ በዘር ማምረትና ሥርጭት ከፍተኛውን ሚና መጫወት የሚያስችሉ እንደ የመሬት አቅርቦት እና የፋይናንስ ተደራሽነት የመሳሰሉት አስቻይና አበረታች ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፣

በክልል የሚንቀሳቀሱ የመንግስት ምርጥ ዘር ኩባንያዎችን አገራዊ ክልላዊ ተሳትፎ በማሳደግ የምርጥ ዘር አቅርቦትን ማሻሻል፡ እነዚህ ኩባንያዎች በክልል ደረጃ ያላቸውን የማሳ እጥረት ለመፍታት የክልል መንግስታት ከሚያመቻቹላቸው ማሳ በተጨማሪ አርሶአደሮችን ማሳ እንዲጠቀሙ ለአርሶአደሮቹ ዕጣ

እንዲሸጡላቸው በማድረግና የባለቤትነት ስሜት በመፍጠር የማሳ እቅርቦቱን በማረጋገጥ የምርጥ ዘር አቅርቦትን አስተማማኝ ማድረግ፡፡

ለውጭ ዘር አምራች ኩባንያዎች ምቹ ሁኔታ መፍጠርና አቅርቦት ማሳደግ፡ የመሬት አቅርቦት፡ የውል ግብርና ልማት ተግባራትን ማጠናከርን፡ የኢንሹራንሽ ስርዓትን ማሻሻልን፣የፋይናንስ ስርዓቱን ማሻሻል እና የቀጥታ ኢንቨስትመንት ሥራ እንዲሰሩ ማደረግ የሚያስችሉ አሰራሮችን ተግባራዊ ማድረግን ያጠቃልላል፡፡ ተደራሽ ላልሆኑ አካባቢዎች ምርጥ ዘር ለሚያቀርቡ ኩባንያዎች ልዩ የማትጊያ ሥርዓት መዘርጋት፡ እነዚህን ማድረግ የሚያስችል መመሪያ በማዘጋጀት መንግስት ልዩ የድጋፍ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ አዳዲስ ዝርያዎችን እና የተመረተ ዘርን በማስተዋወቅ ረገድ ማንናኛውም በምርጥ ዘር ማምረትና ግብይት የተሰማራ ኩባንያ ዕቅድ አንዲኖራቸው የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡

በዘር አቅርቦት እሴት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋንያን ተናብበውና ተቀናጅተው እንዲሠሩ የሚያስችላቸው አሠራር ይዘረጋል፣ አርሶአደሮችና የህ/ሥራ ማህበራት ይራት ያለው ምርት በተሻለ መጠን አንደዲያመርቱና እንዲያሰራጩ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ሥርዓት ማሻሻል

በየዓመቱ እያደገ የመጣውን የአርሶ አደሩን የማዳበሪያ ፍላጎት ለማሟላት አሁን በአቅርቦትና ስርጭት በፍላጎት ዳሰሳ፣ በግዥ ሂደት፣ በማጓጓዝ፣ በክምችትና እና የስርጭት ዙሪያ ችግሮች ያሉበት በመሆኑ እነዚህን ችግሮች፤ መፍታት የሚያስችል አሠራር በመተግበር አርሶ አደሩ ማዳበሪያን በወቅቱ፣ በሚፈልገው ጥራት፤ መጠንና በተመጣጣኝ ዋጋ ገዝቶ በመጠቀም ምርታማነቱን ለማሳደግ በሚያስችል አሠራር ይተገበራል፡፡ እንዲሁም የአፈር ለምነት ፍኖተ ካርታ ምክረ ሃሳብን መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ ፍላጎት ዕቅድ ሥራ ላይ ይውላል፡፡ አሠራሩን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የግል ዘርፉ ተጠያቂነት ባለበት መልኩ በዚህ ሥራ በስፋት የሚሳተፍበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

በግብዓት ኩፖን ሥርዓት የግብርና ግብዓት ሽያጭ ስርዓት ይስፋፋል

በኢትዮጵያ የፋይናንስ እስትራቴጂ ከተለዩትና የገጠሩን ህብረተሰብ ተጨባጭ ሁኔታ ያማከለ የፋይናንስ አቅርቦትን ማመቻቸት ዓላማው የደረገው የግብኣት ኩፖን ሥርዓት በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ክልሎች ለአርሶ አደሩ የአፈር ማዳበሪያን ተደራሽነት ለማሳደግ እየተተገበረ ሲሆን ሥርዓቱ የ10 ዓመቱን መሪ እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በተሻሻለ አሠራር እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

የግብዓት ኩፖን ሥርዓት የሕ/ሥራ ማህበራት የግብዓት ፍላጎት ልየታን ስራ አተኩረው እንዲሰሩ የሚያስችል በመሆኑ ግብዓቶች ያለአግባብ እንዳያድሩ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም ብድሩ የሚሰራጨውና የሚሰበሰበው እስከታችኛው እርከን ድረስ አደረጃጀት ባላቸው ማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ወይንም ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት አማካኝነት በመሆኑ የብድር ማስመለስ ስራውን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡ በግብዓት ኩፖን ሥርዓት የቀጥታ የገንዘብ ንኪኪ ስለማይኖር አርሶአደሮች የተበደሩትን ብድር ለሌላ አላማ እንዳያውሉ ስለሚያደርጋቸው የግብዓት አጠቃቀምን ይጨምራል እንዲሁም ማዳበሪያ በተጨናነቀ ሁኔታ በተወሰኑ ወራቶች ውስጥ ወደ ሀገር የሚገባበትን አሰራር በመቀየር እንደ ሌሎች ምርቶች ዓመቱን ሙሉ ወደ ሀገር የሚገባበትን አሰራር ለመዘርጋት የስችላል፡፡ ይህም ለእቅዱ መሳካት ትልቅ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላትን ማጠናከር

ባለፉት ዓመታት የተገኘውን መልካም ተሞክሮ ከግምት በማስገባት ማዕከላቱን ለማስፋፋትና የግብዓት ተደራሽነት ለማሳደግ በተደረገው ጥረት መሠረት በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ወደ 70 የሚደርሱ ማእከላት የዘርና የኬሚካል ሥርጭትና የምክር አገልግሎት በመስጠት ላይ ሲሆኑ በተለይ በዘር አቅርቦት በኩል 5% ድርሻ አላቸው፡፡ በሂደትም የማእከላቱን ቁጥር በመጨመርና የአሠራራቸውን ማቀላጠፍ ቀስ በቀስ ሥራውን ለግሉ ዘርፍ ለማስተላለፍ መንገድ ይከፍታል፡፡፡፡ ማዕከላቱን ለማቋቋም የሚሳተፉ ባለሃብቶችን የሚያበረታታ አመቺ ሁኔታ በመፍጠርም የግብዓት የተጠቃሚውን ተደራሽነት ለማሳደግ በአሁኑ ጊዜ በውሱን የግብርና ግብዓቶች ማለትም ዘርና ኬሚካሎች ላይ ተወስነው የሚንቀሳቀሱን ማእከላት

ማዳቢያን ለማከፋፈል የነሚያስችላቸው አሠራር በመዘርጋት የግብዓቱን ተደራሽነትና የሥርጭቱን ቀልጣፋነት የማረጋገጥና የመደገፍ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

የግሉ ዘርፍ በማዳበሪያ ከውጭ ማስመጣትና ማሰራጨት ሥራ ላይ መሳተፍ

ማዳበሪያ ለግብርናው ሴክተር ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ግብዓት በመሆኑ፤ ግብዓቱ በሚፈለገው ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራትና ቦታ ተደራሽ ለማድረግ እንደዚሁም ሥርጭቱን ፍትሃዊ እንዲሆን የተጠናከረ የምዝገባ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ መንግሥት ማዳበሪያ ለግብርናው ሴክተር ኢኮኖሚያዊ እድገት ወሳኝ ግብዓት ከመሆኑ አንጻር ግብዓቱን ከውጭ ሀገር ማስመጣትና በሀገር ውስጥ ማሰራጨትን ጨምሮ በርካታ የስራ ጫና የሚታይባቸውን ተግባራት እያከናወነ ሲሆን ቀስ በቀስ ማዳበሪያን በማምረት፣ በማቀነባበር፣ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት፣ በአገር ውስጥ ሽያጭና ወደ ውጭ በመላክ ሥራ ለመሠማራት ለሚፈልጉና የሚወጣውን መስፍርት የሚያሟሉ የኅ/ሥራ ማህበራትን ጨምሮ የግል ባለሀበቶችን መደገፍ፣ ምክረ-ሀሳብ መስጠትና አፈፃፀሙን መቆጣጠር ተሳትፎአቸው እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

የአፈር ማዳበሪያን በሀገር ውስጥ ማምረት እንዲቻል የተጀመረውን ጥረት የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በተለይም በድሬዳዋ የOCP ማዳበሪያ ማምረቻና የያዩ ማዳቢያ ማምረቻን ግንባታ እንዲፋጠን ይደረጋል፡፡የሀገር ውስጥ የምጥን ማዳበሪያ ማቀነባበሪያዎችን ሙሉ በሙሉ ወደ ሥራ እንዲገቡ በማድረግ በተለይም የNPS እና ምጥን ማዳበሪያዎች አቅርቦት ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ አዳዲስ የአፈር ማዳበሪያ ፋብሪካዎችም የሚቋቋሙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

ፀረ ተባይ፣በሽታ እና አረም ኬሚካ አቅርቦት ስርዓት ማሻሻል

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የአነስተኛ አርሶአደሮች የጸረ-ተባይ፣በሽታ እና አረም ፍለጎትና አጠቃቀም በተለይም በአበባና አትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች በከፍተኛ ደረጃ መጨሩን ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ፍላጎት በቀጣዩ አሥር ዓመታትም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚጨምር ታሳቢ በማደረግ፡፡ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በአግሮ ኬሚካል ምርት እንዲሳተፉ የማበረታቻሥርዓት ይዘረጋል፤ በየምርት ወቅቱ የሚፈለገው የአግሮ ኬሚካሎች መጠን ፍላጎትን መሰረት ባደረገ መልኩ እንዲገዛና እንዲሰራጭ ተገቢው ክትትል ይደረጋል፡፡

የኖራ አቅርቦት ስርዓትን ማሻሻል

በኢትዮጵያ የአፈር አሲዳማነት በየጊዜው እየጨመረ የመጣ ሲሆን በአሁኑ ወቅት 3.0 ሚሊዮን ሄክታር የደረሰ ሲሆን በሁለተኛው እቅድና ትራንስፎርሜሽን ዘመን አሲዳማ አፈርን በማከም የነበረውን አፈጻጸም በማሻሻል በ2017 1.5ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማከም ፀቅድ ተይሏል፡፡

የኖራ ዝግጅትና ሥርጭት በማህበር በተደራጁ ቡድኖች/የኃ/ሥራ ማህበራት አማካኝነት እንዲከናወን አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማእከላትን በማጠናከርና ሥርዓት በመዘርጋት በኖራ አቅርቦትና ሥርጭት እንዲሳተፉ ሁኔታዎች **ይመቻቻሉ እንዲሁም ሥርጭቱን የበለጠ ቀልጣፋ ለማድር የግሉ ዘርፍ ኖራን እንዲያምትና እንዲያሰራጭ ማበረታቻዎች ይደረጋሉ**

ሕያው ማዳበሪያ አቅርቦት ስርዓትን ማሻሻል

እስከ 2011 ምርት ዘመን በነበረው ጊዜ ውስጥ የጥራጥሬ ሰብሎች ልማትን ለማሳደግ የህያው ማዳበሪያ አጠቃቀምን በ172,000 ሄ/ር ደረጃ ማሳደግ እንደተቻለ የአቅራቢዎችና የተጠቃሚ ክልሎች ሪፖርት ያመለክታል፡፡ በቀጣይ ዓመታትም ይህን በማስፋት ምርታማነትን የማሳደግ ሥራ ይሰራል፡፡

ህያው ማዳበሪያ (Bio Fertilizer) ለጥራጥሬ ሰብሎች ምርታማነት ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ በተጠቃሚ አርሶ አደሮች ዘንድ አስፈላጊውን ግንዛቤ በመፍጠርና አቅርቦቱ የተስተካከለ እንዲሆን በመደገፍ በተለይ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ጥራጥሬ ሰብሎችን ምርታማነትና ጥራት ለማሳደግ በተሻለ ሁኔታ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ ያለፉት ዓመታን የህያው ማዳበሪያ አጠቃቀም መረጃ

እንደሚያሳው ፍላጎቱ በተወሰነ ደረጃ እየጨመረ መጥቶ በዓመት በአካይ 1ሚሊዮን ባለ 125 ግራም ሳቾት ደርሷል። ይህን እያደገ የመጣ ፍላጎት፣ አሁን ያሉትን አምራቶችና በሂደትም ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ማምረቻዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ታሳቢ በማደረገብ በ2017 የሚቀርበው ይያው ማዳበሪይ መጠን 1.3 ሚሊዮን ባለ125 ግራም ይደርሳል ተብሎ ታቅዷል።

የህያው ማዳበሪያ አምራቶችና ተአቃሚዎች ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ መልኩ የገበያ ትስስር የሚፈጠሩበት ሁኔታ ይመቻቻል። ክትትልና ድጋፍም ማድረግ፤ የግብርና ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት በማእከላት የህያው ማዳበሪያን ከሌሎች ግብኣቶች ጎን ለጎን ለለተጠቃሚው የሚያከፋፍሉበት ሁኔታና አሠራር ማመቻቸት፤ ህያው ማዳበሪያ አምራቾች/አቅራቢዎች ያሉባቸውን ውሱንነቶች በመለየት ድጋፍ በማድረግና ምቹ ሁኔታ በመፍጠር አቅርቦቱ በጥራት፣ በወቅቱና በስተማማኝ እንዲሆን ይሠራል።

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ስርዓት መዘርጋት

እስካሁን ባለው አሰራር ለቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት የሚያስፈልጉ የዘርና የችግኝ አቅርቦትና ስርጭት፣ የዘመናዊ እርሻ መሳሪያዎች አቅርቦት፣ የማዳበሪያና የሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት ሥርዓት የምርታማነት ዕድገት ግቡን ለማሳካት በሚያስችል ደረጃ የተቃኘ አይደለም። ስለሆነም የአርሶ አደር፣ የግል ባለሃብት፣ ሕብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም መንግስት በምርጥ ዘር፣በማዳበሪያ በጸረ-ተባይ እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት እና ስርጭት ላይ እንዲሳተፉ በማድረግ ነባርና አዳዲስ የዘር እና የችግኝ ማባዣ ቦታዎችን በማስፋፋት ዘመናዊ የግብዓት አቅርቦትና ስርጭት ስርዓትን በመዘርጋት ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ ይሰራል።

የግብዓት ፋይናንስ አቅርቦት ማመቻቸት፡-

የገጠር ማይክሮ-ፋይናንስ ተቋማት የሚያቀርቡት የብድር አገልግሎቶች የወለድ መጠን ተመጣጣኝና የሚያበረታታ እንዲሆን ማድረግ፤

2.1.1.5 የሰብል ግብዓት ጥራትና ቁጥጥር

የሬጉላቶሪ አገልግሎት ሲባል የዕጽዋት ዝርያ ብቃትና ዘር ጥራት ማረጋገጥ፣ የዕፅዋት ኳራንቲን (የዕፅዋት ጤና) ፣ የግብርና ምርት ጥራትና ደህንነት፣ የአግሮኬሚካል (ፀረ ተባይና የማዳበሪያ) ፍቱንነት፣ ደህንነትና ጥራት ማረጋገጥ እና የተፈጥሮ እርሻ ማስፈፋት ላይ አተኩሮ የሚሠራ ነው።

አሁን ካሉት በተጨማሪ 10 አዳዲስ የኳራንቲን ጣብያዎች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፤ በአሁኑ ጊዜ ሥራው ያልተጀመረውን የማዳበሪያ የምዝገባ ሥርዓት አስፈላጊውን የሕግና የአሠራር ሥርዓት በማሟላት የምዝገባ ሥርዓቱ እንዲጠናከር ይደረጋል፤ ለሬጉላቶሪ አገልግሎቶች መሠረት የሆኑ የሕግ ማዕቀፎች እንዲሟሉ ይደረጋል፤ የግብርና ምርቶች ከፀረተባይ ቅሪት ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል አንድ የምርመራ ላቦራቶሪ ይደረጃል፤ ለግል ባለሃብቶች የተሰጠው ያልተመዘገቡ ፀረ-ተባዮች በራሳቸው እርሻ ላይ እንዲጠቀሙ የሚፈቅደው አሠራር ወደ መደበኛው አሠራር እንዲካተት በማድረግ እየገጠመ ያለውን የሕግ ጥሰት እንዲቆም ይደረጋል፤ጥቅም ላይ መዋል የማይችሉ 1 ሺህ ቶን ፀረተባዮች አንዲወገዱ ይደረጋል፤ የተፈጥሮ እርሻ በማስፋፋት 1 የሰብልና 1 የእንስሳት ምርቶች በኦርጋኒክ ምርትነት ለገበያ ማቅረብ በዕቅድ ተይዘሏል።

በሰብል ጤና፣ ምርት/ግብዓት ጥራት እና ደህንነት አገልግሎት አሰጣጥ አቅምን በማሳደግ ከውጭ አገርም ሆነ በአገር ውስጥ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ አካባቢ የሚደረጉ የግብዓትና የምርት ዝውውርን ጤና፣ ጥራትና ደህንነት በማረጋገጥ ለምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ይደረጋል፡ ፡ በሀገሪቱ የዕፅዋት ሬጉላቶሪ ተግባርን በአስር አመት ውስጥ ውጤታማ ለለአማድረግ የሚከተሉት ተግባራት ይፈፀማሉ።

የኳራንቲን ተባዮች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ቁጥጥር ማድረግ

በኳራንቲን አሠራር መርህ መሠረት ለአገራችን ስጋት የሚሆኑት በአገራችን የሌሉት ተባዮች ስለሆኑ እነዚህን ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል፤ ስለሆነም የአገራችንን የኳራንቲን ተባይ ዝርዝር በየጊዜው

በመገምገም ወቅታዊነቱ እንዲይዝ ይደረጋል፤ ወደ አገር ውስጥ ከሚገቡ ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ጋር በአገሪቱ የሌሉ ባዕድ ተባዮች ገብተው የዕፅዋት ሃብት እንዳይጎዱ በቅድሚያ የተባይ ስጋት ትንተና ይከናወናል፡፡ ይህንን ማድረግ የሚቻለውም የድኅረ መግባት ኳራንቲን በማቋቋም፣ የፍተሻ መሠረተ ልማት፣ ቁሳቁስና የባለሙያዎች አቅም በማሳደግና በዓለም አቀፍ ደረጃ አገሪቱ በተስማማችባቸው ደረጃዎች መሠረት በመሥራት ይሆናል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ በዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያዎች፣ ባቡር ጣብያዎች፣ፖስታ ቤቶች እና የመግቢያ በሮች አቅም በማሳደግ የተጠናከረ የቁጥጥር ስራ ይሠራል፡፡

የድህረ መግባት ኳራንቲን (Post Entry Quarantine) ጉዳት የሚያስከትሉ ተባዮች ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ከሚመጡበት አገር ወይም አካባቢ ይዘው እንዳይገቡ ለማድረግ የሚያስችል ሥራ የሚሠራበት ፋሲሊቲ በመሆኑ በአገሪቱ በመንግሥትና በግል ባለሃብቶች ጥምረት የድኅረ መግባት ኳራንቲን ፋሲሊቲዎች ተገንብተው ወደ አገር ውስጥ ለመባዛት የሚገቡ ዕፅዋት ከኳራንቲን ተባዮች ነፃ መሆናቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል፡፡

ወደ ውጭ የሚላኩ ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች የተቀባዩ አገር ፍላጎት የሚያሟላ መሆኑን በኢንስፔክሽንና በላቦራቶሪ ምርመራ ውጤት በመታገዝ የማረጋገጥና የዕፅዋት ጤንነት ማረጋጫ ምስክር ወረቀት (Phytosanitary Certificate) ይሰጣል፤የኢንስፔክሽንና ምርመራ አገልግሎቱ ተደራሽ ለማድረግ የብቃት ማረጋገጫ ያላቸው የግልና የመንግሥት ድርጅቶች እንዲሳተፉበት ይደረጋል፡፡

የአገር ውስጥ የኳራንቲን አሠራር በመዘርጋት በአንዱ የአገራችን ክፍል የተከሰተ ተባይ ወደ ሌላው የአገሪቱ ክፍል እንዳይዛመትና እንዳይስፋፋ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የአገር ውስጥ የኳራንቲን ኬላዎች ይጠናከራሉ፤ የሕግ ማዕቀፍም ተቀርፆላቸው በሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

ወደ ውጭ በሚላኩትም ሆነ ወደ አገር ውስጥ በሚላኩ ዕፅዋትና የዕፅዋት ውጤቶች ላይ በፀደቁ ደረጃዎች መሠረት ህክምና የተደረገላቸው መሆኑን በማረጋገጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

ባዕድ ተባዮች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ የኳራንቲን አገልግሎት ማጠናከር

የኤክስፖርት ሰብል ምርት በኳራንቲን ስታንዳርድ አለመሟላት ምክንያት ተቀባይነት እንዳያጡ ይደረጋል፡፡ለዚሁም አገሪቱ አባል የሆነችበት የዕፅዋት ጥበቃ ስምምነት ባፀደቃቸው ኳራንቲን ስታንዳርድ መሰረት የተባይ ስጋት ትንተና፣ የኢንስፔክሽን፣የምርመራና የህክምና አሰጣጥ ሥራ ይሰራል፡፡ ይህ ከውጭ የሚመጡትን ተባዮች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ ብሎም እንዳይስፋፉ በመከላከል የምርት ብክነት ይቀነሳል፡፡

የአፈር ማዳበሪያና የፀረ ተባይ (አግሮኬሚካል) ፍቱንነት፣ ጥራትና ደህንነት ማረጋገጥ

እነዚህ ኮሞዲቲዎች ኬሚካል በመሆናቸው በሰው፣ በእንስሳትና በዕፅዋት ሕይወት እና በአከባቢ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ ቁጥጥር ከሚደረግባቸው ቁሶች መካከል እንዲሆኑ በሕግ ተደንግጓል፤ ስለሆነም በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ፍቱንነታቸውና ደህንነታቸው በመንግሥትና በግል የምርምር ተቋማት እንዲረጋገጥና እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡ በሕገ ወጥ መንገድ የሚገቡትን ለማስቆም ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀትና የሕግ ማዕቀፎችን በማሟላት ጠንካራ የቁጥጥር ሥራዎች ይሰራሉ፡ :

የማዳበሪያ ጥራት ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት፡- እስከአሁን በዚህ ረገድ ያለው ማነቆ ብዙ በመረጃ የተደገፈ ባይሆንም ይህን ችግር የሚያመላክቱ ጥናቶች በማካሄድ መፍትሄ ይሰጣቸዋል፡፡

ፍቱንነቱ፣ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የአፈር ማዳበሪያና ፀረ ተባይ (አግሮኬሚካል) አቅርቦት

በአገር ውስጥ የተመረቱ ሆነ ከውጭ የሚመጡ አግሮኬሚካሎች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ለታለመላቸው ዓላማ ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የፍቱንነትና የደህንነት ሙከራ በምርምር ተካሂዶ ተፈላጊው መስፈርት ሲያሟሉ ምዝገባ ይሰጣቸዋል፡፡ አጠቃቀማቸውና አያያዛቸውም በአምራቹና በምርምር በተረጋገጠውና በሕግ በተደነገገው መሰረት ይከናወናል፡፡ ይኸውም አግሮኬሚካሎች የብቃት ማረጋገጫ ባለው ሰው ብቻ እንዲያዝ የሚያስገድድ አሠራር ይዘረጋል፡፡

በሰብል ዝርያ ብቃት እና ዘር ጥራት ማረጋገጥ

የሰብል ልማት ዓላማዎችን እና ግቦችን ለማሳካት በዝርያ ብቃት እና ዘር ጥራት ማረጋገጥ የሚከተሉት ስትራቴጂክ ተግባራት በቀጣይ አምስት ዓመታት ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

ሀ/ የዝርያ ብቃትና ጥራት ማረጋገጥ የሚመራ አገራዊ ተቋም ማደራጀት፡- የዚህ ተቋም መኖር የውጭ እና የአገር በቀል ኩባንያዎች መብታቸው ተጠብቆ በአገር ውስጥ እንዲንቀሳቀሱ ይረዳል፡፡ ይህን በማድረግም ለአርሶአደሩ ተዋዳዳሪና ቀልብ ሳቢ የሆኑ የሰብል ዝርያዎች ለማቅረብ ይረዳል፡፡ አደረጃጀቱን እውን ለማድረግም የሚያስፈልግ ደንብ ረቆ ይጸድቃል፡፡ አደረጃጀቱም ዘርን፣ሌሎች ግብርና ግብዓቶች፣ኳራንቲንን፣ምርት ጥራትን እና እነዳአስፈላጊነቱም ግብርና ሬጉላቶሪ ሥራዎች ሁሉ አንዲያካትት ይደረጋል፡፡ ኬንያ ራሱን የቻለ ሬጉላቶሪ ተቋም አደራጅታ ለብዙ ዓመታት የመዋቅር ለውጥ ሳታደርግ በመምራቷ በምስራቅ አፍሪካ ታዐማኒ የሆነ የምርት ጥራት ተቋም ለመገንባት ነው፡፡ ይህንንም በማድረግ እስከአሁን የጸደቁ አገር አቀፍ አዋጆች፣ ደንቦች፣መመሪያዎችን ተግባራዊነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ለ/ የዝርያ ለቀቃ እና ጥበቃ አሰራሩ አስገዳጅም ፈቃድኝነትንም ያካተተ እንዲሆን ማድረግ፡- በቀጣይ አምስት ዓመታት በግል እና በመንግስት ጥበቃ የሚደረግላቸው ተወዳዳሪ ዝርያዎች ቁጥር ያድጋል፡፡ በተጨማሪም የዝርያ ለቀቃ ሥርዓቱ አስገዳጅም ፈቃደኝነትም መሰረት ያደረገ እንዲሆን በማድረግ ወደ ምርት ሥርዓቱ የሚገቡ ውጤታማ ዝርያዎች ቁጥር ይጨምራል፡፡ ፈቃደኛ ይሆናል ማለት ለተመረጡ ሰብሎች አግባብነት ባለው ተቆጣጣሪው አካል የዝርያ ብቃት ማረጋገጥ ሙከራ መስራት ሳያስፈልግ የዝርያው ባለቤት በሚያቀርበው የአገር ውስጥ የማላመድ ሙከራ ውጤት መሰረት ጥቅም ላይ የሚውሉበት የአሰራር ስርዓት መዘርጋትን ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ዝርያው ለውጭ ገበያ ብቻ የሚፈለግ ከሆነ ሳይመዘገብ በአገር ውስጥ ተባዝቶ ቀጥታ ወደ ውጭ በላክንም ያካትታል፡፡ ይህን ማድረግ የሚያስችል አሰራር እና ተቋም ይደራጃል፡፡

ሐ/ ምርጥ ዘር ወደ ውጭ ለመላክ የሚያስችለን የብቃት እና የዘር ጥራት ማረጋገጫ አሰጣጥ ሥርዓት ይዘረጋል፡- ይህን ተግባራዊ በማድረግ ለአገር ውሰጥ አዝርዕት፣ሆርቲካልቸር፣ቡና፣ሻይ ቅማመቅመም ማምረት ከሚውለው ምርጥ ዘር በተጨማሪ የውጭ ገበያ ላይ ድርሻ እንዲኖር የሚያደርግ አሰራር በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ይሰራል፡፡ ይህንንም ለማድረግ አገራችን ከዘር ጋር ከሚሰሩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማለትም ISTA, OECD, COMESA እና እንደአስፈላጊነቱ ወይም በረጅም ጊዜ ውስጥ UPOV አባል እንድትሆን ይደረጋል፡፡ ይህንንም በማድረግ ሂደት የብሄራዊ ዘር ላቦራቶሪው ISTA እውቅና አንዲሰጠው የሚያስችል ሥራ ይሰራል፡፡ በእነዚህ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ንቁ ተሳትፎ ከሚያደርጉ አገሮች የታችኛው ሳህራ አፍሪካ አገሮች ይገኙበታል፡፡ ለመጥቀስ ያህል አገሮቹ እአአ በ2012 በበቆሎ ከተመዘገው 2.44 ቢሊየን ዶላር ኤክስፖርት ውስጥ የታችኛው ሳሕራ አገሮች ድርሻ 210 ሚሊዮን ዶላር ነበር፡፡ ከክልሉ ሰባቱ አገሮች የኤክስፖርቱ 99.4 በመቶ ድርሻ ነበራቸው፡፡ እነዚህ አገራት በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ያላቸው ተሳትፎ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ተሳትፎ የላትም፡፡

መ/ የዝርያ ብቃትና የዘር ጥራት ቁጥጥር አቅም ማሳደግ፡- የዘር ጥራትን ማረጋገጥ ለአርሶአደሩ ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ አለው፡፡ የዘር ጥራትን በዘር ሰንሰለቱ ሁሉ ማረጋገጥ የሚያስችልን የሰው ኃይል፣መሰረተ ልማት፣ ሎጅስቲክ፣ቁሳቁስ አቅም ይገነባል፡፡

በየክልሎች የፍተሻ ቁሳቁስ የተሟላለት ሪፈራል የዕጽዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር ላቦራቶሪ መገንባት፡- የዘር ጥራትን ማረጋገጥ ለአርሶአደሩ ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ አለው፡፡ ክልሎች በስራቸው ያሉትን የዘር ላቦራቶሪዎችና በቀጣይም በግል ዘር ጥራት ለማረጋገጥ ፈቃድ የሚሰጣቸውን ላቦራቶሪዎች ብቃት የሚያረጋግጡበት ሪፈራል የዘር ጥራት ላቦራቶሪ ያስፈልጋቸዋል፤ይህንም አቅም በክልል ደረጃ አንዲኖር ጥረት ይደረጋል፡፡

- የድህረ-ጥራት ፍተሻ ጣቢያዎችን ማጠናከር፣ አዳዲስ ማደራጀትና የመስኖ ተደራሽነትን ማረጋገጥ፡- የምርጥ ዘር ጥራት ማረጋገጡ ሥራ በመስክና በላቦራቶሪ ከተጠናቀቀ በኋላ ምርጥ ዘር በማጓጓዝ ሂደት፣ በማጋዘን፣ ሆን ተብሎ በልዩ ጥቅም ፈላጊዎች ለጥራት መጓደል ሊጋለጥ ይችላል፡፡ ከዚህም

በተጨማሪ ኢንስፔክተሮች ባላቸው ሠልጣን ተጠቅመው ማለፍ የማይገባውን ዘር በመስክ ጥራት ቁጥጥር ወቅት አንዲያልፍ በማድረግ ለጥራት መጓደል አስተዋጽኦ ሊኖራቸው ይችላል። ከዚህም ሌላ ደረጃን ያሟላ ዘር አላሟላም በማለት ከአቅርቦት ሥዓቱ እንዲወገድ ሊያደርጉ ይችላሉ፤ ከምርጥ ዘር ሥርጭት በፊትም /ለመነሻ ዘርች/ ሆነ ለአርሶአደሮች ከተሰራጨ በኋላ የዘርን ጥራት መልሶ ለማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር ድህረ ጥራት ፍተሻ ይባለል። ይህ አሰራር ተግባራዊ የሚሆነው በሙከራ ጣቢያዎች ነው፤እነዚህን ጣቢያዎች ለመቋቋምም ሆነ ውስጣዊ ቁሳቁስ ለማሟሟላት የሚያስችል ድጋ ይደረጋል።

- የመስክ ጥራት ማረጋገጥን ማዘመን፤ አቅም መገንባት እና የራስ በራስ ዘር ጥራት ማረጋገጥ ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት/Certification licencing/ ተግባራዊ ማድረግ፥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥራውን ለማዘመን በጂፒኤስና በጂአይኤስ፣በአይሲቲ እና በኤሌክትሮኒክ ታግ ሥርዓት የተደገፈ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል። ከሰብል ዘር የማሳ መበከል ጋር ተያይዞ ወቅቱን የጠበቀ የዘር ጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ ተሽከርካሪ የሚኖረው ሚና ታላቅ ነው።በዚህን ሰዓት ላቦራቶሪዎች አንድ ተሽከርካሪ ከ7000 ሄ/ር ለሚልቅ ማሳ ይጠቀሙበታል።ይህ ደግሞ በወቅቱ በየማሳዎቹ ደርሰው የማሳ ጥራት ቁጥጥር ለማካሄድ እንደማይችሉ አመላካች ነው። ተሽከርካሪን ቁጥር በማሳደግ የምርጥ ዘር ጥራት ቁጥጥሩን መደገፍ ይቻላል።ከዚህም ሌላ ደግሞ አቅም ያላቸውን አምራቾች የ ዘር ጥራት ማረጋገጥን ሥራ በራሳቸው አንዲያከናውኑ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት የመስክ ጥራት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን መ/ቤቶችን ጫና መቀነስ የዘር ጥራትን ማሳደግ ታሳቢ ያደረገ አሰራር ተግባራዊ ይሆናል።

- የዝርያ ብቃት ሙከራና የዝርያ ባለቤትነት የሚረጋገጥባቸው የዝርያ ልዩ መሆን፣ወጥና የማይለዋወጥ መሆኑ የሚፈተሸባቸው ጣቢዎች በአገሪቱ ወካይ ሥነምህዳሮች ማቋቋም፡- የዝርያ ብቃት ገለልተኛ በሆነው በሚኒስቴሩ ተቆጣጣሪ አካል አንዲካሄድ ለማድረግ ብሄራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ NPT) እና የዝርያ ልዩ፣ወጥ እና የማይለወጥ ባህርይ(DUS) ፍተሻ ሥራዎች ማካሄድ የሚያስችሉ ጣቢያዎች እና ቤተሙከራዎች ይደራጃሉ። ይህን በማድረግም ታዐማኒ እና ከምርምር ሥርዓቱ የተለየ የዝርያ ብቃት አረጋገጭ እና የባለቤትነት መብት ጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል።

- የዝርያ ብቃት ሙከራና የዝርያ ባለቤትነት የሚረጋገጥባቸው የዝርያ ልዩ መሆን፣ወጥና የማይለዋወጥ መሆኑ የሚፈተሸባቸው ጣቢዎች በአገሪቱ ወካይ ሥነምህዳሮች ማቋቋም፡- የዝርያ ብቃት ገለልተኛ በሆነው በሚኒስቴሩ ተቆጣጣሪ አካል አንዲካሄድ ለማድረግ ብሄራዊ የዝርያ ብቃት ማረጋገጫ (NPT) እና የዝርያ ልዩ፣ወጥ እና የማይለወጥ ባህርይ(DUS) ፍተሻ ሥራዎች ማካሄድ የሚያስችሉ ጣቢያዎች እና ቤተሙከራዎች ይደራጃሉ። ለምርታማነት የሚለቀቁ አገር በቀል የተሻሻሉ ዝርያዎች አርሶደሮች እንዲጠቀሙአቸው ማድረግ አንዲቻል ከመለቀቃቸው በፊት በአርሶአደር ማሳ በሰፊው የማስተዋወቅ ስራ እንዲካሄድ ይደረጋል።ይህን በማድረግም ታዐማኒ እና ከምርምር ሥርዓቱ የተለየ የዝርያ ብቃት አረጋገጭ እና የባለቤትነት መብት ጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል። ፡- ከዚህም በተጨማሪ ምንም የድኅረ መግባት ኳራንቲን አገልግሎት ከሌለበት በተመረጡ 3 ቦታዎች እንዲቋቋሙና ሥራ ላይ እንዲገቡ ይደረጋል፤ ይህን በማድረግም ታዐማኒ እና ከምርምር ሥርዓቱ የተለየ የዝርያ ብቃት አረጋገጭ እና የባለቤትነት መብት ጥበቃ ሥርዓት ይዘረጋል።

- የአካባቢ ዝርያዎች እውቅና አግኝተው በስፋት አንዲባዙ ለማድረግ የባህርይ ልየታ ፍተሻ ስራዎችን መደገፍ፡-የዚህ ተግባር ዋና አላማ በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙና ተሻሽለው የቀረቡ ከተባሉ ዝርያዎች የተሻለ ምርት መስጠት የሚችሉ ወይም የተለየ ተመራጭ ባህርይ ያላቸውን በመለየት ሕጋዊ እውቅና አንዲያገኙ በማድረግ በስፋት አንዲባዙ እና ለምርትና ምርታማነት ያላቸውን አስተዋጽኦ በተሻለ ሁኔታ እና በስፋት አንዲያበረክቱ ለማደረግ የሚያስችል የአመዘጋገብ ሥርዓትን ለማነቃቃት ነው፡

- የዘር ጥራት ቁጥጥርና የማረጋገጥ ሥርዓቱን ብቃት ለማረጋገጥ የምርምር ተግባራት በአራቱም ክልሎች ማካሄድ፡-የዘር ጥራት አረጋገጭ ተቋማት በህግ የተሰጣቸው ሥልጣን ከፍተኛ መሆኑ ይወቃል። ሆኖም ግን እነዚህ ተቋማት የጥራት ቁጥጥር ማረጋገጥ ሥርዓታቸው ብቃት

የሚፈተሸበት አሰራር እስከአሁን አልተዘረጋም። ብቃታቸውን አስመልክቶ የሚሰነዘርባቸው ትችት ሳይንሳዊ ያልሆነና በመረጃ የተደገፈ የማስተካከያ እርምጃ ለመወሰድም አስቸጋሪ አድርጎታል። ይህም ደግሞ ብዙ ሃብት የፈሰሰባቸው ተቋማት በአግባቡ ሳይገመገሙ ለተደጋጋሚ መፍረስ ሲዳረጉ ቆይተዋል። የዘር ጥራት ቁጥጥሩም ሥራ በግብታዊነት በሚወሰድ ውሳኔ የተነሳ ባለቤት እንዲያጣ ሲደረግ ቆይቷል። ስለዚህ የጥራት አረጋጋጭ ተቋማት ብቃት መገምገም የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት አንዲቻል ምርምር ማካሄዱ ተገቢ ነው። ይህም ኢንቨስትመንት በቀጣይ አንዚህ ተቋማት ለመገምገም የሚያስችል ሞዳሊቲ አንዲኖር ያደርጋል።

- በተመሳሳይ የየክልሎችን አቅም በሰው ኃይል፣ በላቦራቶሪ እና በፍተሻ ቁሳቁስ፣ በድህረ-ጥራት ቁጥጥር ጣቢያዎች፣ ለኢንስፔክሽን በሚሆኑ ተሽከርካሪዎች እንዲጠናከሩ ይደረጋል። የክልል ተቆጣጠሪ ባለስልጣን መ/ቤቶች በፋይናንስ ራሳቸውን አንዲችሉ ለማድረግ ለሚሰጡት አገልግሎት በቂ ገቢ እንዲሰበስቡ የሚያደርግ አሰራር ተግባራዊ ይሆናል። የዘር ጥራት ቁጥጥር ሥራውን ለማዘመን በጂፒኤስና በጂአይኤስ፣በአይሲቲ እና በኤሌክትሮኒክ ታግ ሥርዓት የተደገፈ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

ሠ/ የዝርያ ብቃትና ዘር ጥራት ማረጋገጥ አገልግሎቱን ለ3ኛ ወገን ማካፈልአማራጮችን ማስፋት፡- ይህን ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎቱን ቀልጣፋ. ጊዜ እና የመንግስ ወጪ ቆጣቢ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል። ለዚህም ፈቃደኛ የሆኑ አካላትን የመጋበዝ፣ እንደአስፈላጊቱም የማደራጅት /በተለይ ወጣቶች/ እና አቅም ግንባታ ድጋፍ የመስጠት ሠሥራዎች ይሰራል።አቅም ያላቸው የምርጥ ዘር ኩባንያዎች የዘር ጥራት ማረጋገጥ ሥልጣን እንዲኖራቸው የሚያደረግ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ይዘረጋል።ይህን ለማድረግም የመስክ ጥራት ቁጥጥር፣የላቦራቶሪ ፍተሻ እና የሽያጭ ወኪሎች ራበራስ ሰርቲፊኬሽን ስልጣን አንዲኖራቸው የሚያስል ስርዓት ይገነባል።

የሰብል ልማትና ጥበቃ ማስፈፀሚያ ስልቶች

የተሻሻሉ የሰብል አመራረት ዘዴዎች ማስፋት

የእርሻ ማሳን አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/ከፊል አርብቶ አደሮችም ሆኑ በመካከለኛና ሰፋፊ እርሻ አልሚዎች በዘመነ መልኩ እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ሥርዓት ይዘረጋል። ይህም ምርትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉና በአፈፃፀም ወቅት ክፍተት የነበረባቸውን (missing elements) ተግባራት ማለትም ወቅቱን ጠብቆ ማሳን ማዘጋጀትና መጠንን ጠብቆ መዝራትን፣ በአንድ ዩኒት ማሳ ስፋት ውስጥ መኖር የሚገባውን የቡቃያ/ተክል ቁጥር እንዲኖር ማድረግን፣ ተገቢው አግሮኬሚካል ምክረ-ሀሳቡን በሚያዘው መጠን መጠቀምንና ተገቢ የማሳ አንክብካቤን፣ ምርትን በወቅቱ ማሰባሰብን እና የድህረ-ምርት ብክነትን መቀነስን በማረጋገጥ ተግባራት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል። እስካሁን የነበረውን የልማት ሰራተኞች ትኩረት ያጣ ኃላፊነትና የስራ አተገባበር ባህል በመለወጥ በአንድ አርሶአደር ወይም ከፊል ከፊል አርብቶ አደር ማሳ ላይ የተዘራው ሰብል ተገቢውን ቡቃያ/ተክል ቁጥር የያዘ መሆኑና የተሻሻለ አሰራር እየተከተለ ስለመሆኑ በማሳ ደረጃ ምክር በመስጠት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

የቅድመና ድህረ-ምርት ሜካናይዜሽን አጠቃቀምን ማስፋት/ማሻሻል

አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶአደሮች የሜካናይዜሽን ተጠቃሚነት፣ ምርትና ምርታማት እና የምርት ጥራት የማሳደግ ሥራ ይሰራል። በዋናነትም የሜካናይዜሽን አገልግሎት ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎች አርሶአደሮች በእርሻ ልማት ከተሰማሩ ኢንቬስተሮች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ አገልግሎቱን እንዲያገኙ ይደረጋል። የኪራይ አገልግሎት ሥርዓትም እንዲኖር ይደረጋል። በአካባቢው ኢንቨስተሮች በማይገኙባቸው አካባቢዎች ግን የሜካናይዜሽን አገልግሎትና ጥገና ማዕከላት እንዲስፋፉና ድጋፍ እንዲደረግ በቅንጅት ይሰራል።

የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን ማስፋትና ስርዓተ-ምግብን ማሻሻል

ከአገሪቱ የአየር ሁኔታ፣ አመራረት ስርዓትና አቅምን ያገናዘቡ የድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም በማስፋፋት እንዲሁም ለእሴት ሰንሰለት ተዋናዮች (Value chain actors) በድህረ-ምርት አያያዝና ማቀነባበር አቅም የመገንባት ስራ ይሰራል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የድህረ-ምርት አያያዝና ማቀነባበር

ሳይንስ ትምህርት በከፍተኛና መካከለኛ ደረጃ ተቋማት ተጠናክሮ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በሌላ በኩልም የግሉን ዘርፍ ተሳትፎና አቅም በድህረ-ምርት አያያዝ እንዲሁም ቴክኖሎጂዎችና ማቀናባበሪያዎች ማምረት ስራ ላይ በማጠናከር በአጠቃላይ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ያማከለ የአነስተኛና መካከለኛ ደረጃ የከፊል ምርት ማቀናበርና እሴት የመጨመርን (Semi-processing and value addition) ስራ በማስፋፋት ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ተጠቃሚነት የማረጋገጥ ስራ ይሰራል፡፡

በእሴት መጨመር፣ በድህረ-ምርት አያያዝና ምርት በማቀናበር ስራዎች ዙሪያ ኢንቨስትመንትን ማበረታታት እና ለዚህም የሚረዱ ለማቀናበር ተስማሚ የሆኑና አነስተኛ የድህረ-ምርት ብክነት ያላቸውን ዝርያዎች የማስፋፋት ስራ በመስራት እንዲሁም አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችን በማደራጀት የምርት አቅርቦታቸውን በጋራ በማድረግ የምርት ብክነትን የመቀነስ ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ ትላልቅ የግል ኮሜርሻል እርሻዎች በዙሪያቸው ከሚገኙ አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አምራች አርሶ አደሮች ጋር የአቅርቦት ትስስርን በማጎልበት አግሮ-ኢንዱስትሪዉና ኤክስፖርቱ እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

የተቀነባበሩ ምርቶችን ጥራትና ዋጋ እንዲሁም የህብረተሰቡን ፍላጎት ባገናዘበ መልኩ በማቅረብና አስፈላጊውን የማስተዋወቅ ስራ በመስራት የሆርቲካችልር ምርቶችን የመጠቀም ልምድ እንዲጨምር የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡ ይህም በማቀነባበር ዘርፍ የሚሰማሩ የሀገር ውስጥና የውጭ ኢንቬስተሮችን ሳቢ ያደርጋል፡፡

የሆርቲካልቸር ሰብሎች ምርት ከተሰበሰበ በኋላ ቶሎ ለብልሽት የሚዳረጉ በመሆኑ የድህረ ምርት አያያዝና አጠቃቀም በተለየ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡

አዳዲስ ስነ ምህዳሮችን ለተፈላጊ አዳዲስ ሰብሎች በጥናት በመለየት ልማትን ማስፋት

ከመሀል አገር ራቅ ባሉ እና በጥናት በሚለዩ እንዳንድ አካባቢዎች ለአንዳንድ አዝርዕት ሰብሎች አመራረት አመቺ ማሳዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ እንዳንድ የሩዝ ዝርያዎች ውሃ በሚተኛባቸው አካባቢዎች ሊመረቱ ይችላሉ፡፡ እነዚህን አካባቢዎች በጥናት የመለየት ሥራ ይሰራል፡፡ የሠብል ልማቱም እንዲሰፋፋ ይደረጋል፡፡

እንዳንድ አካባቢዎች ለአንዳንድ **የሆርቲካልቸር ሰብሎች** አመራረት አመቺ ማሳዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ የተራቆቱ አካባቢዎችን በመከለልና እንዲያገግሙ በማድረግ የፍራፍሬ ሰብሎችን የማልማት ተግባር ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ሌሎች ለልማት ያልዋሉና በዘርፉ ያሉትን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም እና ማይክሮ ክላይሜቱን በማሻሻል ያለ አፈር የማልማት /hydroponic technologies/ ተግባር እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ ለዚህም አዲሱን የኢትዮጵያ ሳተላይት/ETRSS-1/ መረጃ መጠቀም የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የሰብል ምክር አገልግሎቱን በቴክኖሎጅ መደገፍ

ለአዝርዕትና ሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት ዕድገት ወሳኝ የሆነ ስነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ የአፈርና ውሀ ተስማሚነት ጥናት ተከናውኖ ማስተር ፕላን የተዘጋጀለትና መሰረት ልማት የተሟላለት የልማት ኮሪደር/ ክላስተርን ያካተተ ለተጠቃሚዎች ምቹ የሆነ የመሬት መረጃ ቋብ ሳይት ይዘጋጃል፡፡ እንደዚሁም በጥናት የተለዩትን የልማት ክላስተሮች አግሮ ኢኮሎጂ እና የምርት ወቅት (Crop-calendar)፣ የገበያ ትንበያና የምርት አመራረት ዘዴ ምክር መስጫ ስርዓት መዘርጋት፣ የመረጃ ስርዓትን በማዘመን አለማቀፍ የምርት ግብይት መረጃዎችን በማሰባሰብ የግዥ ፍላጎት ያላቸውን ተጠቃሚዎች ማስተሳሰር የሚችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ አጠቃቀምና አተገባበርን ለማሻሻል የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

ሀ/ በዋና ዋና የሰብል ልማት አካባቢዎች ሥነምህዳርን መሰረት ያደረገ የግብርና ሜትሮሎጂ እና ግብረመልስ አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፡- የግብርና ሜትሮሎጂ የመረጃ ትንተናና ግብረመልስ አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት የሰብል ልማቱ በግብርና ሜትሮሎጂ መረጃ የተደገፈና የዘመነ እንዲሆንና ለምርትና ምርታማነት ዕድገት አስተዋጽኦ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በሜትሮሎጂ የተደገፈ ሲሆን ወቅቱን የጠበቀ የግብርና አሰራሮችን/በወቅቱ መዝራት፣ በወቅቱ ተባይና በሽታን መከላከልን፣ በወቅቱ

ሰብል መሰብሰብን/ በመተግበር እነዚህ አሰራሮች ለምርትና ምርታማነት ሊሰጡ የሚችሉት አስተዋጽኦ ማሳደግ ይቻላል፡፡ይህንም ለማድረግ ከብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በሃገሪቱ በሚገኙ ወረዳዎች ዘመናዊ የሜትዮሮሎጂ ጣቢያዎች የማስፋፋት ሥራ እንዲጠናከርና የመረጃ ፍሰቱ እንዲሳለጥ ማድረግ

ለ/ በአይሲቲ የተደገፈ የአዝርዕት ቴክኖሎጂ መረጃ ልውውጥ ሥርዓት መዘርጋት፡- ይህን ተግባራዊ በማድረግ የተለቀቁ ሰብል ዝርያዎች ዝርዝር፣ ተስማሚ ስነምህዳር፣ የተሻሻለ አሰራር እና የግብዓት አጠቃቀም መረጃ በቀላሉ ተደራሽ የሚሆንበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡ በተጨማሪም በአዝርዕት ፣ ልማት የኢንቨስትመንት አማራጮች፣ እምቅ አቅም፣ ዝርዝር መዳረሻ የሚያመላክቱ መረጃዎች በቀላሉ ማግኘት የሚቻልበት አሰራር እንዲሆን ተደርጎ ይደራጃል፡፡ በአይሲቲ የተደገፈ የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን መፍጠር

ሐ)የሳተላይትን ምስልና ድሮን በመጠቀም የሰብል አሰሳና ግምገማ ሥርዓት መገንባት፡- እስከአሁን በተግባር ላይ ያለው የሰብል አሰሳና ግምገማ ሥርዓታችን አድካሚ፣ ከፍተኛ የሆነ የግዜ፣ የሰው ኃይልና የገንዘብ ሃብት የሚጠይቅና ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ የሚገኘው መረጃ ታዕማኒነት የጎደለውና አወዘጋቢ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ የደረስንበትን የልማት ደረጃ ለይተን በማወቅ፣ ለቀጣይ ውጤታማ የሆነ የልማት ዕቅድ እንድነድፍ ሲያያርገን ቆይቷል፡፡ ስለዚህ ግብርናን እናዘምናለን ካልን የሳተላይትን ምስልና ድሮን መሰረት ያደረገ የሰብል አሰሳና ግምገማ ሥርዓት መገንባት ይኖርብናል፡፡ ይህን ለማድረግም እነዚህን ቴክኖሎጂዎች በስፋ ተደራሽ በማድረግ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብንና አጠቃቀማቸውን በተመለከተም በስፋት ማስተዋወቅ ይጠይቃል፡፡

መ)ለሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት ዕድገት ወሳኝ የሆነ ስነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ የአፈርና ውሀ ተስማሚነት ጥናት ተከናውኖ ማስተር ፕላን የተዘጋጀለትና መሰረት ልማት የተሟላለት የልማት ኮሪደር/ ክላስተርን ያካተተ ለተጠቃሚዎች ምቹ የሆነ የመሬት መረጃ ቄብ ሳይት ይዘጋጃል፡፡ እንደዚሁም በጥናት የተለዩትን የልማት ክላስተሮች አግሮ ኢኮሎጂ እና የምርት ወቅት (Crop-calendar)፣ የገበያ ትንበያና የምርት አመራረት ዘዴ ምክር መስጫ ስርዓት መዘርጋት፣ የመረጃ ስርዓትን በማዘመን አለማቀፍ የምርት ግብይት መረጃዎችን በማሰባሰብ የግሽር ፍላጎት ያላቸውን ተጠቃሚዎች ማስተሳሰር የሚችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ አጠቃቀምና አተገባበርን ለማሻሻል የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

ሠ) **የሆርቲካልቸር ገበያ መረጃ ማዕከል** (Market Information Platform-MIP) **ማቋቋም፡-** ቀደም ሲል ከጃፓን አለማቀፍ የትብብር ኤጀንሲ (JICA) እና በቀድሞው የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር እና ግብርና ኢንቨስትመንት ባለስልጣን አማካኝነት ተጀምሮ የነበረውን MIP የማቋቋም ስራ በአዲስ መልክ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ይህ ማዕከል በሀገር ውስጥ ያለውን የሆርቲካልቸር አመራረት ሂደት፣ የምርት ዓይነትና መጠን፣ የምርት ጥራት ደረጃ፣ የምርት ዱካ (Tracability) ወዘተ ... መረጃ እንዲሁም አለምአቀፍ ገዢዎች አጠናቅሮ የሚይዝ የመረጃ ቋት የሚኖረው ሲሆን አምራቹን ከገዢው ጋር የሚያገናኝ የመረጃ ስርዓት ነው፡፡ በተጨማሪም ገዢው አካል የተመረተውን ምርት በቀጥታ የሚመለከትበት ሰርቶ ማሳያ ማዕከል/Demo site/ ያካተተ የመረጃ ማዕከል በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡

ረ/ በተንቀሳቃሽ ላቦራቶሪ የአፈር ንጥረ-ነገር ምርመራ መሠረት ያደረገ የማዳበሪያ ምክረ-ሃሳብ አገልግሎት ማስፋፋት፡- አፈርና ሰብልን መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ አጠቃቀም እውን ለማድረግ በስፋት ይዘረጋል፡፡

ሰ) የአግሮ-ሜትዮሮሎጂ መረጃ አጠቃቀምን ማሳደግ፡- ይህንም ለማድረግ ከብሄራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር በሃገሪቱ በሚገኙ ወረዳዎች ዘመናዊ የሜትዮሮሎጂ ጣቢያዎች የማስፋፋት ሥራ እንዲጠናከርና የመረጃ ፍሰቱ እንዲሳለጥ በማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ልማት ለማካሄድ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

ጥቅም ላይ ያልዋሉ የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች አዝርዕትና ሆርቲካልቸር ማሳ ሽፋን ማሳደግ

አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮችና እና አልሚ ባለሀብቶችን በማሳተፍ ያለውን የማሳ ሽፋን ማሳደግ ይቻላል፡፡ የማሳ ሽፋን ማስፋት አፈጻጸሙ ያልተነኩ የደን መሬቶችን ለእርሻ በመመንጠር የሚከናወን ሳይሆን ከደን ልማት ነጻ የሆኑ አርሶአደሩ ግን ለእንስሳትም ሆነ ለሌላ ተግባር ያላዋላቸውን ጦም ያደሩ ማሳዎችን ወደ እርሻ በማስገባት እንዲሁም በደን ውስጥ በማሰባጠር፣ የመሬት አጠቃቀም ግጭትና ሽሚያ በማስወገድ በርካታ ለግብርና አገልግሎት መዋል ያለባቸውን መሬቶች ለሆርቲካልቸር ልማት ሥራ እንዲውሉ በማድረግ፤ የመስኖ መሰረተ ልማት የተገነባላቸውና ያልለሙትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የሆርቲካልቸር ሰብሎች በማልማት ሙሉ አቅማቸውን መጠቀም፣ በግል ባለሃብቶች የተያዙና ለልማት ያልዋሉ ሰፋፊ የእርሻ ይዞታዎች ለሆርቲካልቸር ልማት የሚውሉበት ሁኔታ በማመቻቸት የሚተገበር ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መንግስት ለልዩ ፍላጎት/የውጭ ንግድ፣ ከውጭ የሚገባ ምርት መቀነስ፣ ስርዓተ-ምግብ፣ አፈር ጤንነት ጥበቃ ወዘተ.../ ለወሰናቸው ሰብሎች ልማት የሚውለው ማሳ በሌሎች ሰብሎች ልማት ምትክ ለማሳደግ /crop shift/ የአፈርና ውሃ ተስማሚነት ጥናት በማካሄድ የሚያበረታታ ልዩ የድጋፍ ስርዓት መዘርጋትን ሊያካትት ይችላል፡፡

በቀጣይ **ለአዝርዕትና ሆርቲካልቸር** ልማት ሊውል የሚችል የመሬት ስፋት በጥናት በመለየት እና ለአምራቾች ማስተላለፍ ስራ በሚከተሉት ስልቶች የሚፈፀም ይሆናል፡፡

የመሬት አጠቃቀም ግጭትና ሽሚያ በማስወገድ በተለይ የወል መሬት አጠቃቀምን ማሻሻል

በዚህ መሰረት የወል መሬት በአግባቡ ለወጣቶች እና ለሴቶች በኩታገጠም እርሻ ምክረሀሳብ መሰረት ለልማት እንዲውል የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት የማህበረሰቡን ፍላጎት መሰረት ባደረገና ግጭት በማይፈጥር መልኩ መሬቱን የማስተላለፍ ስራ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የአፈር ጤናንና ምርታማነትን ማሻሻል

የአርሶ አደሩን እንዲሁም የሴቶችና ወጣቶች ከልማቱ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም እንደ ሀገር ካለው ለአዝርዕት ልማት መዋል ከሚገባው መሬት ውስጥ ምን ያህሉ የአፈር ጤንነት ችግር እንዳለበት በጥናት መለየት፤ በጥናት ከተለየው ለማልማት ምቹ ያልሆነ መሬት (የአፈር አሲድነት የተጠቃ) በተለያዩ የአፈር ማከሚያ ዘዴዎች በመተግበር እና በማከም ወደ ልማቱ እንዲገባ ይደረጋል ፡፡

በአነስተኛ መስኖ የሚለማን መሬት መጠን እና አመታዊ የመስኖ ልማት ድግግሞሽን በማሳደግ

በተለይ በሀገሪቱ ቆላማ አከባቢዎች በመስኖ መሰረተ ልማት አለመሟላት ምክንያት ወደ አዝርእት ልማቱ ያልገባ መሬትን በቀጣይ በሙሉ ትኩረት አስፈላጊውን መሰረተ ልማት (የመስኖ አውታሮች፤ የሀይል አቅርቦትና ሌሎች) እንዲሟላ በማድረግ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች ለማልማት ይውላሉ፡፡

በቀሪ እርጥበት እና ደጋፊ መስኖ ልማት

የሰብል ምርትን ማሳደግ ስለሚገባ በመኸር እርሻ ሰብል መሰብሰብ ተከትሎ የሚኖረውን የአፈር ርጥበት በመጠቀም የሚተገበር ሲሆን ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ደጋፊ መስኖን በመጠቀም በስፋት የማምረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በአጭር ጊዜ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ የሰብል ዝርያዎችን መጠቀም

በአግባቡ ያልለሙ እና በአያያዝ ጉድለት የተጎዱ መሬቶችን በጥናት መለየትና የስራ አጥ ወጣቶችን በማደራጀት ለግብርና ልማት እንዲውል ማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡

ፍትሀዊ፤ ቀልጣፋና፤ ግልጽነት የተላበሰ የመሬት ማስተላለፍ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ

ከመሬት ልየታ ጀምሮ እስከ ማስተላለፍ ባለው ሂደት ግልጽነት፤ ተጠያቂነትና ቅልጥፍና በተሞላበት የአካባቢውን ህብረተሰብ ባሳተፈ አግባብ የአሰራር መመሪዎችን መሰረት በማድረግ በቀጣይ አስር የዕቅድ ዓመታት የሚከናወን ይሆናል፡፡ እንደዚሁም የመሬት አቅርቦቱን ተደራሽ ለማድረግ እና ከክልሎች ጋር

የአሰራር ትስስርን ይበልጥ ለማጠናከር እንዲረዳ በክልሎች መሬት ባንኮች የሚቋቋሙበት እና ከፌደራል ጋር የሚተሳሰሩበት አግባብ ይፈጠራል፡

ከዚህ ጎን ለጎን ትኩረት የሚሰጠው ተግባር በፌዴራልና በክልሎች መካከል ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውል መሬት የማስተላለፍ፣ የመከታተልና መደገፍ ስራዎች ዙሪያ የሚስተዋሉ አለመግባባቶችን ለመፍታት እና ተመሳሳይ ችግሮች በቀጣይ እንዳይፈጠሩ ከክልሎች ጋር የሚያግባቡ አሰራሮች በማዘጋጀት የዘርፉን ልማት ዕድገት መሰረት በማድረግ ስምምነት የሚደረስባቸው ይሆናል፡፡ እንደዚሁም መስፈርቱን ለሚያሟሉ ባለሀብቶች መሬቱን ለማስተላላፍ ግልጸኝነትን በተላበሰ አግባብ በጥንቃቄ ያላቸውን ፕሮፋይል በመገምገም ለመመልመል እና መሬት ለማስተላለፍ የሚያግዙ መስፈርቶች በማዘጋጀት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ማሳ ሽፋን

በነባር አምራች አካባቢዎች የማሳ ሽፋን ተጠብቆ እንዲቆይ ለምርታማነት ዕድገት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን በመለየት ምርታማነትን በማሳደግ ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች ልማት ለማስፋፋት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦት እንዲሁም የመሠረተ-ልማት ተደራሽነት የማሻሻል ሠራዎች ይሠራሉ፡፡ በዚህም የቡና ማሳ ሽፋን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻየአነስተኛ አርሶ አደር 921 ሺህ ሄ/ር በመካከለኛና ሰፋፊ እርሻ በድምሩ 130 ሺ 1 ሚሊዮን ሄክታር ለማድረስ ይሰራል፡፡

የሻይ ልማት በተመለከተም ሰፋፊ የሻይ እርሻዎችን ለማስፋፋት የሚያስችል የመሬትና የፋይናንስ አቅርቦት በማመቻቸት ወደ ተግባር ማስገባትና በዙሪያቸው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በስፋት በማቀፍ የምርት ግኝቱን ማሳደግ የሚቻልበትን አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ለሻይ ልማት ተስማሚና ምቹ ስነ-ምህዳር ባላቸው አካባቢዎች አነስተኛ የሻይ ኢንዱስትሪዎች በሚስፋፉበት ሁኔታ ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስራ አጥ ወጣት በልማቱና በማቀነባበሩ የሚሳተፍበትን ዕድል በመፍጠር የሻይ ምርት ሽፋን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡ በዚህም የአነስተኛ እርሻ ማሳ ሽፋን ከ521 ሄ/ር ወደ 872 ሄ/ር እና የሰፋፊ እርሻ ማሳ ሽፋን ወደ 3325 ሄ/ር በድምሩ የሻይ ማሳ ሽፋን 4197 ሄ/ር ለማድረስ ይሰራል፡፡

የቅመማ ቅመም ልማት የማሳ ማስፋት ሥራ በስፋት የሚከናወን ሆኖ የማሳ ሽፋኑ በየዓመቱ 2 በመቶ እያደገ እንዲቀጥል የተቀናጀ ርብርብ በማድረግ ሽፋኑን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 409 ሺህ ሄ/ር ለማድረስ ይሰራል፡፡

መሰረተ ልማት ግንባታ

የዕፅዋት ጥበቃ በአይሲቲ የተደገፈ አሰራር እንዲኖረው ለማስቻል አንድ ማዕከላዊ የአይሲቲ መሠረተ ልማት ገንብቶ ወደ ሥራ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ የአይሲቲ ቴክኖሎጂ በዕፅዋት ጥበቃው ዲሲፕሊን እንዲደራጅ በማድረግ የተባይ ዓይነት፣ የተባይ ክስተት መረጃዎች፣የመከላከያ ዘዴውን፣ በተባይ የሚባክነውን መጠን፣ ጥቅም ላይ የዋለውን ፀረ ተባይና ሌሎች መረጃዎችን በመረጃ ቋት በማስቀመጥ መረጃው ጥቅም ላይ የሚውልበት ሥርዓት በመዘርጋት ለተባይ መከላከሉ ውጤታማነት አስተዋፅዖ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

አዳዲስ 4 የዕፅዋት ጤና ክሊኒኮች እንዲገነቡና 60 ማኅበረሰብ አቀፍ የዕፅዋት ክሊኒኮች በማደራጀት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፤ የተባይ ልየታ፣ የፀረ ተባይ ይዘትና ብቃት የሚመረመርበትና መረጃ የሚመነጭበት ላቦራቶሪ በፌዴራል ደረጃ እንዲገነባ፣ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ እንዲደራጅና ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ የዕፅዋት ጥበቃን ሥራዎች በመስክ ደረጃ ድጋፍ የሚያደርጉ የዕፅዋት ጤና ክሊኒኮች በሰው ኃይል፣ በቁሳቁስና በሎጂስቲክስ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የተባይ መከላከል ችግሮች በቅርበት ተገኝተው በተባይ ልየታና የመከላከያ ዘዴ ምክረ ሐሳብ የሚሰጡ የዕፅዋት ጤና ክሊኒኮች አቅምና ተደራሽነታቸውን በማሳደግ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ ውጤታማና ዘላቂነት ያለው ለአየር ንብረት ለውጥ መባባስ አስተዋፅዖው ዝቅተኛ የሆነ የተባይ መከላከል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

በዕዕዋት ጥበቃ ረገድ በተቀናጀ ተባይ መከላከል ቴክኖለጂዎች፣ የዕዕዋት ጥበቃ መረጃዎች በአይሲቲ መደገፍ፣ የተባይ ክስተት ትንበያ፣ የመከላከል እርምጃ ምክረ-ሐሳብ፣ የተባይ ልየታ፣ በሰው ኃይልና በዘመናዊ መሣሪያዎች የተደራጀ የላቦራቶሪ አገልግሎት መጠቀም እንዲሁም የዕዕዋት ጥበቃ አገልግሎቶች ለመስጠት የተደራጁና ሥራ የተፈጠረላቸው ወጣት ወንዶችና ሴቶች ይኖራሉ፡፡ በተጨማሪም አርሶ/አርብቶ አደሩ ከውጭ የሚመጡ ዕዕዋት ባዕድ የኳራንቲን ተባዮች ይዘው መምጣት እንደሚችሉና ይህንን ማስቀረት ወይም መቀነስ የሚቻለው በኳራንቲን ተቆጣጣሪዎች ታይተው እንዲገቡ የተፈቀደላቸው ብቻ እንደሆኑ የተገነዘበ አርሶ/አርብቶ አደር ይፈጠራል፤ በተመሳሳይ ወደ ውጭ የሚላኩት ዕዕዋት የተቀባዩ አገር የኳራንቲን ፍላጎት ካላሟሉ ምርቶቹ ተቀባይነት የማያገኙ መሆናቸውን አርሶ/አርብቶ አደሩ እንዲገነዘብ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የሆርቲካልቸር ፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮን በመውሰድና ያለውን ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከባቢያዊ ጠቀሜታ መነሻ በማድረግ የሆርቲካልቸር ፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ለዘርፉ ዕድገት የጎላ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህም ከዚህ በፊት በዘርፉ ያሉትን ተግዳሮቶች ከመቅረፍና ፖሊሲ የሚሹ ጉዳዮችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ምላሽ በመስጠት ከዘርፉ ሊገኝ የሚችለውን ፋይዳ ለማጉላት ወሳኝ ይሆናል፡፡

2.1.2 የተስፋፋ የመካከለኛና ሰፋፊ የባለሀብት ሰብል ልማት

ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ለግብርና ኢንቨስትመንት የሚውሉ መሬቶችን ከተጠቃሚዎች፣ ከደንና ከባህላዊ ይዞታ ነጻ መሆናቸውን መለየት፣ ማጥራት (verification)፣ ለባለሀብት ሊተላለፍ በሚችልበትን መልክ ማደራጀትና ወደ መሬት ባንክ በማስገባት በቀጣይ አምስት ዓመታት ዕቅድም ሆነ ከዚያ ባለፈ ለሚፈለገው ፈጣን ልማት ግብዓት ሆኖ ያገለግላል፡፡ በጥናት ተስማሚነታቸው የተረጋገጡ መሬቶችን ለአልሚ ባለሀብቶች የማስተላለፍ ተግባር ፍትሀዊ፤ግልጽና ህጋዊ አሰራርን ተከትሎ የአሰራር መመሪያዎች ተደግፈው የሚከናወኑ ይሆናል፡፡በዚሁ መሰረት ለግብርናው ኢንቨስትመንት ዘርፍ ልማት ተስማሚ የሆኑ መሬቶችን አቅም ያላቸውን ባለሃብቶች ለመሳብ በሀገር ውስጥና በውጪ የማስተዋወቅ ስራ በስፋት የሚከናወን ይሆናል፡፡ ባለሀብቱ የሚሳተፍባቸው ሰብሎች **በመኽርና በመስኖ** በአዝርዕት፣ ሆርቲካልቸር፣ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ሰብሎች ይሆናል፡፡

በሰፋፊ እርሻ ልማት ዘርፍ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ፈቃድ ሲሰጣቸው የኤች.አይ.ቪ ባለሙያ አብሮ እንዲቀጥርና ስራው እንዲሰራ የሚያደርግ አሰራር እንዲፈጠር ማድረግ እና ክትትል ማድረግ፤በሰፋፊ እርሻ ልማት ላይ ለተሰማሩ ይበልጥ ተጋላጭ የቀን ሰራተኞች የኤች አይቪ መከላከል ተግባራትን እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በማካተት ማከናወን፡፡

2.1.2.1 ያደገ የመካከለኛ እና ሰፋፊ ሰብል ልማት ኢንቨስትመንት

የሰብል ኢንቨስትመንት ማስፋት

በመካከለኛና ሰፋፊ እርሻ በባለሀብት በመኽርና በመስኖ በሰብል(በእህል ሰብሎችና አትክልትና ፍራፍሬ) በ2012 የለማውን 986492 ሄ/ር መሬት በ2022 ወደ 2.3 ሚሊየን ሄ/ር በማድረስ በ2012 ከተደረሰበት 50 ሚሊየን ኩንታል በ2022 ወደ 85 ሚሊየን ኩንታል ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል፡፡

ሆርቲካልቸር ኤክስፖርት ኢንቨስትመንት መሬት መጠን ማስፋት

በአበባ ልማት በ2012 በጀት ዓመት ከተመዘገበው 2,466 ሄ/ር በመነሳት ነባር የአበባ ኩባንያዎች በቀጣይ አምስት ዓመታት ለማልማት ያቀረቡትን የማስፋፊያ መርሃ-ግብር እንደ መነሻ በመውሰድ አጠቃላይ ልማቱ በየዓመቱ በአማካይ 5 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ 3,150 ሄ/ር ይደርሳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለአበባ ልማት መሬት ወስደው ካላለሙት ወስጥ በአምስት ዓመት 1,070 ሄ/ር መሬት ወደ ልማት በማስገባት (2013-2017) ምርት ዘመን መጨረሻ ላይ በአበባ ልማት የሚሸፈነው የመሬት መጠን በድምሩ 4220 ሄ/ር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

በአትክልት ልማት በ2012 በጀት ዓመት የለማው 2,596 ሄ/ር መሬት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ 4,185 ሄ/ር የሚሸፈን ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪ ለአትክልት ልማት መሬት ወስደው ካላለሙት ወስጥ በአምስት ዓመት 942 ሄ/ር መሬት ወደ ልማት በማስገባት (2013-2017) ምርት ዘመን መጨረሻ ላይ በአትክልት ልማት የሚሸፈነው የመሬት መጠን በድምሩ 5127 ሄ/ር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

በፍራፍሬ ልማት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ የለማው 11,315 ሄ/ር መሬት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ ከ2013-2017 በጀት ዓመት መጨረሻ 18,225 ሄ/ር የሚሸፈን ይሆናል:: ከዚህ በተጨማሪ ለፍራፍሬ ልማት መሬት ወስደው ያላለሙትን 533 ሄ/ር መሬት ወደ ልማት በማስገባት በፍራፍሬ ልማት የሚሸፈነው የመሬት መጠን በድምሩ 18758 ሄ/ር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

በሽርብስ ልማት በ2012 በጀት ዓመት መጨረሻ የለማው 148 ሄ/ር መሬት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ በየዓመቱ በአማካይ 10 በመቶ በማሳደግ ከ2013-2017 በጀት ዓመት መጨረሻ 240 ሄ/ር የሚሸፈን ይሆናል፡ከዚህ በተጨማሪ ሽርብስ ልማት መሬት ወስደው ያላለሙትን 60 ሄ/ር መሬት ወደ ልማት በማስገባት ሽርብስ ልማት የሚሸፈነው የመሬት መጠን በድምሩ 300 ሄ/ር እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

2.1.2.2 ውጤታማ የመካከለኛ እና ሰፋፊ ሰብል ልማት ኢንቨስትመንት

በመካከለኛና ሰፋፊ እርሻ መሬት ላይ የተሰማሩ ግለሰቦች/ ኢንቨስተሮች የሚኖራቸውን የእርሻ መሬት በአግባቡና ለወሰዱት አላማ ሙሉ በሙሉ ማዋል ይገባቸዋል፡፡ በሀገራችን ያለው የመካከለኛና ሰፋፊ እርሻ አሁን ያለበት ደረጃ ሲታይ ግን በመሬት እና በተሻሻሉ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝቅተኛ በመሆኑ እየተገኘ ያለው ምርትም ዝቅተኛ ነው፡፡በመሆኑም የእርሻ መሬት በመስጠት ወይም በመውሰድ ብቻ ሳይሆን የባለ ሀብቱን ምርታማነት አቅም ማጥናት፤ መሬት ከተላለፈ በኋላም ባለሀብቱ ለማምረት የሚያስፈልጉትን ድጋፍ ሁኔታ በተጠናከረ መልኩ መከናወን ይገባዋል፡ ስለዚህ የእርሻ መሬት ውጤታማነቱን ለማሳደግ የተሻሻሉ የግብርና የቴክኖሎጂ አቅርቦትና አጠቃቀም እንዲሁም አልሚ ባለሀብቱ ለማልማት የወሰደውን የእርሻ መሬት በአግባቡና ውጤት በሚያመጣ መልኩ ስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ ሙያዊ ክትትልና ድጋፎች ተከታታይነት ባለው መልኩ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ልማቱ አካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንነትን በጠበቀ መልኩ ሊከናወን ይገባል፡፡ የሰፋፊ እርሻዎች አተገባበር ስርዓት በመዘርጋት ስራ ላይ የማዋል ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

2.2.2.1 መሬት መለየትና ማስተላለፍ

ለእርሻ ልማት በኢንቨስትመንት የተለዩ እንዲሁም የተላለፉ ማሳዎች ላይ ያሉ ማነቆዎችን በመፍታት ወደ ልማት እንዲገባ ማድረግ፡- ለመካከለኛ እና ሰፋፊ እርሻ ልማት ማስፋፊያ የሚውሉ ከዚህ በፊት ተስማሚነታቸው ከክልሎች ጋር በመቀናጀት የተጠናውን ወደ ተግባር ማስገባት፡፡ በሌላ በኩል በሀገር ደረጃ ለሰፋፊ እርሻ ልማት እንዲውሉ የተለዩ እርሻ መሬት ቢኖሩም ለተፈለገው አላማ ከማዋል አንጻር ከፍተኛ ክፍተት የሚስተዋልበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ በልማቱ የተሰማሩ አልሚ ባለሀብቶች ለማልማት የወሰዱትን መሬት አስገዳጅ የማልማት ሥርዓት በመዘርጋት ወደ ልማቱ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

እስካሁን ልማት ላይ ያልዋሉ መሬቶችን በጥናት በመለየት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ሰብሎች እንዲለማበት ማድረግ፡-

መጠነ ሰፊ የኢንቨስትመንት ልየታ ጥናቶች በማካሄድ ለግል አልሚዎች እና የተደራጁ ወጣቶችና ሴቶች የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ በመስራት፣ የቢዝነስ ፕላን በማዘጋጀትና በማሰልጠን ገበያ ተኮር ሰብል ማልማት ሥራዎችን እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡

2.2.2.2 መሰረት ልማትና አገልግሎት(ቴክኖሎጅ፣ምክርና ስልጠና፣ግብዓት) አቅርቦት

ለመካከለኛ እና ሰፋፊ እርሻዎች ምቹ የልማት ሁኔታ ለመፍጠር መሰረተ ልማቶችን ማሟላት፡

አልሚዎች በሙሉ ፍላጎት ወደ ማልማት ተግባር እንዲገቡ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ሥራ ይሰራል፡፡ በዋናነትም ከዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኙ መጋቢ መንገዶች እንዲሰሩ፣ የሃይል አቅርቦት ፍላጎት መለየትና እንዲመቻች ማድረግ፣ በክፍያ አገልግሎት የሚሰጡ ውሃ ቆጣቢ የመስኖ አውታሮች መገንባት፣ ለነዋሪዎች ምቹ የሆኑ ዘመናዊ የእህል ሰብል ልማት ማዕከላት መገንባት፣ ለሰብል አምራቾች የገበያ መዳረሻ የሆኑ ማእከላዊ የሰብል ምርት ማሰባሰቢያ እና ግብይት ማዕከላት መገንባት እና ምርታቸውን ሊያጓጉዙላቸው የሚችሉ የጭነት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች እንዲደራጁ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ለመስራት ጥረት ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የእርሻ ልማት አካባቢዎች ደህንነትን ለማስጠበቅ ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር መጠነ ሰፊ ውይይቶችን በማካሄድ ከአካባቢያቸው የግል እርሻ ልማት ዘርፍ ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትና ባለቤትነት የሚያዳብሩበት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

የኢንሹራንስ እና የብድር አቅርቦት ተግባራዊ ማድረግ፡-

አልሚዎች ከአቅም በላይ ለሆኑ ሥጋቶችን በመቀነስ ወደ እርሻ ልማት ሥራ እንዲገቡ ለማደረግ ማነቆዎችን በጥናት በመለየት እንደ አስፈላጊነቱ መንግስት የኢንሹራንስ ሥርዓቱ ተግባራዊ እንዲሆን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ በምርት አመራረት ሰንሰለት ሂደት ውስጥ በሚፈጠር ከፍተኛ ጉዳት አልሚዎች ኪሳራ ሲገጥማቸው የኢንሹራንስ ዋስትና አገልግሎት እንዲኖራቸው ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የእርሻ ልማቱን የሚደግፍ የብድር አቅርቦት ሥርዓትም ይጠናከራል፡፡

የሜካናይዜሽን አገልግሎትና ጥገና ሰጪ ማዕከላት እንዲጠናከሩ ማድረግ፡-

የሜካናይዜሽን መሳሪያዎችን በሙሉ አቅማቸው ጥቅም ላይ እንዲውሉ በቂ የሜካናይዜሽን አቅም የገነቡ አልሚዎች የአገልግሎት እና ጥገና ማዕከላት እንዲከፍቱ በማድረግ ወይም ሌሎች ኢንቬስተሮች በእነዚህ አካባቢዎች ማዕከላት እንዲከፍቱ ድጋፍ በመስጠት የሜካናይዜሽን ልማትና ተጠቃሚነት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

የቅድመ እና ድህረ ምርት ቴክኖሎጂ ሽግግር ማጠናከር፡-

በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ዳሰሳ ጥናቶች እንደተረጋገጠው የሀገራችን የግብርና ኢንቨስትመንት የሰፋፊ እርሻ ፕሮጀክቶች በቅድመና ድህረ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዝቅተኛውን ደረጃ ከያዙት የአፍሪካ ሀገሮች መካከል እንደሆነችና ለዚህም በምክንያትነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማንሳት ቢቻልም በትኩረት ሊፈቱ የሚገባቸው ማነቆዎች ዘርፉ ከምርምር ተቋማት ጋር የተሳሰጠ ግንኙነት የሌለው መሆኑ፤ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ሊያስገኝ የሚችለውን ከፍተኛ ጠቀሜታ መገንዘብ

አለመቻል፤ ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት የሚረዱ ማኑዋሎችና ምክረ ሀሳቦች በበቂ ጥራት ተደራጅተው አለመገኘትና ለተጠቃሚው አለመድረስ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በመሆኑም እነዚህን ማነቆዎች ለማስወገድ እንዲቻል በቀጣይ አስር የዕቅድ ዓመታት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በምርምር ተቋማትና በዘርፉ መካከል የግንኙነት ስርአት መዘርጋትና ማጠናከር፤ በምርምር የተለቀቁ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማደራጀትና ለተጠቃሚው በማስተዋወቅ ስለሚያስገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በማስረዳት ግንዘቤ መፍጠር፤ የግሉ ዘርፍ በምርምር ስራ ውስጥ እንዲሳተፍና የእርሻ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን እንዲደግፍ የሚያበረታታ ፖሊሲና ስርዓት እንዲዘረጋ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እንዲቻል የተለያዩ ፓኬጆችንና ማኑዋሎችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ማድረግ፤ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ለማጠናከር የምክርና ድጋፍ አገልግሎት ለመስጠት የሚረዳ የግንኙነት/ኤክስቴንሽን ስርዓት መዘርጋት፤

እንደዚሁም ዘርፉን የሚደግፉ ተቋማትን የሰው ኃይል ክህሎት ለማሻሻልና በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችና ባለሙያዎቻቸውን አቅም በማጎልበት ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል የከፍተኛ የግብርና ቴክኖሎጂ ማሰልጠኛ ማዕከል/ ኢንስቲትዩት እንዲቋቋም ማድረግ ናቸው፡፡

በአነስተኛ ኮመርሻላይዜሽን በመስኖ የሰሊጥ/ለኤክስፖርት/ የሱፍ፣ስንዴ፣ጥራጥሬ እና የሩዝ /ኢፖርትን መተካት/ እና ጥጥ ልማት የማስፋፊት ሥራ ለመስራት የኢንቨስትመንት ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋት

የእነዚህን ሰብሎች ልማት በ ማስፋፋት የውጭ ገቢ ምርቶችን መተካት፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውን ምርት እና የምንዛሬ ማመጨት ተግባራት ማሳደግ፣ የአገሮኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ አቅርቦትን ማሳደግ እና የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ረገድ መጠነ ሰፊ ሥራ መስራትን ያካትታል። ተግባራቱ ዋናነት ወጣቶችን ቅድሚያ በመስጠት ይሰራል።

የግብርና ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ግብዓት ፍላጎት ማሟላትና ከውጭ የሚገባውን ሰብል ምርት ለማስቀረት ወደ ውጭ የሚላከውን መጠን ለማሳደግ የሚያስችል የማትጊያ ሥርዓት መገንባት

የዚህ ተግባር ዋና ዓላማ አርሶአደሮችና አልሚ ኢንቨስተሮች እንደ አገሪቱ የኢኮኖሚ ፍላጎት እየታየ የሰብል ምርቶችን እንዲያመርቱ የሚያበረታታና በእህል አቅርቦቱ ረገድ የአገሪቱን የልማት ስትራቴጂ ለማስፈጸም ምንም ዓይነት ክፍተት እንዳይኖር አስፈላጊውን ጥረት ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ለመገንባት ነው።

2.2.2.3 የባለሀብት እርሻ ከአርሶና አርብቶ አደር ጋር ማስተሳሰር

የግብርና ልማት ውል ስርዓትን ተግባራዊ ማድረግ፡

የመሬት ተደራሽነትንና የአርሶአደሩን ተጠቃሚነትን አንዲሁም የኢንዱስትሪውን ሰላም በመጠበቅ የግብርና ልማት ውል አዋጅን ወደ ተግባር አንዲገባ መጠነ ሰፊ የማስተዋወቅ ሥራ ይሰራል። ሥርዓቱንም ተቋማዊ እንዲሆን ይደረጋል። በመሆኑም በመካከለኛ እና ሰፋፊ እርሻዎች አካባቢ የሚገኙ አርሶ አደሮች በቅንጅት አልሚ እና በውል እርሻ ስርዓት በማስተሳሰር ከልማቱ ተጠቃሚ በማድረግ የዘርፉን ምርት የማሳደግ ስራ ይሰራል።

2.2.2.4 የባለሀብት እርሻ ምርታማነት ፣ አካታችነትና ደህንት ማሻሻል

የሴቶችና ወጣቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፡-

በግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ የሴቶችንና ወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው የጎላ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በቁጥርና አቅም ከፍተኛ ስለሆኑ በዘርፉ ትኩረት በመስጠት እንዲሰማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ ለዘርፉ ውጤታማነትና ቀጣይነት ወሳኝ በመሆኑ በእቅድ ዘመኑ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። በዚሁ መሰረት ይህንን ስትራቴጂ ወደ ስራ ለማስገባት እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች የቅንጅት አልሚና የውል እርሻ ስርዓት ከባለሃብቱ ጋር ለማስተሳሰር ብሎም በሚፈጠሩ የስራ ዕድሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በቀጣይ አስር የዕቅድ ዓመታት በተለያዩ መስኮች የስልጠና አገልግሎት ይሰጣል። እንደዚሁም የመሬት አቅርቦት እንዲመቻችላቸውና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን በማመቻት በቀጥታ በዘርፉ እንዲሰማሩና ራሳቸውንና ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ አስፈላጊው ማበረታቻ ሁሉ የሚመቻች ይሆናል።

ሴቶችና ወጣቶች በመስክ ሥራ ላይ የሚያባክኑትን ጉልበት የሚቆጥቡ መሳሪያዎችን፤ የሰብል ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተሻሻሉና ዘመናዊ ግብዓቶችን እንዲያገኙ ማስቻል፤ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውን ሰብሎች ለገበያ እንዲያመርቱ ማስቻል ያስፈልጋል።

የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ያረጋገጠ ልማት ማካሄድ፡-

የግብርና ኢንቨስትመንትን በዘላቂነት የአካባቢና ህብረተሰብ ደህንነትን ሳያናጋ ውጤታማ ለማድረግ የአካባቢ ጥበቃ የስነ ምግባር መመሪያን የማሻሻልና በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ የሚታሰበው ኢንቨስትመንት ከአካባቢ ጥበቃ አንጻር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር መርምሮ ከወዲሁ የመፍትሄ አቅጣጫ የሚያሳይና የመፍትሄ እርምጃዎችን የሚያመላክት ጥናት (pre-feasibility study) አሰራር ተዘርግቶለት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። እንደዚሁም ልማቱ መካሄድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የሚደረገው የልማት እቅስቃሴ የአካባቢውንና የህብረተሰቡን ደህንነት በጠበቀ መልኩ መካሄዱን ማረጋገጥ እንዲቻል የአካባቢ ተጽእኖ ዳሰሳ (EIA-Environmet Impact Assessment) እና

የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ (EMP) በአግባቡ መዘጋጀቱንና በስራ ላይ መዋሉን የመከታተልና የመደገፍ፤ እንደ አስፈላጊነቱም የማስተካከያ አርምጃ የመውሰድ አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የአለምአቀፍ ገበያ ህጎችንና መስፈርቶችን በስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ

የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ምርቶች በኤክስፖርት ገበያ ላይ ተፈላጊነት እንዲኖራቸው በአቅርቦት፤ በጥራትና በዋጋ ደረጃ ያሉትን ክፍተቶች ከማሻሻል ጎን ለጎን በገበያ ውስጥ ለመግባት የአለምአቀፍ የአመራረት፤ የአካባቢና ህብረተሰብ ጥበቃ መስፈርቶችን ማሟላትና ዕውቅና (certification) ለማግኘት ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በመሆኑም ሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ረገድ ያሉ ፕሮጀክቶች፤ ድጋፍ ሰጪ ተቋማትና ባለሙያዎች ስለ መልካም እርሻ (GAP-Good Agricutural Practices) አተገባበር፣ የተለያዩ የአለም አቀፍ የገበያ ጥራት መስፈርት ሰርተፍኬቶች (Global GAP, BRC, BSI, ETI, TESCO እና የምርት ሀገር ስሪት የHs code) ገበያው የሚፈልጋቸው ደረጃዎችን እንዲያሟሉ የግንዛቤ ማሳደግ ስራ በቀጣይ አምስት ዓመታት በተከታታይ የሚከናወን ተግባር ይሆናል፡፡

2.2.2.5 የዕውቅና አሰጣጥ ስርዓት መተግበር

በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሃብቶች ልማታቸውን ከአካባቢ ጋር በተዋደደ አግባብ እንዲያካሄዱና በአለም ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በአለም አቀፍ ደረጃ የተቀመጡ የነሃስ (Bronze)፣ ብር (sliver) እና ወርቅ (Gold) ደረጃ ለደረሱት እውቅና እየተሰጠ የሚሄድበት ስርዓት ለመዘርጋት በቀጣይ አምስት ዓመታት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ እንደዚሁም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት ለመገንባት በዘርፉ የተሰማሩ ባለሃብቶችን ግንዛቤ ለማሳደግ ተገቢው የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች ይዘጋጃሉ፡፡ በመሆኑም በሆርቲካልቸር ኢንቨስትመንት በአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ጥበቃ ዙሪያ የተሻለ ተሞክሮ ካላቸው ባላሀብቶች በመቀመር የማስፋፋት ስራ በቀጣይ አስር የዕቅድ አመታት በትኩረት የሚተገበር አቢይ ጉዳይ ይሆናል፡፡

2.2.2.6 የተበጣጠሱ የመሬት ይዞታዎችን ወደ አንድ ማምጣት (land consolidation)

የተበጣጠሱ የመሬት ይዞታዎችን ወደ አንድ በማምጣት (land consolidation) መካከለኛ እና ሰፋፊ እርሻዎች ማሰፋፋት

የአነስተኛ ይዞታዎች ቀስ በቀስ እንዲሰባሰቡ በማድረግና የሚተዳደሩበትን የህግ ማዕቀፍ አዘጋጅቶ በማጸደቅ ወደ መካከለኛ እና ሰፋፊ ባለይዞታነት እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡ ይህን ሊደግፉ የሚችሉ መሰረተ ልማቶች የሚገነቡ ሲሆን የሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ይከናወናል፡፡

በሆርቲካልቸር ልማት ላይ ለተሰማሩ ይበልጥ ተጋላጭ ሰራተኞች የኤች አይቪ መከላከል ተግባራትን እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ማከናወን፡፡

2.1.3 ሰብል ምርት ግብይት

የአዝርዕት ሰብል የወጭ ንግድ

በ2012 ቅባት እህሎች የውጪ ንግድ አቅርቦት እቅድ አፈጻጸም ማለት 266 ሺህ ቶን የነበረውን አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የምርትና ምርታማነት ጭማሪ ታሳቢ በማድረግ 406 ሺህ ቶን መጠን ያላቸው የቅባት እህሎች ወደ ውጭ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል፡፡ በተመሳሳይ በ2012 የጥራጥሬ እህሎች የውጪ ንግድ አቅርቦት እቅድ አፈጻጸም ማለት 316 ሺህ ቶን የነበረውን አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የምርትና ምርታማነት ጭማሪ ታሳቢ በማድረግ 399 ሺህ ቶን መጠን ያላቸው የቅባት እህሎች ወደ ውጭ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል፡፡

የሆርቲካልቸር የወጭ ንግድ

ከጽጌረዳና ከበጋ አበባ በመነሻው ዓመት ከተገኘው 222.82 የአሜሪካን ዶላር ወደ 337 የአሜሪካን ዶላር ማድረስ፤ ከቅንጥብ አበባ ምርት በመነሻው ዓመት ከተገኘው 28.55 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 52 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ፤ ከአትክልት ምርት በመነሻው ዓመት ከተገኘው 56.03 ሚሊዮን

የአሜሪካን ዶላር ወደ 116 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ፤ ከኽርብስ ምርት በመነሻው ዓመት ከተገኘው 7 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 20 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ እና ከፍራፍሬ ምርት በመነሻው ዓመት ከተገኘው 11.73 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወደ 25 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በማድረስ በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ (2017) ከሆርቲካልቸር ምርት ኤክስፖርት 550.20 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲደርስ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል።

የቡና ሻይና ቅመማ ቅመም የወጪ ንግድ

በ2012 ቡና የወጪ ንግድ አቅርቦት እቅድ አፈጻጸም ማለት 271 ሺህ ቶን የነበረውን አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የምርትና ምርታማነት ጭማሪ ታሳቢ በማድረግ 444 ሺህ ቶን መጠን ያላቸው የቅባት እህሎች ወደ ውጭ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል። በ2012 የሻይ የወጪ ንግድ አቅርቦት እቅድ አፈጻጸም ማለት 1571 ቶን የነበረውን አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የምርትና ምርታማነት ጭማሪ ታሳቢ በማድረግ 2981 ቶን መጠን ያላቸው የቅባት እህሎች ወደ ውጭ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል።በተመሳሳይ በ2012 የቅመማ ቅመምየወጪ ንግድ አቅርቦት እቅድ አፈጻጸም ማለት 12 ሺህ ቶን የነበረውን አፈጻጸም በቀጣይ ዓመታት ሊኖር የሚችለውን የምርትና ምርታማነት ጭማሪ ታሳቢ በማድረግ 20 ሺ ቶንቶን መጠን ያላቸው የቅባት እህሎች ወደ ውጭ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ታቅዷል።

2.3.1 የግብይት የምክር አገልግሎት

የአነስተኛ አርሶና /አርብቶ አደሮች በእውቀት ላይ የተመሠረተ የማምረትና ግብይት ውሳኔዎችን መወሰን የሚያስችላቸው ክህሎት መዳበር ውጤታማ እንደሚያደርጋቸው እሙን ነው። ስለሆነም አርሶ/አርብቶ አደሮች በገበያ ተፈላጊና የተሻለ ገቢ በሚያስገኙ ምርቶች ላይ እንዲያተኩሩ ምክረ ሃሳብ ማቅረብ እንዲሁም በሀገር ውስጥና በዓለም ገበያ ተፈላጊነት ያላቸውን ምርቶች በመለየት በአርሶ/አርብቶ አደሩ እንድ እንዲለመዱ ይሠራል። በግብርናው ዘርፍ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው እድገት ለማምጣት ግብርናው ርካሽ ከሆኑ ምርቶች ከፍተና ዋጋ ወዳላቸው ምርቶች (High Value Commodities) እንዲሸጋገር አስፈላጊው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንዲሁም ድገፍና ክትትል ይደረጋል።

የግብርና ምርቶችን ገበያው በሚፈልገው ጥራት፣ መጥና ወቅት ለማምረት እንዲቻል ከዓለም አቀፍ ንግድ አመራር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የምክርና ስልጠናዎችን ወቅታዊና ተከታታይነት ባለው መንገድ መስጠት ለአፈጻጸሙ እንዲያድግ ይደረጋል። በዚህም መሰረት የግብርና ምርቶች ገበያን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲመረቱ ተዋንያኑ በአዋጭነት ጥናት፣በንግድ ስራ ዕቅድ አዘገጃጀት፣በንግድ ስራ እንቅስቃሴ አመዘጋገብ ሁኔታ፣ በንግድ ተቋምና የሰው ኃይል አስተዳደር፣ ክትትልና ግምገማ፣ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋትና አስተዳደር፣ የምርት ፕሮፋይል አዘገጃጀት፣የምርት ትውውቅ ስራዎች፣ የንግድ ስራ ስነ ምግባሮች (Business ethics) እና ሌሎች በንግዱ ላይ ጉልህ ሚና የሚኖራቸው ስልጠናዎች እየተለዩ በስፋት እንዲሰጡ ይደረጋል።

2.3.2 የገበያ ትስስር

ገበያ ማስፋፋት፡ የግብርና ምርቶች የኤክስፖርት መዳረሻ ገበያዎችን በጥናት በመለየት በፍላጎትና በአቅርቦት መካከል የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤታማ የሚያደርጉ የአሰራር ስልቶች ይቀየሳሉ፡፡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በውጭ ሀገራትና በሀገር ውስጥ በሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶች ላይ መበሳተፍ ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ መደገፍና አዳዲስ የኤክስፖርት መዳረሻ ሃገራት ገበያዎችን የማስፋፈት ተግባራት ይከናወናሉ፡፡የአገሪቱን የሆርቲካልቸር ምርቶች በአገር ውስጥና በአለም አቀፍ ገበያ ላይ የማስተዋወቅ ስራ ማጠናከር፣ የኢትዮጵያን የሆርቲካልቸር ምርቶች መለያ (ብራንድ ዴቭሎፕምነት) እንዲኖር ማድረግ እናዲሁም የዓለም ገበያ መስፈርቶችን በማሟላትና ተወዳዳሪ ለመሆን በጥራትና ብዛት ላይ ያተኮረ የተጠናከረ ብክነት ያላቸውን ዝርያዎች ማስፋፋት ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡

አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች በአውትግሮወርና በኮንትራት የማምረትን ስርዓት ማጠናከር፣ አርሶ አደሩ በተደራጀና በተሳሰረ የአመራት እና ግብይት ስርዐት ውስጥ ገብቶ እንዲያመርት፣ ቀድሞ የመሸጥ አሰራር ስርዐት መመስረት እንዲሁም በዚሁ አሰራር የህብረት ሥራ ማህበራትን ሚና ማጎልበት ወሳኝነት አላቸው፡፡

የውል ግብይት አሰራርን (contract farming): ገበያ መር የግብርና ልማት ለማረጋገጥና አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ/አርብቶአደሮች የአመራረት ሥርዓት በመቀየር ከፍጆታ ማምረት፣ በገበያ የሚፈለግና የተከለ ዋጋ የሚያስገኝ ምርት ወደ ማምረት ለማሸጋገር ከሰፋፊ እርሻዎች፣ የግብርና ምርት ከሚቀበሉ ኢንዱስትሪዎች፣ ከላኪዎችና የገበያ ማዕከላት ጋር እንዲሁም የምርጥ ዘር አምራች ኩባንያዎችንና ተጠቃሚዎችን በውል ላይ የተመሰረተ ግብይት ትስስር ሥራ ይሠራል፡፡

በውል ግብርና (Contract Farming) ሻጭና ገዢን ህጋዊ በሆነ መልኩ በማገናኘት አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የገበያ ትሥሥር ለመፍጠር የሚሰራ ሲሆን የግብርና ምርት እንደ ግብዓት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉትን ምርት በሚፈልጉት ጥራት፣መጠንና ጊዜ እንዲመረትላቸው ለአልሚ አርሶ/አርብቶ አደርና ባለሃብቶች እውቀት፣ ክህሎት እና ቴክኖሎጂ በማቅረብ ምርትን በመጨመርና ብክነትን በመቀነስ እንዲሁም የምርት ጥራትን በማሻሻል የልማትና ግብይት ትስስር ይፈጠራል፡፡

አርሶ/አርብቶ አደሩን አግሮ-እንዱስትሪያል ፓርኮች፣ ከምርት አቀነባባሪዎች፣ ላኪዎች የግብይት ትስስር ፡ አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች ላመረቷቸው ምርቶች ዘላቂና አስተማማኝ የገበያ ትስስር ሲፈጠርላቸው ምርታቸውን ያለስጋት እንዲያመርቱና የተሻሻሉ ትክኖሎጊዎችን በመጠቀም ጥራትን መሰረት ያደረገ ምርት እነዲያመርቱ ይበረታታሉ፡፡ አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ከህ/ሥራ ማህበራት፣ ከነጋዴዎች፣ ከአቀነባባሪዎች እንዲሁም ከላኪዎች ጋር በማስተሳሰር የየምርቶቻቸው ተቀባዮች የሚፈልጉትን መጠን፣ በሚፈልጉት ጥራትና ወቅት እንዲያገኙ በማስቻል በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም አርሶ/አርብቶ አደሮችን በሀገራችን በመስፋፋት ላይ ካሉት አግሮ-እንዱስትሪያል ፓርኮችና ከምርት አቀነባባሪዎች ጋር የማስተሳሰር ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ትስስሩ የግብርና ምርትን ጥራት፣ የአመራረት ቅልጥፍናና ተወዳዳሪነት እንዲሁም የግብርና እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢነት በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ወሳኝ ከመሆኑም በላይ የግብርና ምርት አምራቾች ገበያ ተኮር የግብርና ምርቶችን ወደ ማምረት በማሸጋገር የግብርና ምርት ከሚያዘጋጁ፣ ከሚያቀነባብሩ፣ እሴት ከሚጨምሩ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከትላልቅ ገዥዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ትስስርን ጥፈጠራል፡፡

አግሮ ቱሪዝምን ማስፋፋት፡ቱሪቶችን ወደ ግብርና ልማት አካባቢዎች የሚስቡ ተግባራትን በመለየትና ሥራ ላይ በማዋል የግብርና ምርቶች የገበያ ትሥሥር ለመፍጠር እንዲሁም ለአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ እድልና የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ይሠራል፡፡ ተደራሽ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት በዙ ወጪ በማይተይቅ መልኩ የአካባቢውን አርሶ/አርብቶ አደሮች ለቱሪስቶች መስህብ የሚሆኑ ቁሳቁሶችንና ባህላዊ አኗኗር አይቤዎችን እንዲሁም ፈሪሽ የግብርና ውጤቶችን ለገበያ ማቅረብ ያስችላል

2.3.3 የገበያ መረጃ ስርዓት መዘርጋት

በአሁኑ ጊዜ በተበታተነና ቅንጅት በጎደለው መልኩ እየተሠራበት ያለውን የግብርና ግብይት መረጃ ሥርዓት ወቅታዊ፣ ታማኒነት ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት የግብርና ምርቶች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ፣ የምርት አቅርቦት፣ ምርቱ ያለበት አካባቢና ሌሎች ጠቃሚ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተንና ለተጠቃሚው በማሰራጨት በተለይ አርሶን አርብቶ አደሮች ገበያው የሚፈልገውን ምረት በማምረትና ገገበያው የተሸለ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሠራር ይዘረጋል፡፡

2.3.4 የግብይት መሠረተ ልማቶችን ማስፋፋት

የግብርና ምርት የግብይት ስርዓቱን ዘመናዊ፣ በውድድር ላይ የተመሰረተ፤ አርሶ/አርብቶ አርሶ አደሩንና ሸማች ከግብይቱ ተጠቃሚ የሚያደርግ ዘመናዊ የግብይት መሰረተ ልማትን ማስፋፋት መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ አሁን ባሉት የገበያ ማእከላት የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ በማእከላቱ ላይ እየታየ ያለውን አያያዝና አስተዳደር ችግሮች በመቅረፍ በአግባቡ ተይዘው ለታሰበው ዓላማ እንዲውሉ በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለው አሰራር መከተል እንዲቻል ክልሎች፣ የከተማ መስተዳደሮችና ከግብይቱ ማዕከላቱ ጋር በጋራ ይሠራል፡፡ ኳራኒኖችና የእንስሳት ማረፊያ ቦታዎች በተሻለ ሁኔት አገልግሎት የሚውሉበት አሠራር ይዘረጋል፡፡

ለሆርቲካልቸር ምርቶች (አትክልት፣ ፍራፍሬና ኽርብስ)፣ የቅባትና ጥራጥሬ የሎጂስቲክስ አገልግሎት አቅርቦትና ዋጋ ውድነት ምክንያት የሚመረተውን ምርት በተወዳዳሪ ዋጋ ኤክስፖርት ማድረግ አልተቻለም፡፡ ይህን ክፍተት በመቅረፍ በተለያዩ ቦታዎች በባለሃብቱ፣ በአርሶ አደሩ እና በሕብረት ስራ ማሕበራት የሚመረተውን የአትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የቅባትና ጥራጥሬ ልምዱና በገበያ መዳረሻዎች ዕውቅና ካላቸው ኒውክለስ እርሻዎች ከማስተሳሰር ባሻገር ምርቱ ተሰባስቦ ሊላክ የሚችልበትን የሎጂስቲክስና ተያያዥነት ያላቸውን ፋሲሊቲዎች የማመቻቸት ተግባር በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን ይሆናል፡፡ በዚሁ መሰረት፡-

በአሁኑ ወቅት የኤክስፖርት ዋጋ (እስከ 60%) እና የሀገር ውስጥ ትራንስፖርት የዋጋ ንረት እንዲቀንስ መስራት፡- ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የባህርና የባቡር እንዲሁም ሌሎች ባለማቀዝቀዣ ተሽከርካሪዎች ትራንስፖርትን በመጠቀም ለሆርቲካልቸር ምርቶች የውጪና የሀገር ውስጥ ገበያ ማጓጓዝ እንደ ዋና የትራንስፖርት አማራጭ መጠቀም በተጨማሪም የአየር ትራንስፖርት ለሆርቲካልቸር ምርቶች ኤክስፖርት አዋጪ የሚሆንበትን ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

የቅዝቃዜ መጠበቂያ መጋዘን እና ሎጂስቲክስ ማመቻቸት፡-የሆርቲካልቸር ምርቶች ጥራታቸው በአግባቡ ተጠብቆ ወደ መዳረሻ ገበያ እንዲደርሱ ለማድረግ ከምርት አካባቢዎች ወደ ወደቦች እና ኤርፖርቶች ለማድረስ ኩልቼይን ሎጂስቲክስ /cool chain logistics/ አገልግሎት አስፈላጊ በመሆኑ በቀጣይ አምስት ዓመታት በዋና ዋና አምራች አካባቢዎች በሚገኙ ኤርፖርቶች (በአርባ ምንጭ፣ በሀዋሳ፣ በድሬዳዋ፣ በጂማና በሌሎች ኮሪደሮች) የቅዝቃዜ መጠበቂያ መጋዘኖች እንዲሟሉ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የኤክስፖርት ምርቶች ማጓጓዣ አገልግሎት ማመቻቸት፡ የግብርና ምርቶችን (የሆርቲካልቸር እና የሰፋፊ እርሻ) ወደ ገበያ ማዕከላት ለማጓጓዝ የተለያዩ የትራንስፖርት ዘዴዎችን (የአየር፣ የየብስና የባህር) ማጓጓዣ ዘዴዎችን መጠቀም የግድ ይላል፡፡ ለማጓጓዝ እንዲቻል የቅዝቃዜ ሰንሰለት የተሟላላቸው ከ3-6 ቶን የመጫን አቅም ያላቸው ትራኮችን በግል ባለሀብቶች እንዲሟሉ የማበረታቻ ስርአት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም በአውሮፕላን ቢጓጓዙ አዋጭ የማይሆኑ የሆርቲካልቸር ምርቶችን በየብስና ባህር ለማጓጓዝ እንዲቻል የሪፈር ኮንቴይነር አቅርቦትና ተያያዥነት ያላቸው የሎጀስቲክስ አገልግሎቶች እንዲመቻቹ ይደረጋል፡፡

ጥራት ያለው የማሸጊያ ቁሳቁስ አቅርቦትን ማመቻቸት፡- አለምአቀፍ ስታንዳርዳቸውን የጠበቁና ለግብርና ኢንቨስትመንት ኤክስፖርት ምርቶች ማሸጊያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በሀገር ውስጥ የሚመረቱበትን ሁኔታ በማጥናት የግሉ ሴክተር በዚህ አገልግሎት ዘርፍ የሚሰማራበትን ሁኔታ ለመፍጠር ተወዳዳሪ የማበረታቻ ስርአት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

2.3.5 የግብርና ምርቶች የመጀመሪያ ደረጃ አሴት ጭመራን መደገፍ

በአሁኑ ጊዜ በዝቅኛ ደረጃ የሚገኘውን የግብርና ምርቶች የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ ለማስፋፋት አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች በሥርዓቱ ላይ ያላቸውን እውቀትና ክህሎት ማዳበር ያስፈልጋል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ ተግባራትን ለማበረታታትና የዘርፉን ተሳታፊ ተጠቃሚ ለማድረግ አርሶ/አርብቶ አደሮች በምርቶታቸው ላይ የተሟላ ክህሎት እንዲኖራቸው ተከታታይነት ያለው የክህሎት ስልጠና በመስጠት፣ እሴት መጨመር በምርቱ ጥራትና በዋጋ ላይ የሚታየውን ችግር መቅረፍ በድህረ-ምርት ቴክኖሎጂዎች አቅርቦትና አጠቃቀም ላይ የሚስተዋሉትን ችግሮች ለመፍታት ይሠራል፡፡ ድህረ-ምርት አያያዝን ማለትም የምርት አሰባሰብና አከማቻቸት ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ የእሴት ጭመራን ለማበረታታት አስተማማኝ የገበያ ትስስር በመፍጠር አስቻይ ሁኔታዎችን መፍጠር የግል ባለሃብቶች የግብርና ምርቶቻችን ላይ እሴት በመጨመር በኤክስፖርት ገበያ ውስጥ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ አሁን ካለውም በበለጠ አጠናክሮ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ አነስተኛ አርሶ/አርብቶአደሮች ለእሴት ጭመራ የበለጠ እንዲነሳሱ የሚያበረታታ የፋይናንስ አቅርቦት ስርዓት ይመቻቻል፡፡

2.3.6 የምርት ግብይት ፋይናንስ አቅርቦት

ለግብርና ልማትና ግብይት እሴት ሰንሰለቱን የተከተለ በቂና የተሟላ የፋይናንስ አቅርቦት አገልግሎት የሌለው በመሆኑ በተለይም የብድር እና ኢንሹራንስ አግልግሎት አሰጣጥ፣ አቅርቦትና ተደራሽነት ዙሪያ ያለው የአሰራር ስርዓት ምቹ እንዲሆኑ መሥራት ያሰፈልጋል፡፡ አርሶ/አርብቶአደሮችአዳዲስ ስራዎች/የሥራ ዘርፎች/ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ፤ ለተለያዩ ግብዓቶች መግዣ፤ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና የእርሻ መሳሪያዎችን ለመጠቀም እና ምርት አምርቶ ገበያ እስከማድረስ ያሉትን የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች ለመሸፈን ተደራሽ የሆነና ራሱን የቻለ የግብርና ባንክ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ ስለሆነም በዘርፉ የሚታየውን ደካማ የፋይናንስ አቅርቦትና የተደራሽነት ክፍተት ለመሙላትና የሃገራችንን የግብርና ግብዓትና ምርት ግብይት በሚፈለገው ልክ ለማድረስ እንዲረዳ በጥናትና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የግብርና ፋይናንስ አቅርቦት ሥራዓት መዘርጋት ለእቅዱ መሳካት ቁልፍ ሚና የሚጫወት በመሆኑ በትኩረት ይሠራል፡፡

የባንኮች የወለድ መጠን ከፍተኛ መሆን፣ የረጅም ጊዜ ብድር አገልግሎት ውሱን መሆን እና የሰብል መድህን ዋስትና (የሰብል ኢንሹራንስ) አግልግሎት ዋጋ ከፍተኛ መሆን ያስከተላቸውን ተግዳሮቶች የሚፈቱበትን አሠራር እንዲሁም በወጪ ንግድ አቅርቦት ምርት ላይ ለተሠማሩ ተዋንያን ግልጽ፣ ተደራሽና ቀልጣፋ የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

የፋይናንስ አቅርቦትና የማበረታቻ ሥርዓት ማጠናከር

በመሆኑም መካከለኛና ሰፋፊ እርሻዎች ልማት ውጤታማነት ለማሳደግና አዳዲስ አልሚዎችን በስፋት ለመሳብ የንዑስ ዘርፉን ባህሪይ ያገናዘበ የፋይናንስና የማበረታቻ ሥርዓ መዘርጋትና አፈጻጸሙን በትኩረት መከታተል ያስፈልጋል፡፡ በተመሳሳይም አነስተኛ ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች የብድር አቅርቦት ችግር እንዲሁም በቡና እና ቅመማ ቅመም ግብይት የተሰማሩ የግብይት ተዋንያን የምርት መግዣ ብድር አቅርቦት እጥረት ለመፍታት የሚያስችሉ ልዩ አሰራሮች ተግባራዊ በሚደረጉበት ሁኔታ ላይ ከፋይናንስ ተቋማትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅት ተፈጥሮ ይሠራል፡፡

2.1.4 የሰብል ምርቶች ጥራትና ደህንነት

2.1.4.1 የምርት ጥራት ደረጃዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ

የሰብል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቡናና ሌሎች ምርቶች ጥራት በሚታወቅ ደረጃ ተመሥርቶ ግብይትና ልውውጥ እንዲካሄድ ለማድረግ በተመረጡ ዋና ዋና ምርቶች ላይ ደረጃዎች እንዲዘጋጁና ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ ደረጃዎቹ መሟላታቸውም በቁጥጥር ይረጋገጣል፡፡ የሰብል፣የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የቡናና ሌሎች ምርቶች፣ ኢንስፔክሽንና ምርመራው በተስማሚነት ምዘና ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ባላቸው የግል ድርጅቶች እንዲሠራ ይደረጋል፡፡ ጥራቱ የተረጋገጠ ምርት ደግሞ ምርቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያደረጋል፡፡

የእርሻ ምርቶች ደረጃዎች እንዲወጡላቸው የሚያስፈለጉ ሰብሎች መለየትና ደረጃ ማውጣት፤ደረጃ ላላቸው ደግሞ ደረጃዎቹ መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይከናወናል፡፡ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ከሆነ ደግሞ የተቀባዩን አገር ወይም ዓለም አቀፍ ሰታንዳርድ መሟላቱን የማረጋገጥ ሥራ በመሥራት የምርት ብክነትን እንዲቀንስ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

2.1.4.2 የምርት ደህንነትን ማረጋገጥ

ደህንነት ከጥራት ጋር ተመሳሳይነት ቢኖረውም አንድ ዓይነት ግን አይደሉም፡፡ ልዩነቱም የደህንነት ደረጃዎች የእንስሳት፣የዕፅዋት ሕይወት እና የሰው ጤናንና የአካባቢ ደህንነትን ስለሚመለከቱ እጅግ ጥብቅና አስገዳጅ ናቸው፡፡ በዚህ ዙሪያም በዓለም አቀፍ ደረጃዎች በመመርኮዝ ወደ ውጭ በሚላኩት ምርቶች ላይ የደህንነት ማረጋገጥ ሥራ ይሠራል፡፡ ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉትን ደረጃዎች ለወጣላቸው ደረጃውን ማሟላታቸው የማረጋገጥ፤ደረጃ ላልወጣለላቸው ደግሞ ደረጃ እንዲወጣላቸው የማድረግ ሥራ የሠራል፡፡ ለጤና ጠንቅ በመሆኑ ምክንያት ተቀባይነት የሚያጣ ምርት በመቀነሱ ምክንያት ምርት እንዲጨምር አስተዋፅዖ ያደረጋል፡፡

2.1.4.3 የኦርጋኒክ እርሻ ማስፋፋት

ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን በፈቃደኝነት የተመሠረተ የተፈጥሮ እርሻ የማስፋፋት ሥራ ይካሄዳል፡፡ ለዚሁ የሚያስፈልጉ ጥናቶችና የሕግ ማዕቀፍ ተሟልተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በዋናነት በዚህ ዙሪያ ለመሥራት ፍላጎት ያሳዩ ሲቪል ሶሳይቲስ፣ የሕብረት ሥራ ማሕበራት ተሳትፎ እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ ከገበያ አንጻር ተፈላጊ የሆኑ እንደ ኦርጋኒክ የእርሻ ስራ አመራርና (Organic farming) አሰራሮችን በመቀመር ማስተዋወቅና ማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡

2.1.4.4 በኤክስፖርት መተላለፊያና መዳረሻ ሀገሮች ለሚከሰቱ ችግሮች (የፀጥታ፣ የተፈጥሮና የተባይ ወዘተ...) የቅድመ-መከላከል ስራ እንዲሰራ ተገቢውን ጥረት ይደረጋል፡- ለዚህም አለም አቀፍ ደረጃን የሚያሟላ የካራንቲን ስርዓት በመዘርጋት የተጠናከረ ክትትል ማድረግ እና ለሆርቲካልቸር ሰብሎች ልማት የኢንሹራንስ ስርዓት ማጠናከር ወሳኝነት አለው፡፡

2.2 ስትራቴጅክ ዓላማ II : ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት

የግብርናው ዘርፍ ስትራቴጂክ ዓላማ አንዱ የሆነውን ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ምርትን ለማሳደግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን የሚጠቀም አርሶና አርብቶ አደር በመገንባትና በገበያ የሚመራ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ለማስፋፋት አቅጣጫ ተጠቀምጧል፡፡ በሚቀጥሉት 5 አመታት የእንሰሳት እና ዓሳ ሀብት ልማት ሁለት የምርት እድገት አማራጮች ማለትም (1) ዝቅተኛ ምርታማነትን በዝርያ ማሻሻል፣ አያያዝ አመጋገብና እና ጤና አጠባበቅን ማሻሻል እና (2) የምርት ፍላጎት ማለትም ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር የሚፈጠሩ የግብዓት ፍላጎት፣ ለውጪ ምንዛሬ ግኝት እንዲሁም የኢኮኖሚ እድገት ጋር የሚመጡ የእንስሳት ምርት መጠንና አይነት ለውጥ ለሚሟላት ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡ በተለምይም የወተት፣ ሰጋ ፣ እንቁላል፣ ዓሳ፣ ማርና የሐር ኩኩባ ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ ይህም የአነስተኛ አርሶ አርብቶ አደር እና ሰፋፊ እንስሳትና ዓሳ አመራረት ስርዓቶች ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡

የወተት ምርትና ምርታማነት

የአነስተኛ አንስሳት እርባታ ወተት ምርት በዳልጋ ከብት፣ ፍየል እና ግመል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ የአመራረት ሰርዓቶችን ታሳቢ በማድረግ በ2012 ከደረሰበት 4.3 ቢሊየን ሊትር በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 7 ቢሊየን ሊትር ለማድረስ የሚያስችል ዒላማ ተቀምጧል። የዳልጋ ከብት (ላም) ወተት ልማት ሶስት የአመራረት ስርዓቶችን የሚከተል ሲሆን አብዛኛው (85 በመቶ) የሚሆነውን የወተት ምርት ሽፋን የሚይዝና በትኩረት የሚሰራ ይሆናል። የተሻሻለ የቤተሰብ ወተት ላም ልማት አንዱና ዋነኛው የአመራረት ስርዓት ሲሆን በአርሶና አርብቶ አደሩ ተይዘው የሚገኙትን የሀገር በቀል የወተት ላም ዝርያዎችን በመረጣ፣ በማዳቀልና አያያዝ በማሻሻል ምርታመነትን ማሳደግ ላይ ትኩረት በማድረግ ከአንድ የሀገር በቀል የወተት ላም የሚገኝ ወተት በቀን በሊትር በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 1.45 ሊትር በ2017 1.7 ሊትር ማድረስ እና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት (lactation milk yield) ከ261 ሊትር ወደ 332 ሊትር ለማሳደግ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። ሌላኛው የአመራረት ስርዓት በአነስተኛ ስፔሻላይዝድ (small specialized dairy production system) ወተት ከብት እርባታ በአንድ ርባታ ጣቢያ ከ5 ያላነሱ የዲቃላና የውጪ ዝርያ ላሞች በመያዝ የሚሰራ ይሆናል። በዚህም የአመራረት ስርዓት የዲቃላ ላሞቸ የቀን አማካይ ወተት ምርት በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 6 ሊትር ወደ 8 ሊትር እና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት (lactation milk yield) ከ1620 ሊትር ወደ 2285 ሊትር ለማሳደግ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። የውጪ ዝርያ ላሞች የቀን አማካይ ወተት ምርት አሁን ከሚገኘው 13 ሊትር በወደ 15 ሊትር እና አማካይ የአንድ አለባ ወቅት የወተት ምርት (lactation milk yield) ከ3920 ሊትር ወደ 4464 ሊትር ለማሳደግ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። ይህንን ምርት ለተጠቃሚዎችና ለአቀነባባሪዎች ሳይባክን የሚቀርቡበትን ሰርአት በማጠናከር የላም ወተት በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ2.6 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 1.8 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ድርሻ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 46 በመቶ ወደ 55 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል።

ሌላው የወተት ምንጭ የግመል ወተት ልማት ሲሆን ከአጠቃላይ የወተት ምርት የ15 በመቶ የምርት ድርሻ የሚሸፍንና በአርብቶ አደሩ ተይዘው የሚገኙትን የሀገረሰብ ዝርያዎቸን በመረጣና በድቀላ በማሻሻል ላይ ትኩረት በማደረግ የሚሰራ ይሆናል። ይህም የወተት እርባታ አሰራር ከአንድ ግመል በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት በቀን በአማካይ 2.9 ሊትር በ2017 ዓ.ም ወደ 3.2 ሊትር ለማድረስ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። ይህንን ምርት ለተጠቃሚዎችና ለአቀነባባሪዎች ሳይባክን የሚቀርቡበትን ሰርአት በማጠናከር የግመል ወተት በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ 10 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 7.1 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ድርሻ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 47 በመቶ ወደ 60 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል።

ሶስተኛው የወተት ምንጭ የፍየል ወተት ልማት ሲሆን ከአጠቃላይ የወተት ምርት አነስተኛ የምርት ድርሻ የሚሸፍን ሲሆን አርሶና አርብቶ አደሩ ተይዘው የሚገኙትን የሀገር በቀል የፍየል ዝርያዎችን በመረጣና ከውጪ ደም ካላቸው ጋር በማዳቀል ምርታመነትን ማሳደግ ትኩረት በማደረግ የሚሰራ ይሆናል። ይህም የወተት እርባታ አሰራር ከአንድ ፍየል 2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት በቀን በአማካይ 0.46 ሊትር በ2017 ወደ 0.48 ሊትር ለማድረስ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። ይህንን ምርት ለተጠቃሚዎችና ለአቀነባባሪዎች ሳይባክን የሚቀርቡበትን ሰርአት በማጠናከር የፍየል ወተት በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ10 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 7.1 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ድርሻ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 44 በመቶ ወደ 53 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል።

የቀይ ሥጋ ምርትና ምርታማነት

የቀይ ስጋ ምርት ከዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል እና ግመል ልማት ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን የተለያዩ የአመራረት ሰርዓቶችን ታሳቢ በማድረግ በ2012 መጨረሻ ከደረሰበት 297 ሺህ ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ 721 ሺህ ቶን ለማድረስ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። ይህ ምርት በአብዛኛው ከአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር የእንስሳት ልማት ይሆናል። ስነምህዳርን መሰረት በማድረግና የቀይ ስጋ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየልና ግመል ሥጋ ምርታማነት በ2012 መጨረሻ ከደረሰበት 110፣ 10.5፣ 8.4 እና 250 ኪ.ግ

ካርካስ ክብደት (carcass weight) በቅደም ተከተል በ2017 መጨረሻ 115.3፣ 11.2፣ 9.2፣ እና 263.6 ኪ.ግ ለማድረስ ይሰራል። ሌላኛው የቀይ ስጋ ምርት ለወተት ሀብት ልማት ተግባር ከሚዳቀሉ እንስሳት የሚወገዱ ወንድ ጥጆችን በፍጥነት አሳድጎ ለስጋ ምርት መዋልና ከወተት እርባታ ጣቢያ የሚወገዱ የወተት እንስሳት በማድለብ ስጋ ለማምረት ዒላማ ተቀምጧል።

ይህንን ምርት ለተጠቃሚዎችና ለአቀነባባሪዎች ሳይባክን የሚቀርቡበትን ሰርአት በማጠናከር ከበሬ ስጋ በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ0.5 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 0.4 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ድርሻ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 51 በመቶ ወደ 57 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል። በሌላ በኩል በበግ ስጋ በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ3 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 2.1 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ምርት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 42 በመቶ ወደ 51 በመቶ ለገበያ ለማቅረብ ኢላማ ተቀምጧል። በተመሳሳይም ከፍየል ስጋ በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ3 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 2.1 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ምርት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 45 በመቶ ወደ 51 በመቶ ለገበያ ለማቅረብ ኢላማ ተቀምጧል። ከግመል ስጋ ምርት በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ8 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 5.7 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ድርሻ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 49 በመቶ ወደ 62 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል።

የቆዳና ሌጦ ምርት

ከስጋ ምርት ጋር በተያያዘ ቆዳና ሌጦ ዋነኛው ተዋፅዖ ሲሆን በ2012 ከተደረሰበት 1. 5 ሚሊየን የቆዳ ምርት፣ 12 ሚሊየን የሌጦ ምርት በ2017 የቆዳ ምርትን 3.7 ሚሊየንና ፣ የሌጦ ምርት 25.5 ሚሊየን ለማድረስ ዕቅድ ተይዟል።

የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትና ምርታማነት

የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን በማሟላት የውጭ ኤክስፖርትን ለማስጀመር የሚያስችሉ የአካባቢ ዶሮች አያያዝን የማሻሻል፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታና የስፔሻላይዝድ ዶሮ እርባታ ተሳታፊዎችን እንዲሁም በየእርባታው የሚያዙትን የዶሮ ቁጥርን መጨመርና ምርታማነትን ለማድረስ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል። በዚህም መሰረት የእንቁላል ምርትን በ2012 መጨረሻ ዓ.ም ከነበረዉ 2.9 ቢሊዮን እንቁላል በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 4 ቢሊዮን እንቁላል የማሳደግ ስራ ይሰራል። አብዛኛው የእንቁላል ምርት (89 በመቶ) ከስፔሻላይዝድ የእንቁላል ዶሮ እርባታ የሚገኝ ሲሆን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 2.6 ቢሊዮን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 3.6 ቢሊዮን ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል። ከተሻሻሉ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የእንቁላል ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 200 ሚሊየን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 268 ሚሊየን በማሳደግ እና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ የእንቁላል ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 107 ቢሊዮን ወደ ከፊል ዘመናዊ እንዲሸጋገር በማድረግ በ2017 ዓ.ም ወደ 99 ሚሊየን እንዲቀንስ በማድረግ ይሆናል።

የዶሮ ስጋ ምርትን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 48 ሺህ ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 70.3 ሺህ ቶን ለማሳደግ ከስፔሻላይዝድ የስጋ ዶሮ እርባታ የሚኖረው የስጋ ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 31.3 ሺህ ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 50.3 ሺህ ቶን በማሳደግ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የዶሮ ስጋ ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 3.4 ሺ ቶን በ2012 ወደ 5.4 ሺ ቶን በማሳደግ እና ከባህላዊ የዶሮ እርባታ የሚገኘው የስጋ ምርት መጠን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ከ13.2 ሺህ ቶን ወደ ከፊል ዘመናዊ እንዲሸጋገሩ በማድረግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 14.6 ሺህ ቶን እንዲጨምር በማድረግ ይሆናል።

የተለያዩ የዶሮ አረባብ ስልተ-ምርትን መሰረት በማድረግና የዶሮ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም አሁን ከአንድ ዶሮ በአመት የሚገኘዉን የእንቁላል ምርታማነት ከስፔሻላይዝድ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 960፣ 188 እና 65 እንቁላል በዓመት በመሪ አቅዱ ዘመኑ መጨረሻ 1110፣ 200 እና 67 ማድረስ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ በቀጣይ አምስት ዓመታት የተለያዩ የዶሮ አረባብ ስልተ-ምርትን መሰረት በማድረግና

የዶሮ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም አሁን ከአንድ ዶሮ በአመት የሚገኘዉን የዶሮ ስጋ ምርታማነት ከስጌሻላይዝድ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 2 ፣ 1.5 እና 1.25 ኪሎ ግራም ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2.2፣ 1.7 እና 1.6 ኪሎ ግራም ማድረስ ይሆናል፡፡

የዓሣ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ

የዓሳ ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትንንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከተደረሰበት ከ55 ሺህ ቶን በ2017 ዓ. ም መጨረሻ ወደ 133 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአኳካልቸር ምርት በ2017 መጨረሻ 2 ሺህ ቶን እንዲገኝ ይሰራል፡፡

የማር ምርትና ምርታማት

የማርና ሰም ምርትን ለማሳደግና ለሀገር ውስጥ ፍላጎት እና ለኤክስፖርት የማር ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 59 ሺህ ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ 95 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል፡፡ እንዲሁም የንብ ፕሮፖሊስ አሁን እየተመረተ ባይሆንም በቀጣይ አምስት ዓመት ውስጥ 5 ቶን ለማምረት ይሰራል፡፡ ስነምህዳርን መሰረት በማድረግ የማርና የሰም ምርትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም ከአንድ ባህላዊ ቀፎ በአንድ ቆረጣ የሚገኝ በአማካይ የማር ምርትን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 5.2 ኪ.ግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 9 ኪ.ግ ለማሳደግ ይሰራል፡፡ ዘርፉን ለማዘመንና ሽግግር በማምጣት የአርሶ አደሩን ግንዛቤ በማሳደግ እና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን በማሻሻል በ2012 ዓ.ም 4 በመቶ የነበረው የተሻሻለ ዘመናዊና ሽግግር ቀፎ ድርሻ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ 13 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

ይህንን የማር ምርት ለተጠቃሚዎችና ለአቀነባባሪዎች ሳይባክን የሚቀርቡበትን ሰርአት በማጠናከር ከማር ምርት በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ10 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 8.9 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ምርት በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 53 በመቶ ወደ 65 በመቶ ለገበያ ለማቅረብ ኢላማ ተቀምጧል፡፡ በተጨማሪም ከሰም ምርት በድህረ ምርት ብክነት ይደርስ የነበረውን የ30 በመቶ ምርት ብክነት ወደ 25 በመቶ ለመቀነስና ጥራቱና ደህንነቱን የጠበቀ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ድርሻ በ2012 ዓ.ም ከነበረበት 22 በመቶ ወደ 27 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል፡፡

የሐር ኩኩባ ምርትና ምርታማነት

ይህ ዘርፍ ቀደም ሲል በስፋት ያልተሰራበትና ትኩረት ያልተሰጠው ሲሆን ሀገራችን ከምትከተለው የኢኮኖሚ እድገት አቅጣጫ እየተስፋፋ ላለው ኢንዱስትሪ በጥሬ እቃነትና በውጪ ገበያ ያለው ተፈላጊነት፣ የሀገራችን ስነ ምህዳር አመቺነት፣ ልማቱ በአነስተኛ መሬት ጉልበትና መነሻ ካፒታል የሚሰራ በመሆኑ፣ በገጠርም ሆነ በከተማ የስራ እድልን ለመፍጠር ማስቻሉና በተለያየ እድሜና ጾታ በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊሰራ የሚችል በመሆኑና በአጭር ጊዜ ምርት በመስጠት የህብረተሰቡን ገቢ በማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ 5 አመታት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡ የደረቅ የሐር ኩኩባ ምርትን በ2012 ዓም መጨረሻ ከተደረሰበት 29.96 ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ 48.24 ቶን ለማድረስ ይሰራል፡፡

2.2.1 ያደገ የተሸሻሉ የአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር እንስሳትና ዓሳ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች አጠቃቀም

የአነስተኛ አርሶና አርብቶ አደር እንስሳትና ዓሣ ልማት በሚቀጥሉት 5 አመታት አብዛኛውን የምርት ድርሻ እየሸፈነ የሚቀጥል ሲሆን ለአርሶ አደሩ የገቢ ምንጭ እንዲሁም የምግብና ስነ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና እና መካከለኛ ገቢ ያለዉ አርሶና አርብቶ አደር ለመገንባት ትልቅ አስተዋፅዎ ይኖረዋል፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ፣ የእንስሳት መኖን በጥራትና በብዛት ማቅረብ እንዲሁም የውሃ አቅርቦትን ማሻሻል፣ የእንስሳት በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር፣ በተጠቃሚው ተቀባይነት ያለው ቴክኖሎጂ አቅርቦት እና ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/አርብቶ አደር ለማፍራት ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ይሆናል፡፡ ይህም

በወተት፣ ሰጋ፣ እንቁላል፣ አሳ፣ ማርና የሐር ኩኩባ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል።

2.2.1.1 በእንስሳትና ዓሳ ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች ላይ ፅውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር

ሀ) የወተት ሀብት ልማት

የወተት ላም ልማት

የተሻሻለ የቤተሰብ የወተት ላም ልማት በቀጣይ 5 ዓመታት ትኩረት ተሰጦ ከሚተገበሩ ስራዎች አንዱ ይሆናል። የአገር ውስጥ ዝርያ በተሻሻለ የአረባብ ዘዴ በሶስቱ ስልተ-ምርት ማለትም በቂ እርጥበት ባለበትና ጥምር ግብርና በሚካሄድበት፣ እርጥበት አጠር በሆነና ጥምር ግብርና በሚካሄድበት እንዲሁም አርብቶ አደር አካባቢ ከላም የሚገኝ ወተት በ2012 ከነበረው 3.6 ቢሊዮን ሊትር በ2017 ወደ መጨረሻ 10 ቢሊዮን ሊትር እንዲደርስ ይሰራል። በቀጣይ 5 ዓመታት ውስጥ በእያንዳንዱ አርሶና አርብቶ አደር እጅ ከሚገኙ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሀገረሰብ ላሞች በ2012 ዓ.ም 11.5 ሚሊየን የነበሩትን በየአመቱ በ2 በመቶ በመቀነስ በ2017 መጨረሻ ወደ 10.2 ሚሊየን ዝቅ እንዲል ይደረጋል። በዚህም ከፍተኛ የወተት ምርት የሚሰጡ የተሻሻሉ ዲቃላና ንፁህ የውጪ ዝርያ ያላቸው ላሞች (316 ሺህ) የ 2.7 በመቶ ድርሻ በማሳደግ በ2017 መጨረሻ ወደ 6.7 በመቶ ድርሻ እንዲኖራቸው ይሰራል። የአገር ውስጥ ዝርያዎችም የተሻለ የቀንና የዓመት ወተት ምርት (daily and lactation milk yield)፣ ረዘም ላሉ ቀናት የመታለብ አቅምን (lactation length)፣ ፈጥኖ አድጎ ለርቢ እንዲደርሱና በየዓመቱ ጥጃ መውለድ እና ማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ የአያያዝ፣ የአመጋገብና ጤና እንክብካቤ ለማሻሻል ጠንካራ ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል። አርሶ አደሩ የወተት ላሞቹን መረጃ መሰረት ያደረገ የተሻለ ምርት የሚሰጡትን እየመረጠ እንዲይዝ የዝርያ ማሻሻል ሥራ ግንዛቤ መፍጠር ሥራ ይሰራል።

በፌደራልና በክልሎች አሁን ያሉትን 24 የፈሳሽ ናይትሮጂን ማምረቻ ማሽኖች ጥገናቸዉን በማጠናከር በሙሉ አቅማቸዉ እንዲያመርቱ በማድረግና ሌሎች አዳዲሶችን በመጨመር ቁጥሩን ወደ 30 በማሳደግ የፈሳሽ ናይትሮጂንን ዓመታዊ ምርት በ2012 ካለበት 287,000 ሊትር በ2017 ዓ.ም መጨረሻ 547,763 ሊትር የማድረስ ስራ ይሰራል። የወተት እንስሳት ዝርያን በሰው ሰራሽ ዘዴ በማዳቀል የተሻሻሉ የወተት ላሞችን ቁጥር የመጨመር ሥራ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ተገቢዉን ትኩረት አግኝቶ የሚፈፀም ይሆናል። በዚህም መሰረት በቀጣዩ 5 ዓመታት በተሻሻሉ ዲቃላና ንፁህ የወተት ዳልጋ ከብት ቁጥር በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 314.5 ሺህ በማሳደግ በ2017 ዓም ወደ 749.5 ሚሊየን ለማድረስ ይሰራል።

የመስክ ማዳቀል አገልግሎት ውጤታማነትን /Field AI Efficiency/ ለማሻሻል በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 2.27 በመቀነስ የጥቂ ድግግሞሹን 2.11 ለማድረስ ይሰራል። የተሻሻሉ የወተት ዲቃላ ላሞች የቀን የወተት ምርት አሁን ከደረሰበት 6 ሊትር በማሳደግ 2017 መጨረሻ 8 ሊትር ማድረስ ታቅዷል።

የግል ባለሀብቱ የተሻሻሉ ጊደሮች የማምረት ስራ ላይ እንዲሰማሩ የመደገፍ፣ የማበረታታትና የገበያ ትስስር መፍጠር ሥራ ተጠናክሮ ይሰራል። በዝርያ ማሻሻል ስራ ተሳታፊ ለሆኑ አርሶ አደሮች ስለተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች አያያዝ፣ አመጋገብና ጤና አጠባበቅ ስልጠና ይሰጣል። በዝርያ ማሻሻል ለሚሳተፉ አርሶ አደሮች በቅድሚያ የተሻሻለ መኖ አንዲያለሙ ይደረጋል። በተሻሻሉ ዝርያዎች የሚከሰተውን የሞት ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችሉ ፓኬጆችን በማዘጋጀት ይተገበራል ።

የወተት እንስሳትን አመጋገብ ስርዓት ለማሻሻል ዝርያቸውን መሰረት ያደረገና የምርታመነታቸው ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ የአመገገብ ስርዓት እንዲኖር ለአርሶ አደር በቤተሰብ ደረጃ ለሚያዘጋጁት መኖ አጠቃቀም የሚረዱ ፓኬጆችን በመቅረፅ እና ስልጠና በመስጠት እንዲተገበር ይደረጋል። አርቢው ህብረተሰብ መኖን በውጤታማነት መጠቀም እንዲችል ትርፍ መኖ በሚኖርበት ወቅት ያለውን መኖ በጥንቃቄ በመሰብሰብ ሳይባክንና ሳይበላሽ እጥረት ባለበት ወቅት እንዲያቆይ የተለያዩ የማቆያ ዘዴዎችን በማሳወቅ እንደ ገፈራ ማዘጋጀት እና ድርቆሽን አዘጋጅቶ እንዲጠቀም ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል። ከመኖ ጥራት ጉድለት የሚመጡ የምርት ጥራት መቀነስና የምርታማነት መቀነስ እንዳናኖር አርቢው

ህብረተሰብ በስልጠናና በመስክ በሚደረግ ድጋፍና ክትትል የሚደገፍ ይሆናል። ከመኖ አጠቃቀም ጉድለትና ከመኖ ብክነት ጋር ተያይዞ የምርት ዋጋ ንረት እንዳይከሰት አርቢው በእርባታ ደረጃ የእርባታ ወጪ የሚያሰላበት እውቀት እንዲኖረው የግንዛቤ ማሳደግ ስራ በተከታታይ እንዲኖረው ይደረጋል። የወተት እንስሳት ጤና አጠባበቅ ለማሻሻል የህክምና ተደረሰሽነት አሁን ካለበት 11 በመቶ በማሳደግ በ2017 ዓ. ም መጨረሻ 21 በመቶ በማድረስ የጤና አያያዛቸው በማሻሻል ህመምና ሞት አሁን ካለበት 15 በመቶ ወደ 11 በመቶ የሚሻሻል ይሆናል። በአጠቃላይ የተሻሻሉ የወተት እርባት ቴክኖሎጅዎችን/አሰራሮችን ለመጠቀም የሞከሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች አሁን ካለበት 28 በመቶ በ2107 መጨረሻ ወደ 40 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል።

የግመል ወተት ልማት

የግመል ወተት ምርታመነትን ለማሻሻል የምንከተለው ስልት አርብቶ አደሩ የተሻለ ወተት የሚሰጡ የግመል ዝርያዎችን መርጦ የሚጠቀሙበት ዘዴ የመምረጫ ማንዋል አዘጋጅቶ ለአርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩን ለሚደግፉ ባለሞያዎች ግንዛቤ በማስጨበጥ አርብቶና አርሶ አደሩ የወተት ግመሎችን መረጃ መሰረት ያደረገ የተሻለ ምርት የሚሰጡትን እየመረጠ እንዲይዝ የዝርያ ማሻሻል ሥራ ግንዛቤ መፍጠር ሥራ ይሰራል። የግመል አመጋገብ ለማሻሻል ግመሎች በተለምዶ ከሚያደርጉት የመቀንጠብ ስርዓት ባሻገር ተጨማሪ ደገፊ መኖዎችን በማስተወወቅ እና ተጨማሪ የምጥን መኖ የመጠቀም ስልት እንዲለምዱ የሰራል።

የወተት ምርት የሚጨምርበትን የአያያዝ ሥርዓቶች በማዘጋጀትና ለአርብቶ አደሩ ሥልጠና በመስጠት እንዲጠቀም የማድረጉ ሥራ ይሰራል። የአገር ውስጥ ግመሎች የተሻለ የቀንና የዓመት ወተት ምርት (daily and lactation milk yield) ፣ ረዘም ላሉ ቀናት የመታለብ አቅምን (lactation length) ፣ ፈጥኖ አድጎ ለርቢ እንዲደርሱና በየዓመቱ ጥጃ መውለድ እና ማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ የአያያዝ፣ የአመጋገብና ጤና እንክብካቤ ለማሻሻል ጠንካራ ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል። የወተት ግመሎች ጤና አጠባበቅ ለማሻሻል የህክምና ተደረሰሽነት በማሻሻል ህመምና ሞት ክስተት አሁን ካለበት 6 በመቶ ወደ 4 በመቶ የሚቀንስ ይሆናል። በአጠቃላይ የተሻሻሉ የግመል ወተት እርባት ቴክኖሎጅዎችን/አሰራሮችን ለመጠቀም የሞከሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች አሁን ካለበት 15 በመቶ በ2107 መጨረሻ ወደ 17 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል።

የፍየል ወተት ልማት

የፍየል ወተት ምርታመነት ለማሻሻል በቆላው አካባቢ የሚገኙ አርብቶ አደሩ የተሻለ ወተት የሚሰጡ ፍየሎችን ዝርያዎችን መርጦ የሚጠቀሙበት ዘዴ የመምረጫ ማንዋል አዘጋጅቶ ለአርብቶ አደሩና አርብቶ አደሩን ለሚደግፉ ባለሞያዎች ግንዛቤ በማስጨበጥ አርሶ አደሩ የወተት ፍየሎችን መረጃ መሰረት ያደረገ የተሻለ ምርት የሚሰጡትን እየመረጠ እንዲይዝ የዝርያ ማሻሻል ሥራ ግንዛቤ መፍጠር ሥራ ይሰራል። እንዲሁም የተዳቀሉ ፍየሎችን ለመያዝ የሚያስችል የአየር ንብረት በለበት አከባቢ ከውጭ የወተት ፍየል ዝርያ ጋር በማዳቀል እንዲያረቡ በስልጠና የማብቃትና በወተት መስጠት የታወቁ የውጭ ደም ያላቸው የፍየል ዝርያዎች በቁም በኮርማ ወይም በሰው ሰራሽ ዘዴ ለማዳቀል በአባላዘር መልክ እንዲቀርብ ይደረጋል። የወተት ፍየሎችን አመጋገብ ለማሻሻል ፍየሎች በተለምዶ ከሚያደርጉት የመቀንጠብና ግጦሽ በተጨማሪ ደገፊ መኖዎችን በማልማትና እና ተጨማሪ የምጥን መኖ የመጠቀም ስልት እንዲጠቀሙ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል።

ለ) የቀይ ስጋ ሀብት ልማት

የሥጋ ሀብት ልማት ዕድገት ምንጭ ሆነው የሚያገለግሉት የሥልተምርት ዓይነቶች የተሻሻለ፣ ተለምዷዊና ስፔሻላይዝድ የእንስሳት ማድለብ ሲሆን የወተት ከብት እርባታ ሥርዓቱ የሚያፈራቸዉ ተባዕት ጥጆችን በማሣደግ ለሥጋ የማዋል ሥራ በስፔሻላይዝድ የሥጋ እንስሳት ማድለብ ያካትታል። በተለምዷዊ አረባብ ሥርዓት የአርሶ አደሩ የእንስሳት እርባታ የሚመሰረተው በዋናነት የአካባቢ ዝርያ በመጠቀም ሲሆን የዚህ ስርዓት የትኩረት አቅጣጫም የእንስሳት መኖ በማሻሻል፣ አሁን ያለውን ከፍተኛ የግልገሎችና ጥጆች ሞት መጠንን በመቀነስ፤ ሥነተዋልዶ ሥርዓቱንና የነፍስ ወከፍ ምርታማነትን በማሻሻል፣ እንዲሁም የንሺ መጠንን በማሳደግ ላይ የሚመሰረት ይሆናል።

በአነስተኛ አርቢ ዘንድ የሚተገበረው የቀይ ስጋ እንስሳት ዝርያ ለማሻሻል

አነስተኛ የስጋ ይዞታ ያላቸው ዝርያዎችን ከተመረጡ የአገር ውስጥ ዝርያዎች ጋር በማዳቀልና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመተካት (ለምሳሌ የአፋር ዝርያ ከብት በቦረና) ማሻሻል፣ የተሸለ የስጋ ማምረት ብቃት ያላቸው ዝርያዎቹ በሚኖርባቸው አካባቢዎች በመረጣ የማሻሻል ሥራ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ዝርያው ከሚኖርበት አካባቢ ጋር ተመሳሳይ ስነምህዳር ባላቸው ሌሎች አካባቢዎችም በዝርያ አሻሻይነት የሚገባበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ በበግና ፍየል ዝርያ ማሻሻል ዙሪያ የቦንጋ፣ ዋሸራ፣ መንዝና ሆሮ ዝርያዎች ላይ የተጀመረው በማህበረሰብ ዝርያ የማሻሻል አካሄድ ተጠናክሮና ሰፍቶ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በስጌሻሊዝድ የስጋ ልማት የምነከተለው የዝርያ ማሻሻል ደግሞ ከአገራችን ውጭ የሚገኙና ለአገራችን ሥነ ምህዳር ተስማሚ የሆኑትን የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል ዝርያዎች በመምረጥና በማስገባት፣ የማላመድና የማዳቀል ስራ በፅቅድ ዘመኑ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ የዚህ ተግባር ዋናው ዓላማ ለቀጣይ የፅቅድ ዘመን መሰረት መጣል ሲሆን የተወሰኑት በፅቅድ ዘመኑ አጋማሽ ይደርሳሉ የሚል ታሳቢ ተወስዷል፡፡በውተት ሀብት ዙሪያ የሚሰሩ የዝርያ ማሻሻል ስራዎች ለስጋ ምርት አቅርቦት ማደግም አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡

የስጋ እንስሳት አመገገብን በተመለከተ ደግሞ በዋናነት ተፈጻሚ የሚሆነው ስልት የመኖ አቅርቦት፣ ጥራትና አመጋገብን ማሻሻል ሲሆን የመኖ ጥራትን ከማረጋገጥ አኳያ በዋናነት የሚፈለገውን ክብደት ጭማሪ ለማምጣት የሚያስችሉ የመኖ ዓይነቶች እንደየአካባቢው/ሥነምህዳሩ ሁኔታ ተመርጠው የሚለሙና የሚቀርቡ ሲሆን የዓመጋገብ ሥርዓቱም ሁሉንም የንጥረነገር ይዘት ሊያሟላ በሚችል መንገድ አቀናጅቶ በማዘጋጀት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ የማድለብ ሥራው ትኩረት የሚያደርገው የተሻለ የመኖና የኢንደስትሪ ተረፈምረት አቅርቦት ባሉባቸው አካባቢዎች ይሆናል፡፡ የማድለብ ሥራ ከፍተኛ የውሃ አቅርቦትን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ እያንዳንዱ አድላቢ የሚያስፈልገውን የውሃ መጠን ለማሟላት የሚያስችል የውሃ መገኛ አማራጭ ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀት የሚሰራ ይሆናል፡ :

የስጋ እንስሳት ጤና ማሻሻል

እንስሳት በሚደልቡበት አካባቢ መኖራቸው ለተረጋገጡ በሽታዎች የመከላከያ ክትባት መስጠት፣ የውጭና የውስጥ ጥገኛ በሽታዎች ማስወገድ፣ የተጠናከረ ባዮ ሴኩሪቲ ሰርዓት መገንባት እንዲሁም እንስሳቱ በቆይታቸው ጊዜም ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይሆናል፡፡ የሚደልቡ ዳልጋ ከብቶች ጤና ጤና አገልግሎት ሽፋን አሁን ካለበት የ7 በመቶ ሽፋን በማሻሻል በ2107 መጨረሻ ወደ 15 በመቶ በማድረስ የህመምና ሞት ክስተት አሁን ካለበት 12 በመቶ ወደ 8 በመቶ የሚቀንስ ይሆናል፡፡ በአጠቃላይ የተሻሻሉ የዳልጋ ከብቶች እርባት ቴክኖሎጅዎችን/አሰራሮችን ለመጠቀም የሞከሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች አሁን ካለበት 51 በመቶ በ2107 መጨረሻ ወደ 63 በመቶ ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል፡፡

የአረባብ ስርዓት ማዘመን

በስጌሻላይዝድ የዳልጋ ከብት ማድለብ ሥራ (specialized cattle feedlots) የተቀመጠው አቅጣጫ የአነስተኛና መካከለኛ የማድለቢያ ማዕከላትን፣ በእያንዳንዱ ማድለቢያ የሚገባውን እንስሳት ቁጥርና የማድለቢያ ዙር (fattening cycle) በመጨመር፣ የግል ባለሃብቱ በዘመናዊ የሥጋ እንስሳ ማራባት (Ranch) ላይ እንዲሰማሩ በመደገፍ የሚተገበር ይሆናል፡፡ እንዲሁም ሴቶችንና ወጣቶችን በማደራጀት የአንድ ጊዜ ፍፃሜ ድቀላን /Terminal Crossing/ መሰረት ያደረገ አቅራቢዎችን በመጠቀም ምርታማነትን ማሻሻልና የሚደልቡ እንስሳትን ከአርብቶ አደር አካባቢዎች በማውጣትና የተሻለ መኖ አቅርቦት ባለባቸው አካባቢዎች እንዲደልቡ ለማድረግ የማስተሳሰር ስራ የሚተገበር ይሆናል፡፡ የገበያ መሰረተ ልማት መገንባት፣ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ሥራን ከመኖ ልማት ጋር በማስተሳሰር መኖን ማልማት፣ የስኳር ፋብሪካዎች ከሚገነቡባቸው አካባቢዎች ጋር በማስተሳሰር የሚገኘውን ተረፈ ምርት በላቀ ደረጃ ለመጠቀም ጥረት ማድረግ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚፈጸሙ ተግባራት ይሆናሉ፡፡ከማዳቀል ስራ የሚገኙ ተባዕት ጥጆች ለተደራጁ ወጣትና ሴት አሳዳጊዎች በመሸጥና ለስጋ እንዲውሉ በማድረግ

ከዲቃላ እንስሳት ሊገኝ የሚችለውን ፈጣን እድገት፣ ከፍተኛ የሰውነት ክብደት፣ የተሻለ የመኖ አጠቃቀም አቅማቸውን መጠቀም እንዲቻል ይሰራል፡፡

በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የአርቢውን አድላቢውን እና ሙያተኛውን አቅም በእንስሳት መኖ አመራረት፣ አዘገጃጀት እንዲሁም አመጋገብ ሥርዓት፤ የሚደልቡ እንስሳት አመራረጥና ጤና ክብካቤ፣ በዝርያ መረጣና ማሻሻል እንዲሁም በእንስሳት አያያዝ ዙሪያ የተጠናከረ አቅም ግንባታ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ሴቶችን፣ ወጣቶችን እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ከሥጋ ሃብት ልማት አኳያ ተጠቃሚ ለማድረግ የብድር አቅርቦትና የስራ ቦታን በማመቻቸት፣ የክህሎት አቅማቸውን በስልጠና በመገንባት እንዲሁም የመኖ አቅርቦትን ለማሟላት ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራና ከአግሮ ኢንደስትሪዎች በተለይም ከስኳር ፋብሪካዎች ጋር በማስተሳሰር ተረፈ ምርቶችን በላቀ ደረጃ በመጠቀም ግብዓት በማምረትና እንስሳትን በማድለብ ተጠቃሚ የሚሆኑበት አሰራር ይዘረጋል፡፡ የሥጋ ምርትን ለማሳደግ ተግባራዊ የሚደረጉ ስልቶች ማለትም የግልገሎችና ጥጆች ሞት መጠንን በመቀነስ፤ ሥነተዋልዶ ሥርዓቱንና የነፍስ ወከፍ ምርታማነትን ማሻሻል እንዲሁም የንሺ መጠንን ማሳደግ የካርቦን ልቀትን በመቀነስ ለዓየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማትን ለማረጋገጥ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል፡፡

ሐ) የዶሮ ስጋና እንቁላል ሀብት ልማት

የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን በማሟላት የውጭ ኤክስፖርትን ለማስጀመር የሚያስችሉ የአካባቢ ዶሮች አያያዝ የማሻሻል፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታና የስጌሻላይዝድ ዶሮ እርባታ ተሳታፊዎችን እንዲሁም በየእርባታው የሚያዙትን የዶሮ ቁጥርን መጨመርና ምርታማነትን ማሳደግን መሰረት ያደረገ ስራ ይሰራል፡፡ የዶሮ ስጋና እንቁላል ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን በማሟላት ለወጪ ንግድ አቅርቦት ለማስጀመር የሚያስችሉ የአካባቢ ዶሮች አያያዝን የማሻሻል፣ የተሻሻለ የቤተሰብ ዶሮ እርባታና የስጌሻላይዝድ ዶሮ እርባታ ተሳታፊዎችን እንዲሁም በየእርባታው የሚያዙትን የዶሮ ቁጥርን መጨመርና ምርታማነትን ለማድረስ የሚያስችል ኢላማ ተቀምጧል፡፡ አብዛኛው የእንቁላል ምርት (89 በመቶ) ከስጌሻላይዝድ የእንቁላል ዶሮ እርባታ የሚገኝ ሲሆን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 2.6 ቢሊዮን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 3.6 ቢሊዮን ለማሳደግ ኢላማ ተቀምጧል፡፡ ከተሻሻሉ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የእንቁላል ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 200 ሚሊየን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 268 ሚሊየን በማሳደግ እና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ የእንቁላል ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 107 ቢሊዮን ወደ ከፊል ዘመናዊ እንዲሸጋገር በማድረግ በ2017 ዓ.ም ወደ 99 ሚሊየን እንዲቀንስ በማድረግ ይሆናል፡፡

የዶሮ ስጋ ምርትን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 48 ሺህ ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 70.3 ሺህ ቶን ለማሳደግ ከስጌሻላይዝድ የስጋ ዶሮ እርባታ የሚኖረው የስጋ ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 31.3 ሺህ ቶን በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 50.3 ሺህ ቶን በማሳደግ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብ ዶሮ እርባታ የዶሮ ስጋ ምርት በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት 3.4 ሺ ቶን በ2012 ወደ 5.4 ሺ ቶን በማሳደግ እና ከባህላዊ የዶሮ እርባታ የሚገኘው የስጋ ምርት መጠን በ2012 ዓ.ም መጨረሻ ከደረሰበት ከ13.2 ሺህ ቶን ወደ ከፊል ዘመናዊ እንዲሸጋገሩ በማድረግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 14.6 ሺህ ቶን እንዲጨምር በማድረግ ይሆናል፡፡

የተለያዩ የዶሮ አረባብ ስልተ-ምርትን መሰረት በማድረግና የዶሮ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም አሁን ከአንድ ዶሮ በአመት የሚገኘውን የእንቁላል ምርታማነት ከስጌሻላይዝድ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 960፣ 188 እና 65 እንቁላል በዓመት በመሪ አቅዱ ዘመኑ መጨረሻ 1110፣ 200 እና 67 ማድረስ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በቀጣይ አምስት ዓመታት የተለያዩ የዶሮ አረባብ ስልተ-ምርትን መሰረት በማድረግና የዶሮ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም አሁን ከአንድ ዶሮ በአመት የሚገኘውን የዶሮ ስጋ ምርታማነት ከስጌሻላይዝድ፣ ከተሻሻሉ የቤተሰብና ከባህላዊ ዶሮ እርባታ በቅደም ተከተል 2 ፣ 1.5 እና 1.25 ኪሎ ግራም ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 2.2፣ 1.7 እና 1.6 ኪሎ ግራም ማድረስ ይሆናል፡፡

መ) የዓሣ ሀብት ልማት

የዓሳ ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትንንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር በ2012 ዓ.ም ከተደረሰበት ከ 55 ሺህ ቶን በ2017 ዓ. ም መጨረሻ ወደ 133 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል። በተመሳሳይ መልኩ የአኳካልቸር ምርት በ2017 መጨረሻ 2 ሺህ ቶን እንዲገኝ ይሰራል። በቀጣይ 5 ዓመታት የዓሳ ምርትን ለማሳደግና የሀገር ውስጥ የምግብና ስነ ምግብ ፍላጎትን ለማሟላት ከሀይቆች፣ ግድቦች፣ ወንዞችና ሌሎች ትንንሽ የውሃ አካላት እንዲሁም አኳካልቸር ሲሆን ከዋናዋና ሃይቆች 39 ሺህ ቶን፣ ከግድቦችና ከትንንሽ የውሃ አካላት 68 ሺህ ቶን ከወንዞች 17 ሺህ ቶን እና በአኳካልቸር ላይ በሰራ ፈጠራና በግል ሴክተሩ በስፋት በማሳተፍ ምርቱን በ2017 መጨረሻ 2 ሺህ ቶን እንዲገኝ ይሰራል።

ሠ) የማር ሀብት ልማት

የማርና ሰም ምርትን ለማሳደግና ለሀገር ውስጥ ፍላጎት እና ለኤክስፖርት የማር ምርት በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 59 ሺህ ቶን በ2017 95 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል። የሰም ምርትን ደግሞ ከ5.5 ሺህ ቶን በ2017 7.5 ሺህ ቶን ለማድረስ ይሰራል። ስነምህዳርን መሰረት በማድረግ የማርና ሰምን ምርት ለማሳደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም ከአንድ ባህላዊ ቀፎ በአንድ ቆረጣ የሚገኝ በአማካይ የማር ምርትን በ2012 ዓ.ም ከደረሰበት 5.19 ኪ..ግ በ2017 ወደ 9 ኪ.ግ ለማድረስ ታቅዷል። የንብን ምርታማነት ለማሳደግ አሁን ያለዉን የባህላዊ ቀፎ ቁጥር በሂደት በየዓመቱ በአማካኝ በ15 በመቶ እንዲቀንስ በማድረግ ወደ ሽግግር ቀፎና ዘመናዊ ቀፎ ለማሸጋገር ይሰራል። ዘርፉን ለማዘመንና ሽግግር በማምጣት የአርሶአደሩን ግንዛቤ በማሳደግ እና የቴክኖሎጂ አቅርቦትን በማሻሻል በ2012 ዓ.ም 4 በመቶ የነበረው የተሻሻለ ዘመናዊና ሽግግር ቀፎ ድርሻ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ 13 በመቶ ድርሻ እንዲኖረው ይደረጋል።

ረ) የሐር ኩኩባ ሀብት ልማት

ይህ ዘርፍ ቀደም ሲል በስፋት ያልተሰራበትና ትኩረት ያልተሰጠው ሲሆን ሀገራችን ከምትከተለው የኢኮኖሚ እድገት አቅጣጫ እየተስፋፋ ላለው ኢንዱስትሪ በጥሬ እቃነትና በውጪ ገበያ ያለው ተፈላጊነት፣ የሀገራችን ስነ ምህዳር አመቺነት፣ ልማቱ በአነስተኛ መሬት ጉልበትና መነሻ ካፒታል የሚሰራ በመሆኑ፣ በገጠርም ሆነ በከተማ የስራ እድልን ለመፍጠር ማስቻሉና በተለያየ እድሜና ጾታ በሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ሊሰራ የሚችል በመሆኑና በአጭር ጊዜ ምርት በመስጠት የህብረተሰቡን ገቢ በማሻሻል ረገድ ያለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ 5 አመታት ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። የደረቅ የሐር ኩኩባ ምርትን በ2012 ዓም ከተደረሰበት 29.96 ቶን በእቅድ ዓመቱ መጨረሻ 48.24 ቶን ለማድረስ ይሰራል።

2.2.1.2 እንስሳትና ዓሳ ሀብት ዝርያ ማሻሻል

በአለማችን ላይ ብዙ የቤት እንስሳት ዘርና ዝርያዎች እንደሚገኙ ይታወቃል።ሀገራችንም ከፍተኛ የሆነ የእንስሳት የዝርያ ተለያይነት ከሚታይባቸው ሀገሮች አንዷ ናት። እነዚህም ተለያይ ዝርያዎች በአንድ አይነት አመጋገብና እንክብካቤ እንዲሁም የጤና አጠባበቅ እየተያዙ የምርታማነት ውጤት ልዩነት ያመጣሉ። ይህም ምክንያቱ በውስጣቸው ያለው ህብለ-በራሄ ቀመር ከዝርያ ዝርያ በጣም ስለሚለያይ ነው።ይህም የምርታማነት ውጤት ልዩነት በሀገር ውስጥ ዝርያዎችና በውጭ ሀገር ዝርያዎች መሀከል ጎልቶ ይታያል።ምንም እንኳን የውጭ ዝርያዎች ከፍተኛ ምርት በመስጠት የሚታወቁ ቢሆንም የኛም ሀገር ዝርያዎች የውጭ ዝርያዎች የሌሏቸው በጣም ጥሩና እምቅ ህብለ-በራሄ ክምችት (Potential use) እንዳላቸው ይታወቃል።

የዝርያ ማሻሻል ስራ ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ጉዳዮች ከግምት በማስገባት የሀገር ውስጥ ዝርያዎችን ምርታማነታቸውን ለመጨመር በመረጣና ከውጭ በመጣ ምርታማ ዝርያ በማዳቀል የሚከናወን ሲሆን ሂደቱም አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮችን በማገናዘብና ከአካባቢ አየር ንብረት ለውጥ ጋር ሳይጋጭ እንዲሁም እንስሳቱ የያዙትን በጊዜ ሂደት ሊገለጽና ተፈላጊነቱ ሊጨምር የሚችል በዝርያቸው የሚያገኙትን እምቅ ገፀ በረከት በማገናዘብ ዘመኑ የሚጠይቀውን የሀገር ውስጥ

የእንስሳት ብዝሀ ህይወት ጥበቃና ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲሁም በምግብ እራስን የመቻል መርህ እየጨመረ ካለው የሀገራት የህዝብ ቁጥር አንጻር የእንስሳት ምርትን ለምርታማነት በሚያወጡት ግብአት መጠን ምርታማነታቸውን በመረጣና ከውጭ በመጣ ምርታማ ዝርያ ጋር በማዳቀል ዝርያውን በማሻሻል ምርታማነቱን የማሳደግ ሂደት የሚያካትት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የእንስሳት ዝርያ ማሻሻል ስራ ውጤታማና ዘመን ተሸጋሪ እንዲሆን የራሱ ፖሊሲዎች፣ እስትራቴጂዎች፣ሕጎች፣ደንቦች እንዲሁም ፕሮግራሞች እንዲኖሩት ያስፈልጋል፡፡ለዚህም ምክንያቱ የሀገሪቱ እንዲሁም የአርቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ አቅም የእንስሳት ዝርያን አሻሽሎ እርባታን ለማዘመን እና ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን የግብአት አቅርቦት ጉዳዮች ከኢኮኖሚ አቅም ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለውና የሀገሪቱ ከፍተኛ የሆነ የስነ-መህዳር ልዩነት የዝርያ ማሻሻል ስራ ውጤታማነትን ስለሚወስን የሚወጡት ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች እንዲሁም ፕሮግራሞች ከእንስሳት ዘርፉ ለሚገኘው ውጤታማነት መሰረታዊ ጉዳዮች መሆናቸው አያጠራጥርም፡፡ በተጨማሪም ዝርያዎችን በተለያየ መልኩ ወደ ሀገራችን ያላግባብ ስናስገባ እንዲሁም ከሀገራችን ስናስወጣ፣ በሀገር ውስጥም ስናዘዋውር፣ የሀገራችን የእንስሳት ዝርያዎች በተፈጥሮአቸው ያገኙትን ልዩ ልዩ ተፈጥሮአዊ የበሽታ መቋቋም እና እምቅ የሆኑ ወደፊት በግዜ ሂደት ሊጠቅሙ የሚችሉ ባህርያት በእንደዚህ መልኩ በዘፈቀደ በሚደረግ የዝርያ ማሻሻል ስራ በውስጣቸው ያለው ህብለ-በራሄ ሊበረዝ፣ ሊሸረሸር እንዲሁም ሊጠፉና ልናጣቸው እንደምንችል የሚታወቅ ሲሆን በተለይ ድንበር ተሸጋሪና በዘር የሚተላለፉ በሽታዎችን በማምጣት አስኳል መንጋዎችን የማጥቃትና ተተኪ እንስሳትን በማሳጣት ትልቅ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ኪሳራ ከማምጣቱም አልፎ ሊቀለበስ በማይችል የዝርያ መሸርሸር፣ መበረዝ አልፎም መጥፋት አደጋ ውስጥ ሊያስገባ እንደሚችል በዘርፉ የተሰማሩ የተለያዩ መሁራን እየገለጹ ሲሆን አንዱ ካጣናቸው ደግሞ መልሰን ማግኘት እንደማንችል በሀገራችን ያለው የእንስሳት ብዝሀ ህይት አጠባበቅ ያለመጠናከር ለዚህ ማስረጃ ሊሆን ይችላል፡፡ለዚህም በጥልቀት ማሰብና የብዙ ሀገራትን ተሞክሮ መመልከት ለውጤታማነት እንደሚረዳ ይታወቃል፡፡

ስለሆነም በሀገራችን የሚገኙትን የለማዳ የቤት እንሰሳት ምርታማነተቸውን አሁን ካለበት ዝቅተኛ አፈጻጸም የዝርያ ማሻሻል ዘዴዎችን በመጠቀም ማለትም የሀገር ውስጥ ዝርያዎችን ስርጭታቸውን ብዛታቸውን በጥናት እንዲለዩ እንዲመረጡ እንዲባዙ እንዲጠበቁና በጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ ሲሆን በተጨማሪም እነዚሁኑ የሀገር ውስጥ ዝርያዎች እንዳስፈላጊነቱ በሚወጣው የዝርያ ማሻሻል ፕሮገራም መሰረት ለእያንዳንዱ እንሰሳት ዝርያ በምርታማነት ከታወቁ የውጭ እንሰሳት ጋር በማዳቀል ማባዛትና ማሰራጨት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም በምርትና በምርታመነታቸው የታወቁ እንስሳትን በመረጣ ወይም በድቀላ እንዳስፈላጊነቱ በሁለቱም አማራጮች የዝርያ ማሻሻል ሥራን በመስራት እና በሀገር ውስጥ የሚገኙት በምርት እና በምርታመነታቸው የተሻሉ እንስሳት ዝርያዎችን ብዛት፣ ሥርጭት እና ሌሎች ተፈላጊ ባህርያትን በመለየት በመገምገም በማጥናትና በማባዛት ማሰራጨት የሚሰራ ይሆናል፡፡

2.2.1.3 የእንስሳትና ዓሳ መኖ ልማት

የእንስሳት ሀብት ልማት ውጤማ ከሚያደረጉት ግብዓቶች አንዱና ዋነኛ ጥራቱን የጠበቀ የመኖ አቅርቦት በመሆኑ በሚቀጥሉት 5 አመታት የመኖን አቅርቦት በጥራት እና በዘላቂነት ለማቅረብ በትኩረት ይሰራል፡፡ በዚህም መሰረት የተፈጥሮ ግጦሽና ሬንጅ ላንድ ምርታማነትን ማሳደግ፣ የእንስሳት መኖ ልማትን ከተፋሰስ ልማት ጋር ማስተሳሰር ፣ የመኖ ዘር አቅርቦትን ማሻሻል ፣ የሰብል ተረፈ ምርት አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል ፣ የእንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችን አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል ፣ የተለያዩ የማቆያ ዘዴዎች በመጠቀም የመኖ ብክነትን መቀነስ እና የተመጣጠነ መኖ አቅርቦትን ማሳደግ ላይ በተኩረት ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

የተፈጥሮ ግጦሽና ሬንጅ ላንድ ምርታማነትን ማሳደግ

የግጦሽ መሬትን ከማሻሻል አንፃር ከሰውና ከእንሰሳት ተከልለው እንዲቆዩ በማድረግ የሳር ምርታቸው እንዲሻሻል ማድረግ፣ የሚፈልገውን ግብዓት (ዘር፤ ማዳበሪያ እና ኮምፖስት) ማቅረብ፣ በላዩ ላይ መዝራት (over sowing) ፣ አረም ማረም፣ በሌላ መኖ እጽዋት መተካት፣ ምቹ ቴክኖሎጂዎችን

በመምረጥ እንዲስፋፋ ማድረግ፣ የወል ግጦሽ መሬትን አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መዘርጋት፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ያለዉን ተሞክሮ ማስፋት ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የግጦሽ መሬት ለረጅም ዘመናት ሲጋጥና የአፈሩ ለምነት እጅግ አናሳ በመሆኑ በእንስሳት በማይበሉ፣ የንጥረ ነገር ይዞታቸዉ ደካማ የሆነ የመኖ ሳሮችና አረሞች እየተወረረ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የግጦሽ መሬት የአፈርና ዉሃ ጥበቃ ስራዎች፣ የአረም ማስወገድ ሥራ ህብረሰቡን ባሣተፈ መልኩ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም የተጋጡ መሬቶች እንዲያገግሙ ይደረጋል፡፡ ከዚህም ሌላ የግጦሽ ቦታውን የአፈር ለምነት ለመመለስ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተፈጥሮ ግጦሽ መሬትን የተሻሻሉ የመኖ እፅዋት ዘሮች በመዝራት/ በመትከል አፈሩ ላይ የሚደርሰውን መደህየት በማሻሻል የእፅዋት ሽፋኑ እና ምርታማነቱን ለማሻሻል ይሰራል፡፡ ይህንን ስራ ለመስራት በቅድሚያ የግጦሽ ቦታ የሚገኝበት ስነ-ምህዳር፣ ለስነ ምህዳሩ ተስማሚ የሚሆኑ የተሻሻሉ የመኖ እፅዋትን፣ የአፈሩን አይነት፣ ምን አይነት የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ የመለየት ሥራ ይሰራል፡፡

በአርብቶ አደር አካባቢ በመጤ አረሞች በተለይም በፕሮሶፒስ የተወረሩ የግጦሽ መሬቶች በማጽዳት ወደ መኖ ልማት እንዲገባ ይደረጋል፡፡ ለዚህ ግብ ተፈፃሚነት የፕሮሶፒስ ቁጥጥር ሥትራቴጂ ላይ ፕሮሶፒስ ለኢነርጂ ምንጭነት ለመጠቀም ያለዉ እንቅስቃሴ በብቃት መምራት፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግና በቁጥጥሩ ስራ እንዲሳተፉ የንቅናቄ ስነድ በማዘጋጀት ማነሳሳት፣ ለቁጥጥር ስራ የሚውል ቴክኖሎጂ ማቅረብ (ለምሳሌ ማሽነሪ) ፣ የጸዳ መሬት ወደ መኖ ልማት ለማስገባት የሚያስፈልግ ግብዓት ማቅረብ፣ ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

ትርፍ መኖ የሚመረትባቸውን አካባቢዎች በመለየት መኖውን በወቅቱ አሰባስቦ ለገበያ ለማቅረብ ሴቶችንና ወጣቶች እንዲሁም አርሶ/አርብቶ አደሩን የማደራጀት ስራ እና በመኖ አመራረት፣ አያያዝ፣ አመጋገብና መኖውን እንዴት ከገበያ ጋር ማስተሳሰር እንደሚቻል ለአርሶ/አርብቶ አደሩ በቂ ግንዛቤ እንዲኖርው የተጠናከረ የኤክስቴንሽን ስራ ይሰራል፡፡ በተጨማሪም የተመረተዉን መኖ ወደ ገበያ ለማቅረብ እንዲችሉ የማሽነሪ አቅርቦትን ማሻሻልና ክልሎች መሰረታዊ የሆኑ ማሽነሪዎች (ትራክተር፣ ቤለር፣ ማጨጃ) እንዲኖራቸዉ ድጋፍ ይደረጋል፡፡ የግል ባለሃብቱ በሰፋፊና ዘመናዊ መኖ ልማት በተለይም በመስኖ መኖ ልማት እንዲሰማራ እና መኖን አምርቶ ለገበያ እንዲያቀርብ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

በአርብቶ አደር አካባቢዎች በመንደር የተሰባሰቡ አርብቶ አደሮችን በጓሮ መኖ ልማት ስራ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋፋት፣ የአርብቶ አደር የኤክስቴንሽን ስርዓት መዘርጋት፣ የውሃ ልማትን መሰረት ያደረገ መኖ ልማትና የእንስሳት መጠጥ ውሃ ተደራሽነት ማሻሻል፣ የምርምር ማዕከላትን ዓቅም በመጠቀም ቀጣይ የግብዓት አቅርቦት (የመኖ ዘር) ማሻሻል፣ የመኖ ባንክ በተለያዩ ቦታዎች ማልማት፣ የመስኖ መሰረተ ልማት እና በመስኖ የመልማት ዓቅም ያላቸው አካባቢዎችን በመለየት መኖ አልምተው ለራሳቸው የሚጠቀሙበትንና ለገበያ የሚያቀርቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት ተጠቃሚ ማድረግ፡፡

በአርብቶ አደር አካባቢ ያለውን የመኖ እጥረት በመቅረፍ ድርቅን የሚቋቋም የእንስሳት ሀብት ልማት ለማስፋፋት በተለያዩ አካባቢዎች በመስኖ ከሚለሙ የመኖ ባንኮች መኖን በድርቆሽ መልክ በማሰባሰብ ማከማቸት፣ የሞላሰስ ማጠራቀሚያ የኮንክሪት ታንከሮችን መገንባት፣ የእንስሳት መጠጥ ውሃ ተደራሽነት ለማሻሻል የሚያስችሉ ስራዎች ይሰራል፡፡

የእንስሳት መኖ ልማትን ከተፋሰስ ልማት ጋር ማስተሳሰር

ተፋሰስን መሰረት ካደረገው የተፈጥሮ ሀብት ልማት እየተስፋፋ ካለው የመስኖ ልማት ጋር በማስተሳሰር መኖ የማልማት ስራ በስፋት ይከናወናል፡፡ እንዲያገግሙ የተከለሉ ቦታዎች ፈጥነው እንዲያገግሙ በተሻሻለ የመኖ እፅዋት አንዲሸፈኑ ማድረግ፣ አርሶ/አርብቶ አደሩ ከዚህ የሚገኘውን መኖ አጭዶ ለእንስሳቱ እንዲመግብ ማድረግ፣ የተደራጁ ሴቶችና ወጣቶች በተፋሰሱ ውስጥ የለማውን መኖ በአረንጓዴነቱ ወይም በድርቆሽ መልክ ለገበያ እንዲያቀርቡና የንብ ማነብ ስራ ላይ እንዲሰማሩ የሚያስችል የአክስቴንሽን አገልግሎትና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

በተፋሰሱ ውስጥ በተሰሩ ስትራክቸሮች ላይ በሚካሄደው የስነ ህይወታዊ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ስራ አብዛኛው በመኖ ዕፅዋቶች እንዲሸፈኑ የመኖ ዘር፣ ችግኞችና ቁርጥራጮች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ግብዓቶች ብዜትና አቅርቦት የስራ ቦታን በማመቻቸት ሴቶችና ወጣቶች በስራው እንዲሳተፉ አስፈላጊው የብድር፣ የስልጠና እና የተጠናከረ የኤክስቴንሽን ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በተፋሰሱ በሚዘረጉ የመስኖ ልማት አውታሮች የሚጠቀሙ አርሶ/አርብቶ አደሮች ከሚያካሂዱት የሰብል ልማት ጎን ለጎን ምርታማ የሆኑ የተሻሻሉ የመኖ እፅዋቶችን እንዲያለሙ አስፈላጊው የግብዓት አቅርቦትና የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የመኖ ዘር አቅርቦትን ማሻሻል

ለተለያዩ ስነምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ የመኖ ዕፅዋት ዘሮችን አቅርቦት ለማሳደግ መስራች ዘሮች በምርምር ማእከላት እንዲወጡ በማድረግ የፌዴራልና የክልል ምርጥ ዘር ድርጅት/ኢንተርፕራይዞች፣ በክለስተር በተመረጡ አርሶ/አርብቶ አደሮች ማሳ ላይ እና በግል ባለሀብቶች የዘር ማባዛት ስራ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የመኖ ዘር ብዜትና ስርጭቱ በኮንትራት ውል ተመርቶ እንዲቀርብ ማድረግ አንድ አማራጭ ተደርጎ የሚወሰድ ሲሆን በልማቱ ለሚሳተፉ ተዋንያን የክህሎት ክፍተት ማሟያ ስልጠናና በዘር ዝግጅት የሚፈለጉ የብድር፣ የማቴርያልና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል፡ የመኖ ዘር በወቅቱ እንዲቀርብ የቀጥታ ዘር ስርጭት ስርዓት በሁሉም ክልሎችና አካባቢዎች በሂደት እየሰፋ እንዲሄድ ይደረጋል፡፡ የጎብረት ሥራ ማህበራት ለአባል አርሶ/አርብቶ አደሮች የሚፈለገውን የመኖ ዘር እና ሌሎች ግብዓቶች በወቅቱ አጓጉዘው ማከማቸት እንዲችሉ ያለባቸው የመጋዘን ክፍተት በጥናት ተለይቶ እንዲያሟሉ ይደረጋል፡፡

የሰብል ተረፈ ምርት አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል

ከሰብል ምርት ጭማሪ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ከፍተኛ የሰብል ተረፈ-ምርት አሰባሰብ፣ ክምችትና አያያዝ እንዲሁም የንጥረ መኖ ይዘትና ተበይነትን ማሻሻል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡ ይህን ለማሳካት በተረፈ ምርት አጠቃቀም ዙሪያ ያለውን ተሞክሮ በመቀመርና በማስፋፋት እንዲሁም አስፈላጊውን ግብዓት በማቅረብና ክህሎት በማሳደግ የሚሰራ ይሆናል፡፡

የእንዱስትሪ ተረፈ ምርቶችን አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል

የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች ከስኳር ልማት፣ ከቢራ ፋብሪካ፣ ከዘይት መጭመቂያ፣ ከዱቄት ፋብሪካዎችና ሌሎች የሚገኘውን ተረፈ ምርት (ሞላሰስ እና ባጋስ፣ የቢራ ብቅልና አተላ፣ የዘይት ፋጉሎ፣ የዱኬት ፉርሽካና ፉርሽኬሎ) ማሰባሰብ፣ ማከማቸት፣ አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በማቅረብና ተግባራዊ በማድረግ ለመኖ አቅርቦት አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ይደረጋል፡፡ የኢንዱስትሪ ተረፈ ምርት በተለይም የስኳር ፋብሪካዎች ባሉባቸው አካባቢዎች የእንስሳት ልማት ኮሪደሮች (ክላስተር) በመፍጠር በዙሪያቸው ያሉ አርሶ/አርብቶ አደሮችና ሌሎች የህብረተሰቡ ክፍሎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ለዚህም እንዲረዳ ከአግሮ ፕሮሰሲንግ የሚገኙ ተረፈ ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው ለእንስሳት ሃብት ልማቱ ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል የአቅርቦት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡የቅባት እህሎች ማለትም ሰሊጥ፣ ኑግ፣ ተልባ፣ አቾሎኒና የመሳሰሉትን በሀገር ውስጥ ወደ ምግብ ዘይት የሚያቀናብሩትን ማበረታት ተረፈምርቶቹን ለእንስሳት መኖ ግብአትነት ከመጠቀም አንፃር ከፍተኛ አስተዋጽዎ ስለሚኖረው እነኝህን ሰብሎች ለሚያቀናብሩ ኢንዱስትሪዎችና የግል ባለሀብቶች ልዩ ድጋፍ በማድረግ ከዘርፉ ተጠቃሚ ለመሆን ይሰራል፡፡ ሴቶችንና ወጣቶችን በማሰልጠንና በማደራጀት ዩሪያ-ሞላሰስና የመዓድናት አሞሌ፣ የተቀነባበረ መኖ ወዘተ ዝግጅትና ግብይት ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

የተለያዩ የማቆያ ዘዴዎች በመጠቀም የመኖ ብክነትን መቀነስ

አርሶ/አርብቶ አደሩ በበቂ እርጥበት ወቀት የሚኖረውን ትርፍ አረንጓዴ መኖን በድርቆሽ፣ በገፈራና የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም እንዲያከማችና የመኖ እጥረት በሚኖርበት ወቅት ለመጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂና የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ በአያያዝ ምክንያት የሚባክን

ተረፈ ምርት እንዲቀንስ በተረፈ ምርቱ አሰባሰብና አቀማመጥ የክህሎትና የእዉቀት ክፍተቶችን ለመሙላት የሚያስችል ሥራ ይሰራል፡፡

የተመጣጠነ መኖ አቅርቦትን ማሳደግ

ለተመጣጠነ መኖ የሚያስፈልገውን ግብዓት በቆሎ፣ አኩሪ አተር፣ ጨዉ እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርባት እንዲጨምር ከባለድርሻ አካላት በቅንጅት የሚሰራ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የግል ባለሃብቶችን በመኖ ልማት ምርት እንዲሰማሩ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ የመኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን አቅም በማሳደግና አዳዲስ ፋብሪካዎችን እንዲቋቋሙ ለባለሃብቶችና ለተማሩ ሴቶችንና ወጣቶችን በማደራጀት ወደ ስራ እንዲገቡ አስፈላጊዉ ድጋፍ ይደረጋል ፡፡ በተጨማሪም አርቢዉ በራሱ ቤት ዉስጥ ለእንሳት የሚያቀርበዉን መኖ አመጣጥኖ እንዲያቀርብ የቴክኖሎጂና የአቅም ግንባታ ድጋፍ ይደረጋል፡፡

የመኖ ምርትን ለመጨመረና ጥራቱን ለማሻሻል እንዲቻል ለአርሶ/አርብቶ አደሩ እና በዘርፉ ለተሰማሩ በመኖ አመራረት፣ አያያዝ፣ ንጥረ ነገር በማሻሻል እንዲሁም በአመጋገብ ዙሪያ ሰፊ የአቅም ግንባታ ስራ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለመኖ ቴክኖሎጂዎችና ግብዓት ስርጭትና ስርፀት ለማከነወን የሚያስችሉ ስልጠናዎችን በተዋረድ በመስጠትና የስርጭት ስልቶችን በመከተል ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በመኖ ምርት ማሻሻያ ፓኬጆች ላይ በተለያየ ደረጃ ለሚሳተፉ የዘርፉ ባለሙያዎች፣ አርሶ አርብቶ አደሮች፣ ሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በዘርፉ ለተሰማሩ እና ለሚሰማሩ በመኖ አመራረት፣ አዘገጃጀት እንዲሁም አመጋገብ ዙሪያ አቅም ግንባታና የኤክስቴንሽን ስራ ይሰራል፡፡

ከስኳር ፋብሪካዎች/ፕሮጀክቶች ሊገኝ የሚችለውን ተረፈ ምርት ደግሞ እንሰሳት በዘመናዊ መልኩ በማርባትና በማድለብ ለቁራዎች ለማቅረብ እንዲሁም በተለያዩ የእንሰሳት ተዋፅኦ ላይ ለሚሰማሩ የምርት ማቀነበቀበሪያ ፋብሪካዎች ለመገንባት ዕድል ሊሰጡ የሚችሉ ፋብሪካዎች ናቸው ፡፡ በእነዚህ ስኳር ፋብሪካዎች/ፕሮጀክቶች ዙሪያ የእንስሳት መኖ ልማትና ማቀነባበር፣ ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ፣ የማድለብና ለሌሎች የተለያዩ አግሮ ፕሮሲንግ ኢንዱስትሪዎች በእሴት ሰንሰለት በማስተሳሰር ሰፊ ልማት ለማልማት ይቻላል፡፡ ሌላው የስኳር ፋብሪካዎች/ ፕሮጀክቶች ባሉቸው አከባቢዎች የሚገኙ አርሶ/አርብቶ አደሮች እና የግል ባለሃብቶች ከላይ በተጠቀሱት የልማት አማራጭ ስራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ ተደጋጋፊና ተመጋጋቢ ብሎም ዘላቂ ልማት በስኳር ፋብሪካዎች አከባቢና በሃገር ደረጃ ማምጣት ብሎም ሃገሪቱ የተያያዘችውን ፈጣን ልማት ማስመዝገብ የምርጫ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ በመሆኑ እና ስራውን ውጤታማ ለማድረግ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከስኳር ኮርፖሬሽን ጋር በቅንጅት መስራት ሚያስችል ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

የእንስሳት ውሃ አቅርቦትን ማሳደግ

ሁሉም የእንሰሳት ሀብት ሥራዎች ከፍተኛ የውሃ አቅርቦትን ይጠይቃሉ፡፡ በመሆኑም የውሀ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች እና በአርብቶ አደር አካባቢዎች በመንደር ለተሰባሰቡ አርብቶ አደሮችን የሚያስፈልገውን የውሃ መጠን ለማሟላት የሚያስችል የውሃ መገኛ አማራጭ ማዘጋጀት የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡ ለዚህም ተመራጭ የሚሆነው አርሶ/አርብቶ አደሩ አነስተኛ የውሀ ማሰባሰቢያ ኩሬዎችን በራሱ በመስራት እና በተጨማሪም በቂ ውሀ ከሚገኝበት አካባቢ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን በማሟላት ወደ ተጠቃሚው እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ከዚህ ሌላ የውሀ አጠቃቀምን መሰረት ያደረገ የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግ፣ ምርጥ ተሞክሮ መቀመርና ማስፋፋት፣ የአርብቶ አደር የኤክስቴንሽን ስርዓት መዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡

2.2.1.4 የእንስሳትና ዓሳ ጤና አገልግሎት

የእንስሳት በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት ማሳደግ የእንስሳትና አሳ ሃብት ምርትና ምርትማነት ለማሻሻል ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱና ዋነኛ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የእንስሳት ጤና ክሊኒክ አገልግሎት ሽፍንና ተደራሽነትን ማሳደግ፣ በመከላከል ላይ ያተኮረ የእንስሳት ጤና ስርዓትን ማጠናከር፣ የተለየ ትኩረት የሚፈልጉ ተላላፊና ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ መከላከልና መቆጣጠር ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የሚከናወን ሲሆን ለዚህም የበሽታ ዳሰሳ እና ቅንኝት

ስርዓትና የጤና ላቦራቶሪ ምርመራና ምርምር ለማጠናከር አቅጣጫ ተቀምጧል። በተጨማሪ የእንስሳት ደህንነት አጠባበቅ ላይ ተጠናክሮ ይሰራል።

ሀ) የእንስሳት ጤና ክሊኒክ አገልግሎት ሽፍንና ተደራሽነትን ማሳደግ

አገራችን የእንስሳትና አሳ ሀብት አንጻር የተደራጀ እና ብቃት ያለው የእንስሳት ጤና አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑ ቢታመንበትም በአሁኑ ጊዜ ያለው የእንስሳት ጤና አገልግሎት በጥራትም ሆነ በተደራሽነት ከበቂ በታች ነው። ይህም የሆነበት ዋና ዋና ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ በመንግስት የሚሰጠው አገልግሎት ያልተናበበ እና ያልተቀናጀ አደረጃጀት የተከተለ መሆኑና ዘርፉ የሚጠይቀውንም ዓለም አቀፍ መስፈርት በሚገባ ያላሟላ፣ የግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት ባለመዳበሩና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማጠናከር አስፈላጊ የሆነው የፖሊሲ ማዕቀፍና የማበረታቻ ፓኬጅ አለመዘጋጀቱ፣ አዳዲስ የእንስሳት ህክምና ምሩቃን ወደ ልማት ስራው እንዲገቡ የሚያስችል የስራ ፈጠራና ባለሙያዎች ስምሪት ስትራቴጂ ባለመኖሩ፣ የተለያዩ የህግ ማዕቀፎች እና ስትራቴጂዎች ቢኖሩም ወቅታዊነት የሚጎላቸውና በረቂቅነት ደረጃ የሚገኙ እና ተገቢው ፕሮግራም ተቀርጾ ወደ ተግባራዊነት እንቅስቃሴ ያልተገባባቸው መሆኑ ይጠቀሳሉ። በመሆኑም በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የክሊኒኮች ደረጃ እና ስታንዳርድ ማሳደግ፣ ተዘዋዋሪ የእንስሳት ጤና ፈንድ አሰራርን ማጠናከርና ማስፋት፣ የእንስሳት ጤና ራሽናላይዜሽን ፍኖተ ካርታን መተግበር፣ የእንስሳት ጤና ምክር ቤትን (Vet. Statutory Body) ማቋቋም እና መተግበር እና የአርብቶ አደር አካባቢ የተለየ የእንስሳት ጤና ስትራቴጅ መተግበር ላይ በትኩረት ለመተግበር አቅጣጫ ተቀምጧል።

የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች ደረጃ እና ስታንዳርድ ማሳደግ

በክሊኒክ ላይ የተመሰረት የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፍንን ለማሳደግ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በመንግስትና በግል ዘርፍ በቅንጅት የሚተገበር ይሆናል። በመሆኑም በክሊኒክ ላይ የተመሰረተ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተደራሽነትን በ2012 ከደረሰበት 83 በመቶ ወደ 90 በመቶ ለማሳደግ አቅጣጫ ተቀምጧል። ከዚህም ውስጥ የግል ዘረፉ ድርሻ 35 በመቶ እንዲሸፍን ኢላማ የተቀመጠ ሲሆን የመንግስት 55 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን ጥራት ማሻሻል ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል። በተጨማሪም የእንስሳት ጤና ክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓትን በማጠናከር የኢትዮጵያ እንስሳት ጤና አገልግሎት ምዘና በ2003 ከደረሰበት 2.65/5 እና በ2012 ከተገመተው 3.0/5 በማሳዳደግ በሚቀጥሉት 5 አመታት 3.25/5 ለማድረስ ኢላማ ተቀምጧል።

ጥራቱን የጠበቀና ዘመናዊ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፍንና ተደራሽነትን በበቂ ደረጃ ለማሳደግ ከባለድርሻ አካለትና ከሌሎች የልማት አጋሮች ጋር የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክሮ ይቀጥላሉ። በተለይም ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ሀሳቦችን በማመንጨት ሰፊውን ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ፤ ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ የመንግስት ሃላፊዎች ጋር በችግሮቹና በመፍትሄዎቻቸው ዙሪያ ግልጽ የውይይት መድረኮችን ደረጃ በደረጃ መፍጠር እንዲሁም የተነሱት ጉዳዮችና የዉይይት መድረኮቹ የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኙ ጥረት ይደረጋል። በመንግስት የተገነቡና አዲስ የሚገነቡ የእንስሳት ጤና ክሊኒኮች አስፈላጊውን የሰለጠነ የሰው ሀይል፣ የቁሳቁስ፣ ሎጅስትክስና በቂ በጀት እና ግብዓት በዘላቅነት መመደብ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል የተዘጋጁ የክሊኒኮች ደረጃ እና ስታንዳርድ ኦፕሬትንግ ፕሮሲጀር (SOP) ሰነዶችን በፌዴራልና በክልሎች አስገምግሞ በማጸደቅ፣ ማሳተምና እስክ ቀበሌ ድረስ በማዉረድ በማስተዋወቅና ስልጠና በመስጠት እንዲተገበሩ አስፈላጊዉን ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል። ይህም አሰራር በመጀመሪያ በተወሰኑ ክሊኒኮችን በሞዴልነት እንዲተገብሩት አስፈላጊዉን የሰዉኃይል፣ በጀት፣ ግብዓትና ሎጂስትክስ በተሟላ መልኩ በመመደብ ስልጠና በመስጠትና ክትትል፣ ግምገማ በማድረግ የተገኘ መልካም ተሞክሮ በመቀመር ወደ ሌሎች ክሊኒኮች ማስፍት ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል። በሌላ በኩል ደግሞ የባለሙያዎችን ሙያዊ ክህሎትና ዕዉቀት ለማሳደግ የተከታታይ ስልጠና እና ምዘና ስርዓትን መዘርጋት በትኩረት ይተገበራል። በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት በጥናት የተለዩ ተከታታይ ክህሎትና ዕዉቀት መዳበርያ ስልጠና ፍላጎቶችንና ክፍተቶችን መሰረት ያደረጉ

የተለያዩ ስልጠና ሞጁሎችን በማዘጋጀት በአቅራብያዉ ካለዉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር በመቀናጀት ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የተከታትይ ስልጠና ይሰጣል፡፡

ተዘዋዋሪ የእንስሳት ጤና ፈንድ አሰራርን ማጠናከርና ማስፋት

አሁን ያለዉን ከፍተኛ የሆነ የክሊኒኮች የበጀት እና የግብዓት አቅርቦት እጥረትን በዘላቅነት ለመፍታት በሀገር ደረጃ እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ ሊተገበር የሚችልና ከዚህ በፊት በአንዳንድ ክልሎች ተጀምሮ ዉጤታማነቱ የተረጋገጠ የክሊኒኮች የተዘዋዋሪ ፈንድ አስተዳደር ስርዓት እና የመድሃኒት እና የሌሎች ግብዓት አቅርቦት አሰራር ስርዓትን በማጠናከርና በማስፍት በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት በሀገር ደረጃ አንድ ወጥ የሆነ የተዘዋዋር ፈንድ አሰተዳደር ስረዓት ለመተግበር የተዘጋጀዉን ማኑዋል በማስጸደቅ ሁሉም ክልሎች እንዲተገብሩት ይደረጋል፡፡

የእንስሳት ጤና ራሽናላይዜሽን ፍኖተ ካርታን መተግበር

የእንስሳት ጤና ክሊኒክ አገልግሎት ሽፋንን ለማሻሻልና የግል ሴክተሩን ተሳተፎ ለማሳደግ የእንስሳት ጤና ራሽናላይዜሽን ፍኖተ ካርታን በመተግባር ለግል ሴክተሩ ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠር አገልግሎቱን በሂደት ለግል ሴክተሩ መልቀቅ ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት በመንግስትና በግል ትብብረ እንዲሁም በግሉ ሰክቱር ብቻ ሊሰሩ የሚችሉ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ተግባራት ላይ በትኩረት ይሰራል፡፡ የፍኖተ ካርታውን ተፈጻሚነት ለመደገፍ ሲባል የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣ ማስጸደቅና በመተግበር አሰቻይ ሁኔታዎችን እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡ ለግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሰጪዎችም የፋይናንስ አቅረቦት ማመቻቸትና ሌሎች የማበረታቻ ፓኬጆችን ማዘጋጀትና መተግበር በትኩረት ይሰራል፡፡ ይህም አዳዲስ የእንስሳት ሕክምና ምሩቃን ወደ ግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት ስራ እንዲገቡ የሚያስችል በመሆኑ በትኩረት ይተገበራል፡፡ ለዚህም የፈጠራና ባለሙያዎች ስምሪት ስትራቴጂ ይዘጋጃል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ የህግ ማዕቀፎችን እና ስትራቴጂዎች አስፈላጊ ሆነው ሲታመንባቸው ይደራጃል፡፡ በተለይም በከተሞች እና ዘመናዊ የእንስሳት እረባታ በብዛት የሚካሄድባቸዉ አካባቢዎች መንግስት የክሊኒክ አገልግሎቱን ለግል የእንስሰት ጤና ባለሙያዎች እና ስራ ፈጥሪዎች እንዲለቅ ይመቻቻል፡፡

የእንስሳት ጤና ምክር ቤትን (Vet. Statutory Body) ማቋቋም እና መተግበር

የእንሰሳት ጤናም ሆነ አጠቃላይ የእንስሳት ሀብት ዘርፍ አደረጃጀት ከፌደራል እስከ ወረዳ ድረስ በአግባቡ ተፈትሾ፣ ምክክር ተደርጎበት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ማሻሻያ እንዲደረግበት በትኩረት ይሰራል፡፡ በሌላ በኩል በእንስሳት ጤና አገልግሎት ለግሉ ዘርፍ የተሰጠውን አነስተኛ ትኩረት እንዲሻሻል፣ እንዲሁም ይህንን ጉዳይ ለማስፈጸም የተዘጋጁ ሰነዶች እንዲጸድቁ እና ወደ ስራ እንዲገባ በትኩረት ይሰራል፡፡ መንግስት የእንስሳት ጤና ሙያተኞችን ለማሰልጠንም ሆነ የተለያዩ ተቋማትን ለመክፈት እያደረገ ያለዉ ጥረት ከፍተኛ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የመንግስትም ሆነ የግል የእንስሳት ጤና ሙያተኞች አገልግሎቱ እና ተቋማቱም ጭምር በከፍተኛ ቁጥጥር እንዲሰሩ፣ ሙያዊ ብቃት እና ስነ-ምግባር ተላብሰው እንዲያገለግሉ ለማድረግ በሁሉም የዓለም ክፍሎች የሚሰራበትን የህግ ማዕቀፍ እና ተቋም ማለትም የእንስሳት ጤና ምክር ቤት (veterinary statutory body) እንዲደራጅ በትኩረት ይሰራል፡፡

የእንስሳት ጤና ሕግ ማዕቀፎችን ማስጸደቅና መተግበር

የእንስሳት ጤና አገልግሎት አሰጣጡ በሥርዓት ላይ የተመሰረተ አንዲሆን ከማድረግና የተቀባይ አገሮችን አመኔታ ከማግኘት አንጻር ጠንካራ የህግ መሰረት እንዲኖረዉ ማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡ በዚህ መሰረት በዕቅድ ዘመኑ አንድ የእንስሳት ጤናና ደህንነት አዋጅ እና 7 ደንቦች (የእንስሳት በሽታዎችን መከላከል፣ መቆጣጠርና ማጥፋት፤ የገቢ፣ ወጪና ተላላፊ እንስሳትና ውጤቶች መቆጣጠሪያ፤ የእንስሳት ጤና ሙያና ሙያተኛውን መቆጣጠሪያ፤ የእንስሳትና ውጤቶች ልየታ፣ ምዝገባና ክትትል፣ የላብራቶር ምርመራ አገልግሎት አሰጣጥ፣ የመጀመሪያ ደረጃ እንስሳት ምርቶች ደህንነት እና የእንስሳት ደህንነትና ባለቤት አልባ እንስሳትን መቆጣጠሪያ) ማዘጋጀት፤ ነባሮቹን የመከለስና የማዕደቅ ሥራ ይሠራል፤ የፀደቁትንም ወደ ስራ መተግበር በትኩረት ይሰራል፡፡

የአርብቶ አደር አካባቢ የእንስሳት ጤና ስትራቴጂ መተግበር

ከዚህ በፊት ተዘጋጅቶ የጸደቀዉ ለአርብቶ አደር አካባቢ ተስማሚ የሆነ የእንስሰት ጤና አግልግሎት ስትራቴጂ የሚተገበር ይሆናል። በመጀመሪያ ስትራቴጂዉ ከአርብቶ አደር አካባቢዎችና ባለድረሻዎች ጋር የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፤ ቀጥሎም በስትራቴጂዉ ዉስጥ የተቀመጡትን ዋና ዋና ተግባራት ለመፈጸም ዕቅድ በማዉጣት እንዲተገበሩ ድጋፍ ይደረጋል። ስትራቴጂዉ በተመረጡ ሞዴል ክሊኒኮች በሙከራ ደረጃ ከተተገበረ በኋላ የሙከራ ውጤቱና ተሞክሮ በማካተት ወደ ለሌሎች ክሊኒኮቸ በስፋት እንዲተገበር ይደረጋል።

ለ) በመከላከል ላይ ያተኮረ የእንስሳት ጤና ስርዓትን ማጠናከር

በመከላከል ላይ ያተኮረ የእንስሳት ጤና ሥርዓትን በማጠናከር በተለዩት አካባቢዎች አጠቃላይ የክትባት አገልግሎት ሽፋን አሁን ካለበት 89.5 በመቶ በማሰደግ በ2017 መጨረሻ ወደ 92.5 በመቶ ማድረስ ይሆናል። ከዘህ ዉስጥም በስጋት ላይ የተመሰረተ የድንበር ዘለል በሽታዎች የክትባት አገልግሎት ሽፋን በ2012 ዓመት መጨረሻ ከደረሰበት 85 በመቶ በማሳደግ በ2017 መጨረሻ 90 በመቶ ለማድረስ ይሰራል። በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀና ጥራት ያለው የእንስሳት በሽታ መከላከያ ክትባት ዓመታዊ የምርት መጠንና ዓይነት አሁን ካለበት 365.34 ሚሊዮን ዶዝ በ2017 መጨረሻ 567 ሚሊዮን ዶዝ ለማድረስ ኢላማ ተቀምጧል።

ስኬታማ የሆነ የበሽታ መከላከል ስርዓትን ለማከናወን በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የዋና ዋና ድንበር ዘለል በሽታዎች ሥርጭት የሚያሳይ ካርታ ይዘጋጃል። እንደ አመቺነቱ በእያንዳንዱ ክልል (ዞን/ወረዳ) የክትባት ካሌንድር እንዲወጣ ይደረጋል። በቂ በጀት በማስመደብ የሚያስፈልገውን የክትባት ዓይነትና መጠን ከብሄራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲቲዩትና ሌሎች ክትባት አምራች ኩባንያዎች ጋር ምርት ውለታ በፈጠር ይመረታል። ከዚህ በፊት በብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሺን ድጋፍ በተለያዩ ማዕከላዊ የሆኑ የሀገርቱ ክፍሎች ዉስጥ ተገንብቶ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያት ርክክብ ያልተደርገባቸዉና አገልግሎት ለመስጠት ያልበቁትን 16 የክትባት ማከማች ዴፖቶችን በመረከብ አስፈላጊዉን እደሳት በማድረግ እና ቁሳቁሶችን በሚሟላት ወደ ሥራ እንድገቡ ይደረጋል። በተጨማርም በየክልሉ ማዕከላዊ በሆኑ ቦታዎች (በዞን አንድ) የክትባት ዴፖዎችን በመገንባትና በአገር ውስጥ የማይመረቱና በበቂ መጠን የማይገኙ ክትባቶችን አቅርቦት በተመለከተ ሃላፊነት በተሰጠው አካል ሲረጋገጥ በአቅራቢዎች ወይም አቅራቢዎች ሊገቡ ባልቻሉበት ሁኔታ በብሔራዊ እንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስትቲዩት በኩል እንዲገቡ በማመቻቸት ዋና ዋና ድንበር ዘለል በሽታዎችን በክትባት መከላከልና የካራንቲንና ባዮሴኩሪቲ ሥርዓታችንን በማጠናከር ይሰራል። በሌላ በኩል የመንግስት እና ግል ዘረፍን ትብብር በማጠናከር ዉጤታማ የሆነና በክትባት ላይ የተመሰረተ የድንበር ዘለል በሽታዎች መካላከል ለግል የእንስሳት ጤና አገልገሎት የሳኒተሪ ኮንትራት ዉል በመስጠት እንዲተገበር ይደረጋል።

ሐ) የተለየ ትኩረት የሚፈልጉ ተላላፊና ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታ መከላከልና መቆጣጠር

በእንስሳት ዘርፍ የወጪ ንግድ ገቢን ለማሳደግ የተቀመጠውን ኢላማ ለማሳካት የተቀባት ሀገራት የሰሳቴራ-ፋይቶሳኒቴር ደንቦችን እና የዓለም ንግድ ድርጅት መርህዎችን ለሚሟላት የሀገራችንን የእንስሳት ጤና አገልግሎት ጥራትና ተደራሽነትንና የዋና ዋና ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችን ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ የቁጥጥር ስትራቴጂ በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ። በአጠቃላይ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎች ቁጥጥር በተመረጡ 19 በሽታዎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ከዚህም ዉስጥ ቅድምያ የሚሰጣቸዉ በሽታዎችን በመለየት ልዩ ትኩረት በመስጠት የቁጥጥር ሥራ ተግባራዊ ይደረጋል። በተጨማሪም በከፍተኛ ተላላፊ የሆኑ በሽታዎች በተለይም የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መከላከል ላይ በትኩረት ይሰራል።

የአፍተግር (FMD) እና የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታ (PPR) መከላከልና መቆጣጠር ስትራቴጅዎችን በተቀናጀ መልክ መተግበር

የእንስሳት የውጪ ገበያን ለማሳደግ እንደ አፈተግረ (FMD) ያሉ ለዉጭ ገበያ መዳረሻ ከፍተኛ ማነቆ የሆኑ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችን ከፍተኛ ስርጭት መኖር በተደራጀ መልኩ መቆጣጠር

እስፈላጊ ቢሆንም በዚህ ረገድ የተለያዩ ስትራቴጂዎች እና ልሎች ሰነዶች ቢኖሩም ተገቢው ፕሮግራም ተቀርጾ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሳይገባ ቆይቷል። ስለዚህ በርካታ እንስሳት ላኪ ሀገራት ፖሊሲያቸውንና አሰራራቸውን በመከለስ ላያ ይገኛሉ። ይህም በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ከፍተኛ የሆነ አውንታዊ ተጽዕኖ የሚኖረዉ ይሆናል። በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በሀገራችንም የአፍተግር (FMD) እና የበጎችና ፍየሎች ደስታ መሰል በሽታን (PPR) የመከላከልና መቆጣጠር ተግባር የተለየ ትኩርት ተሰጥቶት የሚተገበር ይሆናል። ለዚህም ባለፉት 5 ዓመታት በተመረጡ አርብቶ አደር አካባቢዎች የተሞከረው የአፍተዕግር በሽታና እና የደስታ መሰል የበጎችና ፍየሎች በሽታን ለመቆጣጠርና የሚያስከትሉ ተጽኖዎችን ለመቀነስ አገራዊ የቁጥጥር ስትራቴጂ መልካም ተሞክሮ በማስፋት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በሁሉም የሀገሪቱ ክፈሎች የደስታ መሰል በሽታ (PPR)ቁጥጥር በስትራቴጂዉ መሰረት የሚከናወን ይሆናል።

የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ ቁጥጥር

በአገራችን ስራ ላይ ውለው ውጤታማ የሆኑና በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ዝቅተኛ መሆናቸው የተረጋገጡ ቴክኖሎጂዎችን በማቀናጀትና ህብረተሰቡን በማሳተፍ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር ስራ ይሰራል። በገንዲ በሽታ ለታመሙ እንስሳት ህክምና መስጠት የመሳሰሉትን ቴክኖሎጂዎች የየክልሉን የቆላ ዝንብና የገንዲ በሽታ ስርጭት፣ የመሬት አቀማመጥና አመቺነት መሰረት በማድረግ እንዳስፈላጊነታቸው አቀናጅቶ በመጠቀም ይሰራል። በተጨማሪም ከፍተኛ ቅነሳ በተካሄደባቸው አካባቢዎች የቆላ ዝንቦችን በብዛትና በጥራት በማራባትና የመከኑ ወንድ የቆላ ዝንቦችን ቁጥጥር በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በመልቀቅ የዝንቦችን የህይወት ዑደት የመቁረጥ የማጥፋት ስራ ይሰራል።

በዚህም መሰረት በቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ የተወረሩ የአገሪቱ አካባቢዎችን በማጽዳት ከቆላ ዝንብ ወረራ የጸዳ መሬት ስፋት በ2012 ካደረሰበት 96200 ካ.ኪ.ሜ በ2017 መጨረሻ ዓመት 10476ካ.ኪ.ሜ ማድረስ እንዲሁም ቀድሞ የቆላ ዝንብ ቁጥጥር የተደረገበትን መሬት ጨምሮ በ2012 መጨረሻ ዓመት ከደረሰበት 114,600 ካ.ኪ.ሜ በ2017 መጨረሻ ዓመት 56946 ካ.ኪ.ሜ ከዳግም ወረራ ለመከላከል ይሰራል።

መ) የበሽታ ዳሰሳ እና ቅኝት ስራዓትን ማጠናከር

ከዋና ዋና የመረጃ ምንጮች የሚገኘዉን የእንስሳት ጤና መረጃዎችን በዘመናዊ የኢ/ኮ/ቴ በመታገዝ ብሔራዊ የእንስሳት በሽታ ቅኝትና አሰሳ ስርዓት ሽፍንን በ2012 መጨረሻ ዓመት ከደረሰበት 76 በመቶ በማሳደግ በ2017 መጨረሻ ወደ 80 በመቶ ይደርሳል። ለተመዘገቡ በሽታዎች በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ የተመሰረተ የበሽታ ሪፖርት ማድረግ አሰራር ተግባራዊ የተደረገባቸው ጣቢያዎች በ2012 ከደረሰበት 709 በማሳደግ በ2017 መጨረሻ ወደ 1620 ማድረስ። በተመሳሳይ በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ ተመስርቶ የተመዘገቡ በሽታዎች (Notifiable Diseases) ሪፖርት የሚደረጉበት ሥርዓት ላይ ስልጠና የወሰዱ ባለሙያዎች ቁጥር በ2012 ከደረሰበት 709 በማሰደግ በ2017 መጨረሻ 1620 ማድረስ። በዚህም መሰረት በሞባይል ስልክ በመታገዝ ከሚላኩ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ሪፖርቶች ዉስጥ የላቦራቶሪ ምላሽ ያገኙት ብዛት ከነበርበት 57 በቁጥር በማሳደግ በ2017 መጨረሻ 450 ማድረስ። በሌላ በኩል ደግሞ የላቦራቶሪ ድጋፍ ያገኙ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ሪፖርቶች ምጣኔን አሁን ከደረሰበት በቁጥረ 47 በማሳደግ በ2017 መጨረሻ ወደ 360 ማድረስ፤ ከሚመጣው መረጃ በተጨማሪ የመረጃ ምንጮችን በማስፋት የማዘጋጃ ቤት ቄራዎችና ኳራንቲን ጣቢያዎችን ዘመናዊ የእርባታ ጣቢያዎችን፣ የእንስሳት ገበያ ማዕከላትን በማካተት ወደ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት በኢንተርኔት አማካኝነት የማስተላለፍ ስራ ይሰራል።

በፌዴራልና ክልል ደረጃ የኤፒዴሚዮሎጂና የበሽታ ቅኝት (surveillance) ሥራ አጠናክሮ በመቀጠል አሁን ከደረሰበት 40 በመቶ በማሳደግ ደረጃውን የጠበቀና ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት (PDS ጨምሮ) በመፍጠር የተደራጀ ሁሉን አቀፍ የመረጃ ምንጭ እንዲሆን በማስቻል በ2017 መጨረሻ 70 በመቶ ማድረስ። በተመሳሳይም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲሁም የውጭ ንግዱን የሚጎዱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው በሽታዎችን በመለየት (Blue Tongue, Nairobi Sheep Disease, UCD, EHV) አሁን ከተካተቱት 7 በሽታዎች ወደ 11 በሽታዎች በማሳደግ ለቁጥጥር እንዲረዳ በሀገሪቱ

ያሉበትን ደረጃና የስርጭት አድማሳቸውን ለመለየት ሀገራዊ የቅኝትና አሰሳ ሥራ (Active surveillance) ማካሄድ፡፡ በፌዴራልና ክልል ደረጃ የኤፒዴሚዮሎጂና ሰርቬይላንስ ሥራ ደረጃውን የጠበቀና ወጥነት ያለው የአሰራር ስርዓት (PDS ጨምሮ) በመፍጠር የተደራጀ ሁሉን አቀፍ የመረጃ ምንጭ እንዲሆን አሁን ከደረሰበት 40 በመቶ በማሳደግ በ2017 መጨረሻ ወደ 70 በመቶ እንዲያድግ ማስቻል ትኩረት ተሰቶ ይሰራል፡፡

የወረዳዎች የበሽታ ሪፓረት ምጣኔን ለማሳደግ ለተመዘገቡ በሽታዎች በተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ የተመሰረተ ሪፖርት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች መተግበር እና በየወሩ በላቦራቶሪዎች የሚላከው የእንስሳት ጤና ችግሮች ሪፖርት (DOVARII) በተመለከተ ከወረዳዎች ከሚመጣው መረጃ በተጨማሪ የመረጃ ምንጮችን በማስፋት የማዘጋጃ ቤት ቄራዎችና ኳራንቲን ጣቢያዎችን ዘመናዊ የእርባታ ጣቢያዎችን፣ ከእንስሳት ገበያ ማዕከላትን በማካተት ወደ ማዕከላዊ የመረጃ ቋት በኢንተርኔት አማካኝነት የማስተላለፍ ስራ ይሰራል፡፡

የፌዴራል እንስሳት ጤና ተቋማት መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ግብረመልስ ለክልሎችና ላብራቶሪዎች ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም የላቦራቶሪ ድጋፍ ያገኙ የእንስሳት በሽታ ፍንዳታ ሪፖርቶች ምጣኔ ያድጋል፡፡ በሀገር ውስጥ ለማይገኙ ነገር ግን በጎረቤት ሀገራት በመገኘታቸው ከፍተኛ ስጋት ለሆኑት የስምጥ ሸለቆ ትኩሳት (RVF)፣ የምስራቅ ዳርቻ ትኩሳት(ECF) እና ጉንፋን መሰል የወፎች ተላላፊ በሽታ(HPAI) ላይ ተከታታይ ቅኝት በማካሄድ (Active surveillance)፤ በተጨማሪም የተከሰቱ በሽታዎችም በአጭር ጊዜ መቆጣጠር እንዲቻል በአራት ማዕከላዊ ቦታዎች በእንስሳት ጤና ላብራቶሪዎች ስር ፈጣን ምላሽ የሚሰጡ ግብረሃይሎች ይደራጃሉ፡፡ በተጭውማሪመ የዶሮ በሽታ ቅኝት፤ ዳሰሳና የላቦራቶሪ ምርመራና ልየታ ሥራ ይጠናከራል፣ የባለሙያ ክህሎትና የተቋማት አቅምም በዘላቂነት የሚገነባ ይሆናል፡፡

ሠ) የእንስሳት ጤና ላቦራቶሪ ምርመራና ምርምርን ማጠናከር

የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ምርምር ማዕከልን አቅም በመጠቀም ስምንት የክልል እንስሳት ጤና ላብራቶሪዎች (ሁለቱ በአርብቶ አደር አካባቢ የሚገኙ) በምርመራና የጥራት አስተዳደር ሥርዓት አቅማቸው ይገነባል፡፡ በተመረጡ የእንስሳት በሽታዎች ምርመራ፣ ቅኝት እና ሰርቲፊኬሽን ሥራ ለማካሄድ ብቁ ይሆናሉ፣ ዘላቂነት ያለው የላብራቶሪዎች ኬሚካል፣ ሪኤጀንትና ባዮሎጅካል አቅርቦት እና የመሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ካሊብሬሽን ሥርዓትም ይዘረጋል፡፡ ይህንንም ለማስፈጸም የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ምርምር ማዕከል ከእያንዳንዱ ላብራቶሪ ጋር በመሆን ያሉባቸውን ክፍተቶቹን ለመሙላት መሰራት ያለባቸውን ስራዎች ይለያል፣ በየትኞች በሽታዎች ላይ ማተኮር እንደሚኖርባቸው በመወሰን በቀጣይ 5 ዓመታት መድረስ የሚገባቸውን ደረጃ ያመላከተ ዝርዝር እቅድ በማዘጋጀት የክልል ላብራቶሪዎች እና ብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ምርምር ማዕከል የስምምነት ሰነድ በመፈረም ወደ ሥራ ይገባሉ፡፡

በሽታዎች በሚያደርሱት የጉዳት መጠን እየተመዘኑ ቅደም ተከተል እየወጣላቸው ቅድሚያ ባገኙ በሽታዎች ላይ እያደገ የሚሄድ የበሽታ ቁጥጥር ስልት (Progressive Disease Control Strategy) በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ፤ ከዚህ አኳያ በአርብቶ አደር አካባቢ የበጎችና ፍየሎች የደስታ መሰል በሽታ ክስተትን ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠርና በሌሎች የአገሪቱ አከባቢዎች ቁጥጥር ፕሮግራሙን ለማስፋት ይሰራል፡፡ ለወጪ ንግድ የሚዘጋጁ እንስሳት የሚመረቱበትና በተሻሻሉ እንስሳት ዝርያዎች ላይ የተመሰረተው የወተት ከብት እርባታ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የአፍተግር በሽታን ቁጥጥር በመጀመር ወደ ሌሎች የአገሪቱ አካባቢዎች የማስፋት ሥራ ይከናወናል (የክትባት ማምረት አቅማችን ከተገነባ በኋላ የሚተገበር ይሆናል)፡፡ ክልሎች በክልላቸው የሚገኙ ፕሮዳክሽን በሽታዎችን በመለየትና ቅደም ተከተል በማውጣት ቅድሚያ ለሚሠጣቸው በሽታዎች የቁጥጥር ስትራቴጅ በመቅረጽ የሚተገብሩበት ሁኔታ ይጠበቃል፣የፌደራል እንስሳት ጤና ተቋማት በቅደም ተከተል አወጣጥና ስትራቴጅ ቀረጻ ዙሪያ የክልሎችን አቅም ይገነባሉ፡፡ ወደ ውጪ በሚላኩ እንስሳት ላይ ተቀባይ ሀገራት በሚጠይቁት መሰፈርት መሰረት የእንስሳት በሽታዎችን ምርመራ ለማድረግ የሪኤጀንትና አሰፈላጊ ኪቶቸን በበቂ በሚሟላት የሰርተፊኬሽኝ መረጃ በመሰጠት የሚሰራ ይሆናል፡፡

ረ) የእንስሳት ደህንነት አጠባበቅን ማጠናከር

የእንስሳት ደህንነትን መጠበቅ ከፍተኛ ዓለም አቀፍ የእንስሳት ንግድ መስፈርትና ትኩረት ሆኖ በመታየት ለያ ይገኛል በዚህመ መሰራት የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ወጥቶ በመተግበር ላይ ናቸዉ። የቁም እንስሳትና የስጋ ንግድም ከእንሰሳቱ ደህንነት አጠባበቅ ጋርም እየተገናኘ ይገኛል። የእንስሳት ደህንነት ማለት አንድ እንሰሳት በሚኖርበት ሁነታ ዉስጥ እንደት ተቋቁሞ እየኖረ እንደሆነ የሚያሰይ ማለት ነዉ። አንድ እንስሳት ጥሩ የሆነ የደህንነት ሁኔታ ዉስጥ ነዉ ለማለት እንስሳዉ ጤነኛ ፣ የተመቻቸ ሁኔታ ዉስጥ ሲረባ ፣ በደንብ የተመገበ፣ ነፃና የተፈጥሮ ጸባዩን በነፃነት ማንጸባረቅ ሲችል እና ከማንኛዉም የማይመቹ ሁኔታዎች ማለትም እንደ ህመም፣ ፍርሃትና ጭንቀት ነፃ ሲሆን ማለት ነዉ።

በሀገራችንም የእንስሳት ደህንነት ችግር ለመቀነስ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ከዚህ ቀደም የተዘጋጀ የእንስሳት ደህንነት አጠባበቅ ስትራቴጅን በማጠናቀቅ ለመተግበር ስፍ እንቅስቃሴ የሚደረግ ይሆናል። በዚህም መሰረት በእርባታ ወቅት፣ በማጓጓዛ፣ በዕርድና በመሳሰሉት ወቅት የሚያጋጥሙ የእንስሳት ደህንነት ችግር ለመቅረፍ በትኩረት ይሰራል።

2.2.1.5 የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ቴክኖሎጂ አቅርቦት

የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት የተቀመጡ ግቦችን እያሳኩ ለመጓዝ አርሶ/አርብቶ አደሩና የግል አምራቹ ምርታማነትን ለመጨምርና በገበያ ተፈላጊ የጥራት ደረጃን ለማሟላት የሚያስችል የአመራረት ዘዴ እንዲከተሉ ለማድረግ የሚረዱ ተስማሚ የቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴ አማራጮችን ማቅረብ ይፈልጋል። ለዚህም የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብና የወደፊት አዝማሚያውንም አስቀድሞ በመተንበይ የሀገራችን ግብርና ያለማቋረጥ እንዲያድግ የሚያስፈልጉ አስተማማኝ ቴክኖሎጂዎችን እና የተሻሻሉ አሰራሮችን በቀጣይነት ለማቅረብ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ የመሪነት ሚናውን መጫወት ይኖርበታል። ከዚህም አኳያ የእንስሳት ምርምሩም የወተት ምርታማነትን በአማካይ 5000 ሊትር በአንድ የአለባ ወቅት ከአንድ ዲቃላ ላም (high-grade crossbred daidy cow) ለማግኘት የማሻሻል ሥራው አርቢ ማህበረሰቡን በማቀፍና ተጠቃሚነቱንም በሂደቱ በማረጋገጥ የሚከናወን ይሆናል። የበግ ሥጋን ከማሻሻል አኳያም የተመረጡ ሀገር በቀል ዝርያዎች ላይ ያተኮረ የማህበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ዝርያንየማሻሻል አሰራር ዘዴ (community based animal breeding program) በመከተል በመረጣ ወይም በማዳቀል ታግዞ የበግ ግልገል ፈጣን ዕድገት አንዲኖረው ማስቻልና በ6 ወር ዕድሜው አሁን ከሚደርስበት 18 ኪግ የቁም ክብደት ወደ 30-45 ኪግ የሚያሳድግ አጠቃላይ የበግ እርባታ ዘዴን አመጋገብንና የእንስሳቱን ጤና አጠባበቅ ጨምሮ ዒላማ ተደርጎ የሚሠራ ይሆናል።

አዳዲስ ለሚወጡ ቴክኖሎጂዎች በተጠቃሚው ዘንድ እንዲታወቁና ፍላጎትንም ለመፍጠር የሚያግዝ የቅድመ-ኤክስቴንሽን እና ቅድመ-ማስፋፋት ሥራ የታቀደ ሲሆን በቀጣይም ተቀባይነት ላገኙ ቴክኖሎጂዎችም የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት በተለይም የእንስሳት መኖ ዘር አቅርቦቱን ለማሳደግ የሚረዱ ዘዴዎችን በመከተል ለማምረት ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ይሆናል። በዚህም መሠረት ለግብርና ምርምሩ የተግባር መስኮች ማላትም የቴክኖሎጂና የግብርና አሰራር ማሻሻያ መረጃዎች አቅርቦት፣ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ማስተዋወቅና ቅድመ-ማስፋፋት ሥራ፣ የግብርና ዕውቀትና ክህሎትን ወደ ተጠቃሚው ለማሸጋገር የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜትን አስመልክቶ ለመጪው 5 ዓመታት የሚተገበሩ ኢላማዎች ተቀምጠዋል።

የሀገራችንን የእንስሳት ምርታማነት4በመቶ ዕድገት በየዓመቱ ጠብቆ ለመጪዎቹ 5 ዓመታት እንዲቀጥል በማስቻል ወተትን አሁን ካለበት 1.45 ሊትር/በቀን ከአካባቢ ላም (local cow) እና 6 ሊትር/በቀን ከተሻሻለ የወተት ከብት ዝርያ ወደ 1.71 ሊትር/በቀን እና ወደ 8 ሊትር/በቀን ከፍ ለማድረግ ግብ ተቀምጧል። በተመሳሳይ የቀይ ሥጋ ክብደትን (carcass weight) በዳልጋ ከብት 110 ኪግ እና በበግ 10.5 ኪግ የሆነውን በአማካይ ወደ 115 ኪግ ለዳልጋ ከብት እና 12 ኪግ ለበግ ለማድረስ ተቀምጧል። የእንስሳት ሀብት ልማት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ለማሳደግ በተለይም ከኤክስፖርት ገበያ አንፃር ተቃኝቶ በትኩረት ሊሰራበት ይገባል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የሥጋ እንስሳትን ብንመለከትበአርብቶ አደሩና አርሶ አደሩ ዘንድ የሚካሄደው እርባታ ለማድለብ ሥራ

የሚፈለገውን የእንስሳት ቁጥር በየዓመቱ ማቅረብ የሚያስችለው ለእርባታ ዓይነቱ ተስማሚየሆኑ የእንስሳት ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ አሰራሮችንበማቅረብ ጥቅም ላይ ማዋልያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በመጨረሻ የሚደረስበት የሥጋ ምርትና ጥራት በገበያ የሚፈለጉ መመዘኛዎችን (ፈጣን ዕድገት፣ ተፈላጊ የሰውነት ክብደትን በተፈለገው ዕድሜ ላይ ማድረስ፣ የውጭ ገበያን ከሚገቱ የበሽታ ዓይነቶች ነፃ ማድረግ እና የመሳሰሉትን) ማሟላት የሚያስችሉ የተሻሻሉ አሰራሮች ምክረ-ሃሳቦችን ጥቅም ላይ በማዋል ከእርባታው አንስቶ እስከ ምርት አቅርቦቱ ያለውን የዕሴት ሰንሰለት አያይዞ ማስኬድና በጠንካራ የግብይት ሥርዓት ተደግፎ በየደረጃው ሥራውን መፈፀም ይገባል፡፡ ስለሆነም የአርቢው ማህበረሰብ እርባታውን ሲያካሂድ ከወዲሁ ገበያን መሠረት አድርጎ መንገዝ እንዲችል በተደጋጋሚ ሥልጠናና ምክር ሊቃኝ ይገባዋል፡፡ በአጠቃላይ የእንስሳት ሀብት ልማት በአብዛኛው ገበያን መሠረት አድርጎ ማካሄድ የሚጠይቅ ሲሆን ይህም እርባታው (እንደ feedlot system የመሳሰሉት) በሳይንሳዊ እውቀት መታገዝ እንዲችል ተፈላጊ የምርምር ውጤቶች በየወቅቱ ቀርበው ተግባር ላይ የሚውሉ ይሆናል፡፡ በሂደቱም የግል ባለሀብት የሚሳተፍበት ዕድል ሰፊ እንደሆነ ስለሚታመን ለኢንቨስትመንት አመቺ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ እንዲሄዱ በትኩረት መሥራት ይፈልጋል፡፡ ለዚህም ምርምርና ልማቱ በጥምረት በመሥራት ተጠባቂ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር ለተገቢው ተጠቃሚ አካል በትክክለኛው ወቅት ማስተላለፍ የእንስሳት ሀብት ልማቱን ወደፊት ለማራመድ የጎላ እስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

ቴክኖሎጅ ማመንጨትና ማለመድ

ተፈላጊ የእንስሳት ዓይነት (የወተት ከብት፣ የሥጋ ከብት፣ ዶሮ) ዝርዎችን በማዳቀል ማሻሻልና ተመራጭ የውጭ ደም ቅይጡን በመለየት በሂደትም እራሱን የቻለ ዝርያ (synthetic/composite breed) መመስረት፤ የታወቁ የሀገር በቀል እንስሳት ዝርያዎችን በራንች በመታገዝና አርቢ ማህበረሰቡን በማሳተፍ (open nucleus breeding scheme) በመረጣ ማሻሻል፤ የመረጣ ሥራውን ውጤታማነት ለማሳደግ የሚረዱ የባዮቴክኖሎጂ ዘዴዎችን መጠቀም፤ በበግና ፍየል ላይ ለገበያ ተመራጭ የሚሆኑ፣ በፈጣን እድገት ተፈላጊ የሰውነት ክብደት ላይ በቶሎ እንዲደርሱ የሚያስችል የማዳቀል አሰራርን (terminal crossing) ለመከተል የሚረዳ ምርምር ማካሄድ፤ ለኮሜርሻል አመራረት የሚውሉ ሃይብሪድ የዶሮ ዝርያዎችን ለከተማ ግብርና የሚውሉ ጭምር ለተጠቃሚው ለማቅረብ በማላመድ ወይም በማዳቀል ማሻሻል፤ የዓሳ አመራረት አማራጮችን እና በተጓዳኝ ምርታማነትን የሚያሳድጉና የዕሴት ሰንሰለቱ ዙሪያ አሰራሮችን ማሻሻል፤ የንብ አመራረትን፣ የማርና ሰም ጥራት አጠባበቅን ከውጭ ገበያ ፍላጎት ጋር በመቃኘት ማሻሻል፤ የሀር ምርት በሀገራችን በስፋት እንዲለመድና አመራረቱንና የሀር ጥራቱንም የሚያሳድግ አሰራር ለማቅረብ የተጠራከረ ምርምር ይካሄዳል፡፡

ለተለያዩ የግብርና ሥነ-ምህዳራት ተስማሚ የሆኑ፣ ምርታማና ከፍተኛ የመኖ ጠቀሜታ ያላቸው የመኖ ሰብሎችን ለማቅረብ በማላመድና በመረጣ ማሻሻል፣ አመራረቱንና አጠቃቀሙን የሚያሻሽል አሰራር መሻት፤ የተፈጥሮ ግጦሽ ምርታማነትን ለማሳደግ አያያዙንና ዘለቄታዊ አጠቃቀሙን ማሻሻል፤ የእንስሳት አመጋገብን በምርታማነት ላይ ተመርኩዞ ለማውጣት የመኖ ፍላጎትን (animal nutrient requirement) ያሟላ የመኖ ቀመር (ration formulation) በሶፍትዌር ተደግፎ ለእንስሳት ዓይነትና የአመራረት ሁኔታ ለማቅረብ ጥናት ማካሄድ፤ እንስሳትን በተለይም የውጭ ገበያን ያለመ የእንስሳት ማድለብ (feedlot fattening) ምክረ-ሃሳብ ለማቅረብ የተጠናከረ የአመጋገብ ማሻሻል ምርምር ይካሄዳል፡፡

የእንስሳት ሥነ-ተዋልዶ ውጤታማነትን ለማሳደግና ጥቅም ላይ ለማዋል የእንስሳት ፅንስ ዝውውርና የላቦራቶሪ ፅንሰት (invitro fertilization) ቴክኒኮችን ማላመድ፤ የኮርማ ፍላጎት የማቀናጀት አሰራርን ውጤታማ ለማድረግ፣ የተመረጠ ኮርማ አባለዘር ጥራትን ለማስጠበቅ የሚረዱ የአሰራር ዘዴዎችን ለማውጣት ምርምር ማከናወን፤ ተፈላጊ የእንስሳት ባህርያትን የሚወስኑ ዘረመሎችን በመለየት የዝርያ ማሻሻል ሥራው እንዲፋጠን ትኩረት በመለየት ይሰራል፡፡

መነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

በርቢ ባህርይ መመዘኛ (breeding value) መሠረት የወተት ከብት ዝርያ ኮርማን፣ የሀገር ውስጥ፣ የውጭና ዲቃላ የበግ/ፍየል ዝርያዎች አውራዎችን በመምረጥ ለማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሰጡ ማቅረብ፤ የወተት እርባታን ለማሳደግ ዲቃላ የወተት ከብት ዝርያን ቁጥር እንዲጨምር ጊደርን በተለያዩ ሳይንሳዊ አማራጮች (use of sexed semen, mass insemination with synchronization, embryo transfer) ማምረት፤ ለዶሮ፣ ለዓሳ እና ለንብ እርባታ ተፈላጊ የመነሻ ቴክኖሎጂ (የአንድ ቀን የዶሮ ጫጨቶች፣ የዓሳ ጫጨቶች፣ የእናት ንብ እና የሀር ትል) በማባዛት ለተጠቃሚ እንዲተላለፉ በትኩረት ይሰራል። የተሻሻሉ የእንስሳት መኖ ሰብል ዝርያዎችን መነሻ ዘር በተገቢው መንገድ አባዝቶ በማቅረብ በመኖ ዘር ብዜት ሥራው በተለይ የግል ሴክተሩ እንዲሳብና እንዲሳተፍ በማበረታታት መደገፍ በትኩረት ይሰራል።

2.2.1.6 የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ግብዓት አቅርቦት ስርዓት

የተሻሻለ የእንስሳትና አሳ ልማት ግብአትና ቴክኖሎጂ አቅርቦት በአጠቃላይ የተሻሻሉ የእንስሳትና የመኖ ዝርያዎች ፣ የእንስሳት ዝርያ ማሻሻያ የኮርማ አባለ ዘር፣ የንብ ማነቢያ ቁሶች ፣የእንሳት መድህኒትና ክትባቶች ፣ የወተትና ለሚደልቡ ክብቶች የሚሆኑ መኖ ፣ ለመኖ ልማትና ለሎች የሚሆኑ የሜካናይዜሽንና የባዮሎጂካል ቴክኖሎጂን ያጠቃልላል። የተሻሻለ የእንስሳትና አሳ ልማት ግብአትና ቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሳደግ አነስተኛ ይዞታ አርሶና አርብቶ አደሩ ወደና ፈቅዶ ሊጠቀማቸው የሚችሉ ስነ ምህዳር ተኮር፣ ምርታማና ሌሎች ጠቃሚ ባህርያትን የተላበሱ የእንስሳትና አሳ ልማት ግብአትና ቴክኖሎጂዎችን እንዲቀርቡለት የሚያስችል የአገር ውስጥና የውጭ አገር የግል ዘርፉን ተሳትፎ የሚያበረታታ ስርዓት ይዘረጋል። ይህን በማድረግም በአገር ውስጥ አርሶና አርብቶ አደሩ ከፍተኛ ዋጋ ከፍሎ የሚጠቀማቸውን በምርታማነታቸው የላቀ ውጤት ያሳዩትን የእንስሳትና አሳ ልማት ግብአትና ቴክኖሎጂ በብዛትና በመጠን እንዲቀርብለት በማድረግ ተፈጻሚ ይሆናል። የተሻሻሉ የእንስሳትና አሳ ልማት ግብአትና ቴክኖሎጂ ግብዓቶች ከማምረትና ከማስፋፋት እስከ ተጠቃሚው የማድረስ ተግባራት ላይ የግል ዘርፉን ተሳትፎ በማጠናከር በመጪዎቹ አምስት አምታት በንኡስ ዘርፉ ያልተነካውን የግሉን ዘርፍ በስፋት በማሳተፍ ይሆናል።

እንስሳት ክትባትና መድሃኒት አቅርቦት

በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት የተገነባዉ አዲሱ የእንስሳት መድኃኒት ማምረቻ ፋብሪካ በመጀመሪያዉ የምርት ዓመት ከአጠቃላይ የማምረት አቅሙ 60 በመቶ ብቻ በመጠቀም 91.54 ሚ/እንክብሎችን ያመርታል፤ በመቀጠልም በየዓመቱ የማምረት ዓቅሙን በአማካይ በ10በመቶ በማሰደግ በ2017 መጨረሻ ዓመት 115.42 ሚ/እንክብሎችን ያመርታል፡፡

በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ እንስቲትዩት በኩል የታቀዱ ግቦችን ለማሳካት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የተለያዩ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስፈልግ ክትባት በጥራትና በመጠን ለማምረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋና ተግባራቶች የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ የመብራት መቆራረጥና የጎይል ማነስ ችግርን በዘላቅነት በመፍታትና የክትባት ማምረቻ መሳርያዎች ያለማቋረጥ እንድሰሩ ለማድረግና ኢንስትተዩቱ የሚያስፈልገዉን የኤሌክትርክ ኃይል እንድያገኝ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋረ በቅረበት ይሰራል፡፡ የእንስሳት ክትባቶችን በሚፈለገዉ ጥራትና መጠን ለማምራት ልዩ ልዩ ጥሬ ዕቃዎች ከዉጭ ለማስገባት የሚያስፈልግ ስሆን ይህንንም ለሚሚላት የዉጭ ሚኒዛሬ ፍላጎት በተፈለገ ጊዜ እና መጠን ማግኘት እንድቻል የሚሰራ ይሆናል፡፡ አዳዲሰ የማምረቻና የምርምረ ላቦራቶሪዎችን በመገንባትና ቁሳቁሶችን እንደ ሊዮፊላይዘር፤ስቴሪላይዘርና ፍሪዘር የመሳሰሉ ለማሚላት ይሰራል፡፡

ለተለያዩ የድንበር ዘለል በሽታዎች ማለትም ለFMD፣ CCPP፣ Thermostable PPR እና Bovine Pasteurellosis ክትባቶች ጥራትና መጠን ለመጨመር ወደ ተሸሻለ የአመራረት ተክኖሎጂ ለመግባት ከመንግስትና ከግሉ ዘረፍ እንድሁም ከልማት አጋሮች ጋር በመሆን ይሰራል፡፡ በዚህ መሰረትም የነባረ ክትባቶችን የማምረት አቅም ከማጎልበት አንጻርና የተሻሻሉ ተክኖሎጂዎችን እንደ ባዮሪያክተር(bioreactor) እና ቴርሞስቴብል የክትባት ማምረቻ ተክኖሎጅዎችን በመጠቀም፤ የአፍተግርና ተርሞስቴብል የበጎችና ፍየሎች ሳንባ በሽታ ክትባቶችን እንድሁም የሬብስ ክትባትን በማሻሻል በጥራትና በብዛት እንድ መረት ይደረጋል፡፡ በተጨማርም አዳድሰ በምርምር የተገኙ የክትባት ዉጤቶችን ወደ ምርት በማስገባት እንደ ማሬክስ፣ ማይኮፕላዝማ ጋሊሴፕቲከም እና የጋማ ከብት ሊምፋንጃይትስን ክትባቶች በጥራትና በመጠን ተመረቶ ለገበያ ይቀረባሉ፡፡ ሀገርቱ ከሌሎች ክትባትና መድኃኒት አምራች አገራት የላቦራቶሪዎች ጥራት ቁጥጥሩን ለመጨመርና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ለማድረግ እና በአፍሪካ ዕውቅና እንዲያገኙ በማድረግ ለወጪ ንግድ እሰታንዳርዱን ለመጨመር የመልካም አመራረት ዘዴን በምርምር ላቦራቶሪ የተረጋገጠ አራት የላቦራቶሪ ቴሰቶች በ17025 አክሬዲቴሽን እንዲያገኝ የላቦራቶሪውንና የሰውን አቅም በመገንባት ይሰራል፡፡ በሌላ በኩል ዕያደገ የመጣውን የዶሮ ዕርባታና የዝርያ ማሻሻል ሰራዎቸኝ የሚመጥን ክትባቶቸን ለማምረና ከውጭ የሚገዙትን የማምረቻ እንቁላሎች በማሰቀረት የውጭ ምንዛሬን ለመቀነሰ የኤፍሰፒፍ ሞጁል ጫጩት ማሳደጊያ በመግዛትና በማሰገባት ከጀርም ነጻ የሆነ ለክትባት ዝርያ ማራብያ የሚሆን እንቁላል አገር ዉስጥ እንድመረት ይደረጋል፡፡

የእንስሳት መኖ ዘርና መኖ ግብይት

የእንስሳት መኖ በሚፈለገው መጠንና የጥራት ደረጃ መቅረብ አለመቻል በእንስሳት ንዑስ ዘርፉ እርባታና ግብይት ውጤታማነት ላይ መሰረታዊ ተግዳሮት ነው፡፡ በመሆኑም አርቢው፣ የግብይት ተዋንያን ብሎም ሃገሪቱ ከንዑስ ዘርፉ የሚጠበቀውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ማግኘት ባለመቻሉ ችግሩን ሊፈቱ በዘላቂነት የሚችሉ አሰራሮች መከተል ያስፈልጋል፡፡ የእንስሳት መኖ ዘሮች እና መኖ ከአምራቹ እስከ ተጠቃሚው ድረስ የሚደረስበትን አዲስ የግብይት አሰራር ስርዓት እንዲኖር እንዲሆን በማድረግ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የመኖ አቅርቦትና ፍላጎትን ሊያስተካክል የሚችልና ለተጠቃሚው አጠቃቀሙ ቀላል የሆነ የመኖ ዘርና መኖ ገበያ መረጃ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ ሰፋፊ የመኖ ዘርና መኖ አምራቾችን ፕሮፋይል በማዘጋጀት እና የመኖ ፍላጎታቸውን በግዥ የሚያሟሉ ትላልቅ የእንስሳት ግብይት ተዋንያንን በመለየት በውል ላይ የተመሰረተ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

የእንስሳት ምርጥ ዘሮችና የአባለ ዘር አቅርቦት

በሀገራች የመንግሥት ሰው ሰራሽ የእንስሳት የማዳቀል ዘዴ ውጤታማነትና ብቃት ውሱን መሆኑን ጥናቶች ቢያመላክቱም በዘርፉ በብቸኝነት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶዋል :: ይህንን ችግር ለመቅረፍ

በቀጣይ አምስትት አመታት የሀገራቱን ብሪዲንግ ፖሊሲ ለመተግበር የግልና የማህበር የሆኑ ሰው ሰራሽ የእንስሳት የማዳቀል ማእከላት እንዲመሰረቱ በማደረግና ሁለት ሁለተኛ ደርጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ ተማሪዎችን በማሰልጠን ወጣት የማዳቀል ሰራዎችን እንዲያሳልጡ ይደረጋል ።ከዚህ በተጨማሪ በአምስት አመቱ ለሰው ሰራሽ የማዳቀል ዘዴ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች መግዣ ብድር እንዲመቻች የሚደረግ ሲሆን ፡ ላሞችን በአንድ ጊዜ የማስጠቃት ዘዴ (estrus synchronization) መጠቀም አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችና ቁሳቁሶችን በወረዳዎች እንዲማሉ በማድረግ ብዙ ላሞች በፍጥነት በሰው ሰራሽ ዘዴ ለማዳቀል ስራ የሚያስችልና በተለምዶ አንዳንድ ላሞችን ከማዳቀል የተሻለና ውጤታማነትን የሚጨምር አሰራርን በአምስት አመቱ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል። የሰው ሰራሽ የማዳቀል ዘዴ በቀላሉ ማዳረስ በማይቻልባቸው ቦታዎች የግል የኮርማ አገልግሎት ጣቢያዎች እንዲኖሩ ይደረጋል ።

ዘመናዊ የንብ ማነብ ቁሳቁሶች

ዘመናዊ የንብ ማነብ ዘዴዎችን በማስፋፋት የመጠብቀውን ማርና ስም ለማምረትነና ያለውን የማር ምርታማነት ለማሳደግ የሚያግዙ ግብዓቶችን የማቅረብ ስራ በማጠናከር የተቀናጀ የግብዓትነና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ትኩረት የሚስጠው ይሆናል። አርሶና አርብቶ አደሩ በሀገሪቱ ያለውን ምቹ የአየር ንብረት፣ ዛፍ፣ አበባና በቂ ውሃ በዘመናዊ አሰራሮች በመከተል ጥቅም ላይ በማዋል የሀገሪቱን እምቅ የማርና ሰም ምርት ለማሳደግ ታቅዷል። የንብ ማነብ ዘርፍ ለሴቶች፣ ወጣቶችና ለአቅመ ደካሞች ምቹ የስራ መስክ ሲሆን፤ የንብ ቀፎዎችን በገጠር የቴክኖሎጂ ማዕከላትና በጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት በብዛት በመስራት ለንብ አናቢዎች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ የሚደረግ ይሆናል ጋዜጣው። በሀገሪቱ የንብ መንጋ እጥረት እያጋጠመ በመምጣቱን ይህን ችግር ለመፍታት በክልሎች የንግስት ንብ ማራቢያ ማዕከል የሚቋቋም ይሆናል። ባህላዊና ዘመናዊ የንብ ማንቢያ ቀፎችን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለሁሉም ንብ አናቢ አርሶ አደሮች እንዲከፋፈል በማድረግ በበዋጋ ምክንያት ሊዳረሱ ስላልቻሉ አርሶ አደሩ እንደ ጨፈቃ ያሉ የአካባቢ ቁሳቁሶችን ተጠቅሞ የሚሰሩ የቀፎ አይነቶችን በስፋት እንዲተዋወቅ የሚድረግ ይሆናል። አብዛኛው የማር ምርት በከፊል የተቀነባበረም ይሁን ያልተጣራ ማር ከተመረተበት ቦታ ውጪ ሲሸጥ አነስተኛ ጥራት ባላቸው ማሸጊያዎች (ለምሳሌ የማዳበሪያ ከረጢት) ታሽጎ እንዲሆን ይደረጋል ከንግድ ማቀናባበሪያዎች ጋር ትስስር በመፍጠር አምራቾች ምርታቸውን ከፕላስቲክ በተሰሩ መያዣዎች ወይም በማይዝጉ ቆርቆሮዎች እንዲሸጡ ለማድረግ በእቅድ ተይዞዋል።

የአሳ ምርት ግብአት

ኢትዮጵያ በውሃ ሃብት ቀዳሚ ከሚባሉት የአፍሪካ አገራት አንዷ እና ከፍተኛ የአሳ ሃብት ያላት መሆኗን በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ያመለክታሉ። በኢትዮጵያ በማህበርና በግለሰብ ደረጃ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ዜጎች አሳ በማምረት ስራ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የአሳ አመራረትን በማዘመን አቅርቦቱን ለማሳደግ የአሳ ግብአት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት ከፍተኛ የአሳ ክምችት ካለባቸው ሃይቅና ወንዞች መካከል አባይታ፣ ጫሞ፣ ላንጋኖ፣ አባይ፣ ተከዜና አሞ በቀዳሚነት የሚጠቀሱ ቢሆንም በቀጣይ አምስት አመታት የሚንቡና እየተገነቡ ያሉ ስው ሰራሽ ግድቦችና ሀይቆች ክፍተኛ የአሳ ምርት እንደሚኖራቸው ይጠብቃል። በዘርፉ የሰለጠነ ባለሙያ ማደራጀት ጎን ለጎን የአሳ ምርት ግብአቶች አቅርቦትን ማጠናከር ቀጣይነት ያለው ምርት እንዲሰጡ ማድረግ እቅዱን ለማሳካት የተያዘ አቅጣጫ ነው። በግድቦች የአሳ ጫጩት ግብአት በማቅረብ የግድብ አሳ ሃብት ልማትን ማሳድግ ሌላኛው በአምስት አመቱ የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል። የአገር ውስጥ ፍላጎትን ለመደገፍ ከውጭ የሚገቡትን የአሳ ሀብት ልማት ግብዓቶችን በአገር ውስጥ በማምረት ለመተካት ትኩረት የሚስጠው ይሆናል። በዘርፉ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች የአሳ ጫጩትና የመኖ አቅርቦት በበቂ ሁኔታ ለማቅረብ በክልሎች የጫጩት ማስፈልፈያ ማዕከላት ግንባታ እንዲከናውን ይደረጋል ። ስለሆነም በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ የየክልሎቹን ፍላጎት ለመደገፍ የሚያስችሉ ማስፈልፈያዎች በክልሎች እንዲገነቡ ይደረጋል ። ከስራ እድል ፈጠራ አንጻርም ስራ የሌላቸው ሴቶችና ወጣቶች ንግብአት በማምረትና በማቅረብና ዘመናዊ አሰራርን በማስተዋወቅ በዘርፉ የተሻለ ልምድ ካላቸው አገሮች የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች በማስገባት ምርቶችን ለገበያ እንዲያቀርቡ ይደረጋል።

የእንስሳትና ዓሳ ግብዓት አቅርቦትና አገልግሎት ማዕከላትን ማጠናከር

የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማተ ዘርፍ ባቀረበው የእንስሳት ልማት ግብአት ፍላጎት መጠንና አይነት በመነሳት ለዘርፉ የሚያስፈልጉትን ግብአትን አቅርቦትና ስረጭት ውጤታማ ለማደረግ በአገር አቀፍ ደረጃ የእንስሳት ግብአት ምረትን ማሰደግ፣ ከውጭ የምናስገባቸውን በተቀላጠፈ ሁኔታ ላማስገባት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ማደረግ ፣ በከተማና በገጠር ወረዳ ደረጃ ተደራሽ የሆነ የእንስሳት ሀብት ልማት ግብዓት አቅርቦትና ስርጭት የአንድ መስኮት አገልግሎት ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። ይህንን ለማስቻልም በንኡስ ዘርፉ ተዋናዮች አቅምን በማሳደግ በክልሎች ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የእንስሳት ሀብት ልማት የግብዓት አቅርቦት መረብ ትስስር በመዘርጋት በአስመጪዎች፣ በጅምላና በችርቻሮ ሻጮች በሀከል በክልሎች ፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ የእንስሳት ሀብት የግብዓት አቅርቦት መረብ ትስስር መዘርጋት።

በገጠርና በከተማ አዳዲስ የእንስሳት ሀብት ልማት ግብዓት ችርቻሮ መሸጫዎችንና ማሰራጪያዎች እንዲመሰረቱ ማደረግ ለተጠቃሚዎች ለገጠር ባንኮችና የገንዘብ ብድር ተቀማት ለግብአት ግዢ የሚውል ብድር ገንዘብ በማዘጋጀትና ውጤታማ የብድር ገንዘብ አጠቃቀም ለመተግበር የቮቸር ወይም ኩፖን ስርአት መተግበር። የግሉን ዘርፍ በቂ የሆነ የእንስሳት ግብአት ምርትና ስርጭት ንኡስ ዘርፍ እንዲሳተፉ በማደረግ ለአነስተኛና መለስተኛ አምራቾች የእንስሳት ሀብት የግብአት አጥቅምና አጠቃቀም ግንዛቤ መፍጠር ተመጋጋቢ እንዲሆኑ ማስቻል። የለጋሽና አጋር የልማት ፕሮገራሞች የግብርና ግብአቶችን አጠቃቀምን የሚያጎለብቱ የፕሮጀክት አምዶች እንዲኖራችው በሚካተት መልኩ እንዲተገበሩ ማደረግ። በገጠርና በከተሞች አካባቢ የግብርና ግበአት አቅርቦትና ስርጭት የሚያከናውኑ የግል ወኪሎች እንዲመሰረቱ ማድረግ ግብአት ተጠቃሚዎች ግብአቶች የሚገኝበትንና አጠቃቀምንም በተመለከተ መረጃዎችና ግንዛቤን ማሳደግ። በክልሎችና በከተማ መስተዳድሮች በገጠርና በከተማ ወጣቶችን ያሳተፈ የእንስሳት ሀብት ልማት ግብአቶችን የሚመረቱበትና የሚሰራጩበት የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዳስትሪዎችን በመለየት እንዲመሰረቱ ማደረግ።

2.2.1.7 የእንስሳትና ዓሳ ግብዓት ጥራትና ደህንነትን ማረጋገጥ

በእንስሳት መድኃኒት እና መኖ ጥራት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በኩል በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በእንስሳት መድኃኒት አምራቾች፣ አስመጪዎችና ክልል ተሻጋሪ ጅምላ አከፋፋይ ተቋማት ዉስጥ ጥራታቸዉን፣ ፈዋሽነታቸዉን እና ደህንነታቸዉን በምዝገባ፣ በሰነድ ግምገማ፣ በቅድመ ገበያ ኢንስፔክሽን፣ በላቦራቶሪ ምርመራ፣ በድህረ ገበያ ኢንስፔክሽን የማረጋገጥ ሥራ በ2012 ከደረሰበት 88 በመቶ በ2017 ዓመት መጨረሻ ወደ 93 በመቶ ይደርሳል። በተመሳሳይም በየክልሉ የሚገኙ ጅምላ አከፋፋዮችና ችርቻሮ ድርጅቶች ጥራት፣ ፈዋሽነትና ደህንነት የማረጋገጥ ሥራ በ2012 90 በመቶ ለማካናወን የተቻለ ስሆን በ2017 መጨረሻ ዓመትም በተመሳሳይ 95በመቶ ለማከናወን ይሰራል። በሌላ በኩል በንግድ የእንስሳት መኖ አምራቾች፣ አስመጪዎች እና ክልል ተሸጋሪ ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ላይ የእንስሳት መኖ ጥራትና ደህንነት የማረጋገጥ ሥራ በ2012 መጨረሻ ዓመት ከደረሰበት 75 በመቶ በማሳደግ በ2017 መጨረሻ ዓመት 86 በመቶ ይደርሳል። ሕገ ወጥ የእንስሳት መድኃኒት ምርትና ሥርጭትን መከላከልና መቆጣጠርን በተመለከተ በ2012 መነሻ ዓመት ወደ 35 በመቶ መቀነስ የተቻለ ስሆን በ2017 መጨረሻ ዓመት ላይ ወደ 19 በመቶ እንዲወርድ ይሰራል። በተመሳሳይም ሕገ ወጥ የእንስሳት መኖ ሥርጭትን በ2012 መነሻ ዓመት ከነበረበት 40 በመቶ በመቀነስ በ2017 ወደ 22 በመቶ ለማውረድ ይሰራል።

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ ቁጥጥር ባለስልጣን የተያዙ ግቦችን ለመተግባር በዋናነት የባለሥልጣኑን አደረጃጀት በዘላቂነት ለማስተካከል ይሰራል። በክልሎች እና በባለስልጣኑ የቁጥጥር ስልጣን ወሰን ጉልህ ሆኖ እንዲሰመር ይደረጋል፤ ለክልሎች የሚደረገው ድጋፍም እስከምን እንደሆነ በግልጽ ታውቆ ተጠያቂነት ያለው የአሠራር ትስስር ይፈጠራል። የቁጥጥር ስራውን የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀምና የሌሎች ሃገራትን ተሞክሮ ጭምር በመጠቀም የዕለት ከለት የቁጥጥር ስራዎችን በማዘመን ይሰራል። የባለስልጣኑ አዋጅ ያሉት ክፍተቶችን በመለየት እና አሁን በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እየተሰጠ ያለውን የተህዋሲያን መድኃኒትን መላመድን ለመከላከል መካተት ያለባቸውን አካቶ አዋጁ እንዲሻሻል ይደረጋል። በተሻሻሉ የዶሮ እና ሌሎች እንስሳቶች እርባታ ያሉ የበሽታዎች ሁኔታ እና ዝርዝር የሚመለከተው አካል ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ለባለስልጣኑ የሚያሳውቅበትን ዘዴ መዘርጋት፤

በየክልሉ በነበረው አደረጃጀት ተጨማሪ ሥራ ከመስጠት ይልቅ የእንስሳት መድሃኒት እና መኖ መቆጣጠር እና ማስተዳደር በባለቤትነት ወስዶ የሚሰራ አካል እንዲኖር ይደረገል፡፡

የእንስሳት መድሃኒት ጥራት፣ ደህንነት፣ ፈዋሽነትና ቁጥጥርን በተመለከተ ከውጭ በግዥ የሚገባም ሆነ የሃገር ውስጥ መድሃኒትና ባዮሎጅካል አመራረት፣ አያያዝና አጓጓዝ በአግባቡ መሆኑን የጥራት፣ የፈዋሽነትና የደህንነት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን በጥራት መመዘኛዎች መሠረት አስፈላጊው የጥራት ቁጥጥር ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ የህክምናና የላቦራቶሪ መመርመሪያ መሣሪያዎችና ኬሚካሎች ጥራት የማረጋገጥ ሥራዎችም የሚከናወኑ ይሆናል፡፡ ለቁጥጥሩም ዝርዝር መመሪያዎች ይዘጋጃሉ፡፡ በአስመጪ መጋዝኖች፣ በጅምላ አከፋፋይ መጋዝኖች በሃገሪቱ መግቢያና መውጫ ኬላዎች እንዲሁም በመድሃኒት ችርቻሮ ድርጅቶች ላይ የሚደረገው የጥራት ቁጥጥር፣ ክትትልና ድጋፍ ተግባራት በፌዴራልና በክልል ተቆጣጣሪ አካላት ይፈፀማል፡፡ ከመድሃኒት ጥራት፤ ፈዋሽነትና ደህንነት ጋር በተያያዘ ችግር ሲከሰት ተጠቃሚዎች ቅሬታቸውን ለተቆጣጣሪ አካል እንዲያቀርቡ የተዘረጋው ሥርዓት ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ የመድሃኒት ጥራት፣ ፈዋሽነትና ደህንነት ተጠብቆ የእንስሳት ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር አግባብ ላላቸው አካላት በመድሃኒት አያያዝና አጠቃቀም ሥልጠና በተከታታይ የሚሰጥ ሲሆን በተመሣሣይ መልኩ የተቆጣጣሪዎች፣ የላቦራቶሪ ባለሙያዎችና የምርመራ ላቦራቶሪዎች አቅም የሚገነባ ይሆናል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ሕገወጥ የእንስሳት መድሃኒት ንግድና ዝውውር በሃገሪቱ ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ ተንሰራፍቶ የሚገኝ መሆኑ ነው፡፡ጥራቱ፣ ፈዋሽነቱና ደህንነቱ ሳይረጋገጥ የሚመረትና በሕገ ወጥ መንገድ የሚገባው መድሃኒት እንዳይሰራጭና በተለያዩ አካባቢዎች ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚያስችል ሥርዓት ተጠናክሮ ይተገበራል፡፡ ችግሩንም በዘላቂነት ለመቅረፍ እንዲቻል ቅንጅታዊ አሰራር በማጎልበት ቁጥጥሩን ለማጠናከር የሚያስችል ሥርዓት ይዘጋጃል፡፡ ሕገወጥ የእንስሳት መድሃኒት ንግድና ዝውውር የሚካሄድባቸው ዋና ዋና ቦታዎችን የመለየት ሥራዎች ተሰርተዋል፡፡ ከተለዩትና ከፍተኛ ሕገወጥ የእንስሳት መድሃኒት ንግድና ዝውውር በሚካሔድባቸው የሃገሪቱ መግቢያና መውጫ ኬላዎች ባሉባቸውና በዛው መሥመር ባሉ ከተሞች የሕብረተሰብ ንቅናቄ በመፍጠር በሕገ ወጥ መንገድ የሚካሄደው ሥርጭትና አጠቃቀም ቁጥጥር ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

የመኖ ጥራትን ለመቆጣጠር የተያዙ ግቦችን ለማሳካት የመኖ እና የመኖ ጥሬ ዕቃ አምራች፣ አስመጪና ጅምላ አከፋፋይ ድርጅቶች ለመኖ ንግድ ስራ ብቁ የተቋም አደረጃጀትና አግባብነት ያለው ባለሙያ ተሟልቶ ስለመኖሩ የማረጋገጫ ፍተሻ ይደረጋል፤ በዉጭ ሀገርና በሀገር ዉስጥ የሚመረቱ የእንስሳት መኖ ወደ ገበያ ከመግባታቸዉ በፊት አስፈላጊዉ ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ የሳኒተሪ እና ፋይቶ ሳኒታሪ፣ ከለውጥ ሕያው (ጂኤምኦ) ነጻ ሰርቲፊኬት፣ የምርት ምርመራ ውጤት፣ የንጥረ መኖ ይዘት፣ የመልካም አመራረት ተሞክሮ ሰርቲፊኬት እና ተዛማጅ መግለጫዎችና ማስጠንቀቂያዎች ላይ የሰነድ ግምገማ ይካሄደል፣ በሀገር ውስጥ የመኖ ማቀነባበሪያ ድርጅቶች የመልካም አመራረት ተመክሮ እንዲዳብር አግባባዊ ምልከታ በማካሄድ የማስተካከያ ግብረ መልስ እንዲሰጥ ይደረጋል፣ወደ ሀገር የሚገቡ መኖና የመኖ ጥሬ ዕቃዎችን ጥራትና ደህንነት ለማረጋገጥ አምራች ድርጅቶችን የመልካም አመራረት ዶክመንት በመፈተሽ መስፈርትን ለሚያሟሉ ወደ ሀገር የማስገቢያ ፈቃድ ይሰጣል፣የአካባቢ ብክለትን እና የእንስሳት ደህንነትን አደጋ ለመቆጣጠር እንዲያስችል ከመኖ አምራች ተቋማት የሚወጡ የብክለት ምንጮችን በመፈተሽ ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል፡፡

ለመኖ ሬጉላቶሪ መጎልበት ነባር ብሔራዊ የመኖ ደረጃዎች እንዲሻሻሉ፣ አዳዲስ ደረጃዎች እንዲወጡ ከኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ ጋር ደረጃ የማዘጋጀት ሥራ ይከናወናል፣ በሳይንሳዊ መረጃና የስጋት ትንተና ላይ የተመሰረቱ እና የተጠቃሚ አካላትን ፍላጎት መነሻ ያደረጉ የመኖ መልካም አመራረት ሂደት አሠራሮች፣ የጥራት መረጋገጫ መመሪያዎች ይዘጋጃሉ፤ የሬጉላቶሪ ዕወቀትና ክህሎት ክፍተትን ከሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ባላድርሻ አካላት ጋር የሥራ ትስስር በመፍጠር የአቅም ግንባታ ሥልጠዎችን በማካሄድ የሬጉላቶሪ እንዲገለብት ይደረጋል፤መኖና የመኖ ንጥረ ነገሮች ላይ የላቦራቶሪ ጥራት ምርመራ ማጠናከርና የመኖ አፍላቶክሲን (Aflatoxin) መከላከልና መቆጣጠር ላይ ትኩረት በማድረግ ይሰራል፡፡

2.2.2 የተስፋፋ የባለሀብት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

የባለሀብት እንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት በሚቀጥሉት 5 አመታት ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ሲሆን ለማህበረሰብ የምግብና ስነ ምግብ ዋስትና ለማረጋገጥና እንዲሁም ለኢንዱስትሪ ግብዓት እና ለውጪ ምንዛሬ ግኝት ትልቅ አስተዋፅዎ ይኖረዋል። ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ አዲስ ባለሀብቶችን ወደ ልማቱ ማስገባታና ነባሮቹን መከታታለናን ድጋፍ በመስጠት የያደገና ውጤታማ የሆነ የግል ባለሀብት የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል።

2.2.2.1 ያደገ የግል ባለሀብት የእንስሳትና ዓሳ ሃብት ኢንቨስትመንት

ያደገ የግል ባለሀብት የእንስሳትና አሳ ሃብት ልማት ተግባራዊ ለማድረግ መሬት አቅርቦትን ማመቻቸት፤ መሰረት ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ማሻሻል ፣ የባለሀብት ልማት ከአርሶና አርብቶ አደር ጋር ማስተሳሰር ላይ በተኩረት ይሰራል። በዚህም መሰረት በወተት ፣ ሰጋ፣ እንቁላል፣ አሳእና ማርምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል።

በወተት ሀብት ልማት

በወተት ከብት እርባታ የባለሀብቱን ቁጥር ለማሳደግ በቀጣይ በመካከለኛ ስፔሻላይዝድ የወተት ከብት እርባታ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ሲሆን ትግበራው የእርባታ ጣቢያዎችን ቁጥር በመጨመር፤ በእያንዳንዱ እርባታ ጣቢያ የሚኖሩ የተሻሻሉ ዝርያ ላሞችን ቁጥር በማሳደግ፤ የስልጠናና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ድጋፍን በማሻሻል እና የገበያ ትስስርን በማጠናከር እንዲሁም አዳዲስ ባለሀብቶችን ወደ ዘርፉ እንዲገቡ በመደገፍ የሚከናወን ይሆናል። በዚህም መሰረት የመካከለኛ ስፔሻላይዝድ የወተት ከብት እርባታ ተሳታፊ ባለሀብት በ2012 ካለበት 551 ቁጥር በአማካይ በዓመት 10 በመቶ በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 826 ለማድረስ ይሰራል።

ከክልሎችና ባለድርሻዎች ጋር በመቀናጀት አዲስ በዘርፉ መሰማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች በጥናት ላይ የተመሰረተና ለየኢንቨስትመንቱ ዓይነት ተስማሚነቱ የተረጋገጠ መሬት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡ ፡ ስለሆነም በከተሞች አካባቢ የሚደረግ ኢንቨስትመንት የረጅም ጊዜ የከተማ ማስተር ፕላን ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ማድረግ እና ለሁሉም የኢንቨስትመንት መስክ መሬት ጥበቱን ግምት ውስጥ በማስገባት ባለሀብቱ ባቀረበው ቢዝነስ ፕላን መሰረት የመሬት አቅርቦት እንዲመቻችለት የድጋፍና ክትትል ስራዎች የሚሰሩ ይሆናል። የመኖ አቅርቦትን ለማሻሻል በቀጣይ አምስት ዓመታት በአዲስ ወደ ስራ ለሚገቡ 275 ባለሀብቶች እያንዳንዳቸው 6 ሄ/ር ከአርሶ አደሮች ጋር የኮንትራት ውል ስምምነት በመፈራረም ወደ ስራ እንደሚገቡ ይሰራል።

በሥጋ ሀብት ልማት

በተመሳሳይ መልኩ የቀይ ስጋ ምርት የሚሳተፉ የባለሀብቶችን ቁጥር ለማሳደግ በቀጣይ በመካከለኛ ስፔሻላይዝድ የድለባ ስራ (የዳልጋ ከብት እና የበግና ፍየል) ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ሲሆን ትግበራው የማደለብያ ጣቢያዎችን ቁጥር በመጨመርና በእያንዳንዱ ድለባ ጣቢያ የሚኖሩ በስጋ ምርታቻው የሚመረጡ የሀገር በቀል እንስሳት ቁጥር በማሳደግ፣ የስልጠናና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ድጋፍን በማሻሻል እና የገበያ ትስስርን በማጠናከር የሚከናወን ይሆናል። በዚህም መሰረት የመካከለኛ ስፔሻላይዝድ የዳልጋ ከብት ድለባ ባለሀብት በ2012 ካለበት 404 ቁጥር በአማካይ በዓመት 10% በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 604 ለማድረስ ይሰራል። የበግና ፍየል እርባታ/ድለባ ባለሀብት በ2012 ካለበት 65 ቁጥር በአማካይ በዓመት 15 በመቶ በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 105 ለማድረስ ይሰራል።

በዚህም መሰረት የቀይ ስጋ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ተግባራትን በተለይም የመኖ አቅርቦት ዋናው ሲሆን ለዚህም የተቀነባበረ መኖ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግና በዚህ ሚሳተፉ ባለሀብቶችን አቅም መገንባት፤ የተፈጥሮ ግጦሽ ልማትን ማሳደግ፤ የሰብልና ኢንዱስትሪ ተ/ምርትን ማሻሻል ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሲሆን ለዚህም የሚስፈልገውን መሬት በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በኩል እንዲቀርብ አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል።

ሌላው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ የራንች ልማት ሲሆን በራንች ኢንቨስትመንት/ዳልጋ ከብት እና በግና ፍየል እርባታ/ መሳተፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች ሰፋፊና ቆላማ መሬት ባለባቸው ክልሎች /ሱማሌ፣

አፋር፣ ቤንሻንጉል፣ጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ አማራ፣ ትግራይ/ እንዲያለሙ ጥረት ይደረጋል። በቀጣይ አምስት አመታት በአዲስ ከሚሳተፉ ባለሀብቶች ውስጥ 5 ባለሀብቶች በራንች ኢንቨስትመንት እንደሚሳተፉ ታሳቢ በማድረግ የመኖ ልማቱን ጨምሮ ለአንድ ባለሀብት ግምታዊ የመሬት መጠን 500 ሄ/ር እንደሚያስፈልግ መነሻ ተወስዶ በአጠቃላይ 2500 ሄ/ር በክልሎች በኩል እንደሚቀርበርብ ታሳቢ ተደርጓል፡

በእንቁላል እና በስጋ ዶሮ ሀብት ልማት

በቀጣይ 5 ዓመታት በስፔሻላይዝ የዶሮ እርባታ የሚሳተፉ ባለሀብቶች በ2012 ካለበት 189 ቁጥር በአማካይ በዓመት 20% በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 379 ለማድረስ ይሰራል። ትግበራው የእርባታ ማዕከሎችን ቁጥር በመጨመርና በእያንዳንዱ እርባታ ማዕከል የሚኖሩ በስጋና እንቁላል ምርታቻው የሚመረጡ የዶሮ ቁጥር በማሳደግ፣ የስልጠናና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ድጋፍን በማሻሻል እና የገበያ ትስስርን በማጠናከር እንዲሁም ለዶሮ መኖነት የሚያገለግሉ በተለይም በቆሎና አኩሪአተር ልማት ሚሆን መሬት አቅርቦትን በማመቻቸት ሚከናወን ይሆናል።

በአኳካልቸር ልማት

በተለያየ ዓሳ ምርት እሴት ሰንሰለት ውስጥ ለሚሳተፉ ባለሀብቶች በ2012 ካለበት 10 ቁጥር በአማካይ በዓመት 10% በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 15 ለማድረስ ይሰራል። ትግበራው በዚህ ንዑስ ዘርፍ ለመሰማራት ድጋፍ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች የስልጠና እና የምክር እንዲሁም ከሚመለከታቸዉ የክልልና ሌሎች አካላት ጋር በመሆን ኢንቨስትመንቱ የሚጠናከርበትን አሰራር እንዲፈጠር ይደረጋል።

በማር ሀብት ልማት

በማር ማምረትና ማቀነባበር የተሰማሩ ባለሃብቶች በ2012 ከነበረበት 46 በዓመት 10 በመቶ በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ወደ 71 ለማሳደግ ይሰራል። ትግበራው በዘርፉ የሚሳተፉ ባለሀብቶችን በማበረታታት፣ የስልጠናና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ድጋፍን በማሻሻል እና የገበያ ትስስርን በማጠናከር የሚከናወን ሲሆን ለዚህም አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል፡

በእንስሳት መኖ ልማት

በመኖ ልማት ላይ የሚሰማሩ ባለሀብቶች ቁጥር በ2012 ካለበት 8 በአማካይ በዓመት 15 በመቶ በማሳደግ በ2017 ዓ.ም መጨረሻ ወደ 14 ለማድረስ ይሰራል። ትግበራው ለመኖ ዘር ማባዛትና መኖ ልማት የሚሆን መሬት በማግኘት ረገድ የሚታየው ቢሮክራሲ እንዲፈታ ከክልሎች ጋር በቅንጅት ይሰራል። በተጨማሪም የስልጠናና ቴክኖሎጅ አቅርቦት ድጋፍን በማሻሻል እና የገበያ ትስስርን በማጠናከር ዙሪያ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። ለተለያዩ ስነምህዳሮች ተስማሚ የሆኑ የመኖ ዕፅዋት መስራት ዘሮችን አባዝተው የሚያቀርቡ የግል ባለሀብቶች እንዲኖሩ ክትትል ይደረጋል። ሰፋፊ መሬት ባሉበት አካባቢ በመኖ ልማት/በቆሎና አኩሪ አተር፣ሲናር.../ እንዲሰማሩ አስፈላጊው ድጋፍ የሚደረግ ሲሆን በዚህም መሰረት ለአንድ ባለሀብት 500 ሄ/ር ታሳቢ በማድረግ በቀጣይ አምስት ዓመታት 5 አልሚዎች በድምሩ 25000 ሄ/ር መሬት በክልሎች በኩል እንደሚተላለፍ ታሳቢ ተደርጓል።

ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

ለባለሀብቱ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ ምርትና ምርታመነትን ማሳደግ እና እንስሳትና የእንስሳት ውጤቶች ለሚያቀናብሩ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች ተጠቃሚዎች ማቅረብ ቁልፍ ተግባር ሲሆን በዚህም በእያንዳንዱ የምርት ዓይነት በ2012 ከተደረሰበት በመነሻነት በመውሰድ በ2017 መጨረሻ የእርድ ፍየል ከ60529 ወደ 76263፣ እርድ በግ ከ21823 ወደ 28986፣ የዳልጋከብት ከ19705 ወደ 30995 ፣ስጋ ዶሮ ከ98245 ወደ 194525፤ እንቁላል በሚ/ን ቁጥር ከ5.4 ወደ 8.4፣ጥሬ ወተት በሺ/ሊ 3918 ወደ 5222፣ ጥሬ ማር በቶን ከ72.8 ወደ 114.4፣ የመኖ ምርት በሺ/ኩ /በቆሎ፣ አኩሪአተር፣ሲናር/ ከ38 ወደ 65.8 ለማድረስ ግብ ተጥሏል።

ለእንስሳት ኢንቨስትመንት ምቹ የልማት ሁኔታ መፍጠር

እንስሳት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ ባለሀበቶችን ለመሳብ የመንግስት አቅም በፈቀደ መጠን መሰረተ ልማቶችን(የኃይል፤የመንገድ፣ የውሃ፣ የቴሌኮም) ለማሟላት የተለያዩ ጥረቶችና እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ መቆየታቸውና አሁንም በመደረግ ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ የኢንቨስትመንቱን የስራ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት ለኢንቨስትመንት የሚውሉ አካባቢዎችን በመለየትና ቅድሚያ በመስጠት ረገድ ባለው የአፈጻጸም ችግር፤ በአንድ ጊዜ ሁሉም አካባቢ ለማሟላት ካለው የመንግስት አቅም ውስንነት አኳያ መሰረተ ልማት ባለመሟላቱ ለኢንቨስትመንቱ ዋና ማነቆ ሆኖ ይታያል፡፡ በመሆኑም በጥናት ላይ ተመስርቶ ለኢንቨስትመንት የሚውሉ አካባቢዎችን በመለየትና ቅድሚያ በመስጠት በሚመለከታቸው ተቋማት በኩል መሰረተ ልማት እንዲሟሉ የማድረግ ስራ እንዲከናወን የክትትልና ድጋፍ እንዲሁም ቅነጅታዊ አሰራር የሚጠናከር ይሆናል፡፡

የግብዓት አቅርቦትን ማሻሻል

በተለያየ ጊዜ በተደረጉ የዳሰሳ ጥናቶች ከተለዩት የግብዓት አቅርቦት ችግሮች መካከል ዋናዋናዎቹ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎች (የወተት፤ የስጋ እና የዶሮ) አቅርቦት፤ የተሻሻሉ የእንስሳት መኖ ዘር እና የመድኃኒት አቅርቦት ችግር ሲሆኑ በዚህም ምክንያት በዘርፉ በኢንቨስትመንት የተሰማሩ ባለሀብቶች ምርትና ምርታማነት ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም አዳዲስ ራንቾችን በማስፋፋት የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን የማባዛትና አቅርቦቱን የማሻሻል የግል ባለሀብቱ በዚህ ዘርፍ እንዲሰማራ ተገቢውን ድጋፍ የማድረግ ከተሻሻሉ ዝርያዎች በተጨማሪ ውጤታማ የሆኑ ሀገር በቀል ዝርያዎች በመለየት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡ በመኖ ልማት እና ማቀነባበር ለተሰማሩ ባለሀብቶች ሁሉንአቀፍ ድጋፍ ይደረጋል፤ ጥራታቸውንና ደረጃቸውን የጠበቁ የእንስሳት ክትባቶችና መደኃኒቶች በሚመለከተው አካል በኩል ለባለሀብቱ እንዲቀርቡ ግብዓት አቅራቢውን እና ባለሀብቱን የማስተሳሰር ስራ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

የብድር አቅርቦትንና ከቀረጥ ነጻ ማበረታቻዎችን ማሻሻል

በልማት ባንክና በንግድ ባንኮች ያለው የብድር አቅርቦት ውስብስብ ችግር ያለበትና ረጅም ጊዜ የሚወስድ መሆን ከመንግስት የተፈቀደውን የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ ፍታዊነት የጎደለው መሆን የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በጥናት ላይ በመመስረት በእንስሳት ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶች የብድር እና የቀረጽ ነጻ አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበትን ስርአት መዘርጋት እና በዚህ ዙሪያ ያሉ ማነቆዎች እንዲፈቱ የማድረግ ለዚህም ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር እና ክትትልና ድጋፍ ስራዎችን የማጠናከር ስራ ይሰራል፡፡

የባለሀብት እንስሳትና ዓሳ ልማት ከአርሶና አርብቶአደር ጋር ማስተሳሰር

አነስተኛአርሶና አርብቶ አደሮችን እንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ከሰፋፊ አምራቾች ጋር የምርት ትስስር በመፍጠር የሚገኘውን የሁለትዮሽ ጠቀሜታ በአግባቡ ለመጠቀም በሚቀጥሉት አምስት አመታት በትኩረት ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በተለይም በረቂቅ ደረጃ ላይ ያለውን የግብርና ምርት ውል ህግ ተግባራዊ ማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡

2.2.2.2 ውጤታማ የባለሀብት እንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት

የሰፋፊ እስሳትና አሳ ሃብት ልማት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚኖረው የሚታወቅ ሲሆን አሁን ያለበት የውጤታማነት ደረጃ ሲታይ ግን አጥጋቢ እንዳልሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተለይም በመሬት አቅርቦትና አጠቃቀም ችግር ምክንያት እየተገኘ ያለው ምርት ዝቅተኛ ነው፡ ፡ ቀደም ሲል በአራት ክልሎች/ኦሮሚያ፣አማራ፣ትግራይና ደቡብ/ የተደረገው የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው ኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተው ወደ ስራ ለገቡና በተለያዩ የእንስሳት ኢንቨስትመንት መስክ ለተሰማሩ 620 ባለሀብቶች 3963.30 ሄ/ር መሬት የተላለፈላቸው ሲሆን ይህም በተለያዩ ማነቆዎች ውስጥ ያለ መሆኑን በተለይም የማሰፋፊ ቦታ የሌለው፤ በከተሞቹ የረጅም ጊዜ ማስተር ፕላን የተደገፉ አለመሆን እና የከተማ መሬት የሊዝ ዘመንና ኪራይ ክፍያ ተመን የእንስሳት ኢንቨስትመንት ባህሪ ግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆን እንዲሁም የመሰረተ ልማት ያልተሟላለት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት ነባር ባለሀብቱ የወሰደውን መሬት በአግባቡና ውጤት

በሚያመጣ መልኩ ስራ ላይ እንዲያውል ለማድረግ ሙያዊ ክትትልና ድጋፍ ስራዎች ይከናወናሉ፤ የድጋፍ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ከክልሎች እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻዎች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት በመሬት አጠቃቀም ዙሪያ የሚስተዋሉ ችግሮች የሚፈቱበት አሰራር ይዘረጋል።

በመሆኑም በሚቀጥለው አምስት አመታት ክትትልና ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ የእንስሳትና አሳ ሃብት ልማት ምርታማነት ፣ አካታችነትና ደህንነትን ማሻሻል በትኩረት ይሰራል። አሁን የሚገኙበትን የውጤታማነት ደረጃ በማጥናት በሚቀጥለው አምስት አመታት በ25 በመቶ ለማሻሻል ኢላማ ተቀምጧል።

2.2.3 የእንስሳትና ዓሳ ምርት ግብይት

የእንስሳትና ዓሳ ምርት ግብይት ስርዓትን ዘመናዊ በማድረግና ያሉ መሰረታዊ ማነቆዎችን በመፍታት ንዑስ ዘርፉ ለሃገራዊ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ለማስቻል በቀጣይ አምስት አመታት ትኩረት ተሰጥቶ ዘርፈ ብዙ ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል። የእንስሳትና ዓሳ እርባታው ገበያ መር እንዲሆን (የሃገር ውስጥ ገበያ፣ ኢንዱስትሪው እና የወጪ ንግዱ) በሚፈልገው መሰረት እንዲመረት ጥረት የሚደረግ ሲሆን ምርቱ በቀጥታ ለተጠቃሚው እንዲደርስ የገበያ ማስፋፊያ እና ትስስር ስራዎች ይከናወናሉ። በተጨማሪም ግብይቱን በዘመናዊ መንገድ እንዲመራ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶች (የገበያ ማዕከላት፣ ማከማቻ ማዕከላት) እና ሌሎች እንዲሟሉ ይደረጋል። የፋይናንስ እጥረት የሚታይባቸውን ንዑስ ዘርፎችና የግብይት ተዋንያን በጥናት በመለየትና ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በቅርበት መስራት የተጠናከረ የግብይት ፋይናንስ ስርዓት በመዘርጋት ለግብይቱ የሚያስፈልግ የብድር አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል። በመሆኑም በቁም እንስሳት፣ ወተት፣ ዶሮ፣ ማር እና አሳ ምርቶች ላይ በትኩረት ለመስራት አቅጣጫ ተቀምጧል።

የቁም እንስሳት የወጪ ንግድ አቅርቦት

በ2012 የተደረሰበትን የዳልጋ ከብት 58,051 ፣ በግ 249 930፣ ፍየል 13,208 ፣ ግመል 46,205 በሚቀጥሉት በ2017 አቅርቦቱን የዳልጋ ከብት 84,992 ፣ በግ 365,923 ፣ ፍየል 19,338 ፣ ግመል 67,649 ለማድረስ ዒላ ተቀምጧል።

2.2.3.1 የእንስሳትና ዓሳ ምርት ግብይት የምክር አገልግሎት (business advisory services)

የእንስሳትና ዓሳ ምርት ግብይት ምርቶችን ገበያው በሚፈልገው ጥራት፣ መጠንና ወቅት ለማምረት እንዲቻል ከዓለም አቀፍ ንግድ አመራር ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን የምክር (business advisory services) ወቅታዊና ተከታታይነት ባለው መንገድ መስጠት አፈጻጸሙ እንዲያድግ ይደረጋል። በዚህም መሰረት እነዚህ ምርቶች ገበያን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲመረቱ ተዋንያኑ በአዋጭነት ጥናት፣ በንግድ ስራ ዕቅድ አዘገጃጀት፣ በንግድ ስራ እንቅስቃሴ አመዘጋገብ ሁኔታ፣ በንግድ ተቋምና የሰው ኃይል አስተዳደር፣ ክትትልና ግምገማ፣ የፋይናንስ ምንጮችን ማስፋትና አስተዳደር፣ የምርት ፕሮፋይል አዘገጃጀት፣ የምርት ትውውቅ ስራዎች፣ የንግድ ስራ ስነ ምግባሮች (Business ethics) እና ሌሎች በንግዱ ላይ ጉልህ ሚና የሚኖራቸው ስልጠናዎች እየተለዩ በስፋት እንዲሰጡ ይደረጋል።

የቁም እንስሳት እርባታው ገበያ ተኮር በሆነ መልኩ እንዲከናወን ለንዑስ ዘርፉ ትኩረት በመስጠት ተቀባይ ሃገራት በሚፈልጉት ጥራትና መጠን ለማዘጋጀት እንዲቻል ከልማት ዘርፉ ጋር በቅንጅት በመስራት ለእርባታ ተስማሚ የሆኑ ቦታዎችን በመለየትና ለባለሃብቶች የሚተላለፉበትን አሰራር በመዘርጋት ሰፋፊ ኮመርሻል ራንቾች (Commercial Ranches) እንዲቋቋሙ በማድረግና የተጠናከረ ክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በማከናወን በእንስሳት አቅርቦት ላይ የሚስተዋለውን እጥረት እንዲቀረፍ ይደረጋል።

የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ ወቅታዊና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮችን በማዘጋጀት ለክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የግብይት መዋቅር አመራሮችና ፈፃሚዎች፣ ለግብይት ተዋንያንና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ግንዛቤ ይሰጣል። የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓት ዝርጋታ በተመለከተ በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ክትትል እና ግምገማ ማካሄድ፣

በክትትልና ግምገማው ወቅት የታዩ መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና በሌሎች አካባቢ እንዲሰፉ ማድረግ እና ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአፈጻጸም ግብረ መልስ በመስጠት፣ ግብይቱ በተቀመጠው አሰራር ስርዓት መሰረት እንዲመራ በማድረግ አርቢውንና ህጋዊ የግብይት ተዋንያኑን ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረውን የፀረ ኮንትሮባንድ እንቅስቃሴ በተፈጠሩት የፌደራልና የክልል ፀረ-ኮንትሮባንድ አደረጃጀቶችን በማጠናከርና በሚፈለገው ደረጃ በመጠቀም ህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን በመከላከል ህጋዊ የቁም እንስሳት ወጪ ንግድ ላይ የሚያሳድረውን ከፍተኛ ተጽዕኖ በመቀነስ የቁም እንስሳት ወጪ ንግድ አቅርቦት አፈጻጸም እንዲጨምር ይደረጋል፡፡ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከጉሙሩክ ኮሚሽን እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ በመሆን ለህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ በምክንያትነት የሚጠቀሰውን የጠረፍ ንግድ አሰራር ሥርዓት ግንዛቤ እንዲፈጠርና በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ከዝቅተኛ የመሸጫ ዋጋ በታች የሚያስመዘግቡ የቁም እንስሳት ላኪዎች ላይ ከብሔራዊ ባንክና ንግድ ባንኮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን በመስራት እና አሰራሩን በሚመለከት የወጡ መመሪያዎች በአግባቡ እንዲፈጸሙ በማድረግ ከወጪ ንግዱ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

የስጋ ወጪ ንግድ አፈጻጸምን ለማሳደግ ለስጋ ላኪ ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያገለግል የእንስሳት አቅርቦት በዘላቂነት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም አርብቶ አደሩ ገበያ መር የአረባብ ዘዴ እንዲከተል የገበያ ኤክስቴንሽን ስራዎች፣ ግንዛቤ ማስጨበጫዎች፣ ልዩ ልዩ የክትትልና ድጋፎች ስራዎች፣ የገበያ መረጃ ወቅታዊና ተደራሽ የማድረግ ስራዎች በስፋት ይከናወናሉ፡፡ ሰፋፊ የእንስሳት እርባታ ቦታዎችን በመለየትና ባለሃብቶች የሚያገኙበትን አሰራር በመዘርጋት እና ኮመርሻል ራንች (Commercial Ranches) በማቋቋም የስጋ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን እንስሳት በመጠንና በጥራት በማዘጋጀት የአቅርቦት እጥረቱ እንዲቀረፍ ይደረጋል፡፡

ጥሬ ቆዳና ሌጦ በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለቆዳ ኢንዱስትሪው በግብዓትነት እንዲቀርብ ለማድረግ በምርት ግብይት ላይ ያሉ ዋና ዋና ችግሮች እንዲቀረፉ በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ስርዓት በተሟላ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ የምርት ብክነት በመቀነስ የተሻለ የጥራት ደረጃ ያለው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ለቆዳ ኢንዱስትሪው እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡

የዶሮና ዶሮ ምርት በዘላቂነትና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለገበያ እንዲቀርብ ለማስቻል በግብይቱ ዙሪያ የሚስተዋሉ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን መፍታት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ግብይቱን በመሰረታዊነት ለመምራት የሚያስችል ዘመናዊ የዶሮና ዶሮ ምርት ግብይት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም አሁን በግብይቱ ላይ የሚስተዋሉ መሰረታዊ ችግሮችን ለመለየት የሚያስችል መነሻ ጥናት በማካሄድ ዘመናዊ የዶሮና የዶሮ ምርት (ስጋና እንቁላል) ግብይት ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ የግብይት ስርዓቱ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲደረግ በየደረጃው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

የማር ምርት ግብይትን ለመደገፍ ክፍተኛ አምራች በሆኑ አካባቢዎችን በገበያ የሚፈልግውን ጥራትና ተከታታይነት ያለው ምርት አቅርቦትና አያያዝ እንዲኖር የሚያስችል ምክርና ግንዛቤ ማስጨበጫ እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በትኩረት ይሰራሉ፡፡ በተለይም የማርት ምርት በገበያ የሚመራ አቅርቦትን ለመፍጠር የግብዓት አጠቃቀም ምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በሃገራችን በተለያዩ የውሃ አካላት እየተመረተ እና በህገ ወጥ መንገድ ወደ ጎረቤት ሃገራት እየወጣ ያለውን የዓሳ ምርት ዘመናዊ የግብይት ሥርዓት በመዘርጋት እና የገበያ ትስስር በመፍጠርና የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን በማሟላት ንዑስ ዘርፉ ለሃገራዊ ኢኮኖሚ እና የውጭ ምንዛሬ ግኝት ዕድገት አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ይሰራል፡፡

2.2.3.2የእንስሳት ልየታ፣ ምዝገባና የኋልዮሽ ክትትል አሰራርን ማጠናከር

በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ማለትም በ2017 መጨረሻ ዓመት ወደ ዉጭ ሀገር የሚላኩ የዳልግ ከብት በቁም እንስሳትና በስጋ 100 በመቶ በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት እንድያልፊ ይሰራል፡፡

በተጨማርም ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ በግ እና ፍየል (በቁምና በስጋ መልክ) በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት እንዲያልፉ የዳታቤዝ እና የአጠቃቀም ስርዓት በመመስረት የሚሰራ ይሆናል። በዚህም መሰረት ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ በግ እና ፍየል (በቁምና በስጋ መልክ) 50 በመቶ በእንስሳት ልየታና ምዝገባ ስርዓት እንዲያልፉ ይሰራል።

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በገባችባቸው የእንስሳትና ውጤቶች የውጭ ገበያዎች ለመቆየትና በእነዚህ ገበያዎች የደንበኞችን መሰረት ለማስፋት ፣ እንዲሁም በአጭር ጊዜ መስፈርቶቻቸውን ለማሟላት የምንችላቸውንና የተሻለ የሚከፍሉ አማራጭ ገበያዎችን በመለየትና በመግባት የላቀ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት ይደረጋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የእንስሳት ኳራንቲን፣ ኢንስፔክሽንና ሰርቲፊኬሽን ሥርዓቱን በተቀባይ አገሮች መስፈርትና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ ከማጠናከር ጎን ለጎን ከዚህ በፍት የትግበራ ሂደቶቹ የተጠናቀቀ የእንስሳት ልየታ፣ ምዝገባና ክትትል (Livestock Identification and Traceability) ሥርዓት ትግበራን በስፍት ተግባራዊ በማድረግ የሚሰራ ይሆናል። የእንስሳት ልየታና ምዝገባ በሚካሄድባቸዉ አካባብዎችም የእንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጅዎችና አሰራሮች ተጠናክረዉ የሚሰሩ ይሆናል፤ የእንስሳት መለያ ወይም ታግ ማዕከላትም በእነዚህ አካባብዎች እንድመሰረቱ በማድረግ የታግ አቅርቦት ቀላልና በቅርበት የሚገኝ እንድሆን ይሰራል። የእንስሳት ልየታና ምዝገባ አሰራርን በተመለከተየተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች በየደረጃዉ ላሉ ባለድርሻ አካላት የሚሰጡ ይሆናል፤ የህግ ማዕቀፎችና ጸድቁ እንድተገበሩ ይደረጋል። በሚቀጥሉት 5 ዓመታት የእንስሳት ልየታና ምዝገባ አሰራር ከዚህ በፍት ለመከራ ከተለዩ ቦታዎች በተጨማር በማስፋት በለሎች የሀገርቱ አከባብዎች የሚተገበር ይሆናል፤ አሰራሩ ለበጎችና ፍየሎችም መጠቀም እንድቻል ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

2.2.3.3 ውጤታማ የገበያ ማስፋፊያ እና ትስስር ስራዎችን መስራት

አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮች ላመረቷቸው የእንስሳትና አሳ ምርቶች ዘላቂና አስተማማኝ የገበያ ትስስር ሲፈጠርላቸው ምርታቸውን ያለስጋት እንዲያመርቱና የተሻሻሉ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ጥራትን መሰረት ያደረገ ምርት እንዲያመርቱ ይበረታታሉ። አነስተኛ አርሶ/አርብቶ አደሮችን ከህ/ሥራ ማህበራት፣ ከነጋዴዎች፣ ከአቀነባባሪዎች እንዲሁም ከላኪዎች ጋር በማስተሳሰር የምርቶቻቸው ተቀባዮች የሚፈልጉትን መጠን፣ በሚፈልጉት ጥራትና ወቅት እንዲያገኙ በማስቻል በሙሉ አቅማቸው እንዲሰሩ ያስችላቸዋል። በተጨማሪም አርሶ/አርብቶ አደሮችን በሀገራችን በመስፋፋት ላይ ካሉት አግሮ-እንዱስትሪያል ፓርኮችና ከምርት አቀነባባሪዎች ጋር የማስተሳሰር ተግባራት ይከናወናሉ። ትስስሩ የእንስሳትና ዓሳ ምርትን ጥራት፣ የአመራረት ቅልጥፍናና ተወዳዳሪነት እንዲሁም የግብርና እና አግሮ-ኢንዱስትሪ ተመጋጋቢነት በማሳደግ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር እውን ለማድረግ ወሳኝ ከመሆኑም በላይ የእንስሳትና ዓሳ አምራቾች ገበያ ተኮር የግብርና ምርቶችን ወደ ማምረት በማሸጋገር የእንስሳትና ዓሳ ምርት ከሚያዘጋጁ፣ ከሚያቀነባብሩ፣ እሴት ከሚጨምሩ አግሮ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከትላልቅ ገዥዎች ጋር ቀጣይነት ያለው ትስስርን ይፈጠራል። በመሆኑም በ2012 በጀት ዓመት ለቁም እንስሳት ወጪ ንግዱ የቀረበውን ዳልጋ ከብት 58,051፣ በግና ፍየል 263,138 እና ግመል 46,205 እንስሳት በ2017 በጀት ዓመት ዳልጋ ከብት 211,428 ፣ በግና ፍየል 1,202,472 ፣ ግመል 64,897 ለወጪ ንግድ ለማቅረብ ኢላማ ተቀምጧል።

የቁም እንስሳት ግብይት መሰረተ ልማቶችን፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ስራዎች፣ ያሉንን የእንስሳት ዝርያዎችና ምርታማነታቸውን እና ሌሎች ጠንካራ ጎኖችን ለገዢ ሀገራት በስፋት በማስተዋወቅ በነባር የቁም እንስሳት ገዢ ሀገራት ያለንን የገበያ ድርሻ ለማሳደግ ብሎም አዳዲስ መዳረሻ ገበያዎችን ሰብሮ ለመግባት የሚያስችሉ የገበያ ማስፋፊያ እና ትስስር ስራዎች ይከናወናሉ። በተለይም የሃገራችን የቁም እንስሳት ጤና አገልግሎት ለወጪ ንግዱ መስፋፋት መሰረታዊ ጉዳይ በመሆኑ የጤና አገልግሎት አሰጣጥና ተደራሽነት በማሻሻል በዓለም አቀፍ እንስሳት ጤና ተቋም (OIE) የተቀመጡ ዝቅተኛ መስፈርቶችንና የገዥዎቻችንን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል መንገድ ተግባራዊ ይደረጋል። ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በነባር እና በተመረጡ አዳዲስ መዳረሻ ገበያዎች ከሚገኙ ኤምባሲዎች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ኤግዚቢሽኖችና ባዛሮች በመሳተፍና በሀገራችንም እንዲዘጋጅ በማድረግ እንዲሁም ሌሎች የተቀናጁና ጠንካራ የገበያ ማስፋፊያ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቶ

ይሰራል፡፡ በወጪ ንግዱ ላይ የሚስተዋለውን የቁም እንስሳት አቅርቦት እጥረት ለመፍታት የሚያስችል የአቅርቦትና ፍላጎት ዳሰሳዎችን በማድረግ በአቅራቢዎችና ላኪዎች መካከል በጽሁፍ ውል ላይ የተመሰረተ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፤ በትስስሩ ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን በመለየት የክትትልና ድጋፍ ስራዎች ይከናወናሉ፡፡

በቁም እንስሳት ግብይቱ የህብረት ስራ ማህበራትን ሚና ለማሳደግ የተደራጁ የቁም እንስሳት ግብይት ህብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከርና አዳዲስ ህ/ስራ ማህበራትን በአርብቶ አደር አካባቢዎች በማቋቋም፣ የብድር አቅርቦትን በማመቻቸት፣ የስራ እቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ የማህበራቱን የአመራር አካላትን የመምራት ብቃት በማሳደግና ግልፀኝነት ያለውን አሠራር በማስፈን፣ ማህበራቱን ከእንስሳት አድላቢዎች እና ላኪዎች ጋር በኮንትራት ውል ማስተሳሰር፣ ትስስሩን በተመለከተ ከክልሎች ጋር የጋራ መድረክ በመፍጠር የተከናወኑ ስራዎችና የተገኙ ውጤቶችን በጋራ መገምገም፣ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት የቁም እንስሳትን በቀጥታ ከአርቢዎች ወደ ላኪዎች የሚያቀርቡበትን ብሎም እራሳቸው በቁም እንስሳት ላኪነት እንዲሰማሩ በማደረግ ከፍተኛ ሚና እንዲኖራቸው ይሰራል፡፡ በአጠቃላይ የቁም እንስሳቱ ከሚገኝበት አካባቢ ያሉ አድላቢዎችን፣ ነጋዴዎችንና ህብረት ስራ ማህበራት ያሉባቸውን የፋይናንስና ሌሎች ችግሮችን እንዲፈቱ በማድረግ ከስጋ ላኪ ቄራዎች ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር አቅርቦቱን አስተማማኝ ለማድረግ ጥረት ይደረጋል፡፡

ስጋ ላኪ ቄራዎች እና አቅራቢ ነጋዴዎች ለአርድ የሚሆኑ የስጋ እንስሳቶችን ከግብይት ማዕከላት ከገዙ በኋላ ወደ መዳረሻ ቦታዎች እስከሚጓዙ ድርስ የጤና እና ጥራት እንከን ሳያጋጥማቸው በአቅራቢያው የሚቀየቡበት የተለየ ቦታ እንዲኖራቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ቦታ የሚያገኙበትን አሰራር ይፈጠራል፡፡ ስጋ ላኪ ቄራዎች በግብዓትነት የሚገዟቸውን የቁም እንስሳት ገዥዎቻቸው በሚፈልጉት መጠንና የጥራት ደረጃ መሰረት በማዘጋጀት በአቅርቦቱ ላይ የሚታየውን መሰረታዊ ችግር ለመፍታት ብሎም ለመኖ የሚወጣውን ከፍተኛ ወጪ እንዲቀንስ በማድረግ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪነታቸውን ለመጨመር የመኖ ማልሚያ ቦታዎች የሚያገኙበትን አሰራር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

ጥሬ ቆዳና ሌጦ ላይ የተሰማሩ የግብይት ተዋንያን በግብይት ስርዓቱ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ከቆዳ ኢንዱስትሪው ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር አጭር የግብይት ሠንሰለት ተግባራዊ በማድረግ የአምራቹ እና ሌሎች የግብይት ተዋንያንን ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

የወተትና ወተት ተዋጽኦ ጥራቱና ደህንነቱን በጠበቀ መንገድና የግብይት ተዋንያን ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ በሚችል መንገድ የወተትና ወተት ተዋጽኦ ግብይት የህግ ማዕቀፍ (አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና የአሰራር ማንዋል) እንዲቀረጽ በማደረግ የግብይት ስርዓቱ በሚፈለገው ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች በስፋት ይከናወናሉ፡፡ በተለይም የወተት ምርት ግብይት ከባዕድ ነገሮች ጋር ሳይቀላቀል ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ ለተጠቃሚው እንዲደርስ ለማስቻል የምርት ጥራቱን መሰረት ያደረገ የክፍያና የምርት ርክክብ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

የወተትና ወተት ተዋጽኦ ግብይት ስርዓትን በመጠቀም አቀነባባሪዎች ያለባቸውን የምርት አቅርቦት ችግር ሊፈታ በሚችል መልኩ የገበያ ትስስር ስራዎች የሚከናወኑ ሲሆን በዘላቂነት ሊፈታ የሚችል ዘመናዊና በኤሌክቶሮኒክስ ዘዴ የታገዘ የወተት ገበያ መረጃ ስርዓት በመንግስትና በግሉ ዘርፍ ትብብር (PPP) በመዘርጋት እና የማስተዋወቅ ስራ በመስራት የምርት አቅርቦትና ፍላጎት መረጃዎች ለተጠቃሚዎች ተደራሽ ይደረጋል፡፡ አርሶ ወይም አርብቶ አደር ወተት አምራቾች ምርታቸውን በተደራጀ ሁኔታ ለገበያ ማቅረብ እንዲችሉ በህብረት ስራ ማህበር የሚደራጁበትን አሰራር በመፍጠርና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ የምርት ጥራቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ወተት ለአቀባባሪዎች በቀጥታ እንዲደርስ በውል ላይ የተመሰረተ የገበያ ትስስር ይፈጠራል፡፡

ዶሮና የዶሮ ምርት ግብይትን ለማሻሻል በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በዶሮ እርባታ የተሰማሩ አርቢዎችን ፕሮፋይል በማዘጋጀት ከአቀነባባሪ ድርጅቶችና ተጠቃሚዎች ጋር በውል ላይ የተመሰረተ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ የዶሮና ዶሮ ምርት አቅርቦትና ፍላጎትን ሊፈታ የሚችል ዘመናዊ የገበያ መረጃ

ስርዓት በመንግስትና የግሉ ዘርፍ ትብብር ለተጠቃሚው በቀላሉ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

የማር ምርት ግብይትን ለማሻሻል ከማር አቀነባባሪ ኢንዱስሪዎች በግብዓትነት የሚቀርብ ጥሬ ማር ምርት አቅርቦት በመጠንና በጥራት እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ ሰፋፊ የመንግስት ጥብቅ ደኖችን መሰረት በማድረግ ማር ለማምረት እንዲቻል ስራ አጥ ወጣቶችን በማደራጀት፣ ተከታታይ ስልጠናዎችን እና የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን በመስጠት፣ የፋይናንስ አቅርቦት በመፍጠር እና አዳዲስ ቴክኖሎጅዎች ጥቅም ላይ በማዋል፣ አስፈላጊውን የክትትልና ድጋፍ ስራዎችን በመስራት እና ዘላቂ ገበያ ትስስር በመፍጠር ለኢንዱስትሪው የጥሬ ማር ምርት ግብዓት አቅርቦት ችግር ለመፍታት ይሰራል፡፡ የህብረት ስራ ማህበራት በንብ ማነብ እና ማር ምርት ግብይት ስራዎች ላይ በቀጥታ እንዲሳተፉ በማድረግ ለገበያ የሚቀርበውን የማር ምርት ዕጥረት በጥራትና በመጠን እንዲሻሻል የተሻለ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ የማር አምራቾችን የገበያ ችግር ለመቅረፍና በህገ ወጥ እና ኮንትሮባንድ መንገድ ወደ ጎረቤት ሃገር የሚወጣውን የጥሬ ማር ምርት ለመቀነስ የገበያ ትስስር በዘላቂነት እንዲፈጠር የግብርና ኮንትራት ስርዓት (Contract farming system) ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የማር አምራቾች ምርትን በጥራት እንዲያመርቱና የምርት መጠንን ለመጨመር በሚል ከሌሎች ባዕድ ነገሮች ጋር መቀላቀልን (Product adulteration) እንዲቀንስ ለማስቻል በጥራት ላይ የተመሰረተ የክፍያ ስርዓት (Quality based payment system) እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም የጥሬ ማር ምርት አቅርቦት በ2012 በጀት ዓመት ከነበረበት 59 ሺህ ቶን በ2017 ወደ 95 ሺህ ቶን ጥሬ ማር ምርት ለአቀነባባሪዎች እንዲቀርብ ለማቅረብ ኢላማ ተቀምጧል፡፡

የአሳ ምርት ለሃገር ውስጥና ውጭ ገበያ ጥራቱን በጠበቀ መንገድ የሚቀርብበትን የዓሳ ምርት ግብይት ስርዓት የሚዘረጋ ሲሆን በተለይም የግብይት ሰንሰለቱ አጭር የሚሆንበትና አምራቹን እና ላኪውን ተወዳዳሪ ሊያደርግ የሚችል ስርዓት ይፈጠራል፡፡ በዚህም መሰረት ወጣቶችን በማደራጀት በዓሳ አምራችነት እንዲሰማሩና የፋይናንስ አቅርቦትና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ይሰራል፡፡

በተጨማሪም ቱሪቶችን ወደ የእንስሳትና ዓሳ ምርት ልማት አካባቢዎች የሚስቡ ተግባራትን በመለየትና ሥራ ላይ በማዋል የእንስሳትና ዓሳ ምርት ምርቶች የገበያ ትሥሥር ለመፍጠር እንዲሁም ለአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ እድልና የገቢ ምንጭ ለመፍጠር ይሠራል፡፡ ተደራሽ የሆኑ አካባቢዎችን በመለየት በዙ ወጪ በማይተይቅ መልኩ የአካባቢውን አርሶ/አርብቶ አደሮች ለቱሪስቶች መስህብ የሚሆኑ ቁሳቁሶችንና ባህላዊ አኗኗር አይቤዎችን እንዲሁም ፈሪሽ የእንስሳትና ዓሳ ምርት ውጤቶችን ለገበያ ማቅረብ ያስችላል፡፡

2.2.3.4 የግብይት መሰረት ልማት እንዲሟሉ ማድረግ

የቁም እንስሳት አድላቢዎችና ላኪዎች የመሬት እና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግር ከክልሎችና የሚመለከታቸው አካላትን ጋር በቅንጅት በመስራት የመሬት እና የመሰረተ ልማት አቅርቦትን ማረጋገጥ ብሎም በዘላቂነት ለቁም እንስሳት ማድለብና ማቆያ ብሎም ለእንስሳት መኖ ማልማት ስራ የሚውል መሬት ተለይቶ እንዲዘጋጅና ለባለሀብቶች እንዲተላለፍ በማድረግ የግብይት ተዋንያንን የማምረት ወጪ (Cost of Production) እንዲቀንስ በማድረግ ተዋዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

የቁም እንስሳት ግብይት በሚፈለገው ደረጃ እንዲፈጸም የሚያስችሉ የግብይት መሰረተ ልማቶች በተለይም በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት የትግበራ ዕቅድ በማዘጋጀት የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ለአርብቶ አደሩ ቅርበት ባላቸው ቦታዎች እንዲደራጁ በማስተባበርና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ እንዲሁም በግብይት ሥርዓቱ መሠረት ለተደራጁ የግብይት ማዕከላት አስፈላጊ የገበያ መሠረተ ልማቶችን እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ የግብይት ማዕላት ለአርብቶ አደሩ በቅርብት ሲቋቋሙ የገበያ ችግር በመኖሩ ምክንያት ወደ አጎራባች ሃገራት በህገ ወጥ መንገድ የሚወጣውን የቁም እንስሳት ላኪዎች በቀጥታ የሚገዙበት ዕድል ስለሚፈጥር በወጪ ንግዱ የገቢ ግኝት ጭማሪ ላይ አስተዋጽኦ ያድረጋል፡፡

በተጨማሪም የተጀመረውን የቁም እንስሳት ገበያ መረጃ ስርዓት በማጠናከር መረጃው ከሁሉም የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት እንዲሰበሰቡና ለአርቢውና ለግብይት ተዋንያኑ ተደራሽ የሆኑ የተለያዩ

የማሰራጫ መንገዶችን በመጠቀም ወቅታዊነቱን በጠበቀ መልኩ ማሰራጨት፣ የሀገር ውስጥና የውጭ ገበያው የሚፈለገውን የእንስሳት ዓይነት፣ ዝርያ፣ የጥራት ደረጃ፣ የገበያ ወቅቶችና የመሳሰሉ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀትና በመተንተን ለአርቢውና ለግብይት ተዋንያኑ ተደራሽ በማድረግ የምርት ሂደቱ ገበያ መር እንዲሆን እና በወጪ ንግዱ ላይ የሚስተዋለውን የቁም እንስሳት አቅርቦት ችግር በመፍታት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዲኖረው ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራበታል፡፡

ከጅቡቲ ጋር የሁለትዮሽ ስምምነት በማድረግ ከሃገራችን የሚላኩ የቁም እንስሳት ወደ መርከብ እስኪጫኑ ድረስ በጅቡቲ ወደብ የሚቆዩበት ምቹና በቂ የማቆያ ቦታ በተመጣጣኝ ክፍያ እንዲኖር ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚህም ላኪዎች ከዚህ በፊት በወደብ ማቆያ ቦታ የሚወጣውን ከፍተኛ የኪራይና የአገልግሎት ወጭዎችን ብሎም የሚደርስባቸውን ከፍተኛ እንግልት ስለሚቀንስላቸው ለጅቡቲና ሶማሊ ላንድ ከመላክ ባለፈ በቀጥታ ወደ መካከለኛው ምስራቅ መደራሻ ሃገራት እንዲልኩ ስለሚያስችል ወጪ ንግዱ አፈጻጸም መሻሻል ላይ ጉልህ ሚና አለው፡፡

በሃገራችን በመገንባት ላይ ያሉ የቁም እንስሳት ኳራንታይን ጣቢያዎች ግንባታቸው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ እንዲጠናቀቁ በማድረግ የሃገራችን የቁም እንስሳት ተቀባይ ሃገራት በሚፈልጉት የጥራት ደረጃ ተዘጋጅተው ምንጫቸው ኢትዮጵያ (Certificate of Origin) መሆኑን በሚገልጽ የሃገራችን የእንስሳት ጤና ሰርተፊኬት (Veterinary Health Certificate) አማካኝነት በቀጥታ ወደ ተለያዩ መዳረሻ ሃገራት የሚላኩበት አሰራር ይፈጠራል፡፡ በዚህም መሰረት ከዚህ በፊት በጅቡቲ የእንስሳት ኳራንታይን በማስገባት ለተጨማሪ የመኖ፣ ክትባት፣ ትራንስፖርት እና ሌሎች አስተዳደራዊ ወጪዎች የሚዳርጋቸው አሰራር እንዲቀረፍ በማድረግ ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

የእንስሳት ኳራንታይን አስተዳደርን በሚመለከት የሌሎች ሃገሮችን ተሞክሮ በመውሰድ የግል ዘርፉ ሙሉ በሙሉ ወይም ከመንግስት ጋር በቅንጅት (PPP) የሚሳተፍበት አሰራር በመዘርጋት የአገልግሎት አሰጣጡና አስተዳደሩ የተቀባይ ሃገራትን ፍላጎት ሊያሟላ በሚችል መንገድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

በህገ ወጥ መንገድ ግብይት ሲፈጸምባቸው ወይም ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳት በግብይት ህጉ መሰረት አስፈላጊውን አስተዳደራዊ እና ህጋዊ እርምጃዎች እስኪወሰዱ ድረስ የሚቆዩባቸው ማቆያ ጣቢያዎች (Holding Grounds) ከክልሎች ጋር በመቀናጀት በተመረጡ ዋና ዋና መውጫ በሮች (Trade Routes) በማቋቋም እና የውስጥ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉና አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ህገ ወጥ ንግዱ በህጋዊ ወጪ ንግዱ ላይ የሚያሳድረውን ከፍተኛ ጫና እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡

ዘመናዊና ተቀባይነት ያለው የቁም እንስሳት ትራንስፖርትን ስርዓትን በመዘርጋት የቁም እንስሳት ላኪዎችን የእንስሳት ትራንስፖርት ችግር ከትራንስፖርት ሚኒስቴርና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመስራት መፍታት እና ተፈፃሚነቱን በመከታተል የቁም እንስሳት የትራንስፖርት አቅርቦትና ስርዓት ችግር እንዲቀረፍ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም ህገወጥ ደላሎች ምክንያታዊ ያልሆነ የትራንስፖርት ዋጋ ንረት እንዳይከሰት የተሸከርካሪ ባለንብረቶችን ከቁም እንስሳት ላኪው ጋር በተሸከርካሪ ማህበራቶቹ በኩል በቀጥታ ከቁም እንስሳት ግብይት ተዋንያን ጋር ትስስር እንደፈጠር ይደረጋል፡፡

በዘላቂነት ግን የአለም አቀፍ የእንስሳት አያያዝና ትራንስፖርት ደረጃዎችን እንዲያሟሉና በሃገራችን የቁም እንስሳት ወጪ ንግዱን አፈጻጸም ከማሻሻል አንጻር ከፍተኛ ሚና ያለው በመሆኑ ዘመናዊ የቁም እንስሳት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች (Dedicated Trucks) ወደ ሃገራችን የሚገቡበትን አሰራርና ማበረታቻዎችን በመዘርጋት ባለሃብቶች እንዲያስገቡ እና አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ችግሩን በዘላቂነት እንዲፈታ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የሚተገበር ይሆናል፡፡

ለጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይትን ለማሻሻል ከክልሎችና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት እንዲቋቋሙና አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ በማድረግ ግብይት እንዲፈጸምባቸው ይሰራል፡፡

የወተት ምርት ጥራቱን በጠበቀ መልኩ ለአቀነባባሪዎችና ተጠቃሚዎች እንዲቀርብ ለማስቻል በምርት ግብይቱ ላይ የሚስተዋሉ መሰረታዊ ማነቆችን መፍታት መሰረታዊ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ወተት ከሚመረትበት አካባቢ ጥራቱንና ደህንነቱን በማያጓድል ሁኔታ እንዲከማች በማድረግ (food grade)

የሆኑ የጥሬ የወተት ማከማቻ ዕቃዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረግ ሲሆን ለዚህም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ዕቃዎቹ በሃገር ውስጥ የሚመረቱበት እና እንደአስፈላጊነቱ ከሃገር ወጪ በድጎማ የሚገቡበት የማበረታቻ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡ የወተት ምርት ከተመረተበት ወደ ተለያዩ የገበያ መዳረሻዎች በጥራት እንዲርስ ለማድረግ እንዲቻል ተስማሚ የሆኑ ማጓጓዣዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ሌሎች ከሚለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡበትን አሰራር በመፍጠር በትራንስፖርት ችግር ምክንያት ወደ ገበያ የማይቀርብ ብሎም ጥራቱ የሚጓደል ምርትን መጠን በመቀነስ በቂ ምርት ወደ ገበያ የሚቀርብበት ምቹ ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

የወተት ምርት ከተመረተበት ቦታ ወደ ሚፈለገው መዳረሻ እስኪደርስ ድረስ ከክልሎች ጋር በመነጋገር ምርቱ በብዛት በሚመረትበት አካባቢ ደረጃቸውን የጠበቁ እና ወስጣዊ መሰረተ ልማታቸው የተሟላላቸው የወተት ምርት ማሰባሰቢያ ማዕከላት (Milk collection centers) እንዲቋቋሙና አስተዳደራቸውን ዘመናዊ በማድረግ በመሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

የዶሮ የግብይት ማዕከላት በሚቋቋሙበት አቅራቢያ ለሃገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል የዶሮ ስጋን በጥራት የእርድ አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻልና የስራ አጥነት ችግርን በመቅረፍ ብሎም የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ አነስተኛ የእርድ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች በስፋት እንዲቋቋሙ ይደረጋል፣

የማር ምርት ግብይትን ለማሻሻል በተለይም ወደ ውጭ የሚላክ የማር ምርትን ተቀባይ ሃገራት በሚፈልጉት ዝቅተኛ የምርት ጥራት ደረጃ መሰረት መዘጋጀቱን ሊያረጋግጥ የሚችል ዘመናዊ ላቦራቶሪ፣ የተመሰከረለት የማር ምርት ጥራት መለኪያ መሳሪያ አቅርቦት እና አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል የግል ዘርፉ ተሳትፎ እንዲጨምር በማድረግ በገዥዎቻችን በኩል ታማኒነት ያለው አሰራር ይዘረጋል፡፡ በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች የሚመረተውን ጥሬ ማር ምርት ጥራቱንና ደህንነቱን በጠበቀ መንገድ ለአቀነባባሪዎች እንዲደርስ ለማድረግ የማር ማሰባሰቢያና ማቀነባባሪያ ማዕከላት (Honey Collection Centers) ቁጥር በ2012 ከነበረበት 15 ማዕከላት የተለያዩ የበጀት ምንጮችን በማፈላለግና እንዲገነቡና የውስጥ መሰረተ ልማታ ለማሟላት በትኩረት ይሰራል፡፡

የአሳ ምርት በሚመረትበት የወሃ አካል የዓሳ ማዘጋጃና ማቆያ መሰረተ ልማቶች (fish port facilities) በማቋቋምና የምርት ጥራት ቁጥጥር አሰራር ስርዓት በመዘርጋት አቀነባባሪ ኢንዱስትሪው በሚፈለገው የጥራት ደረጃ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

2.2.3.5የእንስሳትና አሳ ምርቶቸ ግብይት ፋይናንስ ስርዓት

በቁም እንስሳት ወጪ ንግድ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ክህሎት ለማሳደግ በዘመናዊ እና አለም አቀፍ እንስሳት ንግድና ግብይት ዙርያ ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት የወጪ ንግዱን፣ የውስጥ የመስራት አቅም፣ ያለውን ሃብት እና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎችን ታሳቢ ያደረገ የወጪ ንግድ ስራ ዕቅድ (Business Plan) አዘጋጅተው እንዲሰሩ በማድረግ፣ በወጪ ንግድ ሂደቱ የሚያጋጥሟቸውን የሎጀስቲክስ አቅርቦት፣ አስተዳደራዊ ማነቆና እንቅፋቶችን በመለየት ተከታትሎ በመፍታት አቅማቸውን እና ተወዳዳሪነታቸውን የማሳደግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

ለቁም እንስሳት የወጪ ንግድ አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው የፋይናንስ አቅርቦት እንዲፈጠር ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ስምምነት ላይ በመድረስ እና የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በቂ፣ ፍትሃዊና ወቅታዊ የብድር አቅርቦ ስርዓት በመዘርጋትና ብድር አጠቃቀሙ ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በወጪ ንግዱ ላይ ያላቸው ተሳትፎ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

2.2.4 የእንስሳትና ዓሳ ምርት ጥራትና ደህንነት

2.2.4.1 የቁም እንስሳት ኳራንታይን፣ ኢንስፔክሽንና ሰርቴፊኬሽን አገልግሎት

በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ወደ ውጭ ገበያ ለሚላኩ የቁም እንስሳት የሚሰጠው የኳራንታይን፣ ኢንስፔክሽንና ሰርቲፊኬሽን አገልግሎት በ2012 ዓመት ካለበት ዳልጋ ከብት 41,000፣ በግና ፍየል 346,000 እና ግመል 19000፣ የከብት ቆዳ 91,000፣ የበግና ፍየል ሌጦ 1,721,000፣ ማር 153.3 ቶን፣ ሰም 147 ቶን በማሳደግ በ2017 ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 305,000 ዳልጋ ከብት፣ 473,000

በግና ፍየል፤ 96,000 ግመል፣ 345,000 የከብት ቆዳ፣ 8,070,000 የበግና ፍየል ሌጦ፣ 1,100 ቶን ሰም እና 2,600 ቶን ማር ኤክስፖርት ለማድረስ ኢላማ ተቀምጧል፡፡

በመገንባት ላይ ያሉ ኳራንታይኖችን በአፋጣኝ እንዲጠናቀቁ ክትትል በማድረግ እና የተጠናቀቁትን የኳራንታይን ጣቢያዎች የተቀባይ ሀገራትን ይሁንታ እንዲያገኙ በማድረግ፣ የእንስሳት ልየታና የኂልዮሽ ክትትል ስራዎችን በማጠናቀቅ እንዲሁም ሌሎች በእንስሳት ጤና ዙሪያ የተጀመሩ ስራዎችን በማጠናቀቅ እና በተቀባይ ሀገራት በማስተዋወቅ በነባርና አዳዲስ የቁም እንስሳት ተቀባይ ሀገራት ያለንን የገበያ ድርሻ የማሳደግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በተቀባይ ሀገራት ከሚገኙ ሚሲዮኖቻችን ጋር በጋራ በመሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ኤግዚቢሽኖች በመሳተፍና በሀገራችንም በማዘጋጀት ወደ መዳረሻ ሀገራት የንግድ ልዑክ በመላክና በመጋበዝ እንዲሁም ሌሎች የተቀናጁና ጠንካራ የገበያ ማስፋፊያ ተግባራትን በማከናወን በወቅቱ ያሉትን ውስን የመዳረሻ ሃገራት አድማስ ማሳደግና ነባሮቹም እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡ የቁም እንስሳት ኳራንቲን ኢንስፔክሽንና ሰርቴፊኬሽን አገልግሎት ማሻሻል፤እንድሁም የእንስሳት ልየታ፤ ምዝገባና የኃልዮሽ ክትትል አሰራርን ለመተግበር ከታች የታዘረዘሩት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡

ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በገባችባቸው የእንስሳትና ውጤቶች የውጭ ገበያዎች ለመቆየትና በእነዚህ ገበያዎች የደንበኞችን መሰረት (Customer Base) ለማስፋት፣ እንዲሁም በአጭር ጊዜ መስፈርቶቻቸውን ለማሟላት የምንችላቸውንና የተሻለ የሚከፍሉ አማራጭ ገበያዎችን በመለየትና በመግባት የላቀ ተጠቃሚ ለመሆን ጥረት ይደረጋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የእንስሳት ኳራንቲን፣ ኢንስፔክሽንና ሰርቲፊኬሽን ሥርዓቱን በተቀባይ አገሮች መስፈርትና ዓለም አቀፍ ደረጃዎች ላይ ተመስርቶ በማጠናከር፣ የእንስሳት ልየታ፣ ምዝገባና ክትትል ሥርዓት (Livestock Identification and Traceability) በመገንባትና የተጀመሩትን 3 ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ ኳራንቲን ጣቢያ ግንባታዎች በማጠናቀቅና ሥራ በማስጀመር እንዲሁም ፣ የሙያተኛውን አቅም በመገንባትና የቁም እንስሳት ወጪ ንግድን የማሳለጥ ሥራ በትኩረት ይሰራል፡፡ የአገራችን እንስሳት የኳራንቲን ጊዜአቸዉን ጨርሶ በጅቡቲ ወደብ በኩል በሚላኩበት ጊዜ አለም አቀፉን የእንስሳት ጤና ድርጅትን መስፈርት ያሟላ የተሳላፊ ስርዓት በወደቡ በኩል ባለመተግበሩ ምክንያት ላልተፈለገ ወጭና የጊዜ ብክነት የመዳረግ ሁኔታ ሰላሌ ይሄንን ለማስቀረት ከሚመለከታቸዉ የጅቡቲና የአገራችን አካላት በተለይ ከዉጭ ጉዳይ ሚኒሰቴርና ከምሰዮኖቻችን ጋር በመነጋገር የስምምነት ሰነድ በመፈረም የቁም እንስሳት ኤክፖርት እንዲሳለጥ ይደረጋል፡፡

በተጨማሪም የብዙ አገሮች መስፈርት እየሆነ የመጣውን የእንስሳት ልየታና ክትትል ሥርዓት ግንባታና የሙከራ ትግበራም በዕቅድ ዘመኑ የሚከናወን ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በልየታ ሥርዓቱ የሚገቡ ዳልጋ ከብቶች ፤በግና ፍየልንም የቡድን ልየታ በቁጥር 800000፤ 1200000 በቅደም ተከተል ሺህ ለማድረስ ታቅዷል፡፡ እንደ ሀገር ከውጪ የሚገቡ የቁም እንስሳትና እንስሳት ውጤቶች ጋር የሚገቡ በሽታዎችንና ቸደጋዎችን ለመከላለል የሚያስችል የቅድመ ካራንቲን ስርዓትና የቁጥጥር ካ/ጣቢያ (Post entry Quarantine System and Facility) እንዲገነባ ይደረጋል፡፡

2.2.4.2 የኤክስፖርት ቁራዎች ኢንስፔክሽንና ሰርቴፊኬሽን አገልግሎት

የኤክስፖርት መስፈርቱን በሚሚላት ደህንታቸውና ጤንነታቸው ተጠብቆ ለኤክስፖርት ቁራዎች የሚቀርቡ እንሰሳት በ 2012 ከነበረበት 1.8 ሚሊዮን እንሰሳት አቅርቦት በ 2017 መጨረሻ ወደ 3 ሚሊዮን እንሰሳት አቅርቦት (0.13 ሚሊዮን ዳልጋ ከብትና 2.87 ሚሊዮን በግና ፍየል) የሚያድግ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በተለያዩየ ኤክስፖርት ቁራዎች የኢንስፔክሽንና ሰርቴፊኬሽን አገልግሎት አግኝቶ የሚላክ ሥጋና ተረፈ ሥጋ አሁን ካለበት 16 ሺህ ቶን በ2017 መጨረሻ ዓመት ወደ 38 ሺህ ቶን (15 ሺ ቶን የከብት ሥጋ፣ 20.5 ሺህ ቶን የበግና ፍየል ስጋ እንዲሁም 2.5 ሺህ ቶን ተረፈ ስጋ) ያድጋል፡፡ ለዚሁ ለሚመረተው የሥጋና ተረፈሥጋ ምርት ዓለም አቀፍ የሥጋ ጤና ሳኒተሪ ሰርተፊኬት አሁን ካለበት 2 ሺህ ሰርተፊኬት በ2017 መጨረሻ 3.5 ሺህ ዓለም አቀፍ የሥጋ ጤና ሳኒተሪ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በመስጠት ኤክስፖርቱ የሚደገፍ ይሆናል፡፡ በመነሻ ዘመኑ ማለትም በ2012 መጨረሻ ዓመት 14 ኤክስፖርት ቁራዎች የሚገኙ ሲሆን በ2017 ዕቅድ ዘመን መጨረሻ ወደ 17 ቁራዎች ያድጋሉ፤ በተመሳሳይ ደግሞ አሁን ያሉት ኤክስፖርት ቁራዎች በመነሻው ዓመት 15

በመቶ አቅማቸው ብቻ እየሰሩ የሚገኙ ሲሆን በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሙሉ አቅማቸዉን 40 በመቶ ይደርሳሉ።

የኤክስፖርት ቁራ ኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የሚገነቡትን የኤክስፖርት ቁራዎች ከግንባታ ቦታ መረጣ ጀምሮ ድጋፍ ፣ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ቁራዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁና ጥራት ያለው የሥጋ ምርት በማምረት እንዲልኩ የኢንስፔክሽን እና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት በመስጠት የበኩሉን ከፍተኛ ዕገዛ ያደርጋል። በአሁኑ ጊዜም በተለያዩ የአገሪቱ ክልሎችና ከተሞች ለሚገኙና ወደ ውጪ ሀገር ምርታቸውን ለመላክ ፈቃድ ላገኙ 12 ኤክስፖርት ቁራዎች (የተወሰኑት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ያቀርባሉ) ይህ አገልግሎት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን በተጨማሪም የእንስሳትን ተረፈ ምርት በማቀነባበር ወደ ውጪ ለሚልኩ 10 ባለሀብቶች ተመሳሳይ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። በመሆኑም በ5 ዓመት መጨረሻ ላይም ወደ ስራ ለገቡት ሁሉ ተመሳሳይ የኢንስፔክሽንና ሰርተፊኬሽን አገልግሎት የሚሰጥ ይሆናል።

እንደሚታወቀው ከበሽታ፤ ከብክለት የጸዳ እንዲሁም ጥራቱን የጠበቀ ሥጋና ተረፈ ስጋ በኤክስፖርት ቁራ ውስጥ ለማምረት በመሰረታዊነት የምንጠቀምበት ግብዓት የዕርድ እንሰሳት እንደ መሆናቸዉ መጠን የዝርያቸውና የጤናቸው ሁኔታ ጋር በእጅጉ የተያያዘ በመሆኑም እንሰሳት በሚረቡበትና በሚኖሩበት አካባቢ የእንሰሳት ጤና አገልግሎት የተስፋፋና በተለይም ድንበር ዘለል ተዛማች (TADS) በሽታዎች የመከላከልና የመቆጣጠር ተግባራት በተጠናከረ መልኩ መተግበራቸውን መረጋገጥ ያለበት ሲሆን ከበሽታ ነጻ ቀጠና መመስረት የሚቻልበትን ሁኔታ ለመፍጠር በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በትኩረት የሚሰራ ይሆናል።

በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በኤክስፖርት ቁራ ኢንስፔክስንና ሰርተፊኬሽን ንዑስ ዘርፍ ውስጥ ጥራቱና ተስማሚነቱ የተረጋገጠ የስጋና ተረፈ ሥጋ ኤክስፖርትን ለማሻሻልና ለማሳደግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ዋና ዋና ተግባራቶች የሚከናወኑይሆናል። ሁሉም ኤክስፖርት ቁራዎች በምግብ ደህንነት ሥርዓት ዕውቅና ዕድሳት ያገኛሉ፣ የእንሰሳት ዕርባታ ሥርዓት ከባህላዊ ወደ ዘመናዊ ይሸጋገራል፣ ለሥጋ ኤክስፖርት የሚፈለጉ የእንሰሳት ዝርያዎች ይስፋፋሉ፣ ምርትና ምርታማነት ይሻሻላል፣ የእንሰሳት ምዝገባና ልየታ ሥርዓት ይተገበራል። የእንሰሳት ዝውውር ቁጥጥር ይደረጋል፣ የድንበር ዘለል በሽታዎች ቁጥጥር በተለይም የአፍ ተዕግርና የበጎችና ፍየሎች የደስታ መሰል በሽታ መከላከልና ቁጥጥር ስራዎች በከፍተኛ ደረጃ ይተገበራሉ፣ በባህርዳር፣ በመቀሌ እና በጅግጅጋ ያሉ ኤክ/ቁራዎች ምርታቸውን እዛው ከሚገኘው የአውሮፕላን ማረፊያ በቀጥታ መላክ እንድችሉ ከሚመለከተዉ አካል ጋር ይሰራል፣ እሴት የጨመረ የእንስሳት ሥጋ የመላክ አቅምን በመገንባት በተለይም አጥንት አልባ የከብት ሥጋ በስፋት ይላካል (Meat Fabrication Deboning and Vacuum packaging) ።

በመካከለኛው ምስራቅ በተለይም በሳውዲ እና በተባበሩት ዓረብ ኤምሬትስ ያለንን ከ4 በመቶ ያልዘለለ የገበያ ድርሻ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ ወደ 8 በመቶ ይደርሳል፣ በዕቅድ ዘመኑ መጀመሪያ በ 2 አገራት ብቻ የተወሰነውን የገበያ መዳረሻ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻከ 1 አገር ጋር የፕሮቶኮል ስምምነት በማድረግ ወደ 3 መዳረሻ ያድጋል፣ በተጨማ ሪም በዕቅድ ዘመኑ የሰለጠነ የሰዉ ሀይል ከሚሟላት አካ,ያ በመጀመሪያ 60 የሥጋ መርማሪ ሀኪሞችና ረዳት ሐኪሞች የሚገኙ ሲሆን በ 5 ዓመቱ የዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 20 የሥጋ መርማሪ ሀኪሞችና ረዳት ሐኪሞች ይቀጠራሉ፣ የእንሰሳት ጤና ደህንትና ቬትሪናሪ ፐብሊክ ሄልዝ አዋጅ ይወጣል፣ ከዚህም በመነሳት የሥጋ ምርመራና ሀይጂን ደንብ ይወጣል፣ ሌሎች መመሪያዎች፣ ጋይድ ላይንና ኤስ ኦ ፒ ይሰራሉ ይከለሳሉ፣ ሁሉም ወደ ተግባር የሚገቡ ይሆናል። ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርና በተቀባይ ሀገራት ከሚገኙ ሚሲዮኖቻችን ጋር በጋራ በመሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በሚደረጉ ኤግዚቢሽኖች በመሳተፍና በሀገራችንም በማዘጋጀት ወደ መዳረሻ ሀገራት የንግድ ልዑክ በመላክና በመጋበዝ እንዲሁም ሌሎች የተቀናጁና ጠንካራ የገበያ ማስፋፊያ ተግባራትን በማከናወን በወቅቱ ያሉትን ውስን የመዳረሻ ሃገራት አድማስ ማሳደግና ነባሮቹም እንዲጠናከሩ ይደረጋል። በዕቅድ ዘመኑ መጀመርያ በስጋ ምርመራ የ6 ወር ስልጠና ወስደው ዕዉቅና የገኙ ስጋ መርማሪ ባለሙያዎች 12 ሲሆኑ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ 50 ተጨማሪ ባለሞያዎችን በማሰልጠን ዕዉቅና የያገኙ ስጋ መርማሪ ባለሙያዎች እንዲሆኑ ይደረጋል።

2.2.4.3 በእንስሳት ሕክምና የማህበረሰብ ጤና አገልግሎትን ማጠናከር (veterinary public health)

ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ የተመረጡ በሽታዎችን በመቆጣጠርና የእንስሳት ውጤቶችን ደህንነት (safety) በመጠበቅ በህዝብ ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መቀነስ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ትኩረት ተሰጥቷቸው ከሚፈጸሙ ተግባራት አንዱ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ተላላፊ በሽታዎችን መቆጣጠርን በተመለከተ የዕብድ ውሻ በሽታን በዋና ዋና ከተሞች መቆጣጠር፣ በወተት ከብቶች ላይ የሚታየውን የዳልጋ ከብቶች ነቀርሳ (ቲዩበርኩሎሲስ) ለመቆጣጠር አገራዊ የስርጭት መጠን የመለየትና አዋጭ የቁጥጥር ስልት በምርምር የመምረጥና በዚሁ ላይ ተመስርቶ የቁጥጥር ስትራቴጅ የመንደፍ ስራ ይከናወናል። የመጀመሪያ ደረጃ የእንስሳት ምርቶችን ደህንነት ማረጋገጥን በተመለከተ የግል ሴክተሩ በቁራዎች ግንባታ የሚሳተፍበትን ሁኔታ በማመቻቸት በተለያዩ ከተሞች የተገነቡ ቁራዎችን ደረጃቸውን (ስታንዳርዱን) እንዲያሟሉ ማድረግና አሁን ካለበት 293 ወደ 393 ማድረስ፣ በማዘጋጃ ቤቶች ተይዘው ያሉ ቁራዎችን ቀስ በቀስ ወደ ግል ወይም በማኔጅመንት ኮንትራት ማስተላለፍ፣ የእንቁላል፣ ወተት፣ ደሮ ስጋ፣ ማርና ሌሎች የእንስሳት ምርቶች ደህንነት ፕሮቶኮል በማዘጋጀትና በማስጸደቅ መተግበር፣ የሚየስፈልገውን የሰው ኃይል ማፍራትና ለሙያተኞች የተሃድሶ ስልጠና መስጠት፣ የምግብ ደህንነት ስልጠና ማዕከል ተገንብቶ ማሰልጠን እስኪጀምር ድረስ ክልሎች እንዲሰለጥኑላቸው የሚፈልጉትን ባለሙያ በዕቅድ ይዘውና በጀት መድበው ሲያሳውቁ ፌደራል ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት ስልጠናውን እንዲያገኙ ያደርጋል። በተጨማሪም በሁለተኛዉ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የተዘጋጁ የቁራ ግንባታ ዲዛይኖችና እስታንዳርድ ኦፔሬትንግ ፕሮሲጀሮች(SOP) በተለያዩ ከተሞች (ቀበሌ፣ ወረዳ፣ ዞንና ክልል ከተሞች) ለመተግበርና የግንባታ ሂደታቸዉን ለማሳለጥ በዕቅድ ዘመኑ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚከናወኑ ይሆናሉ።

ከሰዉ ወደ እንስሳትና ከእንሰሳት ወደ ሰዉ የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ከታች የተዘረዘሩ ተግባራትን ለማከናወን የሚሰራ ይሆናል። በተለይም በእንስሳት ህክምና ህብረተሰብ ጤና የህብረተሰቡን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ፣ አባ ሰንጋን እና የእብድ ውሻ በሽታን ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የተዘጋጁትን የቁጥጥር ሥርዓቶች ከክልሎች ጋር በመተባበር ወደ ሥራ በማስገባት በሕብረተሰብ እና በእንስሳት ጤና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መቀነስ፣ የከብቶች የሳንባ ነቀርሳን (BTB) እና የውርጃ በሽታን (Brucellosis) ለመቆጣጠር እና ለመከላከል የቁጥጥር ሥርዓት አዘጋጅቶ በማፀደቅ እና ወደ ሥራ በማስገባት የቁጥጥር ሥራ መሥራት፣ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችንና በምግብ ደህንነት በተመለከተ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የተለያዩ ሥልጠናዎችን እና በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን (ራዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ብሮሸሮች፣ መጽሔቶች) የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መሥጠት፣ የኢትዮጲያ የተመረጡ አደገኛ ተህዋሲያንን መቆጣጠሪያ አዋጅና ደንብ ዶክመንት ማዘጋጀት፣ ማስተካከልና ማፀደቅና ለክልሎች ማሰተዋወቅ፣ የጊኒወርም በሽታ በሰዉና በእንስሳት ላይ ሙሉ ለሙሉ ለማጥፋት ጉዳዩ ከሚመለከታቸዉ የባለድርሻ አካላትጋር በቅረበት የሚሰራ ይሆናል።

የእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ምግብ ደህንነት ከመጠበቅ አንጻር፤ እንድሁም ለአገር ዉስጥ ፍጆታ የሚዉል የእንስሳት እርድ የሚከናወንበት ቁራዎችን የኢንስፔክሽንና ስርቴፊኬሽን አገልግሎት ለማጠናከር ከታች የተዘረዘሩ ዋና ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል። በተለይም ከሕብረተሰብ ጤና፤ ከእንስሳት ጤናና ከምግብ ደህንነት ተቋማት ጋር በቅንጅት ለመሥራት የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድ ወይም ፕሮቶኮል ማዘጋጀትና እሱንም ደረጃ በደረጃ ማከናወን፣ ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማሳደግ የአንድ ጤና ተግባራትን ማጠናከር ፣ በሃገራችን ያሉትንና ከምግብ ደህንነት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሥራ እንቅስቃሴዎችና ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ እንደ አስፈላግነታቸዉ ሕጎችን፤ደንቦች፤መመረያዎችን ማዘጋጀት ፣ ከዚህ በፊት የተዘጋጀ አዲስ የቁራዎች ዲዛይን መሠረት በማድረግ ዘመናዊ ቁራዎች በክልሎች እንዲገነቡ እና ነባሮቹንም ስታንዳርዱን እንዲያሟሉ ከክልሎችና ከከተማ መስተዳደሮች ጋር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጥርና ድጋፍ መስጠት ፣ ቀደም ሲል በተጀመረው አሠራር መሠረት ተጨማሪ የሥጋ ምርመራ ባለሙያዎች ሰልጠነው በክልሎች ያለውን የባለሙያ ዕጥረት ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መስራት፣ የምግብ ደህነት መመርመሪያ ላብራቶሪን ማጠናከርና በክልሎችም ተመሳሳይ ተቋም መገንባት፣ የክትትል፣ ግምገማ፣ ድጋፍና ግብረ መልስ አሰራርን በማጠናከር የእንስሳት ሕብረተሰብ

ጤና ሽፋንን ማሳደግ ፣ ለተለያዩ የክልል ባለሙያዎች ከእንስሳት ወደ ሰው በሚተላለፉ በሽታዎች፣ በምግብ ደህንነት ዙሪያና AMR ላይ የአጭር እና የመካከለኛ ጊዜ ሥልጠናዎችን በመሥጠት ክህሎታቸውን ማሣደግ፣ የተለያዩ መሣሪያዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ከክልሎች ጋር የሚደረገውን ግንኙነት እና የመረጃ ልውውጥ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በቅረበት መስራት፣ የእንስሳት ጤናን፣ ደህንነትን፣ እና የቬተረነሪ ፐብሊክ ሔልዝን አዋጅ እና የእንስሳት ውጤቶችን ደህንነት መቆጣጠሪያ ደንብን ማስፀደቅ እና በተለያዩ ዘርፎች ላይ የቁጥጥር ሥራ መሥራት እና ለሃገር ውስጥ ፍጆታ ሥጋን በሚያቀርቡ ቄራዎች ምግብ ጥራትና ደህንነት ስርዓት (HACCP) እናዲተገበር ከክልሎች ጋር በቅርበት የሚሰራ ይሆናል።

ስትራቴጂክ ዓላማ III፡ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም

ሚዛናዊነቱን የጠበቀ ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የግብርና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ የምግብና ሥርዓተ-ምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስና ለመቋቋም፣ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባትና ከፍተኛ የስራ ዕድል ለመፍጠር እንዲሁም አጠቃላይ ኢኮኖሚውን ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር ጉልህ አስተዋጽዖ ያደርጋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ የሚገኝ ሰፊ የመሬት ሀብት፣ ለግብርና ልማት ሊውል የሚችል የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች እንዲሁም ለመስኖ ልማት የሚውል ከፍተኛ የገጸ-ምድርና የከርሰ-ምድር የውሃ ሀብት ያላት አገር ናት። ይሁን እንጂ ተገቢ ባልሆነ አያያዝና አጠቃቀም የተነሳ በተፈጥሮ ሀብታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደርሰበት ይገኛል። ለምሳሌ ከ 3 ሚሊየን ሄ/ር በላይ የእርሻ መሬት በአሲድ የተጠቃ ሲሆን በአፈር መሸርሸር ደግሞ በየዓመቱ ከአንድ ሚሊየን ቶን በላይ ለም አፈር ከእርሻ መሬቶቻችን ላይ ስለሚታጠብ ምርታማነቱ በእጅጉ ቀንሷል። ያለንን የውሃ ሀብትም በተገቢው ልክ ለመስኖ አገልግሎት ካለመጠቀማችን በላይ የመስኖ አውታሮቻችን አባካኝ በሆነ የውሃ አጠቃቀም ዘይቤ ቀላል የማይባል የመስኖ መሬት በጨዋማነትና ተዛማጅ ችግሮች ምክንያት ከምርት ውጭ ሆኗል። በተጨማሪም የገጠር መሬት ባለይዞታዎች መሬቱን የመጠቀም አስተማማኝ ዋስትና ስለሌላቸው መሬታቸውን በተገቢ መንገድ እየተጠቀሙ አይደለም። ከዚህም በላይ መሬቱ ባለው አቅም መሰረት ለተለያዩ አገልግሎቶች እንዲውል የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ባለመኖሩ ለእርሻ መዋል የሚገባቸው መሬቶች ለግንባታ፣ ለግንባታ መዋል የሚገባቸው ደግሞ ለሌሎች አገልግሎቶች እየዋሉ መሬቱ መስጠት ያለበትን ጥቅም እየሰጠ አይደለም።

ስለሆነም የተፈጥሮ ሀብታችን ተፋሰስንና ስነ-ምህዳርን መሰረት በማድረግ፣ የተሸሻሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን፣ ዘመናዊ አሰራሮችንና ግብዓቶችን በመጠቀምና ሕብረተሰቡን በተለይ ሴቶችንና ወጣቶችን በንቃት በማሳተፍ ዋነኞቹን የተፈጥሮ ሀብት መሰረቶች ማለትም አፈር፣ ውሃ፣ ደን እና በአርብቶ አደር አካባቢ ያለውን የግጦሽ መሬት በዘላቂነት ማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል። በተጨማሪም ዘላቂ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓትን በአጠቃላይ ደግሞ ዘመናዊ የተፈጥሮ ሃብት የመረጃ ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና በመተግበር እንደዚሁም የተፈጥሮ ሀብታችንን በዘላቂነት መንከባከብና መጠቀም የሚያስችሉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሠራሮችን አርሶ/አርብቶ አደሩ በአግባቡ መጠቀም እንዲችል በየደረጃው የባለሙያዎችንና የአርሶ/አርብቶ አደሩን አመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት ማሳደግ ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የምንከተለው አሰራር አርሶ/አርብቶ አደሩ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጅዎችንና የተሻሻሉ አሰራሮችን ተግባዊ ሲያደርግና ሀብቱንም ዘላቂ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም በማድረግ ነው። በዚህም በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት

የምናከናውናቸው የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ስራችን የአፈር ክለትን አሁን ካለበት 20.5 ወደ 18.2 ቶን/ሄ/ር በዓመት ዝቅ ለማድረግ፣ የባዮማስ መጠንን አሁን ካለበት ከ27 ወደ 37.6 ሚሊየን ቶን ካርበን በሄ/ር በዓመት ከፍ ለማድረግ፣ 158250 ወጣቶች/ዜጎች (ሴት/ወንድ) የስራ ዕድል ለመፍጠር፣ ለ5000 ተፋሰሶች ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ማህበራት አቋቁመው እንዲንቀሳቀሱ ለማድረግ ዒላማ ተቀጧል።

የአፈር ንጥረ ነገር ይዘት አሁን ካለበት ናይትሮጅ ከ2029 ወደ 2131 ሚ.ግ/ኪ.ግ ለማድረስ፣ ፎስፈረስ ከ17.2 ወደ 18.1 ሚ.ግ/ኪ.ግ ለማድረስ፣ ፖታሽ ከ420 ወደ 441 ሚ.ግ/ኪ.ግ ለማድረስ፣ ሳልፈር ከ30 ወደ 31 ሚ.ግ/ኪ.ግ ለማድረስ፣ የአፈር ካርቦናዊ ቁስ ይዘትን ከ1.8 በመቶ ወደ 1.98 በመቶ ለማድረስ እና የጨመረ ዒላማ ተቀምጧል።

3.1 የተሻሻሉ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮች አጠቃቀም

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የሚረጋገጠው አርሶ/አርብቶ አደሩ ለአገራችን ሥነ-ምህዳር ቀጠናዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በአግባቡ ሲጠቀም ነው።አርሶ/አርብቶ አደሩ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በአግባቡ ለመጠቀም ዘላቂ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት ሲሰፍን፤ በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎች ማቅረብ ሲቻል፤ የአፈርና ውሃ ሃብቶችን ለመጠበቅ፣ የአፈር ጤንነትና ለምነት ለማሻሻል እና የመስኖ ውሃን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችሉ አሳታፊ የተቀናጁና ተፋሰስን መሠረት ያደረጉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና አዳዲስ አሰራሮች ላይ ዕውቀቱ፣አመለካከቱና ክህሎቱ ሲያግ፤ የተሻሻለ የተፈጥሮ ሀብት ግብዓትን በሚፈለገው መጠን፣ጊዜ፣ ጥራትና ተመጣጣኝ ዋጋ ሲቀርብ ማቅረብ ሲቻል።

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ተፈጥሮ ሀብታችን በዘላቂነት ለማልማትና ለመጠቀም አርሶ/አርብቶ አደሩ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ሲጠቀም በመካከለኛ ጊዜ በጥምር ደን የተሸፈነ መሬት ስፋት አሁን ካለበት 1.5 ወደ 2.86 ሚሊየን ሄ/ር ለማድረስ፣ ከከፋ የአፈር አሲዳማነት ያገገመ መሬት ከ 82 ሺ ወደ 450 ሺ ሄ/ር ለማሳደግ፣ ከከፋ የአፈር ጨዋማነት ያገገመ መሬት 10 ሺ ሄ/ር ወደ 310 ሺ ሄ/ር ለማሳደግ፣ ።

በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ በሚከናወኑ ማናቸውም ስራዎች የኤች አይ. ቪ ኤድስ መከላከል ተግባራትን በማካተት እና ማንኛውም በዘርፉ በሚካሄዱ ስልጠናዎች፤ የውይይት መድረኮች፡ የክትትልና ግምገማ ስርዓቶች ውስጥ ኤች አይቪን አካቶ መተግበር።

3.1.1 ዘላቂ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት

እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ላሉ አገራት ትልቁ ሀብት መሬት ነው። የመሬት ይዞታና የመጠቀም መብት ለዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም መነሻ ነጥብ። የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መሻሻልና መጠናከር አርሶ/አርብቶ አደሮች በተለይ ሴቶች ለዘላቂ ጥቅም ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ተጠቅመው የተፈጥሮ ሀብትን በባለቤትነት ስሜት እንዲያለሙና እንዲንከባከቡ ያበረታታቸዋል፤ አስተማማኝ ዋስትናም ይሆናቸዋል።

የተለያዩ በወል፣ በግል ወይም በመንግስት ሥር የሚገኙ የገጠር መሬት ይዞታዎችን በስፋት፣ በአቅጣጫና በመሬቱ የመጠቀም መብቶችን ለመለየት የሚያስችል በዘመናዊ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ሥርዓት መዘርጋትና አመች የሕግ ማዕቀፎችን መፍጠር ያስፈልጋል። ይህም የተሻሻለ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት በመዘርጋት ግለሰብ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮችና የግብርና ኢንቨስተሮች በተለይ ሴቶችና ወጣቶች እንዲበረታቱ፣ በይዞታቸው የመጠቀም መብታቸው እንዲጎለብት፣ በመሬት ወሰን ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና ግጭቶችን እንዲቀንስ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብትን በዘላቂነት እንዲንከባከቡ ያደርጋል።

የገጠር መሬት አጠቃቀም ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ በዘላቂ መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል የሚደረግበት ሂደት ነው። የተፈጥሮ ሀብትን በዘላቂነት ለመንከባከብና ለማልማት ለመጭው ትውልድም ጠብቆ ለማስተላለፍ ደግሞ የተለያዩ የአገራችንን የሥነ-ምህዳር ቀጠናዎችንና የመሬት

አቀማመጥን መሰረት ያደረገ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ማዘጋጀትና መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ሥነ-አካላዊና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ መረጃዎች ላይ ተመርኩዞ የመሬት መጎሳቆልንና የአካባቢ ብክለትን ሳያስከትሉ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚያስገኙ አማራጮች የሚወሰኑበትና የሚተገበሩበት የአሰራር ዘዴ ነው፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ዘላቂ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓትን ለመዘርጋት በሚሰሩ ስራዎች የሚጠበቁ የአጭር ጊዜ ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ከመሬት ጋር የተያያዙ ግጭቶችን አሁን ካለበት ከ21 ወደ 15% በመቶ መቀነስ፣ የብድር ተጠቃሚ የመሬት ባለይዞታዎች አሁን ካለበት ከ13 ሺ ወደ 1 ሚሊየን ለማሳደግ፣ በመረጃ ስርዓት የገጠር መሬት ግብይት ተጠቃሚ የሆኑ ባለይዞታዎች አሁን ካለበት ከ100 ወደ 600 ለማሳደግ ዒላማ ተቀምጧል፡፡

በአገራችን የመሬት አጠቃቀም የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ለእርሻ ልማት መዋል የሚገባው ለም መሬት በከተሞችና በኢንዱስቱሪ መስፋፋት እየተወረረና እየተበላ ይገኛል፡፡ ይህም በግብርና ልማት ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓት ባለመዘርጋቱ ከፍተኛ ተዳፋታማ ቦታዎች እንዲታረሱ፣ የመሬት መጎሳቆልና የአፈር መሸርሸር እንዲበባስ፣ የደን ሽፋን እንዲቀንስ፣ የዱር እንስሳት ወደ ሌሎች አገራት እንዲሰደዱ አድርጓል፡፡ ይህም የምግብ ዋስትናን ለማረጋጋጥ እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ የሚስማማ ግብርናን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ላይ ጫና አሳድሯል፡፡ በተጨማሪም የገጠር መሬት በዘመናዊ ስርዓት ተቀይሶና ተመዝግቦ የተያዘ ባለመሆኑ አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ ያለው የመጠቀም ዋስትና አነስተኛ እንዲሆን በማድረግ በመሬቱ ላይ ተገቢ መዋዕለ ንዋይ እንዳያፈስ አድርጓል፡፡ የመረጃ ስርዓቱ ደካማ በመሆኑ በመሬት ወሰን ምክንያት በሚነሱ ግጭቶች አርሶ አደሩ ለልማት ማዋል የሚገባውን ጊዜ በክርክር እንዲያሳልፍ አድርጎታል፡፡

ይህን ችግር ለመቅረፍ በመጀመሪያውና ሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ዘመን የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና የልማት አጋር ድርጅቶችን በማሳተፍ የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓት አበረታች ሥራዎች ተሰርታዋል፡፡ በቀጣይ አምስት ዓመታትም እስከአሁን የተደረጉ ጥረቶችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ ወሳኝ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡

3.1.1.1. የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና ዕቅድ ዝግጅት

የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ለግብርና አገልግሎት መዋል የነበረባቸው መሬቶች (Prime Farmlands) ከግብርና ውጭ ለሆኑ አገልግሎቶች በመዋላቸው ከግብርናው ዘርፍ ሊገኝ የሚችል ከፍተኛ የሰብል እና እንስሳት ምርት ባክኗል፡፡ በ2006 ዓ.ም በተደረገው የመሬት አጠቃቀም ለውጥ ጥናት መሰረት ከ1979 እስከ 2003 ዓ.ም ባሉት 25 ዓመታት ከአዲስ አበባ አምስቱም የመውጫ ኮሪደሮች በ20 ኪ..ሜ ራድየስ ከግብርና አገልግሎት ወደ ግንባታ የተቀየረ መሬት በ384% ጨምሯል፡፡

በሌላ በኩል በርካታ ለእርሻ አገልግሎት መዋል የሌለባቸው መሬቶች በመታረሳቸው ወይም ለእንስሳት የግጦሽ አገልግሎት በመዋላቸው የተፈጥሮ ሃብታችን በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቷል፤ የአየር ንብረት ለውጥን በማስከተሉ ምክንያትም በብዝሃ-ህይወት ሃብታችን እና በውሃ አዘል መሬቶች ላይ የማይቀለበስ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ በተመሳሳይ ጊዜ በደንና በግጦሽ ተሸፍነው የነበሩ መሬቶች ለግብርና አገልግሎት በመዋላቸው የመሬት መጠን ከ44 እስከ 66% ቀንሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በአብዛኛው የደጋማው የአገራችን አካባቢዎች የተበጣጠሰ የመሬት ይዞታ በመኖሩ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም እንዲሁም ድህረ ምርት ማሰባሰብና ጥራት ቁጥጥር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በ2005 ዓም በተደረጉ ጥናቶች በእነዚህ አካባቢዎች 35 በመቶ የሚጠጋ የአርሶ አደር እርሻ መሬት ይዞታ ከ0.5 ሄክታር በታች ሲሆን አማካኝ ይዞታም 0.81 ሄክታር የማይበልጥና እስክ 5 ቦታ የተበጣጠሰ ሆኖ አማካኝ የመሬት መጠኑ 0.19 ሄክታር አይበልጥም፡፡

ስለሆነም በቀጣይ ዓመታት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የገጠር መሬት አጠቃቀም ፖሊሲና የሕግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

3.1.1.2. የተቀናጀ አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም እቅድ ማዘጋጀትና መተግበር

ከላይ በመግቢያው እንደተገለጸው በሃገራችን የተቀናጀ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ በፌደራልም ሆነ በክልሎች በተሟላ ሁኔታ ባለመኖሩ ምክንያት በአንድ በኩል ለግብርና አገልግሎት መዋል የነበረባቸው ምርጥ የእርሻ መሬቶች (Prime Farmlands) ለከተሞች እና ኢንዱስትሪዎች በዘፈቀደ መስፋፋት በመዳረጉ የግብርና ምርት አሳጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በብዙ የአገራችን ደጋማና ወይና-ደጋማ አካባቢዎች የሚኖሩ አርሶ አደሮች በእርሻ መሬት ጥበት ምክንያት ለእርሻ ልማት መዋል የሌለባቸውን ከፍተኛ ተዳፋትነት ያላቸውን መሬቶች ለእርሻ አገልግሎት በማዋላቸው የተፈጥሮ ሃብታችን በከፍተኛ ሁኔታ ተጎድቷል፡፡ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የተቀናጀና አሳታፊ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ በፌደራል፣ በክልሎች፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ በተሟላ ሁኔታ የማዘጋጀትና የመተግበር ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ ይህ ስራ ካላቸው ነባራዊ የአኗኗር ሁኔታ ልዩነት አንጻር በአርሶ አደር አካባቢ በቀበሌ ደረጃ የሚከናወን ሲሆን በአርብቶ አደር አካባቢ ደግሞ በወረዳ ደረጃ የሚከናወን ይሆናል፡፡

3.1.1.3. ጠንካራ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋም መመስረት

በዓለም ላይ፣ ለማንኛውም ሀገር መሬት ውስን ሀብትና እጅግ ከሚያስፈለጉ የልማት ግብአቶች አንዱ እንደሆነ አጠያያቂ አይደለም፡፡ ውስን ሀብት የሚሆንበት ዋናው ምክንያት የአንድ አገር ጠቅላላ የህዝብ ብዛት እየጨመረ መሄዱ የማይቀር ቢሆንም የመሬቱ ስፋት ግን ሊጨምር አይችልም፡፡ ስለሆነም የአንድ ሀገር የህዝብ ብዛት በጨመረ ቁጥር የነፍስወከፍ የመሬት ድርሻ እየቀነሰ መሄዱ የማይቀር ሀቅ ነው፡፡ ስለሆነም ባለው ውስን መሬት ላይ የሚደረገው ሽሚያ ይባባሳል፡፡ ሽሚያው ሲባባስ ግጭት መፈጠሩ አይቀሬ ይሆናል፡፡ ያለውን ውስን መሬት ምርታማ ለማድረግና ለሚፈለጉ የተለያዩ ልማቶች በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል ተገቢ የሆነ የመሬት የአሰተዳደርና አጠቃቀም ስርአት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ ይህ ዕውነታ፣ በተገቢው መንገድ የተደራጀና ጠንካራ ተቋም የመፍጠርን አስፈላጊነት ያጎላዋል፡፡

በዚህ ውስን ሀብት ላይ አንዱ ሌላውን አግላይ የሆኑ በርካታ የልማት ፍላጎቶች አሉን፡፡ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፣ ከተማ የመሰረትንበት ቦታ ላይ በተመሳሳይ ጊዜ መካናይዝድ የሆነ የግብርና ምርት ማምረቻ ሊሆን አይችልም፣ መኪና ለመንዳት የምንገነባው መንገድ ለባቡር መንገጃ አይሆንም ለግብርናም አይሆንም፣ ለብርቅዬ የዱር እንስሳትና አእዋፋት መጠለያ እርባታና ልማት የምንከልለው ቦታ ላይ በአንድ ላይ የሰብል ልማት ማካሄድ አይቻልም፡፡ ሌሎች በርካታ የሆኑ የልማት አይነቶችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ስለሆነም የልማት ፍላጎቶቻችን በቅደም ተከተል አስቀምጠንና ተገቢውን የመሬት አጠቃቀም እቅድ አዘጋጅተን በቁጠባ ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ እነዚህን የልማት ቅደም ተከተሎችና ፍላጎቶች የመሬት ሀብቱ ያለበትን ሁኔታ ተረድቶ ለማስተዳደር ጠንካራ ተቋማዊ መሰረት ይጠይቃል፡፡

ይህንን ውስን ሀብት በተገቢው ሁኔታ ማስተዳደርና መጠቀም አለመቻል የሚያስከትለውን ሀገራዊ ኪሳራ ከራሳችን ታሪክ መማር ይኖርብናል፡፡ በሀገራችን ታሪክ እንደታየዉ ከአጠቃቀም ሽሚያና ወይም የተዛባ የአጠቃቀም ምርጫ በባሰ ሁኔታ የመሬት ባለቤትነትና ተጠቃሚነት ኢ-ፍትሃዊነት የፖለቲካ ሥርዓት ለዉጥን እስከማስከተል የዘለቀ መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ብቻ ሳይሆን የሀብቱን ቁልፍነትና ዘላቂ ተቋማዊ ምላሽ የሚፈልግ ዘርፍ መሆኑን የሚያስረዳ ዕዉነት ነዉ፡፡ በሀገሪቱ ያለው የመሬት መጎሳቆልና ምርታማነቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ መቀነስ እያስከፈለን ያለው አገራዊ ጉዳት በግልፅ የሚታይ ዕውነታ ነው፡፡ ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሚመጣውን የመሬት ፍላጎት ለማስተናገድ በሚደረገው ሂደት እየታየ ያለው ውጥረት መሬታችንን በዘመናዊ አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት

መምራት ካለመቻላችን የተነሳ እንደሆነ አጠያያቂ አይደለም። ስለሆነም ተገቢውን አደረጃጀት ፈጥረን፣ የፖሊሲና የህግ ማእቀፍ ዘርግተንና ምቹ ሁኔታ አረጋግጠን መሬታችንን ማስተዳደርና መጠቀም ለነገ የሚባል ጉዳይ እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

በአለም በሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ፣ የተሳለጠና ሁሉን አቀፍ የሆነ እድገት ያስመዘገቡ አገራት አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ያላቸውን ውስን መሬት በዘመናዊ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት ውስጥ ማስገባታቸውና ጥቅም ላይ ማዋላቸው ነው። ከዚህ አንጻር ሲታይ እኛ እጅግ በጣም ሊባል በሚችል ደረጃ ዘግይተናል ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሀገራችን ወደ ዘመናዊ የመሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ስርአት ግንባታ ስትገባ ከተሳካላቸውና ቀድመው ከጀመሩ ሀገራት በመማርና ከራሳችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማዛመድ ልንፈጥን እንችል ይሆናል።

ከአደረጃጀት ጋር ተያይዞ በአለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት ላይ ከተደረሰባቸው አሰራሮች አንዱ መሬት የሚሰጠው አገልግሎት በሴክተር የተገደበ ባለመሆኑ የአስተዳደርና የአጠቃቀም ስርአቱን ለመወሰን የሚደራጀው ተቋም በአንድ ሴክተር ተጽእኖ ስር መዋል የሌለበት መሆኑ ነው። መሬት ለተለያዩ የልማት ስራዎች መሰረት እንደመሆኑ የተሻለውን አማራጭ የመምረጥ ሀላፊነት የገለልተኛ ተቋም መሆን ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ አጠቃቀሙን መሰረት በማድረግ በተለያዩ አካላት እንዲተዳደር ማድረግ ለምሳሌ የእርሻ መሬት በሚሆንበት ጊዜ በግብርና ሚኒስቴር የመኖሪያ አካባቢ በሚሆንበት ጊዜ በከተማ አስተዳደሮች፣ የኢንቨስትመንት መሬት በሚሆንበት ጊዜ በኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ የማምለኪያ ቦታ በሚሆንበት ጊዜ በሀይማኖት ተቋማት ወ.ዘ.ተ የሚተዳደር ከሆነ የመሬት አጠቃቀም ግጭትና ሽሚያ ስለሚያስከትል መሬቱን በሀገር ደረጃ የላቀ ጥቅም በሚሰጥበት ሁኔታ መጠቀም ስለማያስችል እራሱን በቻለና ገለልተኛ በሆነ ተቋም ቢተዳደር የተሻለ መሆኑን አለማቀፍ ተሞክሮው ያሳያል።

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ላለው የመልካም አስተዳደር እጦት መነሻ የሆነው በገጠርም ሆነ በከተማ ያለው የተዛባ የመሬት አሰተዳደርና አጠቃቀም ስርአት ለመሆኑ የጋራ ግንዛቤ የተያዘበት ጉዳይ ነው። ከችግሮቹ አንዱና ዋነኛው በፌደራል ደረጃ ያለው ደካማ አደረጃጀት እንደሆነ ይታመናል። አደረጃጀቱ ደካማ ከመሆኑ በተጨማሪ በተበታተነ ሁኔታ የመሬት ጉዳይ ለተለያዩ ተቋማት በመሰጠቱና እንዲተዳደር በመደረጉ የመልካም አስተዳደር እጦትን እንዳባባሰው ይታመናል። የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም እንዲሁም በካርታ የተደገፈ የመሬት መረጃ ምንጨታ ሀላፊነቶች ከዘጠኝ ለማያንሱ ተቋማት እንደተበታተነ አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚህ በተጨማሪ ሀገሪቱ ያላት የመሬት አጠቃቀም እጅግ የተዛባ ከመሆኑ የተነሳ ለከተማና ለኢንዱስትሪ እየዋለ ያለው መሬት እጅግ ለግብርናው ዘርፍ ምርታማ የሆነው እንደሆነ በአደባባይ የሚታይ እውነታ ነው። በምሳሌነት ከአዲስ አበባ ደብረዘይት መንገድ ማየቱ በቂ የሆናል። በክልል ከተሞች ዙሪያ ያለው ነባራዊ ሁኔታም ከዚህ የተለየ አይደለም። በመሆኑም እየታየ ያለውን የመሬት አሰተዳደርና አጠቃቀሙን ስርአት መልክ ለማስያዝና በተገቢው ሁኔታ ለመምራት አደረጃጀቱን ማስተካከል ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም።

እንዲኖር የሚፈለገው ዘመናዊ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት ለሁለንተናዊውና ለዘላቂ አገራዊ እድገት ተገቢውን አስተዋጽዎ እንዲያደርግ ይጠበቃል። ይህ እውን ሊሆን የሚችለው ብቃት ያለው የመሬት ግብይት እና ብቃት ያለው የመሬት ማኔጅመንት ስርአትን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ይሆናል። ብቃት ያለው የመሬት ግብይት እና ብቃት ያለው የመሬት ማነጅመንት ስርአትን ለማረጋገጥ እርስ በእርሳቸው የሚመጋገቡ አራት ዋና ዋና ተግባራትን ማለትም የይዞታ መብትን ማረጋገጥ፣ የዋጋ ትመናና መሬት ነክ የሆኑ የገቢና የታክስ ሥርአት መዘርጋትና መተግበር፣ የመሬት አጠቃቀምን መወሰንና የግንባታ ፍቃድ አሰጣጥና አተገባበር ስርአት ዝርጋታን በማከናወን ይሆናል። ለዚህም ደግሞ ምቹ ሁኔታዎች መፈጠር አለባቸው። በምቹ ሁኔታነት መኖር ያለባቸው ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎች፣ በካርታ የተደገፈ ዘመናዊ የመሬት መረጃና የሚፈለገውን ዘመናዊ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት መተግበር የሚችል አደረጃጀት ይሆናሉ። አደረጃጀት ስንል በሙያው ብቃት ያላቸውንም ባለሙያዎች እንደሚጨምር ማስታወስ ያሻል።

በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያለው የከተማና የገጠር መሬት በሚል ተለያይቶ ያለው አደረጃጀት ዘመናዊ የሆነውን የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ስርአት እሳቤ ያልተላበሰ ሆኖ ይገኛል። እንደ ኢትዮጵያ

ሁሉ በሶሻሊስት የፖለቲካ ስርአት ውስጥ ሲተዳደሩ የነበሩ የምስራቅ አውሮፓ አገራት ሩሲያን ጨምሮ አደረጃጀታቸውን አስተካክለው የከተማም ሆነ የገጠር መሬት የሚመራው በአንድ ተቋም ነው። በርካታ የአፍሪቃ አገራትም በተመሳሳይ አደረጃጀት መሬታቸውን ያስተዳድራሉ፣ ይጠቀማሉ። በምሳሌነት ኬንያን ኡጋዳን ጋናን ሩዋንዳንና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል። ከሩቅ ምስራቅ አገራት የቪየትናምንና የደቡብ ኮሪያም ልምድ የሚያሳየው በተመሳሳይ የከተማም ሆነ የገጠር መሬት የሚመራው በአንድ ተቋም መሆኑን ነው። ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ የልምድ መነሻ የምናደርገው ደቡብ ኮሪያን ነው። ስለሆነም በመሬት አስተዳደርና አጠቃቀሙም የኮሪያን ልምድ መውሰዱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታሰባል። ለዚህም ሲባል የክልል የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ቢሮ ሃላፊዎችንና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የፌደራል ሀላፊዎችን ያካተተ የልምድ ልውውጥ በደቡብ ኮሪያ እና በቪየትናም ተካሂዷል። የበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ልምድም የሚያሳየው የከተማም ሆነ የገጠር የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ተቋም አንድ መሆኑን ነው።

3.1.1.4. የ2ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጥና የምስክር ወረቀት መስጠት

የገጠር መሬትን በአቅጣጫ፣ በስፋት፣ በወሰንና በባለይዞታ ዘመናዊ በሆኑ መሳሪያዎች በመለካት፣ በመመዝገብና ለባለይዞታዎች የይዞታ የምስክር ወረቀት መስጠት በይዞታቸው ላይ የሚኖራቸውን ዋስትና እንዲያድግ ያደርጋል። ይህም ባለይዞታዎች በተለይ ሴቶች ገንዘባቸውን መሬታቸው ላይ በማዋልና ከወሰን ጋር የተያያዙ ግጭቶችን በመቀነስ ሙሉ ጊዜያቸውን በልማት ላይ እንዲያውሉ በማድረግ ለምርትና ምርታማነት ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ስለሆነም በደጋማውም ሆነ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የአካባቢውን ባህልና የአኗኗር ዘይቤ መሰረት በማድረግ የ2ኛ ደረጃ ይዞታ ማረጋገጥና የይዞታ የምስክር ወረቀት የመስጠት ተግባራት በቀጣይ ዓመታት ተጠናክሮ ይቀጥላል።

ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘታቸው በራሱ ውጤት ስላልሆነ ይህንን ወደ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት መቀየር ሌላው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። በዚህም መሰረት በአሁኑ ሰዓት ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀታቸውን እንደ ዋስትና በማስያዝ ብድር ከአነስተኛ ገንዘብ ተቋማት በመውሰድ የእርሻ ስራቸውን በማስፋትና በቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ ምርትና ምርታማትን እንዲያሳድጉ ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ መሬት አልባ የሆኑ የገጠር ነዋሪዎችን መሬት በማከፋፈል ማዳረስ ስለማይቻል በኪራይ ግብይት በማከናወን ገንዘብ፣ ዕውቀትና ፍላጎት ያላቸው በኪራይ መሬት አግኝተው ተጠቃሚ የሚሆኑበትን ስልት በመንደፍ ስራዎች ይከናወናሉ ።

ባለይዞታዎች የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘታቸው መንግስት መሬቱን ለህዝብ ጥቅም ሲፈልገው ተገቢውን ካሳ ሳይከፍልና የህግ ስርዓቱን ሳይከተል መሬቱን እንዳይወስድ ያደርጋል። መሬት ለህዝብ ጥቅም ቢወሰድ የተወሰደው የመሬት ስፋት፣ መሬታቸው የተወሰደባቸው ባለይዞታዎች ብዛት፣ የዋጋ ተመን እና የተከፈለ ካሳ መጠን፣ እነዚህን ባለይዞታዎች ለማቋቋም የተሰራ ስራ እና ወዘተን የሚሳይ የመረጃ ስርዓት እንዲኖር በማድረግ ይህንንም ለቀጣይ የፖሊሲ ሃሳብ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚደረግ ይሆናል።

3.1.1.5. የብሄራዊ የመሬት መረጃ ስርዓትን ማስፋፋት

እስከአሁን በስፋት እየተካሄደ የሚገኘውን የ2 ኛ ደረጃ የይዞታ ማረጋገጥና የምስር ወረቀት የመስጠት ስራ ዘላቂነት ይኖረው ዘንድ በመረጃ ስርዓት የተደገፈ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የተጀመረውን ብሄራዊ የገጠር መሬት አስተዳደር የመረጃ ስርዓትን በተጠናከረ መንገድ በሀገሪቱ የማስፋፋትና ከገጠር መሬት ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ግብይቶች ወቅታዊ የማድረግ ስራ ይከናወናል። በተጨማሪም ይህን የመረጃ ስርዓት የሚያመነጫቸውን መረጃዎች ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ የማሳደግ ስራ ይከናወናል። በተጨማሪም የአሳታፊ የቀበሌ መሬት አጠቃቀም ዕቅድና ከዚህ ጋር የተያያዙ መረጃዎን እንዲይዝና ለተጠቀሚው ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ ምርትና ምርታማት እንዲያድግ ብሎም የአየር ንብረት ለውጥን ለመመከት የራሱን ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ይሆናል።

በተጨማሪም ይህን የመረጃ ስርዓት የሚያመነጫቸውን መረጃዎች ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ የማሳደግ ስራ ይከናወናል፡፡

3.1.1.6. የቀበሌ ማዕከላትን ማስፋፋት

በቀበሌ ውስጥ ለሚኖሩ አርሶ/አርብቶ አደሮች የተያዩ መሰረተ-ልማቶችንና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በአንድ ማዕከላዊ ቦታ የቀበሌ ማዕከላትን መገንባት አስፈላጊ ነው፡፡ ለምሳሌ በአማራ ክልል የተጀመረውን የቀበሌ ማዕከላት (የቀበሌ ዋና ከተማ) ምስረታ እንደ ተሞክሮ በመውሰድ በቀጣይ በሌሎችም ክልሎች በስፋት ተጠናክሮ የማስፋፋት ስራ ይሰራል፡፡ ይህ የቀበሌ ማዕከል ግንባታም በሚዘጋጀው አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም ዕቀድ ዝግጅትን መሰረት ያደርጋል፡፡ የገጠር ቀበሌ ማዕከላትን ማስፋፋት እነሱን ተከትለው የግበርና ቴክኖሎጂና ግብአት አቅራቢዎች፣ የግብርና ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲቋቋሙ አስቻይ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ይህም ለአርሶ/አርብቶ አደሮች ለምርታቸው ገበያ በመፍጠር በብዛትና በጥራት እንዲያመርቱና ገቢቸውን እንዲያሻሽሉ በከፍተኛ ሁኔታ ያበረታታቸዋል፡፡ ስለሆነም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት አስፈላጊ ስትራቴጂዎችና የህግ ማዕቀፎችን መሰረት በማድረግ በአገሪቱ የቀበሌ ማዕከላት እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

3.1.1.7. የገጠር መሬት የኩታ-ገጠም ይዞታ አሠራርን ማሻሻል

የኢትዮጵያን እርሻ ለማዘመን በሚደረገው ጥረት እንደ ዋና ተግዳሮቶች ከሚታዩት መካከል የአርሶ አደሮች የመሬት ይዞታ እጅግ አነስተኛ፣ የተበጣጠሰና በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ መሆናቸው ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ አርሶ አደሮች የእርሻ ሜካናይዜሽንንና ሌሎች የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አዋጭ ካለመሆኑም በላይ የድህረ-ምርት ማሰባሰብና ጥራት ቁጥጥር ስራዎችን ለመስራትም አዳጋች አድርጎታል፡፡ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና ዘርፉን ለማዘመን አርሶ አደሮች በመሬታቸው የመጠቀም መብትን በማይነካ ሁኔታና አሰራሩ አዋጭ በሆነባቸው አካባቢዎች ኩታ-ገጠም መሬቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ (Land Consolidation) የኩታ-ገጠም ይዞታ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በረቂቅ የመሬት አጠቃቀም አዋጁ ላይ የተጠቀሱትን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የገጠር መሬት የኩታ-ገጠም ይዞታ አሠራርን የማሻሻል ስራ በስፋት ይሰራል፡፡

3.1.2 በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያለው የተፈጥሮ ሀብት የቴክኖሎጂ አቅርቦት

አርሶ/አርብቶ አደሩ ለአገራችን ሥነ-ምህዳር ቀጠናዎች ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በአግባቡ እንዲጠቀም ተቀባይነት ያላቸው በምርምር የተሻሻሉ ውጤታማ፣ ጊዜ ጉልበትንና ወጭን ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች በሚፈለገው ቦታ፣መጠንና ጊዜ በየዓይነቱ መቅረብ ይገባቸዋል፡፡ እንደዚሁም የሌሎች አገሮች ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ/አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን በመቅሰምና በማሻሻል በሠርቶ ማሳያዎች በማላመድና ተመሳሳይ ስነ-ምህዳር ባላቸው የአገራችን አካባቢዎች በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋል በተጠቃሚዎች ተቀባይነት ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች አጠቃቀምን ለማሻሻል ከፍተኛ አስዋጽኦ ያበረክታል፡፡

3.1.2.1 የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጅ ማመንጨት

የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ውጤታማነትን (ከሰብል ዕድገት ደረጃው ጋር የተገናዘበ የውሃ መጠን፣ የውሃ ማጠጫ ጊዜ-irrigation frequency) የሚያሻሽልና ምርታማነትን የሚያሳድግ ምርምር ለተለያዩ የሰብል ዓይነቶች ማካሄድ፤ የአፈር ጨዋማነት ክስተትን ከመከላከል አኳያ በከርሰ-ምድር ውሃ ቅርበት፣ በከርሰ-ምድር ውሃ ጨዋማነት ሁኔታ እና የመስኖ ውሃ አጠቃቀም መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የቅድመ ማስጠንቀቅ ቴክኒካል መረጃ ለማቅረብ ማጥናትና መከታተል፤ የአየር ንብረት ለውጥ በሚገጥም ወቅት በመስኖ ተኮር ሞዴሎች ታግዞ የሰብልን ውሃ ፍላጎት ትንብያ መስራትና ሰብል ለማምረት የሚያስችል መረጃ ማውጣት፤ የአየር ንብረት ለውጥ በሚገጥም ወቅት በመስኖ ተኮር

ሞዴሎች ታግዞ የሰብልን ውሃ ፍላጎት ትንብያ መስራትና ሰብል ለማምረት የሚያስችል መረጃ ማውጣት፤ የተቀናጀ የተፋሰስ አያያዝን ለማሻሻል ህብረ-ሙያዊ አሰራርን የተከተለ ምርምር ለልማት መተግበር፤
የሰብል ማዳበሪያ ፍላጎት መጠንን የተመለከተ ምክረ-ሃሳብ ለማቅረብ የየአካባቢውን የአፈር ንጥረ-ነገር ይዘት ምርመራና ሰብሉ ለማዳበሪያ በሚያሳየው ምላሽና አዋጭነት ላይ የተመሠረተ ምርምር ማካሄድ፤ የሰብል ምርታማነትን ያስጠበቀ እመራረት የሚያረጋግጥ የማዳበሪያ አጠቃቀም በየአርሶ አደር ማሳ (site specific) ላይ ተመስርቶ በሞባይል የታገዘ ምክረ-ሃሳብ ለተለያዩ ሰብሎች የሚያቀርብ የውሳኔ መስጫ ዘዴ (decision support tool) ለማውጣት የሚያስችል ምርምር ማካሄድ፤ የሰብል ምርታማነትን በኮትቻ አፈር ዓይነት ላይ ማሻሻል የሚያስችሉ አማራጮችን ለመሻት ምርምር ማካሄድ፤ ከኮትቻ አፈር ላይ ትርፍ ውሃን የማጥፈፊያ ዘዴ በማውጣት ውሃውንም ቀጣይ ሰብል ለማምረት ጥቅም ላይ እንዲውል የሚያስችል ምርምር ማካሄድ፤ የኮምጣጣ አፈር ችግርን ለመፍታት የሚስችሉ የኖራ መጠን መወሰኛ ዘዴዎችን መለየትና የማረጋገጫ ጥናት ማካሄድ፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እተሟጠጠ የመጣውን የአፈር ኦርጋኒክ ካርቦን መጠን ለማሻሻል የተቀናጀ የማዳበሪያ አጠቃቀም እና የሰብል ተረፈ ምርት፣ የተመረጡ እፅዋትን በለምነታቸው የእድገት ደረጃ ላይ ከአፈር ጋር በማደባለቅ ዘዴ (cover crop and green manuring) እና ሌሎችንም ለአፈር ለምነት የሚውሉበት አማራጮችን የተመለከተ ምርምር ማካሄድ፤

ናይትሮጂን ማከር (nitrogen fixing) እና ፎስፈረስን ማሟሟት (phosphorus solubilizing) የሚችሉ የአፈር ማይክሮቦችን ከውጭ በማስገባት ማላመድ እና ከራሳችን የአፈር ዓይነቶች በመሰብሰብ ጠቃሚ የሆኑትን በመለየት አዳዲስ ህያው ማዳበሪያ ማዘጋጀት፤ ውጤታማ የሆኑ የቨርሚ ኮምፖስት ቴክኖሎጂዎችን ለማቅረብ ለዚህ ዓላማ የሚፈለጉ የተለያዩ ትሎችን የመለየት ሥራ ማካሄድ፤
ለምግብና መጠጥ አግሮ-ኢንዱስትሪ፣ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ እና ለባዮጋዝ አገልግሎት የሚውሉ ጠቃሚ ማይክሮብስና ኤንዛይሞችን ለማቅረብ ምርምር ማካሄድ፤

ወቅታዊ ጥናትና መረጃን መሰረት ያደረገ የመሬት ፖሊስ ሪፎርም ሂደትን ለመተግበር የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን በምርምር መደገፍ ያሰፍልጋል። ለምሳሌ፡- መሬትና ግጭት፣ የይዞታ ደህንነት፣ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት በወጣቶችና ሴቶች ላይ ያስገኘው ውጤት፣ የመሬት ውርስና ተደራሽነት እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ የመሬት ጉዳዮች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎች በቀጣይ አምስት ዓመት ሊከናወን ይገባል።

እስከዛሬ ከተለመደው አሰራር ባሻገር ከ1981 እ.ኤ.አ ጀምሮ በአገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የተቋቋሙትን የአፈርና ውሃ ጥበቃ የምርምርና የመማሪያ ተፋሰሶችን የበለጠ በማጠናከርና በማስፋት የተሸሻሉ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች እንዲመነጩ በማድረግ እንዲሁም የሌሎች አገሮች ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ/አዋጪ ቴክኖሎጂዎችን በመኮረጅና በማላመድ ተመሳሳይ ስነ-ምህዳር ባላቸው የአገራችን አካባቢዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

በጥምር ደን እርሻ ልማት ለየሥርዓተ ምህዳሩ ተስማሚ የሆኑና ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን በተለይ አገር በቀል ዝርያዎች ዙሪያ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች እንዲመነጩና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

3.1.2.2 የተፈጥሮ ሀብት መነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

ውጤታማ የሆኑ ህያው የማዳበሪያ ዓይነቶችን (rhizobia and phosphorus solubilizing strains) በብዛት ለማምረት ብዜት ማካሄድ፤
የተላመዱ፣ የተሻሻሉና ያለቀላቸው የግብርና ምህንድስና ፕሮቶታይፖች ብዜትን ማካሄድ

3.1.2.3 የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ቅድመ-ማስፋፋት

አዳዲስ የሚወጡ የተፈጥሮ ሀብ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ ወጣቶችና ሴቶችን ያማከለ አዋጭ ቴክኖሎጂ በመለየት ማሸጋገር፤
የቅድመ-ማስፋት ሥራ ማካሄድ፤

3.1.2.4 በተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራሮች ሥልጠና መስጠት

የግብርና ልማት ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴዎችን መከተል እንዲችል የሚያግዝ ዕውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ የሰብል ምርት ተኮር የሆነ ተከታታይ ሥልጠና ለኤክስቴንሽን የግብርና ባለሙያ እና ለተጠቃሚው አካል መስጠት፤ የምርምር የሰው ኃይልን ለማጎልበት በድህረ-ምረቃ ደረጃ በተለያዩ ስፔሻላዜሽኖች ተመራማሪዎችን በማሰልጠን የዕውቀትና የክህሎት ደረጃቸውን ማሳደግ፤ምርምርን በጥልቀት ለማካሄድና አስተማማኝ ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስፈልጉ የምርምር መሠረተ-ልማቶች በተለይም ያሉትን ላቦራቶሪዎች ዘመኑ ባፈራው ሳይንሳዊ መሣሪያዎች እና የኢኮቱ አገልግሎት ከዳታ መሰብሰብ አንስቶ

3.1.3 በተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና የተሻሻሉ አሠራሮች ላይ ዕውቀቱ፣ አመለካከቱና ክህሎቱ ያደገ አርሶ/አርብቶ አደር

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን በማሻሻል የግብርናውን ምርትና ምርታማነት በማሳደግ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚቻለው የተሻሻሉ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች አጠቃቀም ማሳደግ ሲቻል ነው፡፡ ይህንንም እውን ለማድረግ ለተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የሚያገለግሉ አዋጭ አገር በቀል እና ዓለም አቀፋዊ ዕውቀቶችና ቴክኖሎጂዎች በትክክል ተተግብረው ጥቅም ላይ ሲውሉ ነው፡፡ ለዚህም የአርሶ/ከፊል አርብቶ አደሩን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ሊያሳድግ የሚችል በተግባር የተደገፈ ሥልጠናና የልምድ ልውውጥ ስርዓት በመንደፍ፣ በማዘጋጀትና በማስፋት የሚገኘውን ልምድና ዕውቀት ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡

3.1.3.1 የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ምክርና ስልጠና

በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ የምክርና ስልጠና አገልግሎቱ የአፈርና ውሃ ሃብቶችን ለመጠበቅ ቢያግዙ የተፋሰስ ልማት ቴክኖሎጅዎችና የተሻሻሉ አሰራች፣ የአፈር ጤንነትና ለምነት ለማሻሻል የሚረዱ ቴክኖሎጅዎችና የተሸሻሉ አሰራሮች፤ የሬንጅ ላንድ ልማት ቴክኖሎጅዎች፣ የጥምር ደን እርሻ ልማት ቴክኖሎጅዎች፤ የመስኖ ውሃን በቁጠባ ለመጠቀም የሚያስችሉ አሳታፊ የተቀናጁና ተፋሰስን መሠረት ያደረጉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችንና አዳዲስ አሰራሮች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የተቀመጡ ዒላማዎችን ለማሳካት ይቻል ዘንድ በቀጣይ አምስት ዓመታት በተፈትሮ ሀብት ልማና አጠቃቀም ምክርና ስልጠና አገልግሎት የሚከተሉት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል፡፡

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ፓኬጅ ዝግጅት

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ምክር አገልግሎት ለመስጠት የቴክኖሎጅ ፓኬጅ የሚዘጋጅ ሲሆን ፓኬጁ በተፋሰስ ልማት፣ጥምር ደን እርሻ፣ በሬንጅ ላንድ ልማት፣ በአፈር ጤንነትና ለምነት፣ በመስኖ ልማት እና ላይ ከምርምር የወጡ/የሚወጡ ቴክኖሎጅና የመረጃ አቅርቦትን መሰረት አድርጎ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ ዝርዝር የቴክኖሎጅና የተሸሻሉ አሰራሮች ጥንቅር በየትግበራ መስኩ በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል

የአሰልጣኞችና የአርሶ አደር ስልጠና

የተዘጋጀውን ፓኬጅ ወደ አርሶ/አርብቶ አደሩ ለማድረስ በየደረጃው የአሰልጣኞች ስልጠና ይሰጣል በተለይም የልማት ጣቢያ ሰራተኞች በተግባር የተደገፈ ስልጠና እንዲወስዱ በማድረግ በተመሳሳይ ሁኔታ የፓኬጅ ስልጠናውን በአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከል ለአርሶ አደሩ እንዲያደርሱ ይደርጋል፡፡

የመስክ ድጋፍና ክትትል
የአሰልጣኖች ስልጠናንና የአርሶ/አርብቶ አደር ስልጠናዎች ከተሰጡ በኃላ የፓኬጆችን ትግበራና የአፈፃፀም ደረጃ መሰረት በማድረግ ወቅታዊ የድጋፍና ክትትል ስራዎች የሚከናወኑ ይሆናል። የድጋፍና ክትትል አሰጣጥ የድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ በማዘጋጀት ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል።

በሰርቶ ማሳያ ማስተዋወቅ
በምክርና ስልጠና አገልግሎት አሰጠጥ ሌላው ተግባር የተሻለ አፈፃፀም ባላቸው ሞዴል አርሶ አደሮች ማሳ የአርሶ/አርብቶ አደር የመስክ ቀን በማዘጋጀት በአቅራቢያው ያሉ አርሶ አደሮች ትምህርትና ልምድ እንዲወስዱ ማድረግ ነው። ይህ ተግባር በቂ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በየደረጃው የሚከናወን ሲሆን አገር አቀፍ የመስክ ቀን ዝግጅት ግን ዓመታዊ የጊዜ ሰሌዳ ተዘጋጅቶለት ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድረስ በተቀናጀና በተናበበ መንገድ የሚፈፀም ይሆናል።

በመስክ ድጋፍና ክትትልና ከምናካሂዳው ሰርቶ ማሳያዎች የሚገኙ የአዝርዕት ልማት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ አብዛኛው አርሶ አደር ማስፋት ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ይሆናል።

ሀ) የተቀናጀ የተፋሰስ ልማትና አጠቃቀም

ካለው የችግር ስፋትና ከሚጠበቀው የምርታማነት ፍላጎት አንጻር እስካሁን የተሰሩት ስራዎች በቂ ባለመሆናቸው በቀጣይ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን በተቀናጀ መልኩ አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል። የተጎዱ ተፋሰሶችን ከመጠበቅና ከማልማት ባሻገር በተፋሰሱ ውስጥ የንብ እርባታን፣ የመኖ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትንና ሌሎች ተያያዥ የገቢ ምንጭ የሚሆኑ የልማት ሥራዎችን በቅንጅት በማከናወን የአርሶ/አርብቶ አደሩን የምግብና ስነ-ምግብ ዋስትና እንዲሁም አኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በዘላቂነት ለማረጋገጥ በስትራቴጂ መመራት ይገባል።

የተቀናጀ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማትና አስተዳደር ዓላማ የተለያዩ ስነ-አካላዊና ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና የውሀ ጥበቃ ዘዴዎችን በመጠቀም እንዲሁም የተጎዱ መሬቶችን ከንክኪ ነጻ ሆነው እንዲያገግሙ በማድረግ ለምነታቸውንና ምርታማነታቸውን ማሻሻል እንዲሁም በተፋሰሱ ከዝናብ የሚገኘውን ውሃ በአግባቡ በመያዝ/በማቆር በዘላቂነት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ነው። የተፋሰስ ልማት በዝናብ ኃይልና በመሬት ተዳፋትነት የሚከሰተውን አደገኛ ጎርፍና የአፈር መከላትን፣ በተሰሩ ግድቦች ሊፈጠር የሚችለውን የአፈር ደለል ብክለትን ለመከላከልና ለመቀነስ ጉልህ አስተዋጽኦ አደርጋል፤ የእጽዋት ባዮማስን ይጨምራል፤ የሙቀት አማቂ ጋዝን የማግለል አቅምን እንዲሁም ለመጠጥ፣ ለንጽህና፣ ለመስኖ፣ ለአሳ እርባታ የሚውል የውሃ አቅርቦትን ያሳድጋል፤ ለተፋሰስ ልማት ተጠቃሚዎች የስራ ዕድልና ተጨማሪ የገቢ ምንጭ ይፈጥራል፤ የተፋሰስ ልማትና አስተዳደር ተጠቃሚዎችን የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎች የተጠቃሚነት ዕድል ያሳድጋል፣

ከላይ ከተገለጽትና ከሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ከባቢያዊ ትሩፋቶች በዘላቂነት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ የላንድስኬፕ ዘዴ (Landscape Approch) በስፋት ተጠናክሮ ተግባራዊ ይደረጋል። ይህ ዘዴ በአንድ አካባቢ ያሉትን የማህበረሰብ ተፋሰሶችን ለማስተሳሰር፣ ቴክኖሎጂዎችንና የተሻሻሉ አሰራሮችን በሌሎች አካባቢዎች ለማስፋፋት፣ በየደረጃው ያለውን አመራርና አስተዳደር በማቀናጀት በግልጽ የሚታይ ዘላቂ ለውጥ ለማረጋገጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም እቅድን መሰረት ያደረገ የተፋሰስ ልማት እቅድ ማዘጋጀት

ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ፣ ተስማሚነትና መሬቱ ሊሰጠው የሚችለውን ጥቅም ታሳቢ ያደረገ የተቀናጀ አሳታፊ የመሬት አጠቃቀም እቅድና የተፋሰስ

የልማት እቅድ ያስፈልጋል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ በፊት የነበሩ ጥረቶች ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የተቀናጀ ክአሳታፊ የመሬት አጠቃቀም እቅድን የማዘጋጀት ክፍተት ነበር፡፡ ስለሆነም በሚዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የሚካተቱ ተግባራት የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ለመከላከል፣ የውኃ ሀብትን ለማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬት የማምረት አቅም ለማሳደግ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ የህብረተሰቡን የባለቤትነት ስሜት ለማሳደግ ችግሮቹን ከመለየት ጀምሮ ምን ዓይነት የተፋሰስ ልማት፣ የት እና እንዴት መተግበር እንዳለባቸው በጋራ በመወሰን የተቀናጀና አሳታፊ የመሬት አጠቃቀምና የተፋሰስ ልማት እቅድ ይዘጋጃል፡፡

ተፋሰሱ ያለውን ጸጋና ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ የልማት ስራ መተግበር፡-

ለእያንዳንዱ ተፋሰስ የተዘጋጀውን የተቀናጀና አሳታፊ የመሬት አጠቃቀምና የተፋሰስ ልማት እቅድ መሰረት በማድረግ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ፣ ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን እጽዋቶችን የመትከልና ሌሎች የተፋሰስ ልማት ስራዎች ይከናወናሉ፡፡ በተለይ በታላቁ የህዳሴ ግድብ ተፋሰሶች ውስጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡ በተፋሰስ ልማት ሥራ ላይ የግሉ ተሳትፎ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

የተጎዱ ቦታዎችን ከንክኪ ነጻ በማድረግ ማልማት

ልዩ ተኩረት የሚሹና የተጎዱ ቦታዎችን (Hot spot areas) በመለየትና ከንክኪ ነጻ በማድረግ እንዲለሙና በቀጣይም ለህብረተሰቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ ያገገሙ መሬቶች ሴቶችና ወጣቶች ተደራጅተው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች

የተፋሰስ ልማት ሥራውን በዘመናዊ ቴክኖሎጂና ሜካናይዜሽን የታገዘ በማድረግ እንደየመለክዓ-ምድሩን አቀማመጥና ሥርዓት ምህዳር የተለያዩ ስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ የተሰሩ የአፈርና ውሀ ጥበቃ መሰረተ-ልማቶች በጥራት ጉድለት ወይም ብልሽት የጎርፍ አደጋና የሌሎች አሉታዊ ተጽእኖ ምክንያት እንዳይሆኑ የጥራት ቁጥጥርና የጥገና ሥራ ይሰራል፡፡

ስነ-ሕይወታዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች

ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን የተሻሻሉ የዛፍ/ሳር ዝርያዎችን በመለየት ለስነ-ሕይወታዊ የተፋሰስለ ልማት በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡ በዚህም ሙቀት አማቂ ጋዞችን ለመቀነስ/ለማግለል ትኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡

የተራሮች ልማት

ወጣቶችን በማደራጀትና የግሉን ዘርፍ በማሳተፍ ከባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባላቸው እንደ ቀርከሃ በመሳሰሉ የእጽዋት ዝርያዎች ተራሮችን በማልማት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት አማቂ ጋዞችን ለማግለል አስተዋጽኦ ይደረጋል፡፡

የመጤ ወራሪ አረሞችን መስፋፋት መቀነስ

በህብረተሰብ ንቅናቄና ወጣቶችን በማደራጀት የመጤ አረሞች የተስፋፋባቸውን ቦታዎች በመለየትና አረሞቹን ለመቆጣጠር በዘመናዊ ቴክኖሎጂና ሜካናይዜሽን በመታገዝ መሬቱ ለግብርና ምርት እንዲውል ይደረጋል፡፡ የግሉን ዘርፍ በማሳተፍም እነዚህ ወራሪ አረሞች ለእንስሳት መኖ፣ ለሀይል ምንጭና ለሌሎች አገልግሎት የሚውሉበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

የማኅበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚ ማኅበራት በማደራጀት ድጋፍ

የተፋሰስ ተጠቃሚዎችን አግባብ ባላቸው ሕጐች መሠረት በማኅበር በማደራጀትና በባለቤትነት ስሜት የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያስተዳድሩበት የርክክብ፣ የአጠቃቀም፣ የአጠባበቅና የተጠያቂነት አሠራር ሥርዓት በማስፈን ተጠቃሚዎቹ ያለሙትን ሀብት ለማስተዳደር፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ የሚችሉበትን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ለዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ጉልህ አስተዋጽኦ ስለሚያደረግ ትኩረት ተስጥቶት ይሰራል፡፡

ለ) የጥምር እርሻ-ደን ልማት

ጥምር እርሻ-ደን ልማት ማለት ግብርናን ከደን ልማት ጋር በማጣመር በአነስተኛና ሰፋፊ መሬቶችን ላይ የሚተገበር ወጪ ቆጣቢ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ነው፡፡ ጥምር እርሻ-ደን መሬቱን ከአፈር መሸርሸር ለመከላከል፣ የብዝኀ-ሕይወትን ለመጠበቅ፣ የአፈር ለምነትን ለማሻሻል፤ ለሰውና ለእንስሳት ለምግብነትና ለማገዶ የሚውሉ ምርትና አገልግሎትን ይሰጣል፤ የሰብሉን የአፈር ንጥረ-ነገርንና ውሃን የመጠቀም እና ይዞ የማቆየት አቅም ቀልጣፋነት እንዲጨምር ያግዛል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በደን ላይ የሚደርሰውን ምንጣሮ ከመቀነሱም በላይ መጥቀ አማቂ ጋዞችን በማግለል ለአየር ንብረት የማይበገር አርንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ጉልህ አስተወጽኦ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በቀጠይ ዓመታት የጥምር እርሻ-ደን ልማት በስፋት ይከናወናል፡፡

የጥምር እርሻ-ደን ችግኝ ጣቢያዎችን ማስፋፋት

የችግኝ ጥራትና ጤንነት እንዲሁም በችግይ ጣቢያ ውስጥ የሚደረግ እንክብካቤ ችግኙ በሚተከልበት ስፍራ ለሚኖረው ጽድቀት፣ እድገትና ምርታማነት እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም በቀጣይ አምስት ዓመታት ለጥምር እርሻ-ደን ልማት የሚውሉ ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን ችግኞችን በተለያየ ዘዴ በጥራትና በብዛት በማፍላት የአረንጓዴ ልማት ግቦች ለማሳካት ሞዴል የመንግስት፣ የግልና የማህበረሰብ ችግኝ ጣቢያዎችን የማጠነከርና የማስፋፋት ሥራ ይከናወናል፡፡ የቢዝነስ ሞዴሎችን በማዘጋጀትም ህብረተሰቡ በተለይ ሴቶችና ወጣቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ሐ) ዘላቂ የሬንጅላንድ (ሰፊ የግጦሽ መሬት) አያያዝና አጠቃቀም

ቀደም ብለው የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የአርብቶ አደር አካባቢ ከአገራችንን መሬት 62 በመቶ የሚሸፍን ሲሆን ከአገራችን ህዝብ 12 በመቶውን፣ ከአጠቃላይ እንስሳት ብዛት ደግሞ 26 በመቶ የሚሆነውን በውስጡ የያዘ ሰፊ የግጦሽ መሬት ያለበት አካባቢ ነው፡፡ ይህም በሶማሌ (53%)፣ በአፋር (29%)፣ በኦሮሚያ ቦረና ዞን (10%)፣ እንዲሁም በደ.ብ.ብ.ሕ ክልል ባሉ የተለያዩ ዞኖች (8%) የአርብቶ አደር ህብረተሰብ እንደሚገኙ ጥናቶች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ከፍተኛ የዝናብ

እጥረት ያለባቸው በረሃማና ከፊል በረሃማ አካባቢዎች ሲሆኑ ከመሬቱ አቅም በላይ በሆነ የእንስሳት ልቅ ግጦሽ፣ የአየር ንብረት ለውጥና የድርቅ መከሰት፣ ተገቢ ባልሆነ የመሬትና ውሃ አያያዝና አጣቃቀም የተሰነሳ አካባቢው ለከፋ የመሬት መቆሳቆል ችግር የተጋለጠ ሆኗል። በተለይ በደረቃማ ወቅት አርብቶ አደሮች ለእንስሶቻቸው መኖ እና ውሃ ስለሚፈልጉ እንቅስቃሴያቸውን ታሳቢ በማድረግ ለዚህ ሰፊ የአገራችንን መሬት ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። በመሆኑም በቀጣይ አምስት ዓመት የተለያዩ የሬንጅላንድ አያያዝ ሥራዎች ከሚመለከታቸው ጋር በመቀናጀት ይከናወናሉ።

የቁጥቋጦ እና ወራሪ መጤ ዛፎችና ሣሮች መስፋፋትን መቆጣጠር

በአርብቶ አደር አካባቢ በተለያዩ ምክንያቶች ለእንስሳት መኖነት የማይውሉ የቁጥቋጦ እና የመጤ ዛፎችና ሣሮች ዝርያዎች በመስፋፋት በእንስሳት የሚበሉ የቁጥቋጦና የሣር ዝርያዎችን በመተካት ላይ ይገኛሉ። ይህም በአርብቶ አደሩ አካባቢ ከፍተኛ ኢኮኖሚዊና ኢኮሎጂያዊ ኪሳራዎችን በማስከተሉ በእንስሳት ምርታማነት፣በምግብ ዋስትናና በአኗኗር ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ እየፈጠረ ይገኛል። በመሆኑም ይንን ሁኔታ የሚያሻሽሉ ሳይንሳዊና ባህላዊ ተግባራትን በቅንጅት በመፈፀም የአርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት በዘላቂነት ማሳደግ ይገባል። ለዚህም የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ማጥናት፣ ለችግሩ መፍትሔ የሚሆኑ ሳይንሳዊና ፅውቀቶችን ማሰባሰብና የሚተገበሩትን መለየት፣ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ ንቅናቄ መፍጠር፣ ተስማሚ በሆኑ ፅውቀቶችና አሠራሮች የተጠቁ ቦታዎችን በማፅዳት የግጦሽ ምርታማነትን የማሻሻል ሥራዎች ይሰራሉ።

የግጦሽ መሬት አያያዝና አጠቃቀምን በማሻሻል ምርታማነትን ማሳደግ

የሬንጅ መሬቶች ተፈጥሯዊና ሰው-ሰራሽ በሆኑ ምክንያቶች ከፍተኛ ጉስቁልና ካጋጠማቸው የግብርና መሬቶች ውስጥ በዋነኛነት ይመደባሉ። ከምክንያቶቹ ውስጥም በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በተከታታይ ድርቅ መከሰት፣ ሬንጅ መሬቶች ከሚችሉት የእንሰሳት ቁጥር በላይ መሸከም እና በመጤ እጽዋት መወረር ዋናዋናዎቹ ናቸው። እነዚህን ችግሮች መፍታትና ሬንጅ መሬቶችን በዘላቂነት ለመጠቀም የውሃ አቅርቦትን የማሻሻል፣ የእንስሳትን ቁጥር ከመሬቱ የመሸከም አቅም ጋር የማጣጣም፣ ሬንጅ መሬቶችን ምርታማነት ለማሳደግ የሚረዱ አሰራሮችን የማስተዋወቅና ማስፋፋት እና መጤ እጽዋቶችን የመቆጣጠር ስራዎች በውስን ቦታዎች ሲተገበሩ ቆይተዋል። ሆኖም ከችግሩ ስፋት አንጻር እስካሁን የተሰሩት ስራዎች በቂ ባለመሆናቸው በሚቀጥሉት አስር አመታት እነዚህ ስራዎች በስፋትና በጥራት ይሰራሉ።

አርብቶ አደር አካባቢ የውሃ አቅርቦትን ማስፋፋት፡-

በአርብቶ አደር አካባቢ የውሃ አማራጮች በተመረጡ ማዕከላዊና ተደራሽ በሆኖ ቦታዎች በሚፈለገው መጠን ካልቀረበ በእንስሳቱ ረጅም ጉዞ የተነሳ የግጦሽ መሬት መጎሳቆል/መራቆት እንዲስፋፋ ያደርጋል። ስለሆነም ለህብረሰቡም ሆነ ለእንስሳት የሚውል ውሃ ለማቅረብ የተለያዩ የውሃ አውታሮች እንዲስፋፉ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና የልማት አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይሰራል።

መ) ዘላቂ የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ

ኢትዮጵያ በተለያዩ ሥነ-ምህዳሮች ውስጥ የሚገኝ ሰፊ የመሬት ሀብትና ለግብርና ልማት ሊውል የሚችል የተለያዩ የአፈር ዓይነቶች ያላት ቢሆንም በተለያዩ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች የአፈር ሀብታችን ጤንነቱና ለምነቱ የተጎዳ በመሆኑ የግብርናው ዘርፍ በከፍተኛ የምርታማነት ችግር ውስጥ ይገኛል። ከዋናዋና ችግሮች ውስጥ አንዱ ተገቢ ባልሆነ የአስተራረስና አያያዝ ምክንያት የአፈር ንጥረ-ነገሮችና ካርቦናዊ ቁስ ይዘት መመናመን ሲሆን የአሲዳማነትና ጨዋማነት መስፋፋት ሌሎች ችግሮች ናቸው። እንደዚሁም የኮትቻነት ባህሪ ባላቸው የአፈር አይነቶች ባሉባቸው አካባቢዎች በዝናብ

ወራት ለረዥም ጊዜ ውሃ የመተኛትና ኢንዱስትሪዎች ባሉባቸው አካባቢዎች ከጥንቃቄ ጉድለት የተነሣ በዝቃጭ/ፍሳሽ መበከል ሌሎች ችግሮች ናቸው።

ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ስልታዊ በሆነ መንገድ መፍታት ካልተቻለ ቀጣይነት ባለው መንገድ የግብርናውን ዕድገት ማስቀጠል አዳጋች ይሆናል። ስለዚህ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የአፈር ሃብታችንን ጤንነትና ለምነት በዘላቂነት ለማሻሻልና ቀጣይነት ያለው የግብርና ዕድገት ለማስመዝገብ የሚከተሉትን የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ስራዎች መስራት ተገቢ ይሆናል።

ልዩ ትኩረት የሚሹ ችግር ያለባቸው የአፈር ዓይነቶች ምርታማነት ማሻሻል

ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈር ዓይነቶች የሚባሉት አንድም በአፈሩ የተለየ የአፈጣጠር ባህርይ ምክንያት የውሃ መተኛት ችግር ያለበት (ኮትቻማ አፈሮች)፣ በዝናብ መብዛትና ተገቢ ባለሆነ የአሰተራረስ ዘዴ ምክንያት ጠቃሚ ንጥረ-ነገሮች በመታጠባቸው (አሲዳማ አፈሮች) እና በአብዛኛው ተገቢ ባልሆነ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ምክንያት የአንዳንድ ንጥረ-ነገሮች ከመጠን በላይ መከማቸት (ጨዋማ፣ ጨዋማ-ሶዳማ አፈሮች) ናቸው። እነዚህ የአፈር ዓይነቶች የተለያዩ ባህሪያት ስላላቸው እነሱንም ለማልማት የተለያዩ ስትራቴጅዎችን መከተል ያስፈልጋል።

ሆኖም እነዚህን ልዩ ትኩረት የሚሹ አፈሮች ወደ ልማት ስራ ከማስገባታችን በፊት መከናወን ካለባቸው ተግባራት መካከል የመጀመሪያው ስራ ሽፋን፣ ስርጭትና መጠናቸውን የሚገልጽ በካርታ የተደገፈ መረጃ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

አሲዳማ አፈር

የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በአሲዳማነት በከፍተኛ ሁኔታ የተጠቃ ከሦስት ሚሊየን ሄ/ር በላይ የሚሆን የእርሻ መሬት ይገኛል። ይህ መሬት የሚገኘውም ከፍተኛ የዝናብ መጠን በሚያገኙና ከፍተኛ የሰብል ምርት ሊሰጡ በሚችሉ አካባቢዎች ነው። ሥለሆነም የአፈር አሲዳማነት በምርት እና ምርታማነት ላይ በሚያመጣው ተጽዕኖ ላይ የግንዛቤ ማዳበርና ለአሲዳማ አፈር ህክምና ግብዓት የሆነውን የኖራ ቴክኖሎጂ በአርሶ አደሩ ዘንድ እንዲተዋወቅ ሰፊ ጥረት ይደረጋል።

ጨዋማ አፈር

የአፈር ጨዋማነት በተፈጥሮ (geological/parent material)፣ጨዋማነት ባለው የከርሰ-ምድር ውሃ ወደላይ መምጣት፣ ጨዋማነት ይዘት ባለው የመስኖ ውሃ በመጠቀምና ኋላቀርና ውሃ አባክኝ በሆነ የመስኖ ውሃ አመቃቀም ምክንያት ለሊፈጠር ይችላል። በተለያዩ ጊዜያት የተጠኑ ጥናቶች እንዳሚያሳዩት ኢትዮጵያ ከ11 ሚሊየን ሄ/ር በላይ በጨዋማ አፈር በተሸፈነ መሬት ስፋት ከሰሃራ በታች ባለው የአፍሪካ ክፍል አንደኛ ደረጃ መያዝዋንና በቅርብ ጊዜ በአገሪቱ እየተደረገ ባለው የመስኖ ልማት ማስፋፋት ጋር ተያይዞ ችግሩ ከዚህም በላይ እንደሚሰፋ ይገመታል።

በአብዛኛው ከመስኖ ውሃ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የተከሰተውን የአፈር ጨዋማነት ችግር ከመፍታት አንጻር እስካሁን የተሰሩ የልማት ስራዎች አጥጋቢ ባይሆኑም የአፈር ጨዋማነት መንስኤዎች፣ የሚያስከትለው ችግር እና መፍትሄዎች ዙሪያ ችግሩ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ለባለሙያዎች መጠነኛ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። በተጨማሪም ከዓለም አቀፍ የምርምር ማዕከላት ጋር በመተባበር ጨዋማነትን መቋቋም የሚችሉ የሰብል እና መኖ ዝርያዎችን ለማውጣትና በአርሶ/አርብቶ አደሩ ዘንድ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ለማስተዋወቅ የምርምር ስራዎች በተለያዩ ክልሎች እየተሰሩ ይገኛሉ።

ከችግሩ ስፋት አንጻር የተሰሩት ስራዎች እዚህ ግባ የሚባል ባለመሆኑ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በጨዋማነት የተጎዱ አፈሮችን ለማከም እስካሁን የተጀመሩ ስራዎችን አስፋፍቶ ከመቀጠል በተጨማሪ

መስኖ ላይ ከሚሰሩ አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት ጨዋማነትን የማያስከትል የመስኖ ውሀ አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት እና ተግባራዊ በማድረግ ችግሩ እንዳይስፋፋ የማድረግ ስራ በስፋት ይሰራል፡፡

ኮትቻ አፈር ልማት

የኮትቻ አፈር በኢትዮጵያ ለእርሻ አገልግሎት ከሚውሉ የአፈር ዓይነቶች በስፋትም ሆነ በለምነቱ በዋነኛነት የሚመደብ ቢሆንም በዝናብ ወቅት ከፍተኛ የውሃ መጠን የሚተኛበት በመሆኑ የሚጠበቅበትን ያህል ጥቅም እየሰጠ አይደለም፡፡ በአለፉት ዓመታት የኮትቻ አፈርን ለማልማት በተደረጉ ጥረቶች አርሶ አደሩ በማሳው ውስጥ የሚገኘውን ትርፍ ውሀ ለማጠንፈፍ የሚረዳውን የአይባር ቢቢኤም ቴክኖሎጂ መጠቀም እና የተንጣፈፈውን ትርፍ ውሀ በኩሬ በማጠራቀም በዓመት ሁለትና ሶስት ጊዜ ለማምረት ሙከራዎች ተደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ትርፍ ውሀ ማጠንፈፍ በማይቻልባቸው አካባቢዎች አርሶ አደሩ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን (ካምበር ቤድ፣ ተስማሚ የሩዝ ዝርያዎችን መጠቀም) እና ውጤታማ የሆኑ ባህላዊ አሰራሮች እንዲተዋወቅና እንዲጠቀም አማራጭ የመፍጠር ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

ሆኖም ግን ከችግሩ ስፋትና የኮትቻ አፈር ልማት የሰብሎች ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ካለው ከፍተኛ እምቅ አቅም አንጻር እስካሁን የተሰሩት ስራዎች በቂ አይደሉም፡፡ ስለዚህም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኮትቻ አፈር ልማት በስፋት መስራት ይጠበቃል፡፡ ለዚህም ከአጋር አካላት ጋር በመተባበር ነባሩን የኮትቻ አፈር የህዝብ ቅናቄ ስራ አጠናክሮ በማስቀጠል በስራ ላይ የዋሉ የውሀ ማሳባሰቢያ ቴክኖሎጂዎችን የመለየት በሰርቶ ማሳያዎች መከራ ማካሄድ እና ማስፋት ስራዎች ይሰራሉ፡፡ በተጨማሪም ከከፍተኛ ትምህርትና ከምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት አዋጪ እና ተስማሚ የሆኑ የኮትቻ አፈር የውሀ ማሰባሰቢያ ተጨማሪ ቴክኖሎጂዎችን እና አሰራሮችን ማፍለቅና ማሰራጨት ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን አጠቃቀም ማሻሻል

ባለፉት አመታት በተፈጥሮ ማዳበሪያ ስራዎች አርሶ አደሩ የተቀናጀ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ስራዎችን (ISFM) እንዲተገብር ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና አምራች ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት ቴክኖሎጂዎችን ለማስረጽ ጥረት ተደርጓል፡፡ እንደዚሁም አርሶ አደሩ የህየወ ማዳበሪዎችን በስፋት እንዲጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በየደረጃው በመስጠት፣ በአርሶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላት ሰርቶ ማሳያዎች ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ እንዲሁም ከአምራች ድርጅቶች ጋር ተቀናጅቶ በመስራት፣ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች የህየወ ማዳበሪያዎችን የማምረት አቅም በመገንባት የጥራጥሬ ሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም ከምርምር አካላት ጋር በመቀናጀት በኦሮሚያ ፣ በትግራይ እና አማራ ክልሎች የቨርሚኮምፖስት ቴክኖሎጂን በማስተዋወቅና ከማስረጽ አንጻር አበረታች ውጤቶች የተገኙ ሲሆን አርሶ አደሩ ኮምፖስትን በጥራት አምርቶ እንዲጠቀም ለማስቻል የኮምፖስት የጥራት ቁጥጥር የስልጠና ማንዋሎችን በማዘጋጀት ግንዛቤ እንዲፈጠር ከማድረግ ባለፈ መልኩ በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያችና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች የቅርብ ክትትል እና ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በአጠቃላይ በአፈር ለምነት እና ጤንነት ስራዎች ህብረተሰቡን በማነቃነቅ እመርታዊ ለውጥ ለማምጣት የአፈር ለምነት ንቅናቄ ሰነድ በማዘጋጀትና ሰነዱንም ለማስፈጸም የሚያስችል የትግበራ ማንዋል በማዘጋጀት በሁሉም ክልሎች ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ ርብርብ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በሚቀጥሉት አስር አመታት የአፈር ንጥረ-ነገርና ካርቦናዊ ቁስ ይዘት ለማሻሻል የሚረዱ ህየወ ማዳበሪያዎችን፣ የተሳቦ ቀልዝን፣ ኮምፖስትንና ፍግን በመላ አገሪቱ በስፋት ለመጠቀም እንዲቻል በየስነምህዳሩ ያሉትን የአፈር ስነ-ሕይወታዊ አካላት ብዝሀነት ጥናት ማካሄድና የአፈር ስነህይወታዊ ብዝሀነትን ለመጨመር የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን ይገባል፡፡ ለዚህም በተለያዩ የአገራችን

አካባቢዎች የአፈር ስነ-ሕይወታዊ አካላት ብዝሀነት ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ ጥናት ማድረግ፣ በየስነምህዳሩ የተለዩ ጠቃሚ የሆኑ ስነ ህይወታዊ አካላት የሚባዙበትን የአሰራር ዘይቤዎች ማመቻቸት፣ የተባዙትን ስነ ህይወታዊ አካላት በሰርቶ ማሳያ ማስተዋወቅ እና ወደ ኤክስቴንሽን ፓኬጅ ማስገባት ማስፋፋት እና የስነ ህይወታዊ አካላት ትግበራ ክትትል እና ግምገማ በማካሄድ የማሻሻያ ስራዎችን መስራት ያስፈልጋል፡፡ እነዚህ ስራዎችም ከምርምርና ልማት አጋር አካላት ጋር በቅንጅት ይሰራሉ፡፡

የአፈር ንጥረ-ነገር ይዘት ከሚመናመንባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው ሰብሎችን በማምረት ሂደት ከአፈሩ የሚወስዱትን ንጥረ-ነገሮች ወደአፈሩ የመመለስ ባህል ስለሌለ ነው፡፡ ይህንም ችግር ማስወገድ የሚቻለው የተወሰነውን የእርሻ ተረፈ ምርት በእርሻ ማሳ ላይ ለማሰቀረት ወይም ተረፈ ምርቶችን ከሌላ ቦታ በማምጣት መጨመር የሚያስችሉ ስራዎችን ስናከናውን ነው፡፡ በጥናት ላይ የተመሰረተ የዕቀባ እርሻን ማስፋፋት የሚያስችሉ አሰራሮችን ከአካባቢው ባዮፊዚካልና ሶሺዮ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የአፈር ለምነት መራቆት ችግርን ለመቅረፍ ተደጋጋሚ እርሻን በመቀነስና ውስን እርሻ በማካሄድ፣ በሽፋን/አረንጓዴ ማዳበሪያ ሰብሎች/በጉዝጓዝ መልክ በዘላቂነት አፈርን በመሸፈን ለጎርፍ እንዳይጋለጥ በማድረግ የአፈር መሸርሸርን በመቀነስ እንዲሁም በፈረቃ/በስብጥር የሚመረቱ ሰብሎችን በማስፋት የሰብል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ይሰራል፡፡ በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ልምድና እውቀት በመቀመር የእቀባ እርሻ የአሰራር መመሪያ እንዲዘጋጅ በማድረግና በየደረጃው ለሚገኙ አካላት ግንዛቤ በመፍጠር የዕቀባ እርሻን በኤክስቴንሽን ሥርዓት ውስጥ በማካተት በሰርቶ ማሳያዎችና በአ/አደር ማሳ ላይ የማስተዋወቅና የማስፋት ስራ ይከናወናል፡፡

በዚህ መሰረት በሚቀጥሉት አስር አመታት በሀገራችን ለዕቀባ እርሻ ትግበራ በከፍተኛና በመካከለኛ ደረጃ ተስማሚ እንደሆኑ በጥናት በተለዩ አካባቢዎች ቅድሚያ ትኩረት በመስጠት በየደረጃው በቂ ግንዛቤ በመፍጠርና የአመለካከት ለውጥ በማምጣት የዕቀባ እርሻን ለማስፋፋት በተጠናከረ ቅንጅታዊ አሰራር የሚተገበር ይሆናል፡፡ እንዲሁም ከምርምርና ልማት አጋር አካላት ጋር በመቀናጀት የአፈር ለምነት እና ጤንነትን ለማሻሻል የሚረዱ የተፈጥሮ ቁስ አካላትን በስፋት መጠቀም ይቻል ዘንድ ስነምህዳርን ያማከለ የተፈጥሮ ቁስ አካላትን በብዛትና በጥራት ለማምረት የሚቻልበትን ሁኔታ መለየት እና ማመቻቸት፣ በማምረት ላይ የሚሰማሩ አካላትን ማበረታታትና ስራ ላይ ማዋል እና የተመረቱ የተፈጥሮ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ግብዓቶችን በሰርቶ ማሳያዎች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፡፡

የማዕድን ማዳበያዎችን አጠቃቀም ማሻሻል

የአፈር ንጥረ-ነገር መመናመን ችግርን ለመፍታት መሰራት ካለባቸው ስራዎች መካከል የአፈሩን ይዘትና የሰብሎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ ምክረ-ሃሣብ ማዘጋጀት አንዱ ሲሆን ለዚህ ስራ ወሳኝ የሆነው የአፈር ንጥረ-ነገር ይዘት በኢትዮጵያ የአፈር ሃብት መረጃ ስርዓት ፕሮጀክት (EthioSIS) በመላ አገሪቱ በሚባል ደረጃ የተሰራ ሲሆን በዚህም የተነሣ የአፈር ምርመራን መሰረት ያደረገ የማዕድን ማዳበሪያ አጠቃቀም ስርዓት በአገር ዓቀፍ ደረጃ ተተግብሯል፡፡ ከዚህም አንጻር ቀደም ሲል በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁለት ዓይነት የማዕድን ማዳበሪያዎች (ዳፕና ዩሪያ) ብቻ ጥቅም ላይ ሲውሉ የነበረበትን የማዳበሪያ ምክረ ሀሳብ በማሻሻል በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ከሁለቱ የማዕድን ማዳበሪያ ምንጮች በተጨማሪ ፖታሽ፣ ሰልፈር፣ ዚንክ እና ቦሮን የመሳሰሉ የማዕድን ማዳበሪያዎች በምጥን መልክ በማዘጋጀት እና ለአርሶ አደሩ በስፋት በማስተዋወቅ እና ተደራሽ በማድረግ ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ ተችሏል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን የምጥን ማዳበሪያ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ትግራይ እና ደ./ብ/ብ/ሕ ክልሎች እንዲቋቋሙና አገልግሎት እንዲሰጡ ጥረት ተደርጓል፡፡

ሆኖም የተሟላ የማዳበሪያ ምክረ-ሃሣብ ከአፈር ምርመራ ውጤት በተጨማሪ የሰብሎችን የንጥረ-ነገር ፍላጎት ያገናዘበ መሆን ቢኖርበትም ይህ የምርምር ስራ በተሟላ ሁኔታ ባለመሰራቱ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ጊዜ ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት መሰራት ይገባዋል፡፡ የአፈር ዓይነት፣ የመሬት አቀማመጥን፣ ስነ-ምህዳር እና የሰብል ፍላጎትንና የአመራረት ስርዓትን ያማከለ በምርምር የተረጋገጠ የማዕድን ማዳበሪያዎች መጠንና አጠቃቀም ተግባራዊ ለማድረግ ከፌደራልና የክልል ምርምር ተቋማት ጋር በትብብር በመስራት የማዕድን ማዳበሪያዎች ምክረ ሀሳብ ለአገሪቷ የእርሻ መሬቶች ማዘጋጀትና የተዘጋጀውን ምክረ ሀሳብ መረጃ ለተጠቃሚው ማሰራጨትና መተግበር፣ የተዘጋጀውን ምክረ ሀሳብ ያመጣውን ውጤት በመገምገም የወደፊት አቅጣጫ የማስቀመጥ ስራ ይሰራል፡፡

እንደዚሁም ከክልል የግብርና መዋቅር ጋር በመቀናጀት ስነምህዳርን፣ የመሬት አቀማመጥን እና የአፈር ዓይነትን መሰረት ባደረገ መልኩ የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀም የምክር አገልግሎት በየቋንቋዎች የሚሰጥበት መመሪያ ማዘጋጀት፣ መስጠትና አገልግሎት አሰጣጡን በመገምገም እንዳስፈላጊነቱ የማሻሻል ስራ መሰራት፡፡

በተጨማሪም ከፌደራልና የክልል ምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት በመስኖ ለሚለሙ ሰብሎች የማዕድን ማዳበሪያ አጠቃቀም ምክረ ሃሳብ እና ፓኬጅ ማዘጋጀት፣ የትግበራ ዕቅድ ማውጣትና መተግበር እንዲሁም አፈጻጸሙን የመገምገም ስራዎች ይሰራሉ፡፡

የአፈር ብክለት በመቀነስ የአፈር ምርታማነትን ማሻሻል

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገራችን የከተሞችና የኢንዱስትሪዎች መስፋፋትን ተከትሎ ከቁጥጥር ማነስ የተነሣ ቀላል የማይባል የእርሻ መሬት በኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ፍሳሽ የመበከል ችግር እያጋጠመው ይገኛል፡፡ ይህንንም ችግር ለመቅረፍ ከምርምር ማዕከላትና በአካባቢ ደህንነት ላይ ከሚሰሩ አካላት ጋር በመተባበር የአፈር ብክለት ተጋላጭነት ደረጃዎችን በካርታ ማመላከት፣ አካባቢዎችን ከብክለት መከላከል እና የተበከሉትን የማከም ስራዎች ይሰራሉ፡፡

3.3.1.4 የተሻሻለ የተፈጥሮ ሀብት ግብዓት አቅርቦት

ለዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማለትም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ፣ የአፈር ኖራና ጂፕሰም፣ ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ ፓምፖች፣ ሶላር፣ የርጭትና ጠብታ መስኖ ቁሳቁሶች፣ ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸው የዛፍና ፍራፍሬ ዘሮች፣ ስነ-ሕይወታዊና ስነ-አካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የሚውሉ የተለያዩ ቁሳቁሶች ወዘተ በሚፈለገው መጠን ጊዜና በሚፈለግበት ቦታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ የተሻሻለ የተፈጥሮ ሀብት ግብዓት አቅርቦትን ለማረጋገጥ ከተጠቃሚው ዝርዝር የግብዓት ፍላጎትና የሚፈለግ መሥፈርት (ስፔስፍኬሽን) ተዘጋጅቶ ሲቀርብና ከሚመለከተው አካል ጋር በመቀናጀትም የጥራት ደረጃን የማረጋገጥ ሥራ በመስራት የተፈጥሮ ሀብት ግብዓት አቅርቦትን በማሳለጥ የተሻሻሉ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች አጠቃቀም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

የጥምር እርሻ-ደን የግብአት አቅርቦት ሥርዓት መዘርጋት፡-

ፈርጀ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን፣ በምርምር የተሻሻሉና ጥራት ያላቸውን ምርጥ የዛፍ/ሳር/ፍራፍሬ ዘሮችንና ለየሥርዓተ-ምህዳሩ ተስማሚ የሆኑ የተለያዩ የዛፍ/ሳር/ፍራፍሬ ዝርያዎች (ለምሳሌ፡- F. albida)፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ለአርሶ/ከፊል አርብቶ አደሩ በሚፈለገው አግባብ ተደራሽ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የግብአት አቅርቦት ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

ኖራ አቅርቦት ስርዓት መዘርጋት

እንደዚሁም የኖራ ማዕድን መኖሩ በተረጋገጠባቸው ቦታዎች የየኖራ መፍጫ ማሽኖችን በመትከል ለአርሶ አደሩ ተደራሽ እንዲሆን ጥረት ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኖራ ማምረት ሂደት ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ስራውን እንዲደግፉና እንዲበረታቱ በመንግስት በኩል ዕውቅና የመስጠትና የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች የአሲዳማ አፈር ናሙናዎችን በመመርመር የኖራ መጠን ለመወሰን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የመዘርጋት ጅምር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ሆንም ግን ከችግሩ ስፋት አንጻር እስካሁን የተሰሩ አሲዳማ አፈር አይነቶችን የማከም ስራዎች በቂ ባለመሆናቸው ተጨማሪ የኖራ መገኛ ኪስ ቦታዎችን የመለየት እና ካርታ የማዘጋጀት፣ የግብዓቶችን ጥራትና መጠናቸውን በመለየት አዋጪነታቸውን ማጥናትና ለአምራች ድርጅቶች ማሳወቅ፣ ቦታዎቹን ለትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ፣ የዕሴት ሰንሰለትና የገበያ ትስስር መፍጠር፣ የተለዩ ግብዓቶች ምክረ ሀሳብ ማዘጋጀት፣ በምክረ ሀሳቡ መሰረት ግብዓቶቹን ጥቅም ላይ ለማዋል ለአርሶ አደሮች ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡ ከዚህም ጎን ለጎን ከምርምር ተቋማትጋር በመቀናጀት ተስማሚ የሆኑ ዕጽዋቶችን በመምረጥ እና ጥምር ደን-እርሻ አሰራርን በማካተት በተቀናጀ ሁኔታ የመጠቀም ስራ ይሰራል፡፡

3.2 ያደገ የመስኖ ሽፋንና አጠቃቀም

የመስኖ ውሃ በበቂ መጠን ማቅረብና አጠቃቀሙን ማሻሻል የግብርናውን ዘርፍ በዘላቂነት ለማሳደግ ወሳኝ ነው፡፡ ስለሆነም በአገራችን ዋነኛ የመስኖ ውሃ ምንጭ ከሆኑት የዝናብ፣ የከርሰ-ምድርና የገፀ-ምድር ውሃ የምናገኘውን ውሃ ዘመኑ የደረሰባቸውን ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ግብርናውን ከዝናብ ጥገኝነት በማላቀቅ በዓመት ሁለትና ከዚያ በላይ ጊዜ በማምረት ምርትና ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ማሳደግ ይቻላል፡፡ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና አጠቃቀምን ማሻሻል ተገቢ ባልሆነ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ምክንያት የሚከሰተውን የአፈር ጨዋማነትና ተያያዥ ችግሮች ከመፍታት ባሻገር ተፋሰስን መሠረት በማድረግ ለሚሠሩ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ሥራዎች ውጤታማነት ጉልህ አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

ተፈጥሮ ሀብታችን በዘላቂነት ጥቅም ላይ ለማዋል በመካከለኛ ጊዜ ለመስኖ ልማት ዝግጁ የሆነ የመሬት ስፋት አሁን ካለበት 587 ሺ ወደ 897 ሺ ሄ/ር ለማድረስ፣ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም ብቃት በማህበረሰብ የመስኖ አውታሮች የሚለሙ ከ 70 ወደ 74.4 በመቶ እና በቤተሰብ የሚለሙ ከ 30 ወደ 41 በመቶ ለማሳደግ፣ እና የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ አርሶ/ከፊል አርብቶ አደር ብዛት አሁን ካለበት 4 ወደ 7 ሚሊየን ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል፡፡

3.2.1 የተስፋፋ የመስኖ መሰረተ ልማት

የመስኖ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት ከፍተኛ ሀብት የሚጠይቅ በመሆኑ በዘላቂነት ሀብት የሚገኝበትን ሥርዓት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ለባለአነስተኛ ይዞታ መስኖ ልማትና የውሃ ጥንፋፎ (ድሬይኔጅ) የሚያገለግል ብሔራዊ ፈንድ በማቋቋም የተጠናከረ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣ በመንግሥት ገንዘብ በተገነቡ አውታሮች የዉሃ መጠቀሚያ ክፍያንና የአውታር ግንባታ ወጪን መተካት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣ የመስኖ አውታሮችን ግንባታ በጥራትና በወቅት ማጠናቀቅ የሚያስችል አቅም በመገንባት ለመስኖ አውታሮች ግንባታ የተመደበን ገንዘብ በአግባብ ጥቅም ላይ ማዋል፣ በተለያየ ደረጃ የሚተገበሩ የመስኖ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ሀብት ማፈላለግና እንዲመደብ ማድረግ፣ የዉሃ ተጠቃሚ ማኅበራትን በዘላቂነት ለማጠናከር በገቅተኛ ወለድ ብድር የሚያገኙበትን መንገድ ይመቻቻል፡፡

አገራችን ለመስኖ ልማት አመቺ የሆነ መልክዓ ምድርና የውሃ ሀብት ቢኖራትም አብዛኛው ህብረተሰብ ዝናብን ከመጠበቅ ባሻገር የመስኖ ተጠቃሚ ባለመሆኑ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ስለሆነም ተስማሚ የመስኖ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመጠቀም የመስኖ ልማትን ማስፋፋት ያስፈልጋል፡፡

አዳዲስ የመስኖ አውታሮችን መገንባት

አዳዲስ የመስኖ አውታሮችን በመገንባት የመስኖ ሽፋንን ማሳደግ፡- በመስኖ ሊለማ የሚችል መሬት ባለባቸው አካባቢዎች ያሉትን የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውሃን ጥቅም ላይ ለማዋል የአውታር ግንባታዎችን በማስፋፋት የመስኖ ሽፋንን እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

የመስኖ አውታሮችን የውሃ አጠቃቀማቸውን በማሻሻል

ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉ የመስኖ አውታሮችን የውሃ አጠቃቀማቸውን በማሻሻል የመስኖ መሬት ሽፋንን ማሳደግ፡- እስካሁን ያለው የውሃ አጠቃቀማችን የሰብልን ፍላጎት ሳይሆን የውሃ አቅርቦትን ብቻ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ይህንን ውሃ ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችና አሠራሮችን በመጠቀም የመስኖ ሽፋንን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡

የመስኖ አውታሮች እድሳትና ጥገና

እድሳትና ጥገና፡- በተለያዩ ምክንያቶች ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ ወይንም ከአቅማቸው በታች አገልግሎት የሚሰጡ የመስኖ አውታሮችን እድሳትና ጥገና በማካሄድ በሙሉ አቅማቸው አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ የመስኖ ሽፋንን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡

የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ ለመስኖ አገልግሎት ማዋል

የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ ለመስኖ አገልግሎት ማዋል የሚያስችሉ አሰራሮችን በመከተል የመስኖ ሽፋንን ማሳደግ፡- እንደ ሀገር ከፍተኛም ሆነ ዝቅተኛ አማካይ ዓመታዊ ዝናብ ባለባቸውም አካባቢዎች በትርፍነት ጎርፍ ሆኖ የሚባክነውን ውሃ በመያዝ ወደ ልማት መቀየር ቢቻል በዝናብ እጥረትና አለመስተካከል ምክንያት የሚመጣውን የምርታማነት ችግር በከፍተኛ ሁኔታ መፍታት ይቻላል፡፡ ለዚህም በቤተሰብ ደረጃ የሚተገበሩ የወሃ ማሰባሰብ ሥራዎችን ውሃ ከሚቆጥቡ አሰራሮች ጋር በማቀናጀት ይተገበራል፤ በማህበረሰብ ደረጃ አገልግሎት የሚሰጡ ኩሬዎችንና አነስተኛ ግድቦችን በመገንባት የመስኖ መሬቶች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ሌሎች የመስኖ ውሃ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን ጥቅም ላይ ማዋል

ሌሎች የመስኖ ውሃ አማራጭ አቅርቦቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመስኖ ልማት ተደራሽነትን በሁሉም ስነ-ምህዳር ማስፋፋትና ማጠናከር፡- በደጋማ አካባቢዎች የተራራ ላይ የመስኖ ልማትን በማጠናከር፣ በቆላማና በደጋማ አካባቢዎች የከረሰ-ምድር ውሃ አጠቃቀምና አስተዳዳር ሥርዓትን በማጠናከርና በከተሞች አካባቢ የፍሳሽ ውሃን አጣርቶ በመጠቀም የከተማ የመስኖ ልማት ማስፋፊያ ተክኖሎጂዎችን ተግባራዊ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም ሌሎች ውሃና ሃይል ቆጣቢ የሆኑ ቴክኖሎጀዎችን በማላማድና ተደራሽነትን በማስፋት የመስኖ ልማቱን እንዲፋጠን ይደረጋል፡፡

በብዙ የመስኖ አውታሮች አንዳንድ አርሶ አደሮች የመስኖ አውታሮቹ ማልማት ከሚችሉት በላይ የእርሻ መሬት በመያዛቸው ምክንያት ሳይለሙ የሚቀሩ መሬቶች አውታሮቹን በማሻሻል በሙሉ አቅማቸው የሚያለሙበትን ሥርዓት በመዘርጋትና እንዲለሙ በማድረግ የመሬት ሽፋንን የማሳደግ ሥራ ይሠራል፡፡

3.2.2 የተሻሻለ የመስኖ አውታር አስተዳደርና ውሀ አጠቃቀም

በሀገራችን ባለፉት ዘመናት የአርሶ/ከፊል አደሩን ለድርቅ ተጋላጭነት በመቀነስ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ ብሎም ለአጠቃላይ አገራዊ የኢኮኖሚ እድገት አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማድረግ መንግስት ከፍተኛ ሀብት በመመደብ ሰፊ መሬት የማልማት አቅም ያላቸው የመስኖ አውታሮች ተገንብተዋል፡፡ ሆኖም ግን የመስኖ አውታሮቹ የሚጠበቅባቸውን አገልግሎት ከመስጠት አንፃር ከፍተኛ ውስንነት ታይቷል፡፡ የዚህ ውስንነት መንስዔውም ዘመናዊ የመስኖ አውታር አስተዳደር ስርዓት ባለመዘርጋቱ፣ የመስኖ አውታሮቹ ተገቢ የሆነ ጥገናና ዕድሳት የማይደረግላቸው መሆኑና የውሃ አጠቃቀሙም ፍፁም አባካኝና ቁጥጥር የሌለበት መሆኑ ነው፡፡ ስለሆነም ፍትሃዊ የውሃ አጠቃቀም በተላይም ለሴቶች እንዲኖር፣ ውሃን በቁጠባ ለመጠቀም እንዲሁም አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ለመቀነስ የመስኖ ውሃ

ተጠቃሚ ማህበራትን ማደራጀትና አቅማቸውን መገንባት አስፈላጊ ነው። ይህም የተሻሻለ የመስኖ አውታርና ውሀ አስተዳደርና አጠቃቀም በማረጋገጥ የመስኖ ውሃ አቅርቦትና አጠቃቀም ዘላቂ ማድረግ ያስችላል።

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የመስኖ አውታርና ውሀ አስተዳደርና አጠቃቀም ለማሻሻል በሚሰሩ ስራዎች የሚጠበቁ የአጭር ጊዜ ውጤቶች ህጋዊ ሰውነት ያገኙ የመስኖ ውሃ ተጠቃሚ ማህበር ያላቸው አውታሮች ከ1118 ወደ 3340፤ የመስኖ ውሃ አጠቃቀም በላቀ ብቃት የተገበሩ የውሃ ተጠቃሚ ማህበራት 75 በመቶ ለማድረስ ዒላማ ተቀምጧል።በአጭር ጊዜ የተቀመጡ ውጤቶችን ለማሳካት የሚከተሉት ስራዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል።

የተሻሻለ የመስኖ ውሀ አስተዳደርና አጠቃቀም ለማምጣት አዋጭ አገር በቀል እና ዓለም አቀፋዊ ዕውቀቶችና ቴክኖሎጂዎች በትክክል ተተግብረው ጥቅም ላይ ሲውሉ ነው። ለዚህም የአርሶ/ከፊል አርብቶ አደሩን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ሊያሳድግ የሚችል በተግባር የተደገፈ ሥልጠናና የልምድ ልውውጥ ስርዓት በመንደፍ፣ በማዘጋጀትና በማስፋት የሚገኘውን ልምድና ዕውቀት ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው።

3.3 የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ማስፈፀሚያ ስልቶች

የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀምን በዘላቂነት ለማረጋገጥ ነባራዊ ሁኔታውን እየፈተሹ ሥርዓታዊ ማነቆዎችን በየደረጃው መፍታትና የመፈጸም አቅምን በየጊዜው ማሳደግ ይገባል። ለዚህም በቀጣይ ዓመታት የተለያዩ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ሥራዎች ይከናወናሉ።

የገጠር መሬት አጠቃቀም ፖሊሲንና ዕቅድን ተፈጻሚ ለማድረግ፣ የመስኖ አውታር ግንባታ ጥራትንና የተፋሰስና ውሃ ተጠቃሚ ማኅበራትን ፍትሀዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ፣ በአፈር ጤንነትና ለምነት ላይ ባጠቃላይ ደግሞ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ብክለቶችንና ጉዳቶችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ አስፈላጊ የህግ ማዕቀፎችን የመከለስ ወይም የማዘጋጀት ስራ ይሰራል፤ በየደረጃው ተግባር ላይ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል።

የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት የክፍያ ሥርዓት መዘርጋት

የተፋሰስ ልማት ከፍተኛ ጉልበት፣ ጊዜና ገንዘብ የሚጠይቅ ሥራ በመሆኑ አልሚዎቹን በቀጣይነት የሚያበረታታና ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። የተፋሰስ ልማት ሥራ በላኛው/ራስጌ ያሉትንም ሆነ በታችኛው ተፋሰስ አካባቢ የሚኖሩ ህብረተሰቦችን የሚያሳትፍ ቢሆንም ከተጠቃሚነት አንጻር (የውሃ አቅርቦት፣ የመሬት ምርታማነት እድገት፣ ወ.ዘ.ተ) በአብዛኛው ለታችኞቹ ያደላ ነው። ይህም በላይኛው ተፋሰስ አካባቢ ያሉት በባለቤትነት ስሜትና በቀጣይነት አስተዋጽኦ እንዳያደርጉ እንቅፋት ይሆናል፤ ስለሆነም ከልማት ሥራው የሚገኙ ሥርዓተ-ምህዳራዊ አገልግሎቶችና ጥቅሞችን (Ecosystem Service) ዋጋቸውን በመተመን፣ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና የክፍያ ሥርዓት በመዘርጋት ሁሉም በፍትሐዊነት እንዲጠቀሙ ይደረጋል።

ዘመናዊ የተፋሰስ ልማት የመረጃ አያያዝ፣ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጠናከር

መረጃን በወጉ የመሰነድና የማመሳከር ልምዳችን ደካማ በመሆኑ እስከዛሬ በተፋሰስ ልማት ተሰርተዋል ተብለው ሪፖርት የተደረጉ ቢደመሩ ከአገራችን ቆዳ ስፋት ይበልጣሉ። በ2ኛው ዕ.ት.ዕ ዘመን የተጀመሩ ጥረቶችን መነሻ በማድረግ በጂኦ-ስፓሻል ቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የተፋሰስ ልማት መረጃ አያያዝ፣ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት የመዘርጋትና የማጠናከር ሥራ ይከናወናል።

የመስኖ መረጃ ስርዓት መዘርጋት

በ2ኛው ዕ.ት.ዕ. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የመስኖ አውታርና ውሃ አያያዝና አጠቃቀም የመረጃ ሥርዓት ለመዘርጋት የተደረገውን ጥረት መነሻ በማድረግ በቀጣይ ዓመታት እንዲሻሻልና እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡ የመስኖ አውታሮችን ብዛትና የአጠቃቀም ሁኔታና አጠቃላይ ገጽታ የሚያሳይ፤ የሰብል ውሃ ፍላጎትና የመስኖ ውሃ ማጠጫ መርሃ-ግብርን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (ICT) የሚደግፍ የመስኖ አስተዳደር ኢንፎርሜሽን ሲስተም ይጠናከራል፡፡

ዘመናዊ የአፈር ሀብት መረጃና ካርታ ዝግጅት

የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂ የትና በምን ያህል መጠን እነደሚያስፈልግ ለመወሰን፣ የሚፈለገውን የምርት መጠን ለማቀድና ለመተንበይ ወቅታዊና ዝርዝር የአፈር ሀብት መረጃ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም የተለያዩ ዘመናዊ የጂኦ-ስፓሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአፈር ሀብት ዓይነት፣ ጤንነትና ለምነት መረጃዎችን ከእርሻ መሬቶች ላይ በመሰብሰብና በመተንተን በማሳ ደረጃ የአፈር ጤንነትና ለምነት ወቅታዊ ሁኔታ የሚገልጹ እንዲሁም የአፈር ዓይነትን፣ የሰብል የአፈር ንጥረ-ነገር ፍላጎትንና ሥነ-ምህዳር መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ ዓይነት ምክረ-ሀሳብ ካርታዎችን በማዘጋጀት ለተጠቃሚው ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ ከዓለም እንዲሁም ከአፍሪካ የአፈር መረጃ ሥርዓት ጋር ትስስር በመፍጠርና የአገራችንን የአፈር መረጃ ሥርዓት በማጠናከር የአፈር መረጃ ለዘላቂ የልማት ግቦች ልማት ለሚያስፈልገው የመረጃ ግብአት እንዲውል ይደረጋል፡፡

የአፈር ላቦራቶሪዎችን አቅምና የአሰራር ደረጃ ማሻሻል

የአፈር ምርመራ ቤተሙከራዎችን በማጥናት የደረጃ መስፈርት በማዘጋጀት ደረጃ መስጠት፣ ደረጃቸውን በማሻሻል አስተማማኝ፣ ገበያ ተኮር እና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ይገባል፡፡ ለተግባራዊነቱም የብሄራዊ አፈር ምርመራ ማዕከል እና ክልል አፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች ከኢትዩጵያ ተስማሚነት እና ምዘና ደረጃዎች ማረጋገጫ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የአፈር ምርመራ ቤተሙከራዎች ሁኔታ ማጥናት የደረጃ መስፈርት በማዘጋጀት ደረጃ መስጠት እና የአፈር ምርመራ ቤተ ሙከራ መሣሪያዎች ዘላቂ የጥገና ሥርዓት መዘርጋት፡፡ በተጨማሪም የብሄራዊ አፈር ምርመራ ማዕከል እና ክልል አፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎችን በመረጃ መረብ በማስተሳሰርና በማዘመን የብቃት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ ይደረጋል፡፡

እንደዚሁም ከአጋር አካላት ጋር (በተለይ OCP) ጋር በመተባበር ጥራታቸውን የጠበቁ ተንቀሳቃሽ የአፈር ምርመራ ላብራቶሮችን በሙከራ ደረጃ ተግባራዊ በማድረግ እና በማስፋፋት ገበያ ተኮር የሆነ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል እና አገልግሎቱን በስፋት ተደራሽ የማድረግ ስራ ይሰራል፡፡

በሌላ በኩል ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የአፈር ለምነት እና ጤንነት ማሻሻያ ግብአቶች (የኖራ፣ የጂፕሰም፣ የማዳበሪያ ወዘተ...) በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥነት ያለው የጥራት ደረጃ እና የመጠን መወሰኛ ዘዴ መለየትና መጠቀም የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል፡፡ እንደዚሁም የአፈር ለምነትና ጤንነት ቴክኖሎጂ ምዝገባና የልቀት አሠራርና ሥርዓት በመቅረጽ ወደ ሙከራ ስራ ማስገባትና በስፋት በመተግበር ውጤታማነታቸውን የመገምገም ስራ ይሰራል፡፡

የአፈር ሀብት ዓይነት ልየታና ካርታ ዝግጅት

የአፈር ሀብት ዓይነት ልየታና ካርታ ዝግጅት (Soil Characterization and Mapping) ለመሬት አጠቃቀም እቅድና ለተፋሰስ ልማት እቅድ ዝግጅት በአጠቃላይ ለዘላቂ የተፈጥሮ ልማትና አጠቃቀም ሥራዎች መሰረታዊ የመረጃ ግብአት ነው። የአፈር ሀብት ዓይነትና ባህርይ ልየታ ለአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ተግባራት፣ የኮትቻ፣ አሲማ ጨዋማ አፈር ልማት መነሻ በመሆኑ በቀጣይ አምስት ዓመት በ240 ወረዳዎች/ተፋሰስ በ50,000 ስኬል የአፈር ሀብት ዓይነት ልየታና ካርታ የማዘጋጀት ሥራ ይከናወናል።

በማሳ ደረጃ የአፈር ለምነትና የማዳበሪያ ዓይነት ምክረ-ሐሳብ ካርታ ዝግጅት

የአፈር ምርመራ ውጤትን፣ የሰብል የንጥረ-ነገር ፍላጎትንና ሥነ-ምህዳር መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ አጠቃቀም ሥርዓትን ለመዘርጋት በማሳ ደረጃ የአፈር ጤንነትና ለምነት ሁኔታ ወቅታዊ መረጃዎችን በመሰብሰብ በተንቀሳቃሽ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪዎች በመመርመር በዘመናዊ የጂኦ-ስፓሻል ቴክኖሎጂን የታገዘ ምክረ-ሐሳብ ካርታ በሚፈለገው አግባር ማቅረብ ያስፈልጋል። ይህም የትና በምን ያህል ደረጃ የአፈር ንጥረ-ነገር እጥረት እንዳለ በማወቅ ተፈላጊውን የማዳበሪያና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ምክረ-ሐሳብ ለመተግበር ያግዛል።

የአፈር ንጥረ-ነገርና ካርቦናዊ ቁስ ይዘት ለውጥ ዳሰሳ ጥናት

የአፈር ለምነት ሁኔታ እና የማዳበሪያ ፍላጎት ከጊዜ ወደጊዜ ተለዋዋጭ በመሆኑ የአፈር ለምነት ሁኔታን በየአምስት አመት ልዩነት ክትትል በማድረግ የአፈር ለምነት ማሻሻያ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ያስገኘውን አዎንታዊ ውጤት ለመገምገም የአፈር ንጥረ ነገር (NPKS) እና የአፈር ካርቦናዊ ቁስ (SOM) ይዘት ለውጥ በመመርመር ፋርሚንግ ሲስተምን መሰረት ያደረገ የማዳበሪያ ፍላጎትን በማሻሻል ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በቀጣይ 5 ዓመት 1 ጊዜ በተመረጡ 9250 ወካይ ቦታዎች የአፈር ዳሰሳ ጥናት ይካሄዳል።

የተፈጥሮ ሀብት ምርምርን ማጠናከር

ከተፈጥሮ ሀብት የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግና ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ ተፈጥሮ ሀብት ልማትን በምርምር ላይ የተመሰረተ ማድረግ ወሳኝ ነው። ተፈጥሮ ሀብት በምርምር የታገዘ እንዲሆን ሀገራዊ የምርምር ማስተር ፕላን በመንደፍ አግሮ ኢኮሎጂዎችን የሚወክሉ የተፈጥሮ ሀብት ምርምር ተቋማትን የመገንባትና የተጠናከረ የተፈጥሮ ሀብት ምርምር ሥርዓት ዝርጋታ ተግባራት ይከናወናሉ፤ የተፈጥሮ ሀብት ሁኔታን በማጥናት በካርታ የተደገፈ የተፈጥሮ ሀብት ዕምቅ አቅም ይለያል፣ በተፈጥሮ ሀብት ልማት የተገኙ የምርምር ውጤቶችንና መልካም ልምዶችን ለማስፋት በምርምርና በኤክስቴንሽን መካከል ጠንካራ የግንኙነት ሥርዓት ይዘረጋል። የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ክትትል ማድረጊያ ቴክኖሎጂዎች ችግር ፈቺ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብት ምርምር ስራዎችን ተግባራዊ የሚያደረግ የምርምር ስርዓት ይዘረጋል።

የመስኖ ቴክኖሎጂ አቅርቦት ሰንሰለት ማሻሻል

የመስኖ ልማትን ለማስፋፋት ለአነስተኛ መስኖ የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ወቅቱን የጠበቀና በሚፈለገው መጠን በዘላቂነት ማቅረብ፣ ማሰራጨትና ጥገናና ዕድሳት ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መፍጠር ወሳኝ ነው። ለመስኖ አገልግሎት ወደሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚጣለውን ታሪፍ ፍትሃዊ ወደሆነ ደረጃ ለማውረድ ፖሊሲ ጥናት ማካሄድና ማስወሰን፣ ከውጭ ሀገር ለሚገቡ የመስኖ ቁሳቁሶች፣ መሣሪያዎችና መለዋወጫዎች የውጭ ምንዛሪ ቅድሚያ የሚሰጥበትን ስርዓት በመዘርጋት አቅርቦቱን ማፋጠን፣ በመስኖ ቴክኖሎጂዎች ጅምላና ችርቻሮ ንግድ ለሚሰማሩ አካላት የቢዝነስ ሥራ አመራር፣ የፋይናንስና የቴክኒክ ድጋፍ የሚያገኙበትን ስርዓት መዘርጋት፣የመስኖ ቁሳቁስ ጥገና የሚያካሂዱ ኢንተርፕራይዞችን ለማቋቋምና ለመደገፍ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት ወቅታዊ የጥገና አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

ብቃትንና የጥራት ደረጃን ማሳደግ

ምንም እንኳን በህብረተሰቡ ንቅናቄ እስከአሁን የተሰሩት የተፋሰስና መስኖ ልማት እንዲሁም የአፈር ጤንነትና ለምነት ማሻሻያ ስራዎች አበረታች ቢሆኑም በተለያየ ጊዜ የተደረጉ የክትትልና ግምገማ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት ከጥራት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ክፍተት ይስተዋላል፡፡ የዚህ ጥራት ጉድለት ምክንያት የተፈጥሮ ሀብት የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ከመልክዐ-ምድሩ አቀማመጥና ተደራሽነት እንዲሁም ሙያዊ ክህሎት ውስንነት አንጻር የተሟላ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት በመቸገራቸው ነው፡፡ ስለሆነም የመሬት አጠቃቀም ፖሊሲንና የተቀናጀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድን በተገቢው ሁኔታ ለማዘጋጀትና ተግባራዊ ለማድረግ፣ የተፋሰስ፣ የመስኖና አፈር ልማት የጥራት ደረጃን ለማሻሻል፣ የተሻሻሉ የተፈጥሮ ሀብት ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል በየደረጃው ለባለሙያዎች የአጭርና ረጅም ጊዜ ተከታታይ ስልጠናዎች በመስጠት የመፈጸም አቅምንና ብቃትን የማሳደግና ሥራ ይሰራል፡፡

የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር ማጠናከር

በተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ወሳኝ ሚና ያላቸውን የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ የልማት፣ የትምህርትና የምርምር አካላትን ሚና በዝርዝር በመለየት ቅንጅታዊ አሰራርንና ትብብርን መፍጠርና ማጠናከር በእጅጉ ያስፈልጋል፡፡ ይህም የጋራ ግንዛቤን ለመፍጠር፣ የእርስ በእርስ ተሞክሮ ልውውጥን ለማጠናከር፣ የስራ ድግግሞሽንና የሀብት ብክነትን ለመቀነስ፣ በመደመር እሳቤ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም ያሉ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን በየደረጃው በጋራ ለመፍታት ይረዳል፡፡ ለዚህም የተለያዩ ፕላትፎርሞችን/መድረኮችን በመፍጠር የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለማቀላጠፍ እንዲሁም ለስራ እድል ፈጠራ የግል ዘርፉንና የማህበራትን ተሳትፎ ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፡፡

ክፍል III፡ ቁልፍ የስኬት መስኮች

የገበያ ተኮር ግብርና ምርትና ምርታማነትን ከዘላቂ የተፈጥሮ ሃብት ልማት ጋር ለመሳካት ቁልፍ የስኬት መስኮች በትኩረት ይተገበራሉ፡፡ በሚቀጥሉት 5 አመታት የግብርና ምርምርና ኤክስቴሽን ፣ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ የግብርና ሜካናይዜሽ አገልግሎት እና የህብረት ስራ ማህበራት ስርዓት ቁልፍ የስኬት መስክ ሆነው በትኩረት ለመስራት አቅጣጭ ተይሏል፡፡

3.1 የግብርና ኤክስቴንሽን

በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የኤክስቴንሽን ስርዓቱ ለ14 ሚሊየን ለአርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች በአዝርዕት ሰብል፣ ቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም፣ በአትክልት እና ፍራፍሬ፣ በእንሳሳት እና አሳ ሀብት ልማት እና በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ተጠቃሚዎች ያደርጋል፡፡ የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ሲባል በምክርና ስልጠና አቅራቢዎች አማካይነት የሚሰጠውን የተለያዩ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች (የእውቀትና የክህሎት ሥልጠናዎች፣ የምክር አገልግሎት) ተቀብሎ የኤክስቴንሽን ፓኬጁን በሙሉ ወይም በከፊል ሲተገብር ነው፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤት የሚለካው በዕውቀቱ፣ በክህሎቱና በአመለካከቱ ተለውጦ በግብርና ቴክኖሎጂዎችን በመቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብር አርሶና አርብቶ አደር ሲፈጠር ይሆናል፡፡ ከእነዚህ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ውስጥ 71 በመቶ (10 ሚሊየን) የሙሉ ፓኬጅ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ካሉት የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ውስጥ አዳዲስና የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን የሚቀበልና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገብሩ እንዲሁም ለሌሎች አርሶና አርብቶ አደር አርአያ ሊሆኑ የሚችሉ 30 በመቶ (4.2 ሚሊየን) ሞዴል አርሶና አርብቶ አደሮችን መፍጠር ላይ ትኩረት ተደርጐ ይሰራል፡፡ ሞዴል /በግንባር ቀደም/ አርሶና አርብቶ አደር ማለት ገበያ ተኮር በሆነ ምርት ላይ ስፔሻላይዝ ያደረገ እና ሌሎች ምርቶችን በተጓዳኝ እየሰራ ያለ፣ የግብርና ስራ ተግባሩን ቢዝነስ ፕላን አዘጋጅቶ በተገቢው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚተገብር፣ ምርታማነትን በእጥፍ ለማሳደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በተሟላ እና ውጤታማ በሆነ አግባብ ተጠቅሞ ለውጤት የበቃ፣ ለአካባቢው የተቀመጠውን የምርታማነት ግብ/ቤንች

ማርክ በማረጋገጥ ገቢውን ያሳደገ፣ ተገቢውን የእርሻ መረጃ መዝግቦ የሚይዝ እና ለሌሎች አርሶ አደሮች በማሳየት እና በመደገፍ አርአያ የሆነ ነው። ከተጠቃሚዎች ውስጥ በግብርና ሥራ ከተሰማሩ እማወራዎችን 100%፣ ባለትዳር ሴቶች 50%፣ እንዲሁም 10 በመቶ የሚሆኑትን ወጣቶች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ይደረጋሉ።

3.1.1 ለኤክስቴንሽን ሰርዓቱን አስቻይ ብቃትን መፍጠር

የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት ማሻሻል

ግብርናችንን በማዘመን ሂደት አርሶ/አርብቶ አደሮችን ወደ አነስተኛ ኮሜርሻላይዜሽን ደረጃ ለማሸጋገር ለሚደረገው ጥረት አጋዥ የሆኑ የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት መንግስት ከተለያ ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል። አሁን ያሉትን የአርሶ/አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት አደረጃጀት የተቀመጠውን መስፈርት በሚሟላት ውጤታማ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ መሰረት በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት 5400 ማእከላት ወደ መሰረታዊ፣ 4698 ወደ መካከለኛ እና 3615 ወደ ከፍተኛ ማሰልጠኛ ደረጃዎች እንዲደረሱ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር በመሆን እንዲጠናከሩ ይደረጋል። በተጨማሪም ማእከላቱ ለተጠቃሚው ሕብረተሰብ የእውቀትና የክህሎት ሥልጠናዎች፣ የተግባር ሠርቶ ማሣያዎች፣ የመረጃ አገልግሎት በመስጠት የቴክኖሎጂ ፍላጐት መፍጠሪያ እንዲሆኑ የምርምር ማእከላት፣ ማህበራት እና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የሚሰሩበት ማእከል ይደረጋሉ።

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለግብርና ኤክስቴንሽን ሰርዓት ማዋል

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) ለግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ኤክቴንሽኑን ለማዘመንና ለማሳለጥ አንዱና ዋንኛው መሳርያ እንደሆነ ይታወቃል። ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) በኤክስቴንሽን ሰርዓት ውስጥ የኤክስቴንሽን መልእክት ለማስተላለፍ፣ የግብርና መረጃ ለመለዋወጥ (የአየር ንብረት ትንበያ፣ የግብዓት እና ግብይት መረጃ)፣ የአሰልጣኞች ስልጠና ለመስጠት፣ የልማት አካላት ትስስር እና ትብብርን ለማጠናከር እንዲሁም የግብርና እውቀት አስተዳደርን ለማዘመን እና የክትትል እና ግምገማ ስራዎችን በተገቢው መንገድ ለመተግበር ትልቅ ሚና አለው። ስለዚህ በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የኤክስቴንሽን ሥርዓቱን ለማዘመና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማቶች በሁሉም ደረጃ እንዲደራጁ ይደረጋል። የኢ.ኮ.ቴ መፍትሔ ሰጭዎች (ICT solution providers) የኤክስቴንሽኑን ሰርዓት ለማዘመን ለሚደረገው ጥረት ሚና እንዲኖራቸ እና ውጤታማ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል ዓመታዊ የምክክር መድረክ በመመስረት እንዲወያዩ ይደረጋል።

የሰው ኃይል ልማት እና ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት

ከዚህ በፊት በሥርዓተ ትምህርት ልማት እና በሥልጠና አሰጣጥ ውስጥ ትኩረት ማግኘት ሲገባቸው ባለፈው ጊዜ ትኩረት ያላገኙ ርዕሰ ጉዳዮች ማለትም የእሴት ሰንሰለት ልማት፣ ገበያ፣ የተግባቦት፣ የማመቻቸት፣ የግብርና አደጋ ተጋላጭነት ቅነሳ አመራር፣ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚስማማ ግብርና፣ ሥርዓተ ምግብ እና ሥርዓተ-ፆታ ዙርያ በሚቀጥለው አምስት ዓመታት ለሁሉም ባለሙያዎች የአጭር ጊዜ ስልጠና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከግሉ ዘርፍ፣ ከማኅበራትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች) ጋር በመሆን ይሰጣል። ተመሳሳይ መልኩ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከግሉ ዘርፍ፣ ከማኅበራትና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች) ጋር በመሆን በሚቀጠለው አምስት ዓመታት በሰርተፊከት ደረጃ የሚገኙ የልማት ጣቢያ ባለሙያዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ዲፕሎማ ደረጃ ይሸጋገራሉ። እንዲሁም በዲፕሎማ ደረጃ የሚገኙ የልማት ጣቢያ ባለሙያዎች በዲግሪ ፕሮግራም እንዲማሩ ይደረጋል። የግብርና ኤክስቴንሽን በተጠቃሚው ሕብረተሰብ ዘንድ የአመለካከትና የባህርይ ለውጥ አምጥቶ የግብርና ምርትና ምርታማነት ተከታታይነትና ዘላቂነት ባለው መልክ እንዲያድግ ለማድረግ በኤክስቴንሽን ሥራ ላይ የተሰማሩ ባለሙያዎችን የተሸለ አገልግሎት ለሰጡት የማበረታቻ ሰርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። ግንባር ቀደም አርሶ/ አርብቶ/ ከፊል አርብቶ አደሮች በአንጻራዊነት የተሻለ ዕወቀት፣ ልምድና በአካባቢያቸው ተቀባይነት ያላቸው ቴክኖሎጂዎችን በቀላሉ ለማስተላለፍ ምቹ

ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ግንባር ቀደም አርሶ/ አርብቶ/ ከፊል አርብቶ አደሮች ቀስ በቀስ ክፍተታቸውን እየሞሉ ወደ ማህረሰብ ቴክኖሎጂ አሸጋጋሪነት (village level technology promoter) ማሳደግ ያስፈልጋል። ስለዚህ በሚቀጥለው አምስት ዓመታት ግንባር ቀደሞችን ወደ ማህረሰብ ቴክኖሎጂ አሸጋጋሪነት ለማሳደግ ከተለያዩ ባለደርሻ አካለት ጋር በመሆን የአሰራር መመሪያ እንዲወጣ ይደረጋል።

የግብርና ኤክስቴንሽን አደረጃጀት ማሻሻል

የኤክስቴንሽኑ ስርዓት ወደፊት ለመሄድ ለሚደረገው ጥረት ስኬት ሁሉንም የግብርና ልማት መስኮችና አምራቾች በተገቢው ደረጃ የሚያገለግል የተሟላ ዘመናዊ ቁመና ያለው የግብርና ኤክስቴንሽን ሥርዓት በማደራጀት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥረትን ከአገራዊ የግብርና ልማት ፖሊሲ አንፃር እንዲቃኝ አቅጣጫ ለማስያዝ፣ ለማስተባበር፣ ለመደገፍ እና ለመምራት የሚያስችል አደረጃጀት ማስፈን የግድ ይሆናል። በመሆኑም በሚቀጠለው አምስት ዓመታት በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ እና የተናበበ አደረጃጀት እንዲኖር በፌደራል ደረጃ የግብርና ኤክስቴንሽን ተጠሪነቱ ለሚንስትሩ ሆኖ ሁሉንም ዘርፍ /ሰብል፣ እንስሳት፣ ተፈጥሮ ሀብትና ሌሎች/ በእኩል ሊያገለግል በሚችል መልኩ ሊደራጅ ይገባዋል። በተመሳሳይም በክልል፣ በዞንና በወረዳ ደረጃ ተጠሪነቱ ለተቋሙ ለበላይ አካል ሆኖ ሁሉንም ዘርፍ በእኩል ሊያገለግል በሚችል መልኩ መደራጀት ይኖርበታል። ስለዚህ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ እና የተናበበ አደረጃጀት እንዲኖር አንድ ሰነድ ይዘጋጃል፤ ክልሎችም ከራሳቸው ነባራው ሁኔታ በማጣጣም ሰነዱን እንዲተገብሩ ድጋፍ ይደረጋል። በሚቀጠለው አምስት ዓመታት ለአርሶ/አርብቶ/ ከፊል አርብቶ አደሮችን ተደራሽ ለማድረግ እንደ ግብርና ስርዓቱ እና የህብረተሰብ ፍላጎት መሰረት የኤክስቴሽን አደረጃጀት እንዲኖር ይደረጋል።

3.1.2 የኤክስቴንሽን አገልግሎት አካለት፣ አገልግሎት አይነት እና አሰራር ስልቶች

የብዙ ተዋናዮች (Pluralistic) የኤክስቴንሽን የምክር አገልግሎትን ማሳደግ

በአገራችንም መንግሥት ያለበትን የአቅምና የበጀት ውስንነት ለመቅረፍ፣ የአርሶና አርብቶ አደሩን የቴክኖሎጂ ፍላጐት ለማርካት፣ እንዲሁም ሥራ አጥ የገጠር ወጣቶች የኤክስቴንሽን ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ በግብርና ልማቱ ተሰማርተው የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጡ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የግል ዘርፉን፣ ሕብረት ሥራ ማህበራትንና ግብዓት አቅራቢዎች በማቀናጀት የብዙ ተዋንያን/ Pluralistic/ የኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጥበትን ስትራቴጂና የአሰራር መመሪያ ይዘጋጃል። ከዚህም ጋር ተያይዞ ብዙ ተዋናዮች የሚሰጡት የአገልግሎት አይነት፣ የአገልግሎት ፋይናንሲንግ (የገንዘብ አከፋፈል) ዘዴ እና ተደራሽነት እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማዕቀፎችን በጥናት በማዘጋጀት ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የብዙ ተዋንያንን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ጥናት እንዲጠና በማድረግ በየደረጃው እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ እንዲተገበር ጥረት ያደርጋል።

ምልዑ የኤክስቴንሽን አገልግሎት አይነት መስጠት

ገበያን መሠረት ያደረገ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት ከምርት ወደ ዘላቂ የገበያ ተኮር ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማሸጋገር ይቻል ዘንድ የኤክስቴንሽን ስርዓቱ የተጠቃሚውን ማህበረሰብ እና የአግሮ ኢንዱስትሪ ፍላጎት መሰረት ሊቃኝ ይገባዋል። ስለዚህ የኤክስቴንሽን ስርዓቱ የእሴት ሰንሰለትን መሠረት ያደረገ እና ምልዑ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በሁሉም ዘርፎች በመስጠት የግብርናውን ሴክተር ውጤታማ ሊያደርግ ይገባዋል።በዚህም መሰረት በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የኤክስቴንሽን አገልግሎት ቅድሚያ ለሚሰጣቸው የግብርና ምርቶች እና የአካባቢውን ፀጋ ከግንዛቤ በማስገባት በሰብል ልማት፤ በእንሰሳት ልማት፤ በተፈጥሮ ሀብት ልማት፤ በመስኖ ልማት፤ በሜካናይዜሽን፤ በድህረ ምርት፣ ደህንነት እና እሴት ጭመራ፤ በስርዓተ- ምግብ፤ በሥርዓተ ጾታ፤ በአየር ንብረት ሁኔታ ትንበያ መረጃ እና በገበያ ዙርያ የኤክስቴንሽን አገልግሎት በተቀናጀ መልኩ ለሁሉም የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ይሰጣል። የሚዘጋጀው ፓኬጅ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችንና በእሴት ሰንሰለት መቃኘቱን ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

የኤክስቴንሽን አቀራረብ እና ስልቶች ማዘመን

የኤክስቴንሽን አገልግሎቱ በፓኬጅ መልክ የሚዘጋጁ ኢኖቬሽኖችን ለታለመላቸው ተጠቃሚዎች በወቅቱ ለማስተላለፍ በኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ እና የተለያዩ የኤክስቴንሽን መልእክት ማስተላለፊያ ስልቶችን አቀናጅቶ የመጠቀም አሰራርን ሊከተል ይገባዋል፡፡ ስለዚህ በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በገጠርም ሆነ በከተማ ለሚገኘው ሕብረተሰብ ተደራሽ ለማድረግ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርንና ሥርፀትን ለማሳለጥ ግላዊ፣ የቡድን እና የተለያዩ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎችን ማለትም ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ቪዲዮ፣ ተንቀሳቃሽ ስልክ፣ ኢንተርኔት፣ ድረ-ገጽ፣ ማህበራዊ ሚዲያዎችን፣ እና በራሪ ጽሁፎች ወዘተ እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታና እንደ ተጠቃሚው ሕብረተሰብ የኤክስቴንሽን የመቀበል አቅም በተናጠል እና በቅንጅት እነዚህን ስልቶች ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር በመሆን በሁለም የኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ሕብረተሰቡ ደረጃ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኤክስቴንሽን ስርዓቱን ከማዘመንና ተደራሽነቱንም ከማስፋት አንጻር የኢኮቴ ለግብርና ኤክስቴንሽን የአሰራር መመሪያ ይዘጋጃል፡፡

በዞን ደረጃ የሚገኙ የግብርና ኤክስቴንሽን፣ የግብርና ምርምር፣ በግብርና ዙሪያ የሚሰሩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ኮሌጆች ና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በማሰተባበር እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር (mandate zonation approach) የግብርንቴክኖሎጂዎች እና አሰራሮችን የመለየት፣ የማረጋገጥ፣ የማስተዋወቅ፣ የመቀመርና የማስፋት ስራዎች ትኩረት ተሰጥቶት ይከናወናል፡፡ በዚህ መሰረት በአንድ ዞን ያሉ ከላይ የተጠቀሱ ባለድርሻ አካለትን ኃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው መልኩ የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም አንድ ቀበሌ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለማድረግ በሞዴል ቀበሌ (Model Kebele) ቅኝት እንዲመራ ይደረጋል፡፡ ይህ አካሄድ ለሞዴልነት የተመረጠውን ቀበሌ ከላይ ከተጠቀሱት ተቋማት በተጨማሪ በተቀናጀና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ አስፈላጊ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በፓኬጅ መልክ አጣምሮ በመተግበር እና ለሌሎች ቀበሌዎች ማስተማሪያ በማድረግ የማስፋት አካሄድን የሚከተል ይሆናል፡፡ ስለዚህ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በአገር አቀፍ ደረጃ በማንዴት ዞኔሽን አቀራረብ 32 ሞዴል ቀበሌዎች ይመሰረታሉ፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽ ተደራሽነት ማስፋት

የሥርዓተ ፆታ እና ወጣቶችን በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ ማካተት

ሴቶች እና ወጣቶች በኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ አስፈላጊ በመሆናቸው እማወራዎችን፣ ባለትዳር ሴቶችና ወጣቶችን በኤክስቴንሽን አገልግሎት ውስጥ እኩል ተደራሽና ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የኤክስቴንሽን ስርዓቱ በየደረጃው ለሚገኙ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ሥርዓተ-ፆታ ለግብርና ኤክስቴንሽን ትግበራና አስፈላጊነት እና በሥርዓተ ፆታ ላይ የግንዛቤ፣ የዕውቀት፣ የክህሎት እና የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት ሥልጠና ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም ጊዜ እና ጉልበት ቆጣቢ ቴክሎሎጂዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በአርሶና አርብቶ አደር በማስልጠኛ ማእከላት ላይ ሰርቶ ማሳያ እና ስልጠና ለሁሉም እማወራ ይሰጣል፡፡ የሴቶችን እና የወጣቶችን የቴክኖሎጂ ተደራሽነት እና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሴቶች እና የወጣቶች የኤክስቴንሽን ቡድንን በአስር ሞዴል ቀበሌ በማደራጀት በኢኮቴ የተደገፈ የኤክስቴንሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ 100% እማወራዎችን፣ 50% ባለትዳር ሴቶችን የኤክስቴንሽን አገልግሎት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

የሥርዓተ ምግብ ትግበራ በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ ማካተት

በኢትዮጵያ ያለውን የግብርና አመራረት ሥርዓት ሥርዓተ-ምግብን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ የኤክስቴንሽን ሥርዓቱን በየጊዜው መቃኘት ያስፈልጋል፡፡ በቀጣይ አምስት ዓመታት የተሰባጠረ ምግብ አመራረትና አመጋገብ ለማሻሻል፣ እሴት ያልተጨመረባቸው የግብርና ምርቶችን ጥራትና ደህንነትን ለማረጋገጥ፣ የምግብና የንጥረ-ምግብ ብክነትን ለመቀነስና የምርቶችን እሴት ለመጨመር ሥርዓተ-ምግብ ተኮር የኤክስቴንሽን አገልግሎት ለሁሉም የኤክስቴንሽን ተጠቃሚዎች ይሰጣል፡፡ ሥርዓተ-ምግብ ተኮር ግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ለማሳለጥ በአርሶና አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማእከላት ላይ ሥርዓተ ምግብ ተኮር ሠርቶ ማሣያዎች ይተገበራሉ እንዲሁም 100 የሥርዓተ ምግብ ኮርነሮች

ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ይፈጠራሉ፡፡ በተጨማሪም ለሁሉም የቀበሌ ግብርና ባለሙያዎችን በሥርዓተ ምግብ ተኮር የኤክስቴንሽን አገልግሎት ዕንሰ ሀሳብ ላይ ሥልጠና ይሰጣል፡፡

የከተማ ግብርና እና ለግል ባለሃብት የኤክስቴንሽን አገልግሎትን መሰጥት

ለከተማ ግብርና እና ለግል ባለኃብት የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በሚቀጥለው አምስትዓመት ተኩረት ተሰጥቶት ይሰራል፡፡ በዚህም መሰረት ለከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ለመስጠት ይቻል ዘንድ የከተማ ግብርና የኤክስቴንሽን ሰርዓት ይቀረፃል፤ የማሰፈፃሚያ ሰነድ ይዘጋጃል፤ እንዲሁም የኤክስቴንሽን ፓኬጅ በማዘጋጀት ለሚመለከታች አካላት ስልጠና እና ግንዛቤ ይፈጠራል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የግል ባለሀብቶችን የኤክስቴንሽን አገልግሎትን ተጠቃሚ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የግል ባለሀብቶችን የሚፈልጉትን የኤክስቴንሽን አገልግሎትን በመለየት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎት እንዲያገኙ ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር በመሆን ድጋፍ ይደረጋል፡፡

3.1.3. የግብርና ልማት አካላት ግንኙነት ማጠናከር

ሁሉም ባለድርሻ አካላት የግብርና ልማቱን በተልኳቸው መሰረት በውጤታማነት እንዲያግዙ የሚያስችል በመርህ ላይ የተመሰረት ህጋዊ ማዕቀፍና ተቋማዊ ይዘት ያለው የግንኙነት መድረክ ማደራጀት ይገባል፡፡ ስለዚህ በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በሁሉም ደረጃ በበጀትና በሰው ኃይል የተደራጀ ራሱን የቻለ መዋቅር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የመድረኩ አባላት የጋራ እቅድ በማቀድ፣ የውይይት አጀንዳዎችን በመለየትና በመቅረጽ፣ አፈጻጸምን በጋራ በመገምገም እና በየደረጃው የአቅም ግንባታ ሥልጠና በመስጠት እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው እና በባለቤትነት መንፈስ መድረኩን እንዲመሩት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በሁሉም ደረጃ በጋራ የፕሮግራም ዕቅዶችን ለማዘጋጀት፣ ለመተግበር፣ መረጃዎችን በመለዋወጥ፣ የመጣውን ውጤት ለመገምገም፣ የአቅም ግንባታዎችን ለማመቻቸትና የግንኙነት ክህሎትን ለማዳበር በአጋር አካላት መካከል ያለውን የሥራ ትብብር እና የመቻቻል መንፈስ እንዲጠነክር ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት በምርምር፣ ኤክስቴንሽን እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ንዑስ የምክክር መድረክ በክልል ደረጃም እንዲቋቋም ይደረጋል፣ በምርምር፣ ኤክስቴንሽንና አርሶ/አርብቶ አደሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር በፌደራልና በክልል ደረጃ ንዑስ የምክክር መድረክ ይመሰረታል፣ በመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መካከል ንዑስ የምክክር መድረክም እንዲሁ በክልል ደረጃ እንዲቋቋም ይደረጋል፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ከሚሰጡ የግል ተቋማት መካከል ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ለማጠናከር ንዑስ የምክክር መድረክ በክልልና በፌደራል ደረጃ ይቋቋማል፣ በስትራቴጂክ ኮሞዲቴ የተቋቋሙ መድረኮች ለዋናው የግብርና ልማት አጋር አካላት ግንኙነት አማካሪ ካውንስል ተጠሪ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቱን ለማዘመንና ተደራሽነቱን ለማስፋት በኢኮቴ ዙሪያ ከሚሰሩ የግልና የመንግስት ድርጅቶች ጋር በቋሚነት በመወያየት ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኤክስቴንሽን ስርዓቱ ለማስገባት የሚያስችል ንዑስ የምክክር መድረክ በክልልና በፌደራል ደረጃ እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ በተለይም የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኮሎጆች ዘርፉ የሚፈልገውን የመካከለኛ ደረጃ የሰለጠነ የልማት ጣቢያ ሰራተኞች እንዲያፈራ በቅረበት ይሰራል፡፡

3.2 የግብርና ቴክኒክና ሙያ ስልጠና

የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና መርሃ-ግብር የቀጣይ አምስት ዓመታት መሪ ዕቅድ የሚከተሉትን አቅጣጫ በመከተል የሚፈፀም ይሆናል፡፡ የግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥልጠና ሥርዓቱ የአገር አቀፍ የግብርና እድገት እና ኢንቨስትመንት እቅድ አቅጣጫን ተከትሎ፤ በተመረጡ የግብርና ምርቶች የእሴት ሰንሰለት ተከትሎ እና በሥራ ገበያው ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ ውጤት ተኮር የሥልጠና ሥርዓትን በመከተል ለወጣቶችና ሴቶች በግብርና ዘርፍ ስራ ፈጣሪነት ላይ ትኩረት በመስጠት በመደበኛ እና መደበኛ ባልሆነ የሥልጠና መርሃ ግብር ሠልጣኞችን በመቀበል እንዲተበር በትኩረት ይሰራል፡፡ የግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥልጠና አገልግሎት በግብርናው መስክ ለአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ ለተለዩ ሶስቱ ስትራቴጅክ ዓላማዎችን (ገበያ ተኮር የሰብል ምርትና ምርታማነት፣ ገበያ ተኮር የእንስሳትና ዓሳ ምርትና ምርታማነት እና ዘላቂ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም) እንዲሁም ዘርፈ ብዙ ውጤቶችን

ለአብነትም የህብረት ስራ ማህበራት ማስፋፋት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ለማሳካት በአጭር ጊዜ፣ በመካከለኛና ረጅም ጊዜ የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በማቅረብ ለአርሶ አርብቶ አደሩ የምክርና የኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ በማድረግ እና በዘርፉ ለተሰማሩ የግል ባለሀብቶች፣ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እና አግሮ ኢንዲስትሪ ፓርኮች በየደረጃው የሰለጠነ የሰው ሀይል በማቅረብ ረገድ ሰፊ ሚና ይጫወታል፡፡

በእቅድ ዘመኑ 25 ሺህ (45 በመቶ ሴቶች) የመካከለኛ ደረጃ ባለሙያዎችን (ከደረጃ I እስከ V) በደረጃ 4 እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ በተለያዩ ገበያው በሚፈልጋቸው የግብርና ምርቶች እሴት ሰንሰለት ተከትሎ ለ14,000 በሥራ ላይ ለሚገኙ የልማት ጣቢያ እና ኢንዱስትሪ ባለሙያዎች፣ ለ35,000 አርሶና አርብቶ አደሮች፣ ለ14,000 ለሚሆኑ የሀገሪቷ ስራ አጥ ሴቶችና ወጣቶች (50 በመቶ ሴቶች) በክህሎትና በእውቀት አቅማቸውን በሥልጠና እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም በግብርና ጥቃቅንና አነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው በሥራ ላይ ለሚገኙ 1,400 ኢንተርፕራይዞች (5 ሰልጣኝ በአንድ ኢንተርፕራይዝ) ክፍተት ላይ ያተኮረ ሥልጠና በመስጠት ብቃታቸው በአገር አቀፍ ምዘና በማረጋገጥ ምርታማ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለትን ተከትሎ በተለዩ ክፍተቶች ላይ በመመስረት ችግር ፈቺ ምርምር ከሚያደርጉ ማዕከላት ጋር በመሆን የቴክኖሎጂ ማቀብ፣ ማላመድና ማሸጋገር ስራ ይተገበራል፡፡ በዓመት 3 ቴክኖሎጂዎች ከእያንዳንዱ የሥልጠና ተቋም በእቅድ ዘመኑ በጥቅሉ 300 ቴክኖሎጂዎች ተኮርጀ፣ በማቀብ እና በማባዛት ሽግግር እንዲደረግ ይሠራል፡፡ በግብርና ሚኒስቴር እና በክልል ቴ/ሙ/ት/ሥ/ ኤጀንሲ እና ቢሮዎች፣ እና በክልል ግብርና ቢሮዎች ተበጣጥሶ እየተመራ የሚገኘውን የሥልጠና ሥርዓት አገር አቀፍ የግብርና ሥልጠና ማስፈፀሚያ የህግ ማእቀፎች በየደረጃው በማዘጋጀትና የጥራት ማኔጅመንት ስርዓትን ወጥ በሆነ መንገድ በመዘርጋትና ተግባራዊነቱን በማረጋገጥ ሥልጠናው የአገሪቱን የግብርና ኢንቨስትመንት እድገት አቅጣጫ ተከትሎ ውጤታማ እንዲሆን በአንድ ማዓቀፍ በወጥነት እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ የግብርና ሙያ ደረጃ፣ የብቃት ምዘና ደክመንት፣ የሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማርያ ሞጁሎቹ የገበያ ጥናትን መሰረት በማድረግ እንዲከለሱ እና በአዲስ እንዲቀረፁ ይደረጋል፡፡ በሀገራችን የሚገኙ የግብርና ሙያ ስልጠና ተቋማት በተፈላጊ መጠንና ጥራት ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሥጠት እንዲችሉ፣ በተመረጡ የግብርና ምርቶች ሥልጠና የልህቀት እንዲሁም የቴክኖሎጂ ማፍለቂያ፣ ማባዣ እና ማሸጋገርያ ማዕከላት እንዲሆኑ በሚያስችል መጠን በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጅ መመሪያ፤ የፍላጎት ክፍተት የጥናት ውጤት መሰረት እና የሠልጣኝ ቅበላ አቅማቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በመሠረተ ልማት እና በተግባር ሥልጠና መስጫ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ በግብርናው ዘርፍ በሥራ ገበያ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ በሙያ ደረጃ ቀረፃ፣ የብቃት ምዘና ፓኬጅ፣ ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ሞጁል ዝግጅት ተሣታፊ የሚሆኑ በተለያዩ የግብርና ሙያ ዘርፎች 400 ባለሙያዎችን የአጭር ጊዜ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል እንዲሁም 2500 መምህራን የአጫጭርና የረጃጅም ጊዜ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ አጋር አካላትና ድርጅቶች ለግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የቁሳቁስ ድጋፎችን እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተሻሉ ናቸው ተብለው ከተለዩ ሀገሮች የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲለዩና ተቀምረው ለስልጠናው ውጤታማነት በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

3.2.1 *መዋቅራዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት ማሻሻያ*

እየተሰራበት ያለው የግ/ቴ/ሙ/ት/ስ አደረጃጀት በግብርናው ዘርፍ እየተሰጠ ያለውን ስልጠና ለመምራትና ለመደገፍ በሚያስችል ደረጃ የተደራጀ ባለመሆኑ፣ በፌደራል ግብርና ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር እና በክልል መንግስታት፣ ተበጣጥሶ እየተመራ የሚገኘውን የሥልጠና ሥርዓት፣ አገር አቀፍ የግብርና ሥልጠና ማስፈፀሚያ የህግ ማእቀፎች በየደረጃው በማዘጋጀት፣ የጥራት ማኔጅመንት ስርዓትን ተግባራዊነት በማረጋገጥ፣ ሥልጠናው የአገሪቱን የግብርና ኢንቨስትመንት እድገት አቅጣጫ ተከትሎ ውጤታማ እንዲሆን፣ በአንድ ማዓቀፍ በወጥነት እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት

እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡

ይህንንም ወደ ተግባር ለመለወጥ በዋነኝነት በአፍሪካ ህብረት CAADP (Comprhensive African Agriculture Development Program) በአህጉር ደረጃ የተዘጋጀውን የግብርና ቴ/መ/ት/ሥ ማስተግበርያ መመርያን የምንከተል ይሆናል፡፡ ይህንንም መዋቅራዊ አደረጃጀት ተከትሎ በፌደራል እና በክልል መንግስት ሥር የሚገኙ የስልጠና ተቋማት የውጤት ተኮር የሥልጠና ሥርዓትን ለማስፈፀም በሚያስችል መንገድ፣ መዋቅራዊና የአሰራር ሥርዓት ማስተካከያ በማድረግ በመደበኛ፣ መደበኛ ባላሆኑና በኢ-መደበኛ የሥልጠና መንገዶች ሠልጣኞችን ተቀብለው ማሰልጠን እንዲችሉ ተለማጭ፣ የጎንዮሽ እና ወደ ላይ የሥልጠና እድገት ደረጃ አቅጣጫ ያለው እና ብቃት ተኮር የሥልጠና ሥርዓትን እንዲከተሉ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የሚገኙበት አካባቢ በመንግስት ተለይቶ በተመረጠበት የግብርና ምርት ልማት እና ኢንቨስትመንት አቅጣጫ ተከትለው እንደሚዋቀሩና እንደሚደራጁ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

በሥራው አለም የብቃት ፍላጎት እና በሥልጠና ተቋማት ውስጥ በሚሰጥ ሥልጠና መካከል የሚታየውን ልዩነት በማስወገድ፣ በገበያ መር ግብርና፣ ሥራ ፈጣሪ ሴቶችና ወጣቶችን ለማፍራት እንዲቻል፤ ዘመናዊ የግብርና አሠራሮችና ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር፤ እንዲሁም የአገሪቱ እድገት፣ የቴክኖሎጂ አቅምና በቀጣይነት አገሪቱ በዘርፉ ልትደርስበት ያስቀመጠችውን ግብ ማሳካትን ታሳቢ በማድረግ አሁን እየተከተልን ያለነውን የውጤት ተኮር የሥልጠና መርሀ-ግብር ትግበራ አፈፃፀም በማሻሻል፡ በአገር አቀፍ/በክልል ደረጃ በተመረጡ የግብርና ምርቶች ላይ መመሥረት፣የአገራዊና ክልሎች የግብርና እድገት አቅጣጫን ታሳቢ ማድረግ ፣የግብርና ምርቶቹን እሴት ሰንሰለትን በመከተል፣ በሥራ ገበያው የእውቀት እና ክህሎት ፍላጎት ጥናት ውጤት መሠረት፣ የባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የስልጠና ሥርአት ማሻሻያ ተግባራዊ ማድረግ፤ የግብርና ሙያ ደረጃ፣ የብቃት ምዘና ዶክመንት፣ የሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማርያ ሞጁሎች እንዲከለሱ እና በአዲስ እንዲቀረፁ ማድረግ፣ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የሥራ ዓለም ፍላጎትን የሚያሟላ እንዲሆን ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

በቴ/መ/ት/ሥ ስትራቴጂ የተቀመጠውን የ70፡30 የክህሎት እና የንድፈ ሃሳብ ስልጠና ጥምርታ ለማሳካት የተቋም ውስጥ የተግባር ስልጠና አሰጣጥ እና የሥራ ላይ ልምምድን (የትብብር ስልጠና) በተሻለ መንገድ ለማሰራት ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት መሠረታዊ የኢንተርፕራነር ክህሎትና ተዛማጅ የንግድ ሥራ አስተዳደር ሥልጠና በሁሉም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች ውስጥ አካቶ በመስጠት ረገድ ያለውን ዓለም አቀፍ ልምድና ተሞክሮ መሠረት አድርገው ተስማሚ የስልጠና ፓኬጅ እንዲያዘጋጁ ይደረጋል፡፡ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ተቋማዊ የምዘና ስርዓትና አሰጣጥ ተከታታይ የምዘና አሰጣጥ ስርዓትን ተከትሎ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡ አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ምዘና የሙያ ደረጃዎችን መሠረት አድርጎ ተግባራዊ እንዲደረጉ በማድረግ ሠልጣኞች በሰለጠኑበት የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና መስክ ብቁ መሆናቸው በምዘና እንዲረጋገጥና ብሄራዊ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ስራ ይሰራል፡፡ ከግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በተለያዩ የሙያ መስኮች ሰልጥነው ወደ ሥራ አለም የተሰማሩ ባለሙያዎች በዘርፉ ወይም በኢንደስትሪው ያመጡትን ለውጥ ወይም ውጤት እንዲሁም ያጋጠሙ ችግሮችን (Impact Assessment) የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ቀጣይነት ያለው የማሻሻያ ስራ ይሰራል፡፡

3.2.2 የሥልጠና ተቋማት አቅም ግንባታ

መሠረተ ልማት እና ግብዓት

በሀገራችን የሚገኙ የግብርና ሙያ ስልጠና ተቋማትን በተፈላጊ መጠንና ጥራት ላይ ያተኮረ ሥልጠና መሥጠት እንዲችሉ፣ በተመረጡ የግብርና ምርቶች ሥልጠና የልህቀት እንዲሁም፣ የቴክኖሎጂ ማፍለቂያ፣ ማባዣ እና ማሸጋገርያ ማዕከላት እንዲሆኑ በሚያስችል መጠን በአገር አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጅ መመሪያ፤ የፍላጎት ክፍተት የጥናት ውጤት መሰረት እና የሠልጣኝ ቅበላ አቅማቸውን

ከግምት ውስጥ በማስገባት በመሠረተ ልማት እና በተግባር ሥልጠና መስጫ ቁሳቁሶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡ በአሁን ሰዓት በፌደራል የሚተዳደሩ 5 ኮሌጆችን እና በተለያዩ ክልሎች የሚተዳደሩ 15 ኮሌጆች በጥቅሉ 20 የግብርና ቴ/ሙ/ኮሌጆችን አቅም ለመገንባት ታሳቢ ተደርጓል፡፡

የሰው ሀይል

የተቋም አመራሮችና ሠራተኞች እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥልጠና ሥርዓት ላይ ግንዛቤያቸውን በማሻሻል ለመስኩ ዕድገት የሚያደርጉት አስተዋዕዖ ማሳደግ ይቻል ዘንድ በአገር ውስጥና በውጪ አገራት የአጫጭርና የረጃጅም ጊዜ ሥልጠናዎች እና ልምድ ልውውጥ እንደሚያገኙ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ በግብርናው ዘርፍ በሥራ ገበያ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት፣ በሙያ ደረጃ ቀረፃ፣ የብቃት ምዘና ፓኬጅ፣ ሥርዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ ሞጁል ዝግጅት ተሣታፊ የሚሆኑ በተለያዩ የግብርና ሙያ ዘርፎች 800 ባለሙያዎችን በቂ ሥልጠና እንዲያገኙ በማድረግ ለሥራው ብቁ የሰው ሃይል ይፈጠራል፡፡

ሥልጠና በሚሰጥባቸው ሙያዎች፣ በሥራ ገበያው በሚፈለገው የሥራ ክንውን መሥፈርትና ጥራት ደረጃ እንዲሁም በሥራው አለም ጥቅም ላይ እየዋሉ በሚገኙ ቴክኖሎጂዎች ላይ በመመሥረት እና የክህሎት ክፍተትን በመለየት 5 ሺህ መምህራን ተገቢና ብቁ የአጫጭርና የረጃጅም ጊዜ የክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ የግብርና ቴክኒክና ሙያ አሰልጣኝ መምህራን ላይ እየታየ ያለውን የዕውቀት፣ ክህሎት እና አመለካካት ክፍተት በዘላቂነት ለመፍታት ሥልጠና በመስጠት ላይ ከሚገኙ የግብርና ቴክኒክ ሙያ ተቋማት መካከል በመምረጥ ወይም አዲስ ተቋም በማቋቋም በፌደራል ደረጃ የግብርና የቴ/ሙ/ት/ሥልጠና ተቋማት ሰልጣኞችን አሰልጣኝ መምህራንን የሚያፈራ የሥልጠና ተቋም በመፍጠር ችግሩ በዘላቂነት ለመቅረፍ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የመምህራን ፍልሰትን ለመቀነስ የአሰልጣኞች የሥራ ላይ ውጤት እውቅና እና ማበረታቻ ሥርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

3.2.3 የአጋርና የባለድርሻ አካላት ትስስር

ሥልጠና በሚሰጥባቸው በተመረጡ ሙያዎች በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትንና በዘርፉ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶችን በመለየት፣ የፍላጎት ትንተና በመሥራትና በሚኖራቸው ድርሻ ደረጃ መሰረት የግንኙነት እና ትስስር ህጋዊ ሥርዓት በማበጀት በሙያ ደረጃ እና ብቃት ምዘና ፓኬጅ ቀረፃ፣ በትብብር የክህሎት ሥልጠና፣ በቴክኒክና በሥልጠና ዶክመንቶች እና መረጃዎች አቅርቦት፣ በግብአት እና በበጀት ድጋፍ እንዲሳተፉ በማድረግ የሥልጠናውን ጥራት በማስጠበቅ የሥራ ገበያው በአውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት የበቃ የሰው ሀይል ፍላጎትን በማሟላት ረገድ ትልቅ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡ አጋር አካላትና ድርጅቶች ለግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የቁሳቁስ ድጋፎችን እንዲያደርጉ ይደረጋል፡፡ በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ የተሻሉ ናቸው ተብለው ከተለዩ ሀገሮች የተገኙትን ምርጥ ተሞክሮዎችን እንዲለዩና ተቀምረው ለስልጠናው ውጤታማነት በስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

በግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍ በተሻለ ደረጃ ላይ ከሚገኙ የውጪ ሀገር ተቋማት እና ተዛማጅ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥ ተቋማት ጋር የትብብር ግንኙነት እንዲመሰረትና እንዲጠናከር ይሰራል፤ ብቃትና ህጋዊነት ላይ የተመሠረተ ስርዓትና አደረጃጀት እንዲኖር በማድረግ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ጠንካራ አጋርነት ለመፍጠርና የተለያዩ የልማት አጋር ድርጅቶች ድጋፎችን በላቀ ደረጃ ለመጠቀም ይሰራል፡፡ የግብርናው ዘርፍ ገና እያደገ ያለና ብዙ የኢንቨስትመንት እድሎችን ሊፈጥር ከመቻሉ ጋር ተያይዞ ብዙ የሰው ሀይል የሚፈልግ ከመሆኑ አንፃር በመንግስት ብቻ በተገቢው መጠን ለማከናወን ስለሚያዳግት የግል ባለሃብቱ አዋጭነቱን በጥናት በማረጋገጥ በዘርፉ እንዲሳተፍ ማድረግን ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የሥልጠናው ዘርፍ የባለድርሻ አካላት ከሥርአቱ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ይሰራል፤ ያበረከቱትንም አስተዋዕዖ በመለየት እውቅና እና ማበረታቻ ይሰጣል፡፡ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ለማሳለጥና የስራ ግልፀኝነትና ቅልጥፍናን ለመፍጠር በማስልጠኛ ተቋማት እና በባለድርሻ አካላት መካከል የመረጃ አያያዝና ልውውጥ እና አጠቃቀም ሥርዓትን በማዘመን ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

3.2.4 ብቃት ተኮር ትምህርትና ሥልጠና

በቀጣይ አምስት አመታት የግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥልጠና በሀገራዊ የግብርና እድገት ላይ ያለውን ሚና በማሳደግ እንዲሁም የግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥልጠና ተደራሽነት አድማስን በማስፋት ከመደበኛ ሥልጠና መርሃ-ግብር በተጨማሪ መደበኛ ባልሆኑ (አጫጭር ስልጠናዎች) እና ኢ-መደበኛ (በልምድ ለተገኘ ክህሎት እውቅና የመስጠት) የሥልጠና መርሃ-ግብር ትኩረት በመሥጠት በትምህርት ደረጃ፣ በፆታ፣ በእድሜ ...ወዘተ ባልተገደበ መንገድ ሠልጣኞችን በመቀበል በመረጡት የሥራ ሙያ ተፈላጊ የተግባር ሥራ እና የሥራ ፈጣሪነት ክህሎት እና እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ በአራት የሥልጠና ፕሮግራሞች አገልግሎት ይሰጣል።

እነዚህም ለሥራ ፈጣሪ ሴቶችና ወጣቶች በመረጡት የግብርና ሥራ ዘርፍ የሚሰጥ መደበኛ ያልሆነ የአጭር ጊዜ ሥልጠና፣ ከደረጃ I እስከ V እና በአጫጭር ሥልጠና በግብርና ኢንቨስትመንቶች ውስጥ ለተቀጣሪ ባለሙያ መደበኛ ሥልጠና፣ ከደረጃ I እስከ V የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያ መደበኛ ሥልጠና ላይ በትኩረት ይሰራል። በተጨማሪም የእውቀት እና ክህሎት ክፍተትን ተከትሎ የሚሰጥ አጫጭር ሥልጠና በሥራ ላይ ለሚገኙ የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች፣ በሥራ ላይ ለሚገኙ የግብርና ኢንቨስትመነት ተቀጣሪ ባለሙያዎች፣ በግልም ሆነ በመደራጀት በሥራ ተሰማርተው ለሚገኙ ጥቃቅን፣ አነስተኛ እና መካከለኛ ደረጃ የግብርና ኢንተርፕራይዞች እና ለአርሶ/አርብቶ አደር እና ለገጠር ወጣቶችና ሴቶች የሚሰጥ ይሆናል።

3.2.5 ቴክኖሎጂ ማላመድ፣ ብዜት እና ሽግግር

አርሶ/አርብቶ አደሩ የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ የአርሶ/አርብቶ አደሩን የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለማርካት ታሳቢ ተደርጓል። ከግብርና ምርምር ማዕከላት/ከግብርና ዩኒቨርሲቲዎች የሚወጡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በተለያዩ የግብርና ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች በማላመድ እና ጥቃቅንና አነስተኛ አንቀሳቃሾችን በማሰልጠን ቴክኖሎጂዎችን ለማሸጋገር ታሳቢ ተደርጓል። በተጨማሪም የግብርና ቴ/ሙ/ት/ስ ኮሌጆች ከአርሶ/አርብቶ አደሩ ማሰልጠኛ ማዕከላት ጋር ባላቸው የሁለትዮሽ ግንኙነት የአርሶ/አርብቶ አደሩን ችግርና የቴክኖሎጂ ጥያቄ በቅርበት በመረዳት የግብርና ምርት እሴት ሰንሰለትን ተከትሎ በተለዩ ክፍተቶች ላይ በመመስረት ችግር ፈቺ ምርምር ከሚያደርጉ ማዕከላት ጋር በመሆን የቴክኖሎጂ ማቀብ፣ ማላመድና ማሸጋገር ስራ ይተገበራል። በዓመት 3 ቴክኖሎጂዎች ከእያንዳንዱ የሥልጠና ተቋም በእቅድ ዘመኑ በጥቅሉ 600 ቴክኖሎጂዎች ተኮርጆ፣ በማቀብ እና በማባዛት ሽግግር እንዲደረግ ይሠራል።

ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የማያቋርጥ የቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር ማዕከላት በመሆን የቴክኖሎጂውን ዕድገት ከግሉ ባለሀብት ጋር በመሆን የሚመሩና ችግር ፈቺ የሆኑ ጥናቶችን በማካሄድ ፕሮግራም የሚቀርፁ ማሰልጠኛዎች እንዲሆኑ እና በግብርና ቴ/ሙ/ት/ስልጠና ዘርፍ በውጤት ተኮር ስልጠና አሰጣጥና በቴክኖሎጂ አቅም ክምችትና ሽግግር በሀገር አቀፍ ደረጃ ሞዴልና የልህቀት ማዕከል የሆኑ የግብርና ቴ/ሙ/ት/ስ/ተቋማት እንዲፈጠሩ ይሰራል። የግብርና ቴ/ሙ/ት/ስ/ኮሌጆች የሰርቶ ማሳያዎች፣ የልማትና የቴክኖሎጂ ማስተዋወቂያና ማባዣ መድረኮች ለአካባቢው አርሶ/አርብቶ አደር፣ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፣ ለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በዘርፉ ለተሰማሩ መንግስታዊ የልማት ድርጅቶችና የግል ባለሃብቶች፣...ወዘተ እንደ ሞዴልነት እንዲያገለግሉ ይደረጋል።

በሥልጠና ተቋማት ተዘጋጅተው ወደ አርሶ/አርብቶ አደሩ የተሸጋገሩና ውጤታማ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በአገር አቀፍ ደረጃ የማስተዋወቅ እና የማሸጋገር ሥራ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ በመሥራት ተደራሽነትን ማሳደግ ታሳቢ ተደርጓል። የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ተቋማት የወረዳው ልማት ጣቢያ ባለሙያዎችን በማሳተፍ በዙሪያቸው የሚገኙ የአርሶና አርብቶ አደር ማሰልጠኛ ማዕከላትን ለአርሶ/አርብቶ አደርች፣ ለወጣት እና ሴቶች፣ እንዲሁም ለኮሌጅ ሰልጣኞች የተግባር ሥልጠና መስጫና የቴክኖሎጂ ብዜት እና ሽግግር ሥራዎችን ማከናወኛ ማዕከላት እንዲሆኑ ይሰራል።

3.3 የግብርና ምርምር

ግብርናን ምርታማና ተወዳዳሪ በማድረግ የአርሶና አርብቶ አደሩን ገቢ ለማሳደግ፣ የምግብና ሥርዓተ ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እና ለመዋቅራዊ ሽግግር አስተዋፅኦ ለማድረግ በመጪዎቹ አምስት

ዓመታት የዘርፉን አማካይ እድገት 6 በመቶ ጠብቆ ማሳደግ እንደ አጠቃላይ አገራዊ ግብ ተይሏል። ከዚህም አኳያ የዘርፉ ዕቅድ ለስኬት እንዲበቃ እያንዳንዱን ጥቅም ላይ የሚውል የምርት ግብዓት ውጤታማነት የሚያልቁ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎች የማያቋርጥ አቅርቦት መኖርን ታሳቢ ያደረ ነው። በመሆኑም የሀገራዊ ግብርና ምርምር ሥርዓቱ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ሂደት እንደ ሀገር ከሚጠበቁ የዘርፉ ልማት ግቦች አንፃር መቃኘት ያስፈልጋል። በምርት ዓይነቶቹ ላይ የሚደረገው ምርምር ያለንን ውስን የምርምር አቅም አሰባስቦ የቅድሚያ ቅድሚያ በተሰጣቸው አገራዊ ስትራቴጂያዊ የምርት ዓይነቶች ላይ የበለጠ አተኩሮ በመሥራት የሚሻሻለው ቴክኖሎጂም በጥራቱ ደረጃውን የጠበቀ፣ በገበያ ለተወዳዳሪነት የሚበቃና በአቅርቦቱም አስተማማኝ የሆነ ሊደረግ ይገባል። ስለዚህም ለተጠቃሚው የሚቀርቡ የግብርና ቴክኖሎጂዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸውና ለልማቱ አስተዋፅኦ አንዲያደርጉ የምርምር ሥርዓቱ ተጠባቂ ሚናውን በተለዩት የዘርፉ ስትራቴጂያዊ ዓላማዎች መሠረት የሚጫወት ይሆናል።

በግብርና ልማቱ የተቀመጡ ግቦችን እያሳኩ ለመጓዝ አርሶ/አርብቶ አደሩና የግል አምራቹ ምርታማነትን ለመጨምርና በገበያ ተፈላጊየጥራት ደረጃን ለማሟላት የሚያስችል የአመራረት ዘዴ እንዲከተሉ ለማድረግ የሚረዱተስማሚ የቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴ አማራጮችን ማቅረብ ይፈልጋል። ለዚህም የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብና የወደፊት አዝማሚያውንም አስቀድሞ በመተንበይ የሀገራችን ግብርና ያለማቋረጥ እንዲያድግ የሚያስፈልጉ አስተማማኝ ቴክኖሎጂዎችን እና የተሻሻሉ አሰራሮችን በቀጣይነት ለማቅረብ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ የመሪነት ሚናውን መጫወት ይኖርበታል፡ ፡ ስንዴን በምርምር ጣቢያ አሁን ካለበት 80 ወደ 90 ኩ/ል በሄክታር፣ በቆሎን የድቃይ ዝርያዎች (hybrids) በማውጣት ከ120 ወደ 135ኩ/ል በሄክታር እና ጤፍን ደግሞ ከ28 ወደ 32.5ኩ/ል በሄክታር ለማድረስ በትኩረት ለመሥራት ታቅዷል። ይህንንም የምርታማነት ደረጃ ለማስጠበቅ የሚፈለግ የተሻሻለ የሰብል አያያዝና እንክብካቤ (optimum agronomic practice and crop protection) ምክረ-ሃሳብ በተጓዳኝ ማቅረብ በአርሶ አደሩ ዘንድ ጎልቶ የሚታየውን የምርታማነት ክፍተት ለማጥበብ (narrowing the yield gap) በእጅጉ የሚረዳ ይሆናል። በተመሳሳይ የእንስሳት ምርምሩም የወተት ምርታማነትን በአማካይ 4000 ሊትር በአንድ የአለባ ወቅት ከአንድ ዲቃላ ላም (high-grade crossbred daidy cow) ለማግኘት የማሻሻል ሥራው አርቢ ማህበረሰቡን በማቀፍና ተጠቃሚነቱንም በሂደቱ በማረጋገጥ የሚከናወን ይሆናል። የበግ ሥጋን ከማሻሻል አኳያም የተመረጡ ሀገር በቀል ዝርያዎች ላይ ያተኮረ የማህበረሰብ አቀፍ የእንስሳት ዝርያንየማሻሻል አሰራር ዘዴ (community based animal breeding program) በመከተል በመረጣ ወይም በማዳቀልታግዞ የበግ ግልገል ፈጣን ዕድገት አንዲኖረው ማስቻልና በ6 ወር ዕድሜው አሁን ከሚደርስበት 18 ኪግ የቁም ክብደት ወደ 24-31.5 ኪግ የሚያሳድግ አጠቃላይ የበግ እርባታ ዘዴን አመጋገብንና የእንስሳቱን ጤና አጠባበቅ ጨምሮ ዒላማ ተደርጎ የሚሠራ ይሆናል።

አዳዲስ ለሚወጡ ቴክኖሎጂዎች በተጠቃሚው ዘንድ እንዲታወቁና ፍላጎትንም ለመፍጠር የሚያግዝ የቅድመ-ኤክስቴንሽን እና ቅድመ-ማስፋፋት ሥራ የታቀደ ሲሆን በቀጣይም ተቀባይነት ላገኙ ቴክኖሎጂዎችም የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት በተለይም የሰብል ዘር አቅርቦቱን ለማሳደግ የሚረዱ ዘዴዎችን በመከተል ለማምረት ከፍተኛ ጥረት የሚደረግ ይሆናል። በዚህም መሠረት ለግብርና ምርምሩ የተግባር መስኮች ማላትም የቴክኖሎጂና የግብርና አሰራር ማሻሻያ መረጃዎች አቅርቦት፣ የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ማስተዋወቅና ቅድመ-ማስፋፋት ሥራ፣ የግብርና ዕውቀትና ክህሎትን ወደ ተጠቃሚው ለማሸጋገር የአቅም ግንባታ ሥልጠና እና የመነሻ ቴክኖሎጂ ብዜትን አስመልክቶ የ አምስት ዓመታት ዒላማዎች ተቀምጧል።

3.3.1 የግብርና ቴክኖሎጅ ማመንጨት

የሀገራችን ግብርና ልማት ዕድገት እንዲፋጠን የሚረዱ ተፈላጊ ቴክኖሎጂዎችን በዘላቂነት ማቅረብ ከምርምር ሥርዓቱ የሚጠበቅ ውጤት ነው። ይሁንና የምርምር ሥርዓቱ እስካሁን ያካበተው ልምድ ላይ እየገነባ ለመሄድ የሚያስችል መነሻ እንዳለው ቢታወቅም ላለንበት ዘመን የሚሆኑ ተወዳዳሪ (በምርታማነት፣ በምርት ጥራት፣ በተቀባይነት እና በመሳሰሉት) የምርት ዓይነቶችን ለማቅረብ በአሁኑ

ጊዜ እየገጠሙ ያሉ ፈታኝ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ከእነዚህም መካከል የግብርና መሬት የመጣበብ ዝንባሌ ማሳየት፣ የአፈር ለምነት እየተሟጠጠ መምጣትና የአፈር ጤንነት ችግር መከሰት፣ ለመስኖ የሚውል ውሃ አቅርቦትና ብክለት ችግር መባባስ፣ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለው ስጋት፣ ከዚህ በፊት ተከስተው የማያውቁ በሽታዎችና ተባዮች ችግር መበራከት፣ የብዝሃ-ህይወት ሀብት መመናመን፣ የምግብ ደህንነት ጉዳይ አሳሳቢእየሆነ መምጣት እና የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ለሚያስከትሉት ተዕዕኖ መፍትሄ ያላቸው የግብርና ቴክኖሎጂዎች ማቅረብን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም አስተማማኝ የሆኑ ውጤቶች ላይ ለመድረስ እንዲቻልበምርምር ሂደቱ ከተለመደው የአሰራር ዘዴ (conventional research) ባሻገር በባዮቴክኖሎጂ ቴክኒኮችም መታገዝ እንደሚያስፈልግና ግድ እንደሆነም የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ያሳያል፡፡ከዚህ አኳያም የምርምር ሥርዓቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በሙሉ ፍላጎትና ተነሳሽነት ለመወጣት የሚያስችል የምርምር ዕቅድ በማዘጋጀት ከዓለም አቀፍ የምርምር ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትብብር በመፍጠር አቅም እየገነባ መንቀሳቀስ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ሀገራችን ካላት ሰፊ የግብርና ሥነ-ምህዳር ተለያይነት አንፃር ሁሉን አካባቢዎች በቴክኖሎጂ ተደራሽ ለማድረግ እገዛ ማድረግ የሚችሉ የግል ምርምር ተቋማት ቢመጡ ወይም ቢቋቋሙ ጠቃሚ እንደሚሆን ይታመንበታል፡፡ በሌላም በኩል ሀገራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቱ እንደ ሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ ሁሉ ለአብነት ያህልም የብራዚሉ ኢምብራፓ የምርምር ተቋም በሂደት በከፊል እራሱን የሚችል ድርጅት (semi-commercial) ቁመና እንዲይዝ ለቀጣይ አካሄዱ እንደ አቅጣጫ ለመከተል በጥናት የተደገፈ ውሳኔ ለመስጠት የሚታይ ይሆናል፡፡

በመጪዎቹ 5 ዓመታት ከምርምር የሚወጡት የግብርና ቴክኖሎጂዎች በተጠቃሚው ዘንድ ተቀባይነት ከማግኘትም ባለፈ የኤክስፖርት ገበያ የሚጠይቃቸውን የምርት ጥራት መመዘኛዎች ከማሟላት አንፃር እየተፈተሹ በተጠናከረ የቴክኖሎጂ በተለይም የዝርያ አለቃቀቅ አሰራር ሥርዓት መመራት ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም በአንድ የሰብል ዓይነት በቁጥር የበዙ ዝርያዎች እየወጡ ነገር ግን ወደ ምርት ሳይገቡ ወይም በበሽታ ወዲያው ተመተው ከምርት የሚወጡ ከሚሆኑ ይልቅ ምርምሩ ጠለቅ ብሎ በልማቱ የሚገጥሙ ችግሮችን የሚፈቱና ተቀባይነት አግኝተው ወደ ልማቱ በቶሎ የሚገቡ ጥቂት ዝርያዎች ማውጣት የሚመረጥ እንደሆነ በሁሉም ዘንድ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳየው ምርታማነትን በከፍተኛ ሁኔታ ከማሳደግ አኳያ በተመረጡ የሰብል ዓይነቶች ማለትም በስንዴ፣ ገብስ፣ ሩዝ፣ አትክልትና ፍራፍሬ በመሳሰሉት ልክ እንደ በቆሎ ሁሉ ዲቃላ ዝርያዎችን (hybrids) ለማውጣት እንደ አቅጣጫ ተወስዶ በልዩ ትኩረት ምርምሩ ሊሠራ ይገባዋል፡፡ በዚህም መሠረት የግብርና ምርምር ባሉት አራት ዋነኛ የተግባር መስኮች ማለትም የግብርና ቴክኖሎጂና የአሰራር ማሻሻያ መረጃ፣ የግብርና መነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት፣ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅና ቅድመ-ማስፋፋት እና የግብርና ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድግ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ሥር እንዲተኮርባቸው የተለዩት የምርምር ተግባራት አንደሚከተለው ተጠቃለው ቀርበዋል፡፡

3.3.2 የግብርና መነሻ ቴክኖሎጂ ብዜት

የሰብል ዝርያን መነሻ ዘር (early generation seed) በበቂ መጠንና በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ለማቅረብ እንዲቻል መስኖን በመጠቀም በዓመት ሁለት ጊዜ የማምረት ስልቶችን እና ሌሎች ተግባራዊ አማራጮችን መከተል፤ለዘር ብዜት ቀዝቃዛ ሥፍራን (chilling temperature) ለሚፈልጉ የአትክልት ሰብሎች ተስማሚ የአየር ሁኔታ ያላቸውን አካባቢዎች በመምረጥ ለተወሰኑ የአትክልት ዓይነቶች የማባዛት ሥራን ማስጀመር፤ የመነሻ ዘር ጥራቱን እና ምርታማነቱን የሚያስጠብቅ የተሟላ የሰብል አያያዝ (አግሮኖሚ እና ሰብል ጥበቃ) አሰራርን በመከተል የብዜት ሥራን እስከ ማከማቸት ሂደት (eg. seed processing, seed treatment, drying, packaging) ድረስ ያለውን በአግባቡ ማከናወን፤ የሰብል መነሻ ዘር ብዜት ሥራውን እና የዘር ጥራቱን ስታንዳርድ ለማስጠበቅ የአሰራር ሥርዓቱን ማጠናከር፤ በርቢ ባህርይ መመዘኛ (breeding value) መሠረት የወተት ከብት ዝርያ ኮርማን፣ የሀገር ውስጥ፣ የውጭና ዲቃላ የበግ/ፍየል ዝርያዎች አውራዎችን በመምረጥ ለማህበረሰብ አገልግሎት እንዲሰጡ ማቅረብ፤የወተት እርባታን ለማሳደግ ዲቃላ የወተት ከብት ዝርያን ቁጥር እንዲጨምር ጊደርን በተለያዩ ሳይንሳዊ አማራጮች (use of sexed semen, mass insemination with synchronization, embryo transfer) ማምረት፤ለዶሮ፣ ለዓሳ እና ለንብ እርባታ ተፈላጊ የመነሻ ቴክኖሎጂ (የአንድ ቀን የዶሮ ጫጨቶች፣ የዓሳ ጫጨቶች፣ የእናት ንብ እና የሀር ትል) በማባዛት ለተጠቃሚ እንዲተላለፉ ማቅረብ፤ የተሻሻሉ የእንስሳት መኖ ሰብል ዝርያዎችን መነሻ ዘር በተገቢው መንገድ አባዝቶ በማቅረብ በመኖ ዘር ብዜት ሥራው በተለይ የግል ሴክተሩ እንዲሳብና እንዲሳተፍ በማበረታታት መደገፍ፤ ውጤታማ የሆኑ ህያው የማዳበሪያ ዓይነቶችን (rhizobia and phosphorus solubilizing strains) በብዛት ለማምረት ብዜት ማካሄድ፤ የተላመዱ፣ የተሻሻሉና ያለቀላቸው የግብርና ምህንድስና ፕሮቶታይፖች ብዜትን ማካሄድ

3.3.3 የግብርና ቴክኖሎጂ ማስተዋወቅና ቅድመ-ማስፋፋት

የተቀናጀ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ምርታማነትንና ውጤታማ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምን የሚያሳድጉ መንደሮች (technology village) መመስረትና ማስፋት፤ አዳዲስ የሚወጡ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ፣ ወጣቶችና ሴቶችን ያማከለ አዋጭ ቴክኖሎጂ በመለየት ማሸጋገር፤ በቅርቡ እየተቋቋሙ ላሉት የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች የግብርና ምርት አቅርቦትን ለማሳደግ በተመረጡ የግብርና ኮሞዲቲዎች አመራረት ላይ የቅድመ-ማስፋት ሥራ ማካሄድ በትኩረት ይሰራል።

3.3.4 የግብርና እውቀትና ክህሎት የሚያሳድግ ሥልጠና

የግብርና ልማት ሳይንሳዊ የአሰራር ዘዴዎችን መከተል እንዲችል የሚያግዝ ዕውቀትና ክህሎትን ለማስተላለፍ የግብርና ምርት ተኮር የሆነ ተከታታይ ሥልጠና ለኤክስቴንሽን የግብርና ባለሙያ እና ለተጠቃሚው አካል መስጠት፤ የምርምር የሰው ኃይልን ለማጎልበት በድህረ-ምረቃ ደረጃ በተለያዩ ስፔሻላዜሽኖች ተመራማሪዎችን በማሰልጠን የዕውቀትና የክህሎት ደረጃቸውን ማሳደግ፤ ምርምርን በጥልቀት ለማካሄድና አስተማማኝ ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስፈልጉ የምርምር መሠረተ-ልማቶች በተለይም ያሉትን ላቦራቶሪዎች ዘመኑ ባፈራው ሳይንሳዊ መሣሪያዎች እና የኢኮቱ አገልግሎት ክዳታ መሰብሰብ አንስቶ እስከ ትንታኔ ያለውን እንዲያግዝ እንዲሁም ለባዮኢንፎርማቲክስ ለማዋል ማደራጀት በትኩረት ይሰራል።

3.4 የግብርና ሜካናይዜሽ አገልግሎት

የሰብል አመራረት፣ የእንስሳት እርባታና መኖ ልማት (በሁሉም ሥነ ምህዳር በተለይም በቆላማው አካባቢ) አሰራር፣ አያያዝና አጠቃቀምን በሜካናይዜሽን፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም በመደገፍ በሂደትም የአርሶ አደሩን ቁጥር እንዲቀነስ በማድረግ ግብርናችን በዘመናዊ ቴክኖሎጅና አሰራር እንዲካሄድና የተማረ ሃይል እንዲቀላቀለው በማስቻል ኋላቀሩን ግብርና በየደረጃው በመቀየር የግብርናውን ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግር አፋጥኖ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና በግብርናና ከግብርና ውጪ ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶታል። የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት የሚከተሉትን የግብርና ዘርፎች በሰብል ልማት፣ በእንሰሳት ልማት

በተፈጥሮ ሀብት ልማትና አጠቃቀም (በመስኖ ልማት፣ በዕቀባ እርሻ፣ በአረንጓዴና እስማርት ግብርና)፣ በአነስተኛ ሆርቲካልቸር (ማድረቂያ፣ ማከማቻ ፣ እሽጋት፣ ቅድመና መለስተኛ ማቀነባበር) የሚደግፍ ይሆናል፣ የሜካናይዜሽ ዘርፍ ለወጣቶች የሥራ ዕድል መስክ እንዲሆን ትኩረት ተደርጎ የሚሰራ ይሆናል።

3.4.1 በግብርና ሜካናይዜሽን የተደገፈ የሰብል ልማትና ጥበቃ ሥራ

በዕቅድ ዘመኑ 05 (አምስት ዓመታት) ውስጥ ከሚታረሰው ለመካናይዜሽን ምቹ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው 13,000,000 ሄ/ር መሬት ውስጥ 3,656,250 ሄ/ር ማለትም 37.5% የማሳ ዝግጅቱ በትራክተር ለማከናወን ኢላማ ተቀምጧል። ለስበት ሃይል መጠን ወሳኙ በ1 ስኩዌር ሳንቲ ሜትር የማረሻው አካል ላይ ከሚታረሰው መሬት አፈር የሚከሰተው የተቃርኖ ሃይል በመሆኑ ለዚህ ስሌት ሲባል በጠንካራ መረሬ አፈር ላይ በባለ 3፣ 4 እና 5 ማረሻ ጥቅም ላይ እንደሚውል ተገምቶ የተራክተር ቁጥር በ3 ዓይነት የፈረስ ጉልበት ምድብ ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመላከተው ተሰልቷል። በተጨማሪም 40 በመቶ የብዕር እና እንደ በቆሎ ያሉ የአገዳ ሰብል ምረት በዐጭዶ መውቂያ ይሰበሰባል፣ በሪፐር ሃርቨስተር እና በሰው ሃይል የሚታጨደው ሰብል በአነስተኛ መውቂያና መፈልፈያዎች ይወቃል። እንዲሁም 12.5 % በክላስተር አካባቢ የተመረተ ጤፍ በሁለገብ መወቂያ ይወቃል፣ በክላስተር የተመረተ ስንዴ 100 % በኮምባይነር ይሰበሰባል።

ተ.ቁ	የፈረስ ጉልበት	የማረሻ እግር	ሄ/ር በቀን	በዓመት የእርሻና ክስካሶ ቀን		የሚታረሰው ሄ/ር	የሚያስፈልግ የትራክተር ቁጥር	ማብራሪያ
				እርሻ	ክስካሶ			
1	60-75	3	5	30	30	1,500,000	10,000	ከእርሻ ስራ በኋላ ከመከስከሱ በፊት ማሳው ከ10-15 ቀን ለጸሀይ መጋለጥ ይኖርበታል
2	80-90	4	7	30	30	1,233,300	8,222	
3	120-150	5	10	30	30	922,950	6,153	
ድምር						3,656,250	24,375	

በክላስተር አካባቢ የሚገኙ እርሻዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የሚሰራ ሲሆን 50 በመቶ የክላስተር አካባቢዎች ማሳ በሜካኒካል ቴክኖሎጂ ይዘጋጃል። በእነዚህ አካባቢ የሚገኙ እማወራዎች 100% የሜካናይዜሽን ተጠቃሚ ይደረጋሉ።

በአገራቱ የክላስተር እርሻ አካባቢ የሚገኙ እማወራዎች ማኘ የመድረግ ሥራ ይሰራል። የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲያገኙ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል።

በቆላማው አካባቢ የስንዴና ተከታይ ሰብሎች ማሳ ሙሉ በሙሉ በሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂ ይዘጋጃል ከዚህም ውስጥ 1000 ሄ/ር ማሳ በላዘር ሌቭለር እንዲስተካካል ይደረጋል። አንድ ስፋቱ 2.5 ሜ/ር የሆነ በትራክተር ተጎታች ላዘር የተገጠመለት ሌቭለር እንደ ጎርባጣነቱ መለያየት በቀን ከ 3-5 ሄ/ር መሬት ማስተካከል ይችላል መሬት የማስተካከሉን ሥራ ተከትለው ሌሎች የመስመር ማውጣት እና የዘር መዝራት ተግባራት የሚከናወኑ ሲሆን ክክስካሶ በኋላ ቢያንስ ለ30 ቀናት የማስተካከሉን ስራ መስራት ቢቻልና 15 ሌቭለር ቢኖሩን 2,250(ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሀምሳ ሄ/ር) ሊስተካከል ይቻላል። በ5 ዓመት 11,250(አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሀምሳ ሄ/ር) መሬት ይስተካከላል በዚህም የመስኖ ውሃ አጠቃቀምን በ 35 % ይቆጠባል፣ የአፈር ለምነት ይጠበቃል፣ ምርታማነትን 50% በማሳደግ የግብዓት ብክነትን በማስወገድ አጠቃላይ ወጪን መቀነስና የልማቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ ይቻላል። በቆላማው አከባቢ የተመረተ ስንዴ ሙሉ በሙሉ በኮምባይነር ይሰበሰባል።

የቆላ ስንዴ በ 300,000 ሄ/ር መሬት ላይ የሚለማና አልሚዎቹ ከጥጥ በኋላ ስንዴን የሚያስከትሉ ከሆነ ጥጡ በመሳሪያ ተነስቶ ማሳውም ከጥጥ ግንድ ቅሪት ፀድቶ ለስንዴ ዝግጁ መደረግ ስለሚኖርበት የጥጥ መልቀሚያና የተክሉ መንቀያና መከረታተፊያ መሳሪያ ያስፈልጋል።

በመሆኑም 10 በመቶ የጥጥ ምርት በዘመናዊ መንገድ ይለቀማል። በቆላው 300,000 ሄ/ር ስንዴ ከሚያለሙት አርሶ/አርብቶ አደርና ባለሃብቶች መሃከል 10,000 ሄ/ር ጥጥ የሚያለሙ ከሆነ የመስራት ስፋቱ 1.8 ሜትር የኦፕሬሽን ፍጥነቱ 10 ኪ/ሜ በሰዓት የሆነ የጥጥ ግንድ መንቀያና መከረታተፊያ መሳሪያ በቀን 8 ሰዓት ቢሰራ በአንድ የሥራ ቀን 14.4 ሄ/ር የጥጥ ማሳ ያፀዳል። መሳሪያው በመስመር ላልተዘራ የጥጥ ማሳ ዓይነተኛ መፍትሄ ተደርጎ ተወስዷል። ይህው መሳሪያ ከለቀማ እስከ ስንዴ ዘር ጅማሮ ለ20 ቀናት ቢሰራ 288 ሄ/ር መሬት ማፅዳት ይችላል። ከ 300,000 ሄ/ር ውስጥ በ5 ዓመታት ውስጥ ቢያንስ 10 % ጥጥ የሚለማበት ቢሆንና በመነሻ ዓመቱ 2000 ሄ/ር ቢለማ የጠጥ መልቀሚያና የጥጡን ግንድ አንስቶ ማሳው ላይ የሚነሰንስ መሳሪያ በመጠቀም ስንዴን እንደ ሁለተኛ ሰብል ለማምረት ይቻላል። በመነሻ አመቱ ከ10,000 ሄ/ር ውስጥ 2,000ሄ/ሩ በጥጥ የሚሸፈን ከሆነ ለ10,000 ሄ/ሩ ለ 20 የጥጥ ቅሪት ማንሻ ቀናት 40 የጥጥ ግንድ መንቀያና መከረታተፊያ መሳሪያዎች ያስፈልጉናል።

ለ1,000 ሄ/ር በፈሮ ኢሪጌሽን ለሚለማ ማሳ በ25 የለቀማ ቀናት 28 በትራክተር ተገጣሚ ባለ 3 መስመር ጥጥ መልቀሚያ ያስፈልጋል።

የሰሊጥ ምርትም እንደዚሁ 100% ሜካናይዝ ይደረጋል። በትራክተር ተገጣሚ ሆኖ በሰዓት ከ 6-8 ሄ/ር ማሳ አጭዶ የሚያስር መሳሪያ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። በስታንዳርዱ መሰረት ለ1000 ሄ/ር 3 ዓሃድ ያስፈልጋል።

የተዛማጅ ተባዮች መከላከል ከአይሮፕላንና ከነፍስ ወከፍ መርጫዎች በተጨማሪ በሰው ዓልባ የዓየር ላይ ተሽከርካሪ (ድሮውን) እና በተሽከርካሪ/ትራክተር ተደጋኝ መሳሪያዎች እንዲካሄድ ይደረጋል።

የተዛማጅ ተባዮች ክስተት ከዓየር ንብረት ለውጡ ጋር ተያይዞ በሚፈጠርላቸው አመቺ ሁኔታዎች ድግግሞሻቸው እየጨመረ ስለሚሄድ በዓየርና በተወሰነ ደረጃ በምድር በነፍስ ወከፍ መርጫዎች የሚካሄደውን የመከላከል ሥራ በተለየ በድሮውን እና በተሽከረካሪ ተደጋኝ (በፒክ አፕና በትራክተር) ማጠናከር ይኖርብናል።ይህም አቅም በግል ባለሀብቱ በንግድ ሥራ መንፈስ እንዲፈጠር ጥረት የሚደረግ ሲሆን በተለዩ የስጋት አካባቢዎች ፈጥነው መንቀሳቀስ የሚችሉቱ በማዕከልና በተመረጡ ቦታዎች እንዲገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። ድሮውን መረጃዎችን በቀጥታ ወደ ታብሌት የሚያስተላልፉና የቅኝትና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያን ሥራን ፈጣን በማድረግና ክትትልን በማሳለጥ ውጤታማና ከብክነት የፀዳ ርጭት በማካሄድ የተሳካ መከላከልን ለማድረግ ያስችላል። በተለምዶው አሰራር እንደሚታየው ሳይሆን ሰዎች ከኬሚካል ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት በጣም ዝቅተኛ ስለሚሆን የተጎጂነትንና የተጋላጭነትን ስጋት ይቀንሳል። አስፈላጊው የአጠቃቀም ሥልጠናና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመሆን የበረራ ደህንነት እንዲረጋገጥና ሥርዓት እንዲዘረጋ ይደረጋል። ለዚህም ቢያንስ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ወስጥ በቀን 100 ሄ/ር መሬት መርጨት የሚችል የመርጨያ መሳሪያ የተገጠመላቸው 30 ያህል በተሽከርካሪ ተደጋኝ መርጫዎችን ተገዝተው በሥራ ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል፣ 10 ድሮውኖች ስትራተጂክ በሆኑ የስጋት ቀጠናና የትመት አቅጣጫዎችን መሰረት ባደረጉ ጣቢያዎች እንዲመደቡ ይደረጋል።

3..4.2 በግብርና ሜካናይዜሽን የተደገፈ የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት

25 በመቶ የእንሰሳት መኖ ማቀነባባር በመካከለኛ መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ይከናወናል። በዓለም ባንክ የተጨማሪ ፈንድ ግኝት መሰረት በምሩቃን ወጣቶች የሚንቀሳቀሱ የእንሰሳት መኖ(የ ዶሮ፣ ዓሳ ወዘተ) ማቀነባበሪያዎች ይገነባሉ። አንዱ የመካከለኛ ደረጃ ማቀነባበሪያ በሰዓት 5 ቶን መኖ ያዘጋጃል በተፈለገው መጠን ያሽጋል። በአንድ ፈረቃ 400 ኩንታል ያቀነባብራል፣ (ለ 21 ሰዎችም የሥራ ዕድል ይፈጥራል)። በአገራቱ ዝቅተኛው አካባቢ የሚለማው መኖ ሙሉ በሙሉ ሜካናይዝ ይደረጋል። በቆላማው የአገራችን ክፍል ከ4000 ሄ/ር በላይ የእንስሳት መኖ በመስኖ በመልማት ላይ ይገኛል። ይህን የመኖ ምርት ለመሰብሰብ በትራክተር ተጎታች ማጨጃ ፣ ማናፈሻ መንሽ እና የመኖ ማሰሪያ ያስፈልጋል። ከ 1 ሄ/ር 7 ቶን ድርቆሽ እንደሚገኝ የሚገመት ሲሆን ታጭዶ በሶስት ቀናት ውስጥ እንዲናፈስና እንዲታሰር ለማድረግ 500 ሄክታርን እንደ መነሻ በመውሰድ 5 ትራክተሮች፣ 5 ማጨጃ፣ 5 ማናፈሻ መንሽ፣ 3 ሳር ማሰሪያዎች፣ 3 ጋሪዎች ለሰርቶ ማሳያ ያስፈልጉናል ።(ሁሉም መሳሪያዎች በትራክተር ላይ ተገጣሚ ናቸው) :: በተለያዩ የሃገሪቱ ክፍሎች በቁጥር 10 አነስተኛ የእንሰሳት መኖ ማቀነባበሪያ ኢንተረፕራይዞች ይደራጃሉ።

3.4.3 የግብርና ሜካናይዜሽን አገራዊ ፖሊሲ ማዘጋጀት

የግብርና ሜካናይዜሽንን ለማስፋፋት አሁን በሥራ ላይ ያለውን የግብርና ሜካናይዜሽን እስትራተጂ በአግባቡ ወደ መሬት ለማውረድና ክልሎችም ከአካባቢያቸው የግብርና ስልተ ምረት ጋር በመጣጣም የራሳቸውን መቀየስ እንዲችሉ የግብርና ሜካናይዜሽን ልማታችን የፖሊሲ ማዕቀፍ ሊኖረው ይገባል። ማዕቀፉም በሚከተሉት መሰረታዊ ጭብጦች ላይ ያተኩራል።

የግብርና ሜካናይዜሽን ተቋማት ቅንጅትና ትብብር፣ በሜካናይዜሽን ልማት የመንግስትና የግል ዘርፉ ድርሻ፣ ምርምር ትምህርት ሥልጠናና ኤክስቴንሽን፣ የግብርና ሜካናይዜሽን ፍተሻ ፣ምዝገባ ፣ዕውቅና

አሰጣጥና ደረጃ፣ የፋይናንስ አቅረቦትና ተደራሽነት፣ የግብርና ሜካናይዜሽን እሴት ሰንሰለትን ተከትሎ የትኩረት ቅድም ተከተል፣ የአገሪቱን የግብርና ሜካናይዜሽን ኢንደስትሪ ልማት፣ አቅረቦትና ከሽያጭ በኋላ ጥገና፣ ለግብርና ሜካናይዜሽን የንግድ ሥራና አገልገሎት አሰጣጥ ምቹ ሁኔታና ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፡፡

3.4.4 የግብርና ሜካናይዜሽን ተቋማዊ ዓቅም መገንባትና የሰው ሃብት ልማት

በሥራ ላይ ያለውን የግብርና ሜካናይዜሽን ኦፕሬተሮችን እና የጥገና ቴክኒሺያኖችን በሌቭል በማሰልጠን ያለን 1 ኮሌጅ ማጠናከርና በ 2 ተጨማሪ ኮሌጆች የትምህርት ክፍሉን መክፈት፣ የቁሉምሳ የግብርና ሜካናይዜሽን የኦፕሬተሮችና የጥገና ቴክኒሺኖች ማዕከል እንደ ሞዴል ይጠናከራል 1 አዲስ ይመሰረታል፡፡

3.4.5 የፍተሻና የስርቲፊኬሽን ማዕከል ማቋቋም

በአገራችን የተለያዩ የግብርና ሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች ወደ ሃገር ውስጥ ተስማሚነታቸውና ጥራታቸው ሳይረጋገጥ ወደ ሃገር ውስጥ ይገባሉ፡፡ በሌላ በኩል አነስተኛ እንደ መውቂያና መፈልፈያ፣ ማረሻና ቦይ ማውጫ የመሳሰሉ የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎች በሃገር ውስጥ ይመረታሉ፣ከምርምርም ይለቀቃሉ፡፡ ብዙዎቹ ቴክኖሎጂዎች ተስማሚነታቸው ተፈትሾና ተረጋግጦ ወደ ሃገር ውስጥ እንዲገቡ ባለመደረጉ ባሀገር ሃብት ላይ ብክነትና በአገልግሎት አሰጣጡም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አሳድሯል፡፡ ምርምር ራሱ አፈላቂ ሆኖ የራሱንና የሌሎችንም ያፀድቃል ይህ አሰራር ነባና ፍትሃዊ አይደለም፡፡ በተቋማችን ጥያቄና ባለቤትነት ረጅም ጊዜ ተወስዶበትና ሁሉንም ያገባኛል የሚሉ ተቋማትና አካቶ በተደረጀ የቴክኒክ ኮመቴ አማካኝነት ከ 200 በለይ የኢትዮጵያ የግብርና ሜካናይዜሽን ደረጃና ከአለም ዓቀፉ የደረጃዎች ድርጅት ለአገራችን የተመለሱ ደረጃዎች እንዲወጡ ቢደረግም ደረጃዎችን የሚያስፈፅም አሰራር አለመዘርጋቱና ተቋማዊ አደረጃጀትም ባለመፈጠሩ ደረጃዎቹን በማስከበር አስመጪዎችን፣ አቅራቢዎችን፣ አገልግሎት ፈላጊዎችን፣ የማምረቻ ድርጅቶችን፣ የምርምርና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ተጠቃሚ ማድረግ አልተቻለም፡፡

በመሆኑም የወጣውን ስታንዳርድ በሥራ ላይ ለማዋል ከውጭ የሚገቡትንም ሆነ በሃገር ውስጥ የሚመረቱት ለሃገራችን ተስማሚ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሥርዓት ሊዘረጋ አሰራርና ተቋም ሊደራጅ ይገባል፡፡

በግብርና ሚኒስቴርና አጋሮች የተጠኑ የአስፈገላጊነት የጥናት ሰነዶችን አሰባስቦ ዳሰሳ ማካሄድ፣ የሌሎች አገሮችን ልምድ ለመቅሰም እንዲቻል የባለሙያዎች ቡድን ጉብኝት ማዘጋጀት፣ በአማካሪ ቡድን የአዋጭነት ጥናት ለማካሄድ እንዲቻል ቢጋር ማዘጋጀት፣ የዲዛይን ሥራ መስራት ፣ ፈንድ ማፈላለግ/በጀት ማስያዝ፣ ወደግንባታ መሸጋገር፣ መሳሪያ ተከላና የሰው ሃብት ልማት፣ ፍተሻ ርክክብና ሥራ ማስጀመር፡፡

3.4.6 የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ድረጅቶችን ቁጥር ማሳደግና አሰራሩን በኢ.ኮ.ቴ መደገፍ

20 እያንዳንዱ የአገልግሎት መስጫ ማዕከል በጥሪ መዕከል አገልግሎቱን ለመስጠት በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለዚሁ ተግባር በተለየ አፕሊኬሽን ይደገፋል፡፡ የማዕከሉ ንብርት የሆኑና ለሎች በማዕከሉ ዙሪያ በግል የተያዙ የሜካናይዜሽን ቴክኖሎጂዎችን (ማረሻ፣ መከስካሻ፣ መዝሪያ፣ መውቂያ፣ መፈልፈያ ወዘተ) በመረጃ ቋቱ በመያዝና በእያንዳንዱ ቴክኖሎጂ በተለይም ትራክተሮችና ኮምባይነሮች ቦታን መጠቆሚያ መሳሪያን በመግጠም አገልግሎት ፈላጊዎችንና አገልግሎት ሰጪዎችን በሞባይል መረብ (ኔት ዎርክ) በማገናኘት ስምሪትንና አገልግሎት አሰጣጥ ይቀላጠፋል በዚህ ስርዓት ውስጥም መሃልተኞች ይተካሉ፡፡ እንዲሁም የክፍያ፣ የገበያና ሌሎች የግብርና ልማት መረጃዎች በሞባይል በማዕከሉ ዙሪያ ላሉ አርሶ/አርብቶ አደሮች ይደርሳል፡፡ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ክፍያቸውን በሞባይላቸው መፈፀም ያስችላቸዋል፡፡ ዕለታዊና ወቅታዊ(ሪል ታይም) መረጃዎች ይሰጣሉ፡፡ በሂደቱም የመሳሪያዎች ምዝገባ፣ ስምሪት፣ ቁጥጥር፣ የመሳሪያዎቹ ቴክኒካዊ ሁኔታ መረጃ(ለወቅታዊ ጥገና) ፣ የደምበኞች ምዝገባና የአገልግሎት ማግኛ ወረፋ በቴክኖሎጂ ስለሚደገፍ ለተማሩ ቴክኖሎጂ ዘመም ወጣቶች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ በትራክተርና ኮምባይነሮች ላይ የሚገጠም ጂ.ፒ.ኤስ፣ የሥራ መጠን መለኪያ መሳሪያ፣ የአካባቢው ማሳዎች መግለጫዎች፣ መሳሪያዎች የሚገኙበት ቦታን ማፕ ማድረግ፣ የተገልጋዮች መመዝገቢያና፣ በአካባቢ ክላስተር ማድረጊያ እና ወረፋ ማስተዳደሪያ ሶፍት ዌር፣ የትራክተርና ኮምባይነሮችን እንቅስቃሴ ለማወቅና ስምሪት ለመስጠት የሚያስችል ሶፍት ዌር የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ አሁን ያሉትን የግል ባለሀብት አገልግሎት ሰጪዎችን ቁጥር 20 በመቶ ማሳደግና አገልግሎቱን በኢ.ኮ.ቴ መደገፍ፤ መቶ የህብርት ሥራ ማሕበራት ለአባሎቻቸው ቢያንስ ሦስት ዓይነት የሜካናይዜሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ማብቃት፤ በያንስ በየክልሉ በአማከይ 3 የግብርና ሜካናይሽን የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት እንዲቋቋሙ የሚያስችል ሥራ መስራትና አገለግሎት አሰጣጡን በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ መደገፍ ፤ በተደራጁ ወጣቶች 100 የሜካናይዜሽን አገልግሎት ሰጪ ኢንተርፕራይዞችን መመስረት የሚያስችል ሥራ መስራት

3.5 የህብረት ስራ ማህበራት

በኅብረት ሥራ ዘርፍ ከተለዩ የትኩረት መስኮች የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ድርሻ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጠባና እንቨስትሜንት እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ደህንነት እና ሕጋዊነት ናቸው፡፡ ሆኖም በዚህ መነሻ ዕቅድ ውስጥ ሁሉንም የሴክቴሩን የትኩረት መስኮች የሚያካትት ባለመሆኑ ከዚህ በታች የተቀመጡ አመላካቾች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፡፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል ሊፈጥሩ የሚችሉ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን በማስፋፋት ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ለማድረግ አስፈላጊው ድጋፍ እና ክትትል ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተለያዩ የእሴት መጨመር ተግባራትን ስያስፋፋ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት ምርቶቻቸውን ለማሸግ፣ ምልክት ለማድረግ፣ ለማጓጓዝ እና ሌሎች ተግባራት በማከናወን ዜጎች ሰፊ የሥራ እድል እንዲያገኙ የሚያስችሉ አሰራሮችን በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሴቶችና ወጣቶች የሚመቹ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ይሰራል፡፡

3.5.1 የኅብረት ሥራ ማህበራትን ማጠናከር

የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥር በ2012 ዓ.ም 26 ሚሊየን የደረሰ ሲሆን እዲገቱ እስከ 2007 ዓ.ም ከነበረው መረጃ ጋር ስነጻጸር 48.7 ከመቶ እንዳደገ ያሳያል፡፡ ይህንን የአባላት እድገት ለማስቀጠል የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባለት እድገት በገጠር ከሚኖረው እና የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት መሆን ከሚችሉት ውስጥ 73 ከመቶ ኅብረት ሥራ ማህበራት አባል እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በግብርናው ዘርፍ ላይ ተደራጅተው አገልግሎት ከሚሰጡ ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ 45 ከመቶ የሚሆኑት በላቀ ደረጃ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም የኅብረት ሥራ ማህበራት የኅብረት ሥራ እና የግብርና ኤክስቴንሽን ጽንሰ-ሃሳቦችን አባሎቻቸውን እና ሕብረተሰቡን ማስጨበጥ

ከተግባሮቻቸው መካከል አንዱ ነው። በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት መስጠት የጀመሩትን የኤክስቴንሽን አገልግሎት በማጠናከር በሚቀጥለው 5 ዓመታት ውስጥ ካሉት የግብርና የኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ 43 ከመቶ የሚሆኑት አገልግሎቱን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ ይደረጋል።

በመሆኑም በሚቀጥሉት 10 አመታት በጥናት ላይ በመመስረት አዳዲስ የኅብረት ሥራ ማህበራትን ከማደራጀት ጎን ለጎን ቀደም ሲል ተደራጅተው ያሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው ፍላጎት በመከፈል ወይም በመዋሃድ እንዲጠናከሩ ማድረግ፣ ኅብረት ሥራ ማህበራት የገጠር ከተማ ትስስርን በማጠናከር የግብርና እና እንዱስትሪ ምርቶች ቅብብሎሽ የተሳለጠ በማድረግ አምራችና ሻማቹን ተጠቃሚ ማድረግ፣ ጠንካራና ውጤታማ የኅብረት ሥራ እና የግብርና የኤክስቴንሽን ስርፀትና የኢንዱስትሪ ግንኙነት ስርዓትን ማጠናከር በትኩረት ይሰራል።

3.5.2 የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች ግብይት አገልግሎት ማጠናከር

የአገራችን ኢኮኖሚ መሠረቱ ግብርና እንደመሆኑ በዚህ ዘርፍ ላይ የተሰማራው የሕዝብ ቁጥር በርካታ ነው። የሕዝቡ አሰፋፈርም የተበታተነ በመሆኑ ለግብርናው ምርት እድገት ወሳኝ የሆኑ ግብዓቶችን ተደራሽ ማድረግ አስቸጋር ነው። ለዚህ ችግር መፍትሄ የሚሆኑት የኅብረት ሥራ ማህበራት ናቸው። በመሆኑም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሰብል ምርት ወሳኝ የሆነውን የአፈር መዳበሪያ አቅርቦት አገራዊ ድርሻቸው በ2017 ዓ.ም 98.5 ከመቶ ለማድረስ ታቅዷል። በተመሳሳይ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተባዝቶ የሚቀርብ የሚርጥ ዘር በቶን 44787 ማድረስ ነው። የኅብረት ሥራ ማህበራት አርሶ/አርብቶ አደሩ የሚፈልጋቸውን የጸረ-አረም፣ ጸረ-ተባይ እና ጸረ-በሽታ ግብዓቶች አቅርቦት 658 ቶን በማቅረብ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል። በግብርናው ዘርፍ ላይ የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለሕብረተሰቡ የሚያቀርቡት የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት በቁጥር 516 ማደረስ ነው።

በመሆኑም በሚቀጥሉት 5 አመታት የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች በዋናነት በኅብረት ሥራ ማህበራት በኩል ቀርቦ እንዲሰራጭ ማድረግ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት በተለይ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶችን የሚያቀርቡ እና የሚያሰራጩት ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት መስራት፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡትን እና የሚያሰራጩትን ማንኛውም ግብዓቶች በራሳቸው አቅደው እንዲያቀርቡ ማድረግ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቀርቡት ምርጥ ዘር ከሚመለከታቸው የምርምር ተቋማት ጋር ተቀናጅተው በመስራት የዘር አቅርቦቱን በብዛትና በጥራት እንዲቀርቡ ማድረግ፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት በራሳቸው አቅም ምርጥ ዘር አባዝተው እንዲጠቀሙ እና አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች የአፈር ማዳበሪያ በራሳቸው አቅም ወይም በጆይንት ቬንቸር የማዳበሪያ ፋብሪካ አቋቁመው እንዲያመርቱ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች የአፈር መዳበሪያን ከውጭ አገር በማስገባት አርሶ አደሩን እንዲገለግሉ ይደረጋል፣ አርሶ አደሮች የሚጠቀሙት የአፈር ማዳበሪያ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች እና ፌዴሬሽኖች የአፈር መመርመሪያ መሳሪያዎችን በመገንባት እና በሙያው የሰለጠኑ ባለሙያዎችን በመቅጠር የአፈር ምርመራ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ሌሎች የአፈር ለምነትን በማሻሻል ምርታመነትን ለማሳደግ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማምረት እና በማቅረብ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያሰራጯቸው መሣሪያዎች በቂ መለዋወጫ ያላቸው መሆኑን በማረጋገጥ እንዲገዙ ማድረግ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች፣ ፌዴሬሽኖች እና አቅም ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ማሽነሪዎች (የሜካናይዜሽን መሣሪያዎችን) የሚያስፈልጉ መለዋወጫዎችን በጥናት በመለየት በማቅረብ፣ በማሽን ጥገና ሙያ ያላቸው ባለሙያዎችን በመቅጠር እና በማሰልጠን የጥገና ወርክሾፖችን በመክፈት በትኩረት ለመተግበር አቅጣጫ ተቀምጧል።

3.5.3 የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ምርቶች ግብይት አገልግሎት ማጠናከር

የኅብረት ሥራ ማህበራት ተበታትኖ የሚመረተውን የግብርና ምርቶች በማሰባሰብ፣ በማንጋገዝ፣ በማከማቸት፣ ለምርቱ ምልክት በመስጠት እና በምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ በማቅረብ አምራቹንና ሸማቹን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ይህን በጎ ጅምራቸውን በማላቅ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶች ግብይት አገራዊ ድርሻቸውን 34 ከመቶ ማድረስ አንዱ ነው፡

፡ ኅብረት ሥራ ማህበራት በዋና ዋና ግብርና ምርቶች አገራዊ የወጪ ግብይት በሚላክ ምርት መጠን እና በሚያስገኙት ዶላር ድርሻቸው 32 ከመቶ ለማድረስ ታቅዷል።

በግብርና ምርት ግብይት ውስጥ ያሉ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርቶችን በብዛት እና በጥራት በማሰባሰብ፣ በማከማቸት፣ በማንጓዝ፣ በማሸግ፣ ደረጃ በመስጠት እና እሴት በመጨመር የመደራደር አቅማቸውን በማጎልበት ከሌሎች የኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመፍጠር ለምርቱ የተሻለ ገበያ በማፈላለግ እንዲሸጥ የማድረግ ተግባር በትኩረት ይሰራል፣ የግብርና ምርት ግብይት እሴት የሚጨምር፣ ወጭን የሚቀንስ፣ የተንዛዛ የግብይት ሰንሰለትን የሚያሳጥር እንዲሆን የሚያስፈልግ አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራትን የመደራደር አቅም በማጠናከር የገበያ መዳረሻዎችን የማስፋፋት ተግባር በትኩረት ይሰራል፣የኅብረት ሥራ ማህበራት በእንሰሳት እና እንሰሳት ተዋጽኦ ምርት ግብይት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርት ዓይነት፣ ጥራትና መጠን በመለየት እና ለምርቱ ደረጃ በመስጠት፣ የምርት ዱካን የማመላከት እና ምርቱን ቀድሞ የማስታዋወቅ ሥራዎች ተጠናክሮ ይሰራል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የምርት ጥራትን መሠረት ያደረገ የክፍያ አሰራር በመዘርጋት እንዲሰሩ ይደረጋል።

በአገራችን በውጭ ግብይት ላይ ለመሰማራት አቅም ካላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ እየተሳሰፉ ያሉት ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ አቅም ፈጥረው በውጭ ግብይት ላይ በስፋት እንዲሳተፉ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት የውጭ ገበያ መረጃ አያያዝን ለማዘመን የሚያስፈልጉ ሶፊት-ዌሮችንና ድህረ-ገጾችን በመገንባት እና ሌሎች ዘመናዊ አሰራሮችን በመዘርጋት ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፣ የውጭ ገበያ መዳረሻዎችን ማስፋፋት፣ በውጭ ግብይቱ ላይ የሚታየውን የተንዛዛ የግብይት ሂደት በማሳጠር ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን ዓይነት፣ መጠን፣ ጥራት እና ወቅታዊነትን ጠብቆ መላክ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዲሰሩ ይደረጋል፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶችን በጥሬ ከመላክ ይልቅ እሴት በመጨመር እና ለምርቱ ልዩ ምልክት በመስጠት መላክ የምርት ዱካ (traceablity) ስለሚያረጋግጥ ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፣ በውጭ ግብይት ላይ የሚሰማሩ የኅብረት ሥራ ማህበራት መንግስት ልዩ የማበረታቻ እና ድጋፍ የሚያገኙበትን አሰራር ይዘረጋል፣ በጥናት ላይ በመመስረት የኅብረት ሥራ ማህበራት ግብይት ስርዓትን የማጠናከር ተግባር ይከናወናል፣ የኅብረት ሥራ ማህበር የገበያ ጥናት ሳይጠና እና አዋጭነቱ ሳይረጋገጥ የሚደረግ የግብይት ተግባር የኅብረት ሥራ ማህበራትን ለኪሳራ ስለሚዳርግ የገበያ ጥናት ትኩረት ተሰጥቶ እንዲሰራ ይደረጋል። በተመሳሳይ የግብርና ምርት ግብይቱን ለማሳለጥ እንዲቻል ጥናት በማድረግ በመላው አገርቱ ውስጥ 65 ቦታዎች ላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት መረጃ ማዕከላት ተቋቁሞ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

3.5.4 የኅብረት ሥራ ማህበራት በእሴት ጭመራ ተሳትፎ ማሳደግ

የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ምርት ላይ እሴት በመጨመር ለገበያ ማቅረብ የጀመሩትን ተግባራት በማጠናከር ከቀላል እስከ ከባድ የማቀነባበሪያ እንዱስትሪዎችን በማቋቋም አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበራቱን ቁጥር 1,322 ለማሳደግ ታቅዷል። የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰበስቧቸውን የግብርና ምርቶች ለተጠቃሚው (ሸማቹ) በቀላሉ ማቅረብ እንዲቻል ለማድረግ 8 የገበያ ማዕከላትን በመላው አገርቱ ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ውስጥ በመገንባት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል።

የኅብረት ሥራ ማህበራት በግብርና ምርት ላይ እሴት ለመጨመር የሚረዱ ከቀላል እስከ ትላልቅ የምርት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው የሚደረገው የእሴት መጨመር ተግባር ዘርፉ ተለይቶ፣ በጥራት ደረጃ፣ በዋጋ ተወዳዳር እና አዋጭ መሆኑ፣ ተቀባይነት፣ ቀጣይነት እና የተጠቃሚነት ደረጃ በጥናት በማረጋገጥ በስፋት እንዲሰራ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች በግብርና ምርት ግብይት ላይ የአባላትን የመደራደር አቅም በማጎልበት፣ የገበያ መረጃ አገልግሎት መስጠት፣ የገበያ ትስስርን በማመቻቸት፣ የመጋዘን አገልግሎት በመስጠት፣ እሴት በመጨመር እና የትራንስፖርት አገልግሎቶችን በማመቻቸት ላይ ልዩ ትኩረት በመስጠት እንዲሰሩ ይደረጋል፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽኖችን ትላልቅ የእሴት መጨመሪያ ኢንዱስትሪዎችን በማቋቋም፣ በአገር አቀፍ የኅብረት ሥራ ማህበራት መካከል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመዘርጋትና በማለዋወጥ፣ ፋይናንስ ማመቻቸት፣ የኅብረት ሥራ

ማህበራት የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን በማስተባበር እና የመደገፍ ተግባራት ላይ እንዲያተኩሩ ይደረጋል፣ የጎብረት ሥራ ማህበራት ከአባሎቻቸው የሚሰበስቡትን የምርት ዓይነትና መጠን ለማከማቸት የሚያስፈልጉ ለደረቅ፣ ለፈሣሽ፣ ለአትክልትና ፍራፍሬ፣ ለኬሚካል እና ሌሎች ዓይነት ምርቶች ማከማቻ የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ መጋዘኖች በጎብረት ሥራ ማህበራት፣ በመንግስት እና በሌሎች አቅም ገንቢ አካላት ዘመናዊ እና አስፈላጊ መሳሪያዎችን ያሟሉ መጋዘኖች የሚገነቡበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፣ ጎብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ምርት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ማድረስ እንዲችሉ በከተሞች፣ በኢንዱስትሪ አካባቢዎች እና በመንገድ ዳር ላይ የተለያየ ዓይነት ደረጃ ያላቸው የገበያ ማዕካላት ገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ የጎብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ሂደት እንዲሳለጥ እንደየምርቱ ባህሪ የአባላት ምርቶችን በማሰባሰብ በአገር ውስጥ ለአካባቢ፣ ለማዕከላዊ፣ ለተቀናጀ የግብርና ኢንዲስትሪዎች፣ እሴት መጨመሪያ ቦታዎች እና ለውጭ ገበያ ለማድረስ እንዲሁም አባላት የሚፈልጉትን የምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች እና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ፋጣን እና ምቹ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ይደረጋል፣ ለጎብረት ሥራ ማህበራት ቀልጠፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት የሚያስችሉ የተለያዩ ዓይነትና ምቹ ሶፍትዌሮችን በመገንባት እና አቅም በመፍጠር እንዲጠቀሙበት ይደረጋል፣ የጎብረት ሥራ ማህበራት የመረጃ ስርዓት የማደራጀት፣ የማጠናከር፣ የመተንተን፣ የማሰራጨት (የአየር ሁኔታ፣ የገበያ ዋጋ፣ የምርት፣ የማምረቻ መረጃዎችን አጠቃላይ መረጃ) ስራዎች ተጠናክረው እንዲሰሩ ይደረጋል፣

3.5.5 የጎብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ ተደራሽነትን ማሳደግ

አገራችን በፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት (Financial inclusion) ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሉት አገሮች አንዷ ነች። በመሆኑም የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራትን በማጠናከር፣ ጎብረት ሥራ ባንክ እና እንሹራንስን በማቋቋም አገልግሎት እንዲሰጡ በማድረግ ችግሩን እንዲቀረፍ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በዚህ መሠረት የፋይናንስ ጎብረት ሥራ ማህበራት አሁን የሰበሰቡትን የቁጠባ መጠን ብር 48.5 ቢሊየን እንዲያሰባስቡ በማድረግ እንደ አገር ከሚሰበሰበው አገራዊ የግላሰብ ቁጠባ (Household saving) ውስጥ ድርሻቸውን 20 ከመቶ ማድረስ ነው።

የፋይናንስ ጎብረት ሥራ ማህበራት የሰበሰቡትን ቁጠባ እና ከሌሎች ምንጮች የሚያገኙትን ገንዘብ ለአባሎቻቸው የብድር አገልግሎት እንዱሰጡ ለማድረግ በትኩረት ይሰራል። በዚህ መሠረት የሚሰጡት የብድር መጠን ብር 46.5 ቢሊየን እንዲሰጡ ይደረጋል። በአለም ላይ የጎብረት ሥራ ማህበራት ለዜጎች ምቹ የሥራ እድል በመፍጠር በቀዳሚነት ከምታወቁ ተቋማት መካከል አንዱ ናቸው። በመሆኑም አሁን በጎብረት ሥራ ማህበራት የተፈጠረውን የሥራ ዕድል በማሳደግ ለ558 ሺ ዜጎች ቋም የሥራ እድል እንዲፈጥሩ ይደረጋል።

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ጠንካራና ወጥ እንዲሆን ይደረጋል፣ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት አባል ያልሆኑትን የሕብረተሰብ ክፍሎች የፋይናንስ ክህሎታቸውን በማዳበር አባል በመሆንና በመቆጠብ ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ይደረጋል፣ በገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የሴቶችን እና ወጣቶች የአባልነትም ሆነ አመራርነት ተሳትፎአቸውን በስፋት የማሳደግ ተግባር ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራ ይሆናል፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጡት የቁጠባና ብድር የፋይናንስ አገልግሎት ማስፋፋት፣የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት የአባላት መደበኛ ቁጠባ መጠን ማሳደግ፣ በገጠር የግብርና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ለአርሶ/አርብቶ አደሩ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች መግዣ፣ ለግብርና ምርት ግብይት እና እሴት ለመጨመር የሚሆነውን ፋይናንስ በማመቻቸት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ይደረጋል፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት ብድርን እና ቁጠባን መሰረት ያደረገ ወይም ሌሎች አነስተኛ የመድን ዋስትና አገልግሎቶችን በራሳቸው ወይም ከሌሎች ኢንሹራንስ ሰጭ ተቋማት ጋር በመቀናጀት አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት የውስጥ አሰራራቸውን ለማዘመን ሶፊትወሮችን በመገንባት ወይም በመዘርጋት የሚጠቀሙበት አሰራር በዘርጋት አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፣ በከተማ እና ገጠር የሚገኙ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ ማህበራት መርሆ በማይጻረር መልኩ ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ የፋይናንስ ግብይት ትስስር እንዲኖር ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል፣ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ጎብረት ሥራ

ማህበራት ዘመናዊ የክፍያ አሰራሮችን በመዘርጋት ከሌሎች የጎብረት ሥራ ማህበራት ጋር በመቀናጀት የሚሰሩበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ይደረጋል፣ የሁሉም ዓይነት የጎብረት ሥራ ማህበራትን እና አርሶ/አርብቶ ሕብረተሰብ ክፍል የፋይናንስ ችግር ሊፈታ የሚችል የጎብረት ሥራ ባንክ ማደራጀት፣ የጎብረት ሥራ ማህበራትን የአደጋ ስጋት ለመቀነስ እንዲቻል የጎብረት ሥራ ኢንሹራንስ ማደራጀት፣

ክፍል IV፡ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች

4.1 ምግብ ዋትስና

ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በመደበኛ ፕሮግራም እና ፕሮጀክቶች የምግብ ዋስትና መታጣት ችግርን ለመፍታት ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በመሆኑም እ.ኤ.አ ከ 2010 እስከ 2015 የምግብ ድህነት አመልካች (Food Poverty Index) በ 11.8 በመቶ ወይም በ 6.9 ሚሊዮን ዚጎች እንዲቀንስ ማድረግ ተችሏል። በተመሳሳይ ወቅት የአገሪቱ ህዝብ ብዛት በ 10 ሚሊዮን ጭማሪ አሳይቷል (CSA, 2016)። የህዝብ ብዛት በ2.5 ዓመታዊ የእድገት ምጣኔ መጨመሩን ተከትሎ የምግብ ዋስትና እጦት ችግር ሆኖ ዘልቋል። ለዚህም በምግብ ሰብል ምርት እና በኢኮኖሚ የተገኘው ዕድገት ከህዝብ ቁጥር ዕድገቱ ያነሰ መሆኑ ዋናው ምክንያት ነው። የምግብ ዋስትና ዕጦት በቀጥታ ማዕዳዊ ንጥረ ምግብ (dietary nutrient) ጉድለት በማስከተል እንዲሁም በተዘዋዋሪ ደግሞ በህጻናት ምገባ ላይ ተጽዕኖ በማሳደር እድሚያቸው ከአምስት አመትና በታች በሆኑ ህጻናት ላይ መቀንጨር እና በነፍሰ ጡር እና በሚያጠቡ እናቶች ላይ ደግሞ የንጥረ ምግብ ጉድለትን (malnutrition) እንዲከሰት ያደርጋል። በአጠቃላይ የምግብ ዋስትና ዕጦት ችግር እና ተያያዥ አሉታዊ ተጽእኖቹን ለመቅረፍ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበቸው የሚገቡ ተግባራት መኖራቸውን ያመላክታል።

ካለፉት 15 ዓመታት የአራት ምዕራፎች ትግበራ አበረታች ውጤት በመነሳት ከ2013 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ 2017 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ የሚተገበር የአምስተኛው ምእራፍ የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም በቀረጸ ሂደት ላይ ይገኛል። በዚህም ፕሮግራም በጥልቅ ድህነት (Extrem Poverty) እና ሥር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ የሚገኙ በገጠር የሚኖሩ 8 ሚሊዮን የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ከምግብ ዋስትና ችግር በማላቀቅ በዘላቂነት የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ለማስቻል ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቷል።

ልማታዊ ሴፍቲኔት

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የምግብ ዋስትና መታጣት መሰረታዊ መንስዔዎችን ለመቅረፍ የተቀረጸ የመንግስት ፕሮግራም ሲሆን ስር ለሰደደ ምግብ ዋስትና በተጋለጡ ወረዳዎች ውስጥ በምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ ለሚገኙ የገጠር ህብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ (transfer) በማቅረብ በቤተሰብ ደረጃ ጥሪታቸው እንዳይሟጠጥ ማድረግና በማህበረሰብ ደረጃ ተጨማሪ ጥሪት እንዲፈጠር ትኩረት አድረጎ ይተገበራል።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ «በገጠር የሚኖሩና ለምግብ ዋስትና የተጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች አደጋን የመቋቋም አቅማቸው እንዲጎለብት፣ ኑሯቸው እንዲሻሻል፣ የምግብ ዋስትናቸው እና ስርዓተ ምግባቸው እንዲሻሻል ማድረግ ነው። በጥልቅ ድህነት ውስጥ የሚኖሩና ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው ተጠቃሚዎች በተመረጡ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ በመሳተፍ በቤተሰብ ደረጃ ተጨማሪ ገቢና ጥሪት በመፍጠር የምግብ ክፍተታቸውን በራሳቸው አቅም መሙላት እንዲችሉና የተፈጥሮ እና ሰውሰራሽ አደጋን ተከትሎ የሚከሰት መጠነኛ አደጋ ክስተት (Modest Shock) የመቋቋም አቅም እንዲፈጥሩ በማስቻል ከፕሮግራሙ ማስመረቅ ነው።

በዚህ መሰረት በቀጣይ አስር አመታት ውስጥ ወቅቱን በጠበቀ ክፍያ የምግብ ክፍተትን በመሙላትና ልዩ ልዩ ስልጠናዎችንና የብድር አቅርቦትን በማቀናጀት በሚቀርብ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ (80 በመቶ) የፕሮግራሙ የማህበረሰብ ስራ ተጠቃሚዎች ከፕሮግራሙ ድጋፍ ውጪ በራሳቸው አቅም ዓመታዊ የምግብ ፍጆታቸውን አሟልተውና በተፈጥሮ አደጋ የሚከሰት መጠነኛ አደጋ ክስተት (Modest Shock) (ለሶስት ወራት) መቋቋም የሚያስችል አቅም ፈጥረው ከፕሮግራሙ ይመረቃሉ።

በማኔጅመንት መረጃ ስርዓት የተደገፈና ወቅቱን የጠበቀ ክፍያ ስርዓት በመገንባት ተጠቃሚዎች ለሰሩት ስራ ክፍያቸውን በወቅቱ እንዲያገኙና የምግብ ክፍተታቸውን በመሙላት ጥሪታቸውን እንዳይሟጠጥ ይደረጋል፤ በተጓዳኝ በሚሰጥ በተግባር የተደገፈ መሰረታዊ የሆኑ የቢዝነስ/ኢንተርፕራነርሺፕ ስልጠና እና በቁጠባ ተሳትፈው በሚቀርብላቸው የብድር ድጋፍ በቤተሰብ ደረጃ አዋጭ በሆኑ የገቢ ማስገኛ ስራዎች በመሳተፍ የገቢ ምንጫቸውን እንዲያሰፉ፣ ተጨማሪ ሃብት እንዲያፈሩ እና የአመጋገብ ስርዓታቸው እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ ለሴቶች ልዩ ትኩረት በመስጠት በማህበረሰብ እና በቤተሰብ ደረጃ የውሳኔ አሰጣጥ እና የኢኮኖሚ አቅማቸው እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

የትግበራ መስኮች

የፕሮግራም ማኔጅመንት ስርዓት መገንባት

የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሲስተምን በመዘርጋት አገልግሎት ላይ እንዲውል ማድረግ፣ የተጠቃሚዎችን መሰረታዊ መረጃ ማደራጀት (Household Registery)፣ የ e-payment ክፍያ ስርዓት እንዲሰፋፋ ማድረግ፣ ፔሮል እና አቴንዳንስ ሶፍትዌር ማሻሻል (PASS update) እናየማህረሰብ ስራዎችን በአይነትና በቦታ ሊያሳይ የሚችል የመረጃ ቋት ግንባታ ናቸው፡፡

ተጠቃሚዎችን የምግብ ክፍተታቸው እንዲሟላ ማድረግ

ወቅቱን በጠበቀ ክፍያ የምግብ ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ሃብት ማሰባሰብ ለክልሎች መላክ ያለበትን ሃበት በወቅቱ እንዲላክ ማድረግ ፤ ወቅታዊና ተመጣጣኝ ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል የክፍያ ስርዓት፣ ተጨማሪ ወራት ድጋፍ ክፍያ (Scalability-continuum of response) በመኸር እና በልግ ጥናት ውጤት መሰረት ለተጨማሪ ወራት ድጋፍ (Extended Months of Support) ከተለያዩ ምንጮች በሚቀርብ የበጀት ድጋፍ ለሴፍቲኔት የማህበረሰብ የልማት ተሳታፊዎች እና ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው ወረዳዎች ውስጥ ከሴፍቲኔት ዉጪ ለሆኑ የእለት ደራሽ ተጠቃሚዎች ድጋፍ ማድረግ፣ : ፣

የማህበረሰብ የልማት ስራዎች የስርዓተ ፆታ ፤ ማህበራዊ ጉዳዮች እና የስርዓተ ምግብን ባካተተ መልኩ እንዲተገበሩ ማድረግ

በፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ተሳትፎ የማህበረሰብ የልማት ስራዎች በማከናወን የወል ጥሪት እንዲገነባ ማድረግ ነው ይህውም 6.8 ሚሊየን በሚሆኑ የልማታዊ ሴፍቲኔት ተጠቃሚዎችን በልማት ስራዎች ላይ በማሰማራት፤ የሰው ጉልበትን በስፋት መጠቀምና በተቻለ መጠን ከፍተኛ ወጪን የማይጠይቁ ቁሳቁሶች በመጠቀም እንዲሁም በሕብረተሰቡ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚሰሩ የማህበረሰብ የልማት ስራዎችን በመለየት፤ በማቀድ፤ የሚተገበር እና ክትትልና ግምገማ የሚደረግበት ነው፡፡

የሚካሄዱት የማህበረሰብ የልማት ስራዎች ተጠቃሚዎች በቅርብ ርቀት የሚደርሱበት ቦታ መሆን እና የወረዳው የልማት እቅድ አካል መሆን ይኖርባቸዋል በተጨማሪም የተፋሰስ ልማት አግባብን የተከተሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ከሚተገበሩት የማህበረሰብ የልማት ስራዎች ዋና ዋናዎቹ ለመጥቀስ ያህል የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች፣ የአነስተኛ መስኖ ልማት ስራዎች ፣ ውሃ የማሰባሰብ ስራዎች ፣ምንጭ የማጎልበት ስራዎች ፣የእጅ ጉድጓድ ቁፋሮ፣ የደን ልማት ፣የገጠር የመሰረት ልማት ግንባታና ጥገና፣ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታና ጥገና ወዘተ .. ናቸው

የልማታዊ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ተጠቃሚዎች በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት እንዲገነቡ ማድረግ

የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም (ቁጠባ)፣ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ዕቅድ ዝግጅት፣ የቴክኒክ ክህሎት እና የስርዓተ ምግብ ስርዓተ ጾታ እና ማህበራዊ ልማት ላይ ስልጠናዎች መስጠት፣ የፋይናንስ አገልግሎት፡- ብድር አቅርቦት፣ የደሃ ደሃ ለሆኑ (Ultra poor clients) ተጠቃሚዎች የአንድ ጊዜ የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ (Livelihood Transfer)፣ የምርት ግብዓቶች፣ የምርት እና አገልግሎት ገበያ ትስስር መፍጠር፣ የማህበረሰብ የልማት ስራዎች እና የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻል ተግባራት ተሳስረው የሚተገበሩበት የእቅድ ዝግጅት፣ ክትትል እና ድጋፍ ስርዓት ማጠናከር

ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የሚከናወነው በመንግስትና ከተለያዩ የልማት አጋር ድርጅቶች በሚመደበው በጀት ነው፡፡ ስለሆነም በመንግስትና በለጋሾች/ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የበጀት ድጋፍ የሚከናወኑ የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች ተቀናጅተው የልማት እቅድ አካል እንዲሆኑ ተደርገው መተግበር አለባቸው፡፡

ለአብነትም ለመጥቀስ ያህል የልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ማንዋል ለፕሮግራሙ ዋና ዋና ተግባሪ ያላቸውን ባለድርሻ አካላት ሀላፊነትና ተግባር በግልፅ ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህን በማስተባበር ሂደት ለፕሮግራሙ ውጤት ጠንካራ ቅንጅትና አሰራር እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ተቋማዊ የአቅም ልማት

የምግብ ዋስትና ፕሮግራም የተለያዩ ውሳኔ ሰጪ አካላትንና አስፈፃሚዎች የሚሳተፉበት በመሆኑ ለባለድርሻዎቹ ሁሉ ስለፕሮግራሙ ዓላማ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ሥራን በጋራ አቅዶና አስተሳስሮ ለመምራት ወሳኝ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የችግሩ ተጋላጭ የሆነው ሕብረተሰብ የፕሮግራሙን አካሄድና አፈፃፀም በግልፅና በተጨባጭ ማሳወቅ ከእያንዳንዱ ፕሮግራሙን ከሚያስፈፅም አካል ይጠበቃል፡፡ ሕብረተሰቡ ከፕሮግራሙ የሚያገኘውን ፋይዳ ጠንቅቆ እንዲያውቅና የሚጠበቅበትን ግዴታ እንዲያሟላ ለማድረግ በየጊዜው ተከታታይ ሥልጠና መስጠት ተገቢ ነው፡፡ በመሆኑም የቁሳዊ አቅም ግንባታ ድጋፍና ስልጠና መስጠት፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም አፈፃፀም ክትትል፣ ግምገማ እና መማማር ስርዓትን ማሻሻል ለፕሮግራሙ ውጤታማነት አስፈላጊ ነው፡፡

የምግብ ዋስትናቸውን ያረጋገጡ ተጠቃሚዎች ከፕሮግራሙ ማስመረቅ፣

ከምግብ ዋስትና ፕሮግራም መመረቅ (Graduation) በሁለት ደረጃ የሚታይ ሲሆን አንደኛው የምግብ ዋስትና ችግር ያለባቸው ቤተሰቦች በሴፍቲኔት ፕሮግራም እየታገዙ የምግብ ጉድለታቸውን በማሟላትና ያላቸውን ጥሪት (Asset) እንዲጠብቁ በማድረግ በቤተሰብ የኑሮ ማሻሻያ የስራ መስክ ተሳትፈው ጥሪት ገንብተው ከሴፍቲኔት ፕሮግራም እንዲመረቁ ማድረግ ሲሆን ይህም በአጭር ጊዜ ሊደረስበት የሚቻልና በምግብ ዋስትና ፕሮግራም የቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው ተግባር ነው፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ምረቃ ደግሞ ከሴፍቲኔት ፕሮግራም የተመረቁ ቤተሰቦችን በቤተሰብ የኑሮ ማሻሻያ የስራ መስክ እንዲቀጥሉ በማድረግ በሚያገኙት የፓኬጅ ብድር በግብርናና ከግብርና ውጭ ባሉ ገቢ በሚያስገኙ የልማት ስራዎች ላይ በመሳተፍ በሚያገኙት ገቢ በአስተማማኝ ሁኔታ በቤተሰብ ደረጃ ጥሪት በመገንባት ከአጠቃላይ ፕሮግራሙ ማስረመቅ ነው፡፡

ተጠቃሚዎች በቀረበላቸው ድጋፍ ተጠቅመው ያመጡትን ለውጥ ክትትል ማድረግ እና ተጓዳኝ ድጋፎችን ማቅረብ፣ በመሪጃ ላይ የተደገፈ ታአማኒነት ያለው የምረቃ ማስተግበሪያ ስርኣት መዘርጋት፣ ከፕሮግራሙ የተመረቁ ተጠቃሚዎች የድህረ ምረቃ ክትትል እና ድጋፍ ስርዓት መዘርጋት፡፡

4.2 ስርዓተ ምግብ ዋስትና

ከአመጋገብ ስርአት አለመስተካከል ጋር በተያያዘ በሀገራችን የሚታየውን መቀንጨር፤ መቀጨጭ፤ አነስተኛ ክብደት ወዘተ ለመቀንስና በዚሁ ምክንያት በዜጎች ላይ የሚደርሰውን የተዛባ አካላዊ እድገትና በተለያዩ በሽታዎች መጠቃትን ለማስወገድ የግብርናው ልማት ጉልህ ሚና እንዳለዉ የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ የዜጎችን የሥርዓተ ምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም እንዳለዉ ይታወቃል፤ በሥርዓተ ምግብ ምጓደልም የግብርና ምርቶች በ 17 % እንደሚቀንሱ ይገመታል፡፡ በቅርቡ በጸደቀዉ የምግብና ስራዓተ ምግብ ፖሊሲ (FNP) ከጠቀመጡት ሰባት የፖሊሲ አቅጣቻዎች ሶስቱ በቀጥታ የግብርና ሚኒስቴር ሥርዎች ሲሆኑ ሶስቱ ደግሞ ክሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር ቀጥተኛ ያልሆነ ግኑኝነት አላቸዉ፡፡ በነዚህ ምክንያቶች የግብርና ምርትና ምርታማነት እንደዚሁም የአመራረት ስልቱ ሥርዓተ ምግብ ተኮር እንዲሆን ማድረግ ወሳኝ ተግባርና ለሚኒቴር መ/ቤቱም ተልዕኮ ግብ መምታት የበኩሉን አስተዋጻኦ የሚያደርግ ነው፡፡

ግብርናዉን ሥርዓተ ምግብ ተኮር እንዲሆን ለማድረግ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸዉ፡፡ የሥርዓተ ምግብን የትግበራ መስኮች (interventions) በሚመለከታቸዉ የግብርና ዳይሬክተሮች መደበኛ ሥራዎች ዉስጥ ተካቶ እንዲሠራ ማድረግ (

Mainstreaming)፣ የዜጎች የአመጋገብ ሥርዓት ማለትም የምግብ ስብጥር፤ ምግብ የሚመገቡበት ድግግሞሽ (Meal frequency) ዓለም አቀፍ ደረጃዉን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣ በተለይም የገበያ ተደራሽነት በሌለባቸዉ የገጠር አካባቢዎች ስብጥር የአመራረት ሰልት (production diversity) እንዲሰፋፋ ማድርግ ፣ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና መልዕክቶችን በማስተላለፍ በህብረተሰቡ ዉስጥ ግንዛቤ መፍጠርና ብሎም የባህርይ ለውጥ ማምጣት፣ በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመዉን የምግበና ሥርዓተ ምግብ ማስተባበርያ ቢሮ ተሞክሮ ላይ በመመርኮዝ በክልሎችና በተዋርድ የግብርና ቢሮዎችና ጽ/ቤቶች የምግብና የሥርዓተ ምግብ ትግበራዎችን የሚያስተባበር መዋቅር መዘርጋት፣ ግብርው ሴክተር የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ተግባራት የተጠናከረ የክትትል እና ግምገማ ስርዓት በመዘርጋ እንዲሁም የመረጃ ቋት በመፍጠር ለአዳዲስ እውቀት ምንጭ እንዲሆን ማስቻል፣ የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ፕሮግራም በመቅረጽ የግብርና ሚኒስቴር የስርዓተ ምግብ ተኮር ስራዎች በተደራጀ መልኩ መምራት፣ በተለያዩ የአግሪቷ ክፍሎች አግሮ ኢኮሎጂን መሰረት ባደረገ መልኩ ሞዴል የስርዓተ ምግብ ተኮር ግብርና ማሰለጥኛ ማእክላትን በማደራጀት የቴክንሎጂ እና የክህሎት ሽግግር እና ስርጸተን ማጎልበት፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የስርዓተ ምግብብ ተኮር ግብርና ማሳያ ማእከላት እንዲሆኑ የሙያ እና የግባት አቅርቦት ድጋፍ ማድርግ፣ የስርዓተ ምግብ እቅድ እና ክትትል በግብርናው ሴክተር ተጠናክሮ የመደበኛ የስራ አካል እስኪሆን ድረስ ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ፣ የስርዓተምግብ ተኮር ስራዎችን የማስተባበር አቅምን ማጎልበት፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት ማሳደግ ይሆናል፡፡

4.3 ስርዓተ ፆታ

በአባወራና በእማምራ መካከል ያለውን የምርታማነት ልዩነት ማጥበብ

የግብርና ኤክስቴንሽንና ሌሎች የግብርና አገልግሎቶች ተደራሽነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ

በሚቀጥለው አምስት ዓመታት የኤክስቴንሽን ስርዓቱ ለ14 ሚሊየን ለአርሶ/አርብቶ/ከፊል አርብቶ አደሮች የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎች ያደርጋል፡፡ ከእነዚህ የኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚዎችው ውስጥ በግብርና ሥራ ከተሰማሩ እማወራዎችን 100%፣ ባለትዳር ሴቶች 50%፣ እንዲሁም 10 በመቶ የሚሆኑትን ወጣቶች የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ ሲሆን በዋናነት ሀገራዊ የግብርና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገዉ እንቅስቃሴ ሴቶች እና ወጣቶች ጉልህ አበርክቶ ይኖራቸዉ ዘንድ በሰብል ልማት፤ በእንሰሳት ልማት፤ በተፈጥሮ ሀብት ልማት፤ በመስኖ ልማት፤ በሜካናይዜሽን፤ በድህረ-ምርት፣ ደህንነት እና እሴት ጭመራ፤ በስርዓተ-ምግብ፤ በሥርዓተ-ጾታ፤ በአየር ንብረት ሁኔታ ትንብያ መረጃ እና በገበያ ዙርያ በተቀናጀ መልኩ በኤክስቴንሽን ተጠቃሚ ማድረግ ነዉ፡፡

በግብርና ሜካናይዜሽን በዕቅድ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ውስጥ ከሚታረሰው 1300000 ሄ/ር መሬት ውስጥ 9750000 ማለትም 75% የማሳ ዝግጅቱ በሜካናይድ እርሻ ማከናወን፤ 80 በመቶ የሰብል ምርት በአጭዶ መውቂያ (በኮምባይነር) ይሰበሰባል በአነስተኛ መውቂያና መፈልፈያዎች የሚወቃ ሲሆን በዘርፉ የተሰማሩ እማ-ወራዎችን 100% ተጠቃሚ ማድረግ፣ እንዲሁም ለወጣቶች የስራ-እድል ለመፍጠር የሚያስችሉ የትኩረት መስኮችን በመለየት ተጠቃሚ ማድረግ፡፡ በተጨማሪም ከሚመለከታቸው አካለት ጋር በመቀናጀት ሴቶች እና ወጣቶችን በማደራጀት ጊዜ፣ ጉልበት ቆጣቢና እሴት የሚጨምሩ የግብርና ቴክሎሎጂ ግብዓቶችን በማቅረብ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸዉን ማሳደግ፤ እንዲሁም የመጠቀምና የመግዛት አቅማቸዉን ለማሳደግ የስልጠናና የብድር አቅርቦት ስርዓትን በመዘርጋት ተግባራዊ ማድረግ፡፡ በእንስሳት ልማት በሙሉ ፓኬጆች የሴቶች እና ወጣቶች ተጠቃሚና ተሳታፊ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ተግባራት ይከናወናሉ፡፡ የህፃናትን አስተዳደግ ከተመጣጠነ ምግብ እጥረት የሚከሰቱ የመቀንጨርና የመቀጨጭ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት የስርዓተ- ምግብ ተደራሽነትን ማሳደግ፣

4.4 አካባቢና አየር ንብረት ለውጥ

በግብርና ሴክተር የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣምያ ስልት ውስጥ የተለዩ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስራዎችን በመደበኛ ስራዎች እቅድ ውስጥ በማካተትና በመተግበር በ2012 ዓ/ም ከተደረሰበት 36.84

ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት ጋዝ ቅናሳ በ2017 ዓ/ም 89 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶንማድረስ፡፡ ይሄንን በተቋም ደረጃ የተቀመጠውን ግብ ለማሳካት በሰብል ልማት ዘርፍ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ስራዎችን በመደበኛ የልማት እቅዶች ጋር በማካተትና በመተግባር በ2012 ዓ/ም ከተደረሰበት 7.23 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት ጋዝ ቅናሳ በ2017 ዓ/ም 25 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማድረስ፡፡

በእንሳሳት ልማት ዘርፍ ከአየር ንድረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ፣ የእንስሳትን ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ስራዎችን በመደበኛ የልማት እቅዶች ጋር በማካተትና በመተግባር በ2012 ከተደረሰበት 12.06 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት ጋዝ ቅናሳ በ2017 32.6 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማድረስ፡፡ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ዘርፍ የተጎዱ ቦታዎችን በተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ስራ በማልማትና ተመልሰው እንዲያገግሙ በማድረግ የሙቀት አማቂ ጋዝ የሚያገሉ የስነአካላዊ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎችን በመደበኛ የልማት እቅዶች ጋር በማካተትና በመተግባር በ2012 ዓ/ም ከተደረሰበት 17.55 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የሙቀት ጋዝ ቅናሳ በ2017 ዓ/ም 30ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ማድረስ፡፡

ይህንን ግብ በተቋም ደረጃ ለማሳካት በሰብልና በእንስሳት ልማት ዘርፍ በግብርና የማጣጣምያ ስልት ውስጥ የተቀመጡትን ከአይር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣሙ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በስፋት መተግበር፣ ተፋሰስን መሰረት የደረገ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን ማጠናከርና ሰፊ የእርሻ መሬት ያለባቸው ቆላማ ቦታዎች ላይ የእርሻ ስራን በመስፋፋት ደገው አከባቢ በሚገኙ የተፈጥሮ ሀብታችን ላይ የሚደርሰውን ጫና በመቀነስ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታን በተቋም ደረጃ ማሳከት ይቻለል፡፡ በተጨማሪም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተስማሙ የግብርና ስራዎች በመተግበራቸው የተቀነሰውን የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን ለማስላት የሚያስችል በሀገር አቀፍ ደረጃ የክትትል፣ ዘገባና መረጋገጥ ስረአት ይዘረጋል፡፡

4.5 ስራ ዕድል ፈጠራ

እንደ ሀገር ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳይ አንዱ የሥራ ዕድል ፈጠራ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ከ2008ዓ.ም ጀምሮ የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራን የማስተባባር ተልዕኮ ለሚኒስቴር መስራቤታችን ሰጥቶ ስራውን የሚመራበት ስትራቴጂ በመቅረጽ ወደ ስራ እንዲገባ ተደርአጎል፡፡ በገጠር ስር ዕድል ፈጠራ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል አማራጭ የስራ እድሎችን በማስፋት የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ቴክኖሎጂን በመጠቀም እና የስራ ባህልን በማሻሻል ምርት እና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የገጠር እና የከተማ ትስስርን ማጠናከር እና የገበያ አማራጮችን ማስፋት፣ አላስፈላጊ ፍልሰትን እና ስራ አጥነትን መቀነስ፣ የገጠር ኢንተርፕረንሽፕ በማጎልበት የገጠር ኢኮኖሚያዊ ትረንስፎርሜሽን ማሳለጥ፣ ምርታማ፤ውጤታማ፤ ጥራት ያለዉና ዘለቂ የሆነ የገጠር የሥራ ስምሪት መፍጠር፣ በገጠር ሥራ ፈጠራ ሴቶችንና ወጣቶችን ተጠቃሚ ማድረግ፣ የገጠር ሥራ አጥነትን በመቀነስ ለአገር ዕድገት አስተዋጽዖ ማድረግ የሚሉት ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በሚቀጥሉት 5 ዓመታት በግብርና 5 ሚሊየን ወጣቶች የስራ እድል ለመፍጠር ዒላማ ተቀምጧል፡፡

በዚህ የሥራ ዕድል ፈጠራ ተጠቃሚ የሚሆኑ ዜጐች በዋናነት ሥራ አጦች /Unemployed/ ሲሆኑ እንዲሁም ከፊል ሥራ አጥ ዜጐችንም /Underemployed/ ያካትታል፡፡ ከ15 /አሥራ አምስት/ ዓመት የእድሜ ክልል በላይ ያሉ ወንዶችና ሴቶች፣ የተማሩና ያልተማሩ፤ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ የሌላቸው፣ትምህርታቸውን ያቋረጡ፣ የቴክኒክና ሙያ ትምርትና ስልጠና፣ የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን የጨረሱ፤ ልዩ ድጋፍ የሚፈልጉ አካል ጉዳተኞችን እንዲሁም በከተሞች መስፋፋት፤ በኢንዱስትሪ ልማትና በመሳሰሉት ምክንያቶች ከመሬታቸው በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ አርሶና አርብቶ አደሮችን ያካትታል፡፡

የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ስትራቴጂክ የትኩረት መስኮች

የገጠር ስራ እድል ፈጠራ የህግ ማዕቀፎች፣ የማስፈጸም አቅምና ስርዓቶችን መፍጠር፡-

የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራን በተጠናከረ መልክ ለመምራትና ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ የህግ ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ስራ ላይ ይውላሉ፡፡ የሀገሪቱን የአሁንና የወደፊቱን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ትኩረት ያደረጉና የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራን የሚያበረታቱ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በማውጣትና የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በተዋረድ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳና በቀበሌ ተግባራዊ ይደረጋል፣ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ በተሻለና በብቃት መምራትና መተግበር የሚያስችል የማስፈጸም አቅም (መዋቅር፣ የሰው ኃይልና ሌሎች ደጋፊ አደረጃጀቶችን) በመፍጠር በሁሉም የመስተዳደር እርከን ስራ ላይ ይውላል፣ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ትግበራን ለማሳለጥ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎች፣ ማንዋልና የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

አመለካከት ክህሎትን በማሳደግ ላይ ያተኮረ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፡-

ማንኛውም ተግባር በላቀ ደረጃ ለመፈፀምና ለማስፈፀም የአቅም ግንባታ ስራ ወሳኝ ድርሻ ያለው በመሆኑ ከከፍተኛ አመራር እስከ ፈጻሚና ተጠቃሚ ድረስ ያለውን የአቅም ክፍተቶችን በመለየት አስፈላጊውን ግብዓቶች በማመቻቸት ተከታታይ የአመለካከት፣ የእውቀትና የክህሎት ማሳደጊያ ስልጠናዎች እንዲያገኙ በትኩረት ይሰራል፣ የሚከናወኑት የአቅም ግንባታ ተግባሮች ወደ ሥራ የሚሰማራውን ሥራ ፈላጊ አመለካከት በመቅረጽና ክህሎትና ዕውቀት በማሳደግ ላይ ያተኮረ መሆን ይገባዋል፡፡ የገጠር የሥራ እድል ፈጠራን ለማጎልበት ተያያዥነት ያላቸው የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፣ የስራ እድል ፈጠራ ጽንሰ-ሃሳብ ለማሳደግ ከፌደራል እስከ ቀበሌ አስተዳደር በየደረጃው የተለያዩ የግንዛቤ መፍጠሪያ የሕዝብ ንቅናቄ መድረኮች እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

ወጣቶችና ሴቶች ተኮር የሆኑ ፕሮግራሞችና ድርጊቶች፡-

ሴቶችና ወጣቶች በስራ ፈጠራ ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችል በቂ እገዛ አለመኖር ከተጠቀሱት የስራ እድል ፈጠራ ተግዳሮቶች ውስጥ አንዱና ዋነኛው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ዋነኛው የትኩረት አቅጣጫ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚሁም አንጻር ሴቶችና ወጣቶች በተሻለ መንገድ ወደ ስራ እንዲገቡ ለማስቻል በመረጃና በጥናት ተግዳሮቶቻቸዉን ማወቅና መፍታት ያስፈልጋል፡፡ ሴቶችንና ወጣቶችን በበለጠ ሊሰማሩባቸው የሚችሉ የስራ አማራጮችን መለየትና መተግበር ያስፈልጋል፡፡ የሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስራዎች የሴቶችና የወጣቶች አቅምና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ካላቸው ቁጥርና ተጠቃሚነት አንጻር እንዲሁም ለአጠቃላይ ሀገራዊ እድገት ካላቸው አስተዋጽኦ ሴትና ወጣት ተኮር የሆኑ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡

ለገጠር ስራ እድል ፈጠራ የተቀናጀ ድጋፍ መስጠት፡-

የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራን በተጠናከረ መንገድ ለመተግበር ሁለንተናዊና የተቀናጀ ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል፣ በገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሳተፉ ዜጐች በግል፣ በቡድን፣ በማህበር በኢንተርፕራይዞችና ሌሎች አደረጃጀቶችና ስራዎች ተሰማርተው ውጤታማ ለማድረግ ቀጣይነት ያላቸው ዘርፈ-ብዙ የአንድ ማእከል አገልግሎትና በከላስተር ድጋፍ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

የሥራ ዕድል አማራጮችን ማስፋት፡-

አማራጮችን በመለየት እና ለስራ እድል ፈጠራ ሊኖራቸው የሚችለውን ድርሻ እና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ትንተና በማካሄድ በውጤታማነታቸው መሰረት ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ በየአካባቢው ያሉ የስራ እድል አማራጮችን በጥልቀት በመፈተሽ የተለዩትን አማራጮች ለተሻለ ውጤታማነት ሲባል እንዲበለጽጉ በማድረግ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን እንዲሁም አዳዲስ የስራ ዕድሎችን በየጊዜው በማጥናት እና በመቀመር አዋጭ የሆኑትን ለተግባር ዝግጁ የማድረግ አሰራር በመከተል ተግባራዊ ይደረጋል፣ የተለዩት አማራጭ የስራ እድሎች የሥራ ፈላጊ ዜጎችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን እና በስራ እድል ፈጠራ ማእቀፍ ውስጥ የሚኖራቸውን ድርሻ እና ውጤታማነታቸውን በመተንተን በአዋጭነት ቅደም ተከተላቸው መሰረት ወደ ተግባር የሚገባበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፣ ከተለዩት አማራጭ የስራ እድሎች ውስጥ በጊዜያዊነት እና

በዘላቂነት የሚከናወኑትን በመለየት ሁሉም ባለድርሻ አካላት እና አጋሮች ውጤታማ በሆነ መንገድ መተግበር የሚችሉበት የአሰራር ስርዓት ይፈጠራል፣ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የስራ ስምሪት እንዲኖር እና የባለቤትነት ስሜትን ለማጎልበት ሲባል ተጠቃሚዎች በስራ እድል አማራጮች ልየታ እና ትንተና ላይ በቀጥታ እንዲሳተፉ ይደረጋል።

አረንጓዴና ተስማሚ ስራን ማጠናከርና ማስፋት፡-

የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ልማት አስተዋጽኦ ሊያበረክት በሚችል መልኩ ይተገበራል፣ በገጠር የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎች የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን የሚቋቋሙ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ከዚህም አንፃር የተፈጥሮ ሀብትን በማልማትና፣ በመንከባከብ ለስራ ዕድል ፈጠራ በዘላቂነት በመጠቀም የሥራ ፈላጊዎችን ገቢ በአስተማማኝ ሁኔታ እንዲያድግ ይደረጋል፣ በዚህ ረገድ ውጤታማ የሆኑ አገሮች ተሞክሮ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የአረንጓዴ ልማትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዙ ከአየር ንብረት ብክላ የጸዱ የፀሀይ ኃይል፣ የኃይል ቆጣቢ ምድጃዎችና ሃይል ቆጣቢ የቤት አሰራሮች እንዲውሉ ይደረጋሉ፣ ከኃይል ምንጭ ተያያዥነት ያላቸውን ስራዎች ለማስፋት የውኃ፤ መስኖና ኤሌክትሪክሲቲ ሚኒስቴር በመንቀሳቀስ ላይ ሲሆን ከስራ እድል ፈጠራ እንድቻኑ በማድግ ለስራ እድል ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንድኖራቸው ማድረግ ይቻላል፡፡ እንዲሁም አረንጓዴ ልማትን የሚያጠናክሩ የክህሎት ስልጠናና የማበረታቻ ስራዎች በማካሄድ አረንጓዴ ስራ መሰረት ያደረጉ የስራ እድሎችን ማስፋት ይቻላል፣ ደን መሰረት ያደርጉ የስራ እድሎች በአሁኑ ጊዜ የተራቆቱ መሬቶችን እንዲያገግሙ በማድረግና የተራራዎች ልማት ከአጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና የደን ልማት ጋር በማገናኘት ዛፍን መሰረት ያደረጉ የስራ እድሎች እየተፈጠሩ ይገኛሉ፡፡ የአገሪቱን መልከአ-ምድርና የተለያዩ ስነ-ምህዳሮች መኖር ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸውን የዛፍ አይነቶች በማልማት ዘላቂ የገቢ ምንጭ እንዲሆኑና ከስራ እድል ፈጠራ ጋር እንዲቃኙ በማድረግ የስራ እድል ከመፍጠር በተጓዳኝ ለአረንጓዴ ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ ይቻላል፣ በገጠር አካባቢ የሚፈጠሩ የስራ እድሎች ለስራ ፈላጊ ተስማሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እያደጉና እየተፈጠሩ ያሉትን የገጠር ከተሞች በመሰረተ ልማት (ለምሳሌ በኮብል ድንጋይ መንገድ ግንባታ ማካሄድ)፣ በፋሲሊቲ (መብራት፣ውኃ የመሳሰሉትን) እና አገልግሎት (ቴሌኮም፣የፋይናንስ አገልግሎት የመሳሰሉትን) እንዲስፋፉ በማድረግ ለስራ እድል ፈጠራ አመቺ ሁኔታን መፍጠር ይቻላል፡፡ የስራ እድል ፈጠራ ማፍለቂያ ቦታዎች ሆነው እንዲያገለግሉ የገጠር ከተሞች በእቅድ እንዲመሩና እንዲያድጉ ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በገጠር ከተሞችና አመቺ በሆኑ የገጠር አከባቢዎች ከቱሪዝምና የመዝናኛ ማእከላት እንዲስፋፉ በማድረግ የስራ እድል ፈጠራ አማራጮችን ማሰፋትና ለወጣቶች ተስማሚ አካባቢ በመፍጠር የገጠር አካባቢዎችን ሳቢ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፣ የገጠር ህብረተሰብ የአሰፋፈርና የገጠር ቤቶች አሰራር ከአጠቃላይ የሃገሪቱ እድገት አቅጣጫና ከስራ አድል ፈጠራ እንዲቃኙና የማህበረሰቡ ባህላዊ፣ ማህበራዊና ታሪካዊ እሴቶችን ሳይለቁ በጥናት ላይ በመመስረት ማሻሻልና ማሳደግ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የገጠር የአሰፋፈርና የገጠር ቤቶች አሰራር ለኢኮ-ቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ በሚችሉበት ሁኔታ መቅረጽና ማሳደግ ይቻላል፡፡

የገጠር ኢንተርፕረነርሽፕ እና የግሉ ባለሀብት፡-

የገጠር ሥራ ዕድል ፈጠራ የልማታዊ ባለሃብት መፍለቂያ በሚሆን መልኩ ይተገበራል፡፡ የገጠር ሥራ ፈላጊዎች ገና ከጅምሩ የሥራ ስምሪት ሲሰጣቸው በእድገት ሂደታቸው በአመለካከትና በተግባር ልማታዊ አስተዋጽኦ በማበርከት የመጠቀም፣ ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ ምርት የማምረት እንዲሁም ስራ ፈላጊዎች ትክክለኛውን የዕድገት አቅጣጫ ጠብቀው ሃብት የማፍራትን ስራ እንዲሰሩ በማድረግ በገጠር የግብርና ሥራዎችን በዘመናዊ መንገድ የሚያካሂዱ፣ በእሴት ሰንሰለቱ በመሳተፍ ሀብት የሚፈጥሩ በርካታ ልማታዊ ባለሃብቶች መፍጠር ይቻላል፣ ከአነስተኛ ካፒታል እና የቴክሎጂ አቅም በመነሳት በልማታዊ ጥረት እያደገ የሚሄድ የካፒታልና የቴክኖሎጂ አቅም እንዲገነባ ይደረጋል፡፡ በገጠር ያሉ ሥራ ፈላጊዎችን አመለካከት በመቅረጽ ታታሪ፣ በልማቱ ተሳታፊና በተሳተፉት ልክ የመጠቀም አስተሳሰብ ያላቸው፣ የቁጠባ ባህላቸው የዳበረና በየጊዜው እያደገ የሚሄድ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንዲኖራቸው ይደረጋል፣ አነስተኛ የገጠር ከተሞች መስፋፋት የሥራ ዕድል ለመፍጠር ጠቃሚ በመሆናቸው በከተሞቹ የሚደረገው የመሰረተ ልማት መስፋፋት ለአካባቢ የገጠር ቀበሌዎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በሚያስችል መንገድ መምራትና መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ የገጠር ኢንተርፕረነርሽፕ እና የግሉ ባለሀብትን ለመደገፍ የሚያስችሉ የፊሲካል፤ የፋይናነስ እንዲሁም አስተዳደራዊ ድጋፎች ይደረጋሉ፡፡

የገጠር ስራ እድል ፈጠራ የግብዓት አቅርቦት፡-

በገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራን ውጤታማ ለማድረግ ተዋናዮችን ባሳተፈ መልኩ አስፈላጊው የግብዓት አቅርቦት ይመቻቻል፣ የገጠር ስራ ፈላጊዎችን በዘመናዊ ግብርናና ከግብርና ውጭ ለማሰማራት የማልሚያና የመስሪያ ቦታ፤ የመነሻ ካፒታልና ቴክኖሎጂዎች ያስፈልጋል፡፡ ፣ ይህንን የማሟላት ጉዳይ ያለተዋናዮቹና ቤተሰቦቻቸው ተሳትፎ የተሟላ ውጤት ሊመጣ አይችልም፡፡ ይህ አለመሆኑ ደግሞ በገጠር የሚፈጠሩ የሥራ ዕድሎችን ስፋት ሲገድብ የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ችግሩን ለማቃለል መንግስት የሚጫወተው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ ተዋናዮቹና ቤተሰቦቻቸው የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ በሚችሉበት አግባብ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

የገጠር ስራ እድል ፈጠራ የገበያ ትስስር፡-

የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራን ከኢንዱስትሪ፣ ከግብርና እና ከአገልግሎት ልማቶች ጋር በማስተሳሰር ሀገራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር እንዲጠናከር ይደረጋል፣ በዚህም ለገጠር ስራ ፈላጊዎች የስራ አማራጮችን በማስፋትና በማመቻቸት አላስፈላጊ የሰዎች ዝውውር እንዲቀንስ ይደረጋል፣ በክልሎች መረጃ ልውውጥ በመፍጠር፤ ምርጥ ተሞክሮችን በመቀመርና በማስፋት የስራ ዕድሎችና የገበያ ትስስር የሚያጎለብቱ አሰራሮችን በመዘርጋት በክልሎች መካከል የስራ ዕድል በመፍጠር ሀገራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር እንዲጎለብት ይደረጋል፣ ኢንተርፕራይዞች የእርስ በእርስ፤ከመንግስትና ከባለሃብት ጋር የገበያ ትስስር እንዲፈጥሩ ይደረጋል፡፡

የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ጥናትና ምርምር፡-

የገጠር ስራ እድል ፈጠራ በእውቀት ላይ የተመሰረተ እና የተመረጡ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋልን መሰረት አድርጎ የሚተገበር ይሆናል፣ በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ ምርጥ ተሞክሮዎች በመለየትና በመቀመር ከሃገራዊ እና ከየአካባባዊ ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ጥቅም ላይ የሚውሉበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ በሁሉም አካባቢዎች የሚተገበሩ የገጠር የስራ እድል ፈጠራ ፕሮግራሞች ምርት እና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ እና ግብርናን በማዘመን ትራንስፎርም ማድረግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት ይተገበራሉ፣ በገጠር የሚፈጠሩትን የተለያዩ የስራ እድል አማራጮች ስራ አጥን የመሸከም አቅም ኖሯቸው ውጤታማ እንዲሆኑ እና ለተለያዩ ስራ ፈላጊ ዜጎች በፍላጎት መሰረት ምላሽ መስጠት እንዲቻል በጥናት እና ምርምር እንዲታገዙ በማድረግ የተገኘውን ምክረ-ሃሳብ መሰረት ያደረገ ድጋፍ እንዲሰጥ ይደረጋል፣ የገጠር የስራ እድል ፈጠራ እቅድ በመረጃ ላይ ተመስርቶ ተገልጋዮችን እና ተጠቃሚዎችን ባሳተፈ መልኩ የሚታቀድና ትግበራውም በዚሁ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፣ እንድሁም ጥናትን መሰረት በማድረግ የተመረጡ ልምዶች፤ ፈጠራና ቴክኖሎጂዎችን ማስፋት፡ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ በእውቀት ላይ የተመሰረተና የተመረጡ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋልን መሰረት አድርጎ የሚተገበር ይሆናል፣ በተለይም የፈጠራ ስራዎቹ የአገር ውስጥና የውጭ ምርጥ ተሞክሮዎችን መሰረት አድረገው የሚዳብሩ ናቸው፡፡ እስከ ዛሬ ከተለመደው አካሄድ በተለየ ተነሰሽነት የአሰራር መሰረታዊ ለውጥን በመተግበር በተሻሻለ ቅልጥፍናና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሥራን የመከወን ኃላፊነት ተግባራዊ ይሆናል፣ የገጠር ስራ እድል ፈጠራ በቴክኖሎጂ በታገዙ አሰራሮችና መሳሪያዎች በመታገዝ ይበልጥ ምርታማና ውጤታማ እንዲሆኑ ትኩረት ይሰጣል፣ በግብርናው ዘርፍ ዘመናዊ መሳሪያዎችንና ግብአቶችን በመጠቀም ምርታማነት የማሳደግንና ተጨማሪ እሴት በማፍራት ተፈላጊውን ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት የሚያስችሉ መሆን ይገባቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት በእውቀት ላይ የተመሰረቱ አግባብነት ያላቸውና የተመረጡ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በግብርናና ከግብርና ውጪ ያሉ የስራ እድሎችን በማዘመን በስራ ፈላጊዎች ዘንድ ተመራጭ እንዲሆኑ ይደረጋል፣ ዘመናዊ መሳሪያዎች እና ቴክኖሎጂዎች በባለሀብቱ እንዲሁም መንግሥት በሊዝ ክፍያ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርብላቸው አማራጭ መንገዶች ይመቻቻሉ፡፡

ክፍል V: የማስፈፀሚያ ስልቶች

በ አምስት ዓመቱ ዕቅድ ላይ ለማድረስ የግብርና ትራንስፎርሜሽን ስኬት እድልን ለመጨመር በአዲስ የሥራ አሰራር መንገደ መምራት አለበት፡፡ ከእነዚህ መካከል በዋናነት የክልል እና የፌደራል መንግስታት የ 5 ዓመት ርዕይ እና ፕሮግራም የጋራ ማድረግ፣ በየደረጃው በጣም አስፈላጊ የሆኑ የችሎታዎችን ፣ የዕውቀትን የአመራር ስለት ማዳበረና መለወጠ (ከአመራር እስከ ግብርና ባለሙያው)

፣ የብሔራዊ ቅንጅታዊ አሰራረ እቅድ ማጎልበትና መተግብረ ፣ የተሻሻሉ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ማፅደቅና መተግብር ፣ የተረጋገጡ የስኬተ ሞዴሎቸን መስፋፋትና ምርታማነትንና የገበያ ትስስሮች ለማሳደግ የሚረዱ አቀራረቦችን ማጎልበት(Cluster approach) ፣ የግሉ ዘርፍ በግብርናው ዘርፍ እንዲሰማሩ የመሳቢያ ስልቶቸ ማዘጋጀት (በአጠቃላይ የእሴት ሰንሰለት) ፣ ማዳበሪያ እፅዋት የማዋሃድ እና የኩራነቲን ተክል ወደ ግሉ ሴክተር መስተላልፊ እነዲሁመ በግብርና ስትራቴጂ ላይ እሴት የማይጨምሩ አገልግሎቶችን መስውገድ ::

5..1 ተቋማዊ ትራንስፎርሜሽን

ግብርና በአዋጅ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣትና በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ሊያሳካ ያቀዳቸውን ውጤቶች መፈፀም የሚችል ተቋማዊ መዋቅርንና የሰው ሃብትና ክህሎትን በፊደራልና በክልል ደረጃ መልሶ ማቋቋምትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል። ይህ ተግባር ከተለዩት የሪፎርም አጀንዳዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ወደ ተግባር ተገብቶ አደረጃጀቱና የሰው ኃይል ፍላጎቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ የምዘናና የማበረታቻ ስርዓት (ለአርሶ/አርብቶ አደሩና ለግሉ ባለሃብቱ፣ ለማህበራት፣ ለመንግስት ባለሙያዎች) ስትራቴጂ የሚነደፍ ይሆናል።

5.2. የግብርና ልማትን ዲጅታላይዝ ማድረግ

የግብርና ልማትን በቴክኖሎጅ የተደገፈ ለማድረግ የግብርና ባለድርሻ አካላት የሚጠቀሙበት የግብርና መረጃ መረብ መሰረተ ልማት (AgriNet) በመዘርጋት የግብርና ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ በመደገፍ ጥራት ያለውና ቀልጣፋ አገልግሎት ለደንበኞቹ መስጠት እንዲችል ይደረጋል፡ በሚቀጥሉት 10 ዓመታ ምክር አግልግሎት፣ የግብዓት ማሰባሰቢያና ስርጭት ክትትል ስርዓት፣ የግብርና በሽታና አደጋ ክትትልና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት ፣ የግብርና ገበያ መረጃ ስርዓት፣ የግብርና ምርቶች አመራረት ዱካ ስርዓት፣ የተቀናጀ የግብርና መረጃ ስርዓት፣ ክትትልና ግምገማ ስርዓት እና የተሞክሮና እውቅት አስተዳደር ስርዓት ትኩረት የሚደረግባቸው ይሆናሉ።

5.3. የፖሊሲ ሪፎርም አጀንዳዎች

በሀገር ደረጃ እየተሰራ ያለውን አገር በቀል የኢኮኖሚክ ፖሊሲ ማሻሻያን መሰረት በማድረግ ግብርናም በዘርፍ ደረጃ የፖሊሲ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች በጥናት በመለየት የዘርፉን ስትራቴጃዊ ማነቆዎች ሊፈቱ የሚችሉና ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ስምንት ጉዳዮች እንዲለዩ ተደርጓል። እንደተለዩት ጉዳዮች ባህሪ የአሠራር ማሻሻያ፣ የስትራቴጂ ለውጥ፣ የፖሊሲና የሕግ ለውጦችና ማሻሻያዎች በማድረግ የግብርናን ትራንስፎሜሽን ለማረጋገጥና ዘርፉ ለጥቅል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ያለውን አስተዋፆ በተገቢው መንገድ እንዲወጣ በአስር ዓመቱ መሪ ዕቅድ ማዕቀፍ ውስጥ የአጭር፣ የመካከለኛና ረጅም ጊዜ የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት የሚፈፀሙ ይሆናል። የሚከተሉት ጉዳዮች ማለትም የግብርና መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም፣ ቴክኖሎጅና ግብዓት አቅርቦት፣ ግብርና ፋይናንስና ኢንሹራንስ፤ ሀገር ውስጥና የወጪ ንግድ ግብይት፣ አዋጪ የመስኖ ልማትና ውሃ አጠቃቀም፣ አዋጪ የግብርና አገልግሎት መሰረት ልማት፣ የግል ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ፣ የግብርና ዘርፍ የማስፈፀም አቅም ማጠናከር የፖሊሲ ማሻሻያ የሚደረግባቸው ይሆናሉ።

5.4 የገጠር ከተማ ትስስር

የግብርና ልማት በማፋጠን አገራዊ ልማትን ለማረጋገጥ የገጠርና ከተማና ትስስር ወሳኝ በመሆኑ ተሟላና ዉጤታማ የግብርናና ገጠር ልማት ላይ በትኩረት ይሰራል። በመሆኑም የተገናጀ ቤተሰብ ትኮር አሰራሮች በሙከራ ደረጃ መፈተሽና በሚቀጥሉት 10 አመታት በስፋት ለመተግበር አቅጣጫ ተቀምጧል። በተለይም በሙከራ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የዘርፈ ብዙ ወረዳ ትራንስፎርሜሽን ውጥን ማስፋት ላይ በትኩረት ይሰራል። ከየዘርፈ ብዙ ወረዳ ትራንስፎርሜሽን ጽንሠ-ሃሳብ የኢትዮጵያን የዕድገት ጉዞን ዘለቄታዊና አካታች በመድረግ የተጀመረውን አገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያ በቤተሰብ ደረጃ ጉልህና ዘለቄታዊ ለውጥ ማምጣት እንዲያስችል ወረዳን ማዕከል ያደረገ የአሰራር ማሻሻያዎችን በሁሉም ዘርፍና ደረጃ ማድረግ ነው። ይህም ቤተሰቦች የተሻለ ገቢ፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ የእውቀት ደረጃና ጤናማ ቤተሰብ እንዲኗራቸው የሚያስችል እንደሚሆን ይታመናል። በተጨማሪም ለአካባቢያችው

ሁለንተናዊ ደህነነት፣ በባለቤትነትና አብሮነት እንዲተጉ የትብብር አውዶችን ያለማሰለስ የሚያመቻች፤ ለህበረተሰቡ የቀረበ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ልምምድን የሚፈጥር መርሃ ግብር ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ለዚህም የመንግስት ተቋማት፣ የህብረተሰቡ፣ የግሉ ዘርፍ እና መንግሰታዊ ያልሆኑ አጋር አካላትን ተሳትፎ ለማጥናከር የሚስችል አሰራርን በዘላቂነት ለመዘርጋት የሚያስችል ሲሆን የመንግስት ተቋማት ተናቦና ተቀራርቦ መስራትን በሁሉም ደረጃ በተለይም ለህብረተሰቡ ቅርበት ባላቸው አካላት ላይ ትኩረት አድረጎ መስራትን ቅድሚያ የሚሰጥ አሰራር ነው፡፡

በዚህ የልማት ስልት የተሻሻለ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፤ አማራጭ የስራ እድል ፈጠራ፤ የተሻሻለ መሰረታዊ የመሰረተ ልማት አቅርቦት (ውሃ፣ መንገድ፣ ኃይል አቅርቦት) ፤ የተጠናክሩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ፤ጠንካራ የማስፈፀብ አቅም ግንባታ፤ ተመጋጋቢ የገጠርና ከተማ መስተጋብርን ለመፍጠር ቁልፍ ተግባራት ናቸው፡፡ ይህ የገጠርና ከተማ መስተጋብር ምርታማነትን በማሻሻል፤ የገበያ አማራጮችን በማስፋት፤አገልግሎትን በማሳለጥ፤ አመጋገብን በማሻሻል ጤናማና ዘለቄታ ያለው እድገት አንዲመዘገብ የራሱን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህ አሰራር የህብረተሰቡን እምቅ የልማት ኃይልን እና የማደግ ፍላጎትን አዋህዶ የቤተሰብ ለውጥን በማሳለጥ፣ የቀበሌ፣ ወረዳ፣ ክልል እና አገራዊ እምረታው ለውጥን በአጭር ጊዜ በማምጣት የዘላቂ ልማት ግቦችን አካታች በሆነ መልኩ ለማሳካት የሚያስችል እንደሚሆን ተሳቢ ተደርጓል፡፡

5.5 የክትትልና ግምገማ ስርዓት

ለአንድ መ/ቤት የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግመገማ ሥርዓት መጠናከር እንዲሁም ጠንካራ የመረጃ ሥርዓት መኖር በሁሉም ደረጃ ለሚደረገው የወሳኔ አሰጣጥ ትልቅ ድጋፍ ይሰጣል ፡፡ እውነተኛ መረጃን መሰረት ያደረገና ተጠያቂነትን ሊያሰፍን የሚችል የውሳኔ አሰጣጥ እንዲኖር ያደርጋል፡፡በአፈጻጸም ሂደት የሚገኙ ልመዶችን በመቀመር ለተሻለ አፈጻጸም ያበቃል፡፡ ክፍተቶችን በመለየት ለመፍታት እድል ያመቻቸል፡፡ በመሆኑም በሚቀጥሉት ዓመታት የግብርና ሴክተር የዕቅድ ክትትልና ግምገማ እና መረጃ ሥርዓትን ለማጠናከር በቀጣይ ሊከናወኑ የሚገቡ ዋና ዋና ተግባራት

5.5.1 ተቋማዊ አደረጃጀትን ማሻሻል እና ከክልል ግብርና ቢሮዎች ጋር ያለውን የአሰራር ግንኙነት ማጠናከር

ሀ) የዕቅድ ክትትልና ግምገማ የስራ ክፍልን ማጠናከር

የእቅድ ዝግጅት ክትትልና ግምገማ የስራ ክፍል አደረጃጀት አስፈላጊ የስራ ፍሰትን ባካተተ መልኩ እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ የስራ ክፍሉ በዚህ መልክ ከተደራጀ የሚጠበቅበትን ተግባርና ኃላፊነት (mandate) በተሟላ መልኩ እንዲወጣ የሚያሥችለው የሰው ኃይል የሚሟላ ይሆናል፡

ለ) በግብርና ሚኒስቴር እና በክልል ግብርና ቢሮዎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር

የተጀመረውን የግብርና ሚኒስቴር እና ክልል ግብርና ቢሮዎች ተቀናጅተውና ተናበው የሚሰሩበትን አሰራር መመሪያ አጠናቆ እንደ የመካከለኛ ጊዜ መፍትሄ (Interim solution) የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሞ በሥራ ላይ አንዲውል ማድረግ በቀጣይ ግን የሰላም ሚኒስቴር የተለያዩ አገሮችን ልምድ መሰረት በማድረግ በማዘጋጀት ላይ ያለውን የፌደራል እና የክልል መንግስታት ግንኙነት የፖሊሲ ማዕቀፍ መሰረት በማድረግ በመመሪያው ላይ ማሻሻያ ማድረግ ፡፡

5.5.2 ውጤትን መሰረት ያደረገ የዕቅድ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ማዘጋጀት

በሚዘጋጀው የግብርና ዘርፍ ስትራቴጅክ የውጤት ማዕቀፍ መሰረት የ10 ዓመቱን መሪ ዕቅድ አፈፃፀም ለመለካት ለተለዩ የአፈፃፀም አመልቾች ማኑዋል (Indicator Handbook) እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

5.53 የግብርና ሴክተር የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ያሉበትን ችግሮች በመለየት ማጠናከር

የመረጃ አስተዳደር ስርዓት አወቃቀሩን (Data base architecture) በ10 ዓመቱ መሪ ዕቅድ ስትራቴጅክ የውጤት ማዕቀፍ እና ውጤቱን ለማሳካት በተቀረው ፕሮግራሞች መሰረት እንዲስተካከል ማድረግ፡፡

ክፍል VI: የሰው ኃይልና የፋይናንስ ፍላጎት

6.1 የሰው ኃይል ፍላጎት

በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በፌደራል ደረጃ ተጠሪ ለግብርና ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ መስሪያ መ/ቤቶችን ጨምሮ የሚያስፈልገው የሰው ሃይል በየዘርፉና በየሙያ መስኩ ተለይቶ እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

6.2 የፋይናስ ፍላጎት

በዕቅዱ ላይ የተቀመጡትን የግብርና ዘርፍ ምርትና ምርታማነት ዒላማዎች ከግብ ለማድረስ እንደየንዑስ ዘርፎቹ የተለያዩ የትግበራ መስኮች የተለዩ ሲሆን ለነዚህም የትግበራ መስኮች ማስፈፀሚያ የሚውል የገንዘብ ትመና ተሰርቷል፡፡ ይኸውም ለእያንዳንዱ የትግበራ መስክ ቁልፍ የወጪ ዓይነቶችን በመለየት የተጀመረ ሲሆን ለየንዑስ ዘርፉ እንደ አስፈላጊነቱ የወጪዎቹን ድግግሞሽ በማስላት የተሰራ ነው፡፡ በወጪ ትመናው ሂደት ላይ የዋሉ ቁልፍ የወጪ ዓይነቶችም፤ ስልጠና፣ አውደ-ጥናት፣ የአቅም ግንባታና ክትትል ስራዎች፣ በአማካሪ የሚሰሩ ስራዎች፣ የሰው ኃይል፣ የግንባታ ስራዎች፣ የቁሳቁስ ግዢ፣ የአይቲ መሰረተ-ልማቶች እንዲሁም የትግበራ መስኮቹ እንደ የባህሪያቸው የሚኖሯቸው የወጪ አይነቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት "ሌሎች" የሚል የወጪ ዓይነትን ያጠቃልላል፡፡ከነዚህ የወጪ ዓይነቶች ውስጥ በተለያዩ ንዑስ ዘርፎች ውስጥ የመሰረተ ልማት ግንባታ ስራዎችና የቁሳቁሶች ግዢ ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ፣ ከዚሁ ስራ ጎን ለጎንም ለየተግባራቱና የወጪ ዓይነቶች ዋነኛ የገንዘብ ምንጮችን የማመላከት ስራ ተሰርቷል፡፡ እነዚህም ዋነኛ የገንዘብ ምንጮች መንግስት፣ የግሉ ዘርፍ፣ እንዲሁም አጋር አካላት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በቀጣይ አምስት አመታት የሚኖረው የተሰላ የካፒታል ወጪም ወደ 1 ትሪሊየን ብር የሚጠጋ ሲሆን ከዚህም ውስጥ በመንግስት በጀት የሚሸፈነው ወጪ ብር 673 ቢሊየን (ከአጠቃላይ ወጪ በመቶኛ 36%) ከተለያዩ አጋር አካላት በእርዳታና በብድር መልኩ ደግሞ ወደ 130 ቢሊየን ብር ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል (ከአጠቃላይ ወጪ በመቶኛ 13%)፤የአጋር አካላት ሚና ክፍተኛ ይሆናል ተብሎ የሚጠበቀው በተለይም የግሉ ዘርፍ ፍላጎት ላያሳይባቸው በሚችልባቸው ንዑስ ዘርፎች እና በመንግስት መደበኛ ወጪም ሊሸፈኑ በማይችሉ ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ የትግበራ መስኮች ላይ ነው፡፡ ለአብነት ያህልም በተፈጥሮ ሃብት ዙሪያ የሚደረጉ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች (የመስኖ፣ የተፋሰስ ልማትና ከዘላቂ የሬንጅላንድ (ሰፊ የግጦሽ መሬት) ልማት ጋር የሚገናኙ ግንባታዎች ዋነኞቹ ናቸው፡፡

ለዚህ እቅድ መሳካት የግሉ ዘርፍም ያላሰለሰ ሚና እንደሚጫወት ይጠበቃል፤ በ5 አመቱ ከሚያስፈልገው አጠቃላይ ወጪም ወደ 202 ቢሊየን ብር (ከአጠቃላይ ወጪ በመቶኛ 20%) በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ የሚሟላ ይሆናል፡፡ ሆኖም በዘርፉ ያለውን ዝቅተኛ የሆነውን የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳድግ አሁንም ከፍተኛ የሆነ ስራ መስራት የሚጠይቅ ጉዳይ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል፡፡

7.1 የግብርና ዘርፍ የ5 ዓመት የመካከለኛ ጊዜ ዕቅድ የውጤት ማዕቀፍ

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
መኸር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የሰፋፊ እርሻ አንቨስትመንት							
ጤፍ	በሺህ ሄክታር	3,108.77	3,113.89	3,119.19	3,124.70	3,130.44	3,136.44
ገብስ	በሺህ ሄክታር	954.19	954.33	954.50	954.72	954.97	955.27
ስንዴ	በሺህ ሄክታር	1,895.34	1,905.83	1,917.18	1,929.45	1,942.73	1,957.11
በቆሎ	በሺህ ሄክታር	2,362.02	2,385.28	2,410.59	2,438.23	2,468.56	2,501.95
ሰሊጥ	በሺህ ሄክታር	649.83	685.98	724.25	764.77	807.67	853.10
ቲማቲም	በሺህ ሄክታር	7.64	7.88	8.13	8.39	8.66	8.94
ሽንኩርት	በሺህ ሄክታር	37.12	37.98	38.86	39.77	40.70	41.65
አቮካዶ	በሺህ ሄክታር	21.09	23.51	26.20	29.22	32.58	36.34
ሙዝ	በሺህ ሄክታር	68.96	70.93	72.96	75.06	77.24	79.48
ማንጎ	በሺህ ሄክታር	18.97	21.41	24.18	27.30	30.83	34.82
ቡና	ሄ/ር	863.66	888.91	915.08	942.23	970.39	999.62

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
መሸር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት (ጠቅላላ ምርት)							
ጤፍ	ሚሊየን ኩንታል	57.5	59.8	62.3	64.9	67.5	70.3
ገብስ	ሚሊየን ኩንታል	23.9	24.5	25.2	25.9	26.6	27.3
ስንዴ	ሚሊየን ኩንታል	56.7	59.9	63.3	67.0	70.9	75.0
በቆሎ	ሚሊየን ኩንታል	100.0	106.9	114.4	122.5	131.3	140.8
ሰሊጥ	ሚሊየን ኩንታል	4.9	5.3	5.8	6.4	7.0	7.6
ቲማቲም	ሚሊየን ኩንታል	1.7	1.9	2.1	2.3	2.5	2.7
ሽንኩርት	ሚሊየን ኩንታል	6.6	6.9	7.3	7.7	8.1	8.6
አቮካዶ	ሚሊየን ኩንታል	1.1	1.3	1.6	2.0	2.4	3.0
ሙዝ	ሚሊየን ኩንታል	5.6	6.5	7.7	9.0	10.6	12.5
ማንጎ	ሚሊየን ኩንታል	1.3	1.5	1.7	1.9	2.2	2.5
ቡና	ሚሊየን ኩንታል	5.6	6.2	6.7	7.4	8.1	8.9

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
መኸር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የሰፋፊ እርሻ							
ጤፍ	ኩንታል በሄክታር	18.5	19.2	20.0	20.8	21.6	22.4
ገብስ	ኩንታል በሄክታር	25.0	25.7	26.4	27.1	27.8	28.6
ስንዴ	ኩንታል በሄክታር	29.9	31.4	33.0	34.7	36.5	38.3
በቆሎ	ኩንታል በሄክታር	42.4	44.8	47.5	50.2	53.2	56.3
ሰሊጥ	ኩንታል በሄክታር	7.5	7.8	8.1	8.3	8.6	9.0
ቲማቲም	ኩንታል በሄክታር	224.4	238.6	253.6	269.7	286.7	304.8
ሽንኩርት	ኩንታል በሄክታር	177.0	182.5	188.2	194.0	200.1	206.4
አቮካዶ	ኩንታል በሄክታር	50.4	55.5	61.1	67.2	73.9	81.3
ሙዝ	ኩንታል በሄክታር	80.8	92.3	105.4	120.4	137.5	157.0
ማንጎ	ኩንታል በሄክታር	67.7	68.8	69.8	70.9	72.1	73.2
ቡና	ኩንታል በሄክታር	6.5	6.9	7.4	7.8	8.3	8.9

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
የመኽር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች (የለማ መሬት)							
ጤፍ	በሺህ ሄክታር	3101.17	3,105.1	3,109.1	3,113.1	3,117.1	3,121.1
ገብስ	በሺህ ሄክታር	950.74	950.5	950.3	950.1	949.9	949.7
ስንዴ	በሺህ ሄክታር	1789.31	1,790.3	1,791.3	1,792.3	1,793.3	1,794.3
በቆሎ	በሺህ ሄክታር	2271.44	2,281.2	2,291.1	2,301.0	2,310.9	2,320.9
ሰሊጥ	በሺህ ሄክታር	375.12	391.9	409.4	427.8	446.9	466.9
ቲማቲም	በሺህ ሄክታር	5.98	6.2	6.3	6.5	6.7	6.9
ሽንኩርት	በሺህ ሄክታር	36.28	37.1	37.9	38.7	39.5	40.4
አቮካዶ	በሺህ ሄክታር	20.88	23.2	25.9	28.8	32.0	35.6
ሙዝ	በሺህ ሄክታር	66.84	68.6	70.4	72.3	74.2	76.2
ማንጎ	በሺህ ሄክታር	16.34	18.5	20.9	23.7	26.8	30.3
ቡና	በሺህ ሄክታር	756.85	774.8	793.2	812.0	831.3	851.0

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
የመኽር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች (ምርት)							
ጤፍ	በሚልየን ኩንታል	57.36	59.69	62.12	64.65	67.28	70.02
ገብስ	በሚልየን ኩንታል	23.78	24.42	25.07	25.74	26.43	27.14
ስንዴ	በሚልየን ኩንታል	53.15	55.90	58.78	61.81	65.00	68.36
በቆሎ	በሚልየን ኩንታል	96.28	102.35	108.79	115.65	122.93	130.67
ሰሊጥ	በሚልየን ኩንታል	2.63	2.86	3.11	3.39	3.69	4.02
ቲማቲም	በሚልየን ኩንታል	1.18	1.29	1.40	1.53	1.67	1.83
ሽንኩርት	በሚልየን ኩንታል	6.35	6.67	7.02	7.38	7.76	8.17
አቮካዶ	በሚልየን ኩንታል	1.04	1.28	1.57	1.92	2.35	2.88
ሙዝ	በሚልየን ኩንታል	5.39	6.32	7.42	8.70	10.20	11.97
ማንጎ	በሚልየን ኩንታል	1.05	1.21	1.40	1.62	1.86	2.15
ቡና	በሚልየን ኩንታል	4.83	5.26	5.74	6.26	6.83	7.45

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
የመኽር የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች (ምርታማነት)							
ጤፍ	ኩንታል በሄክታር	18.50	19.23	19.98	20.77	21.59	22.44
ገብስ	ኩንታል በሄክታር	25.00	25.68	26.37	27.08	27.82	28.57
ስንዴ	ኩንታል በሄክታር	29.71	31.23	32.82	34.49	36.25	38.10
በቆሎ	ኩንታል በሄክታር	42.39	44.87	47.49	50.26	53.20	56.30
ሰሊጥ	ኩንታል በሄክታር	7.00	7.29	7.60	7.92	8.25	8.60
ቲማቲም	ኩንታል በሄክታር	197.13	208.99	221.55	234.87	249.00	263.97
ሽንኩርት	ኩንታል በሄክታር	174.94	180.07	185.34	190.78	196.37	202.12
አቮካዶ	ኩንታል በሄክታር	50.05	55.08	60.61	66.70	73.40	80.78
ሙዝ	ኩንታል በሄክታር	80.64	92.15	105.29	120.32	137.49	157.11
ማንጎ	ኩንታል በሄክታር	64.36	65.61	66.90	68.20	69.53	70.89
ቡና	ኩንታል በሄክታር	6.38	6.79	7.24	7.71	8.22	8.76

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
የመኽር ሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት (የለማ መሬት)							
ጤፍ	በሺህ ሄክታር	7.6	8.7	10.1	11.6	13.3	15.3
ገብስ	በሺህ ሄክታር	3.4	3.8	4.2	4.6	5.0	5.5
ስንዴ	በሺህ ሄክታር	106.0	115.5	125.9	137.1	149.4	162.8
በቆሎ	በሺህ ሄክታር	90.6	104.0	119.5	137.2	157.6	181.0
ሰሊጥ	በሺህ ሄክታር	274.7	294.1	314.8	337.0	360.8	386.2
ቲማቲም	በሺህ ሄክታር	1.7	1.7	1.8	1.9	1.9	2.0
ሽንኩርት	በሺህ ሄክታር	0.8	0.9	1.0	1.1	1.2	1.2
አቮካዶ	በሺህ ሄክታር	0.2	0.3	0.3	0.4	0.6	0.7
ሙዝ	በሺህ ሄክታር	2.1	2.3	2.5	2.8	3.0	3.3
ማንጎ	በሺህ ሄክታር	2.6	2.9	3.2	3.6	4.0	4.5
ቡና	ሄ/ር	106.8	114.1	121.9	130.2	139.1	148.6

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
የየመኽር ሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት (ምርት)							
ጤፍ	በሺህ ኩንታል	115.87	141.46	172.71	210.85	257.42	314.27
ገብስ	በሺህ ኩንታል	99.33	112.48	127.38	144.24	163.34	184.97
ስንዴ	በሺህ ኩንታል	3,525.34	4,002.59	4,544.44	5,159.65	5,858.15	6,651.20
በቆሎ	በሺህ ኩንታል	3,749.14	4,577.53	5,588.96	6,823.87	8,331.64	10,172.56
ሰሊጥ	በሺህ ኩንታል	2,252.63	2,476.82	2,723.31	2,994.34	3,292.34	3,620.00
ቲማቲም	በሺህ ኩንታል	536.08	594.52	659.33	731.21	810.91	899.31
ሽንኩርት	በሺህ ኩንታል	226.25	257.56	293.20	333.77	379.96	432.55
አቮካዶ	በሺህ ኩንታል	18.68	24.68	32.60	43.05	56.87	75.12
ሙዝ	በሺህ ኩንታል	179.79	221.74	273.49	337.31	416.02	513.10
ማንጎ	በሺህ ኩንታል	232.91	259.21	288.49	321.07	357.33	397.68
ቡና	በሺህ ኩንታል	793.56	889.77	997.63	1,118.57	1,254.17	1,406.21

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ				
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017
የየመኽር ሰፋፊ እርሻ ኢንቨስትመንት (ምርታማነት)							
ጤፍ	ኩንታል በሄክታር	15.24	16.17	17.15	18.20	19.31	20.48
ገብስ	ኩንታል በሄክታር	28.81	29.68	30.58	31.51	32.47	33.45
ስንዴ	ኩንታል በሄክታር	33.25	34.65	36.10	37.62	39.20	40.85
በቆሎ	ኩንታል በሄክታር	41.39	44.00	46.77	49.72	52.86	56.19
ሰሊጥ	ኩንታል በሄክታር	8.20	8.42	8.65	8.88	9.13	9.37
ቲማቲም	ኩንታል በሄክታር	322.52	330.24	338.13	346.22	354.50	362.97
ሽንኩርት	ኩንታል በሄክታር	267.40	268.63	269.87	271.11	272.36	273.61
አቮካዶ	ኩንታል በሄክታር	85.92	89.97	94.22	98.66	103.31	108.18
ሙዝ	ኩንታል በሄክታር	84.76	95.72	108.09	122.07	137.85	155.67
ማንጎ	ኩንታል በሄክታር	88.75	88.79	88.82	88.85	88.88	88.91
ቡና	ኩንታል በሄክታር	7.43	7.80	8.18	8.59	9.02	9.46

		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017	2018	2019	2020	2021	2022
በልግ												
የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች (የለማ መሬት)												
ጤፍ	በሺህ ሄክታር	161.21	168.44	175.99	183.89	192.14	200.75	209.76	219.17	229.00	239.27	250.00
ገብስ	በሺህ ሄክታር	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92	202.92
ስንዴ	በሺህ ሄክታር	108.85	109.45	110.06	110.66	111.27	111.88	112.50	113.12	113.74	114.37	115.00
በቆሎ	በሺህ ሄክታር	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28	799.28
ቲማቲም	በሺህ ሄክታር	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69	4.69
ሽንኩርት	በሺህ ሄክታር	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60	47.60
የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች (ምርት)												
ጤፍ	በሚልየን ኩንታል	2.98	3.24	3.52	3.82	4.15	4.50	4.89	5.31	5.77	6.26	6.80
ገብስ	በሚልየን ኩንታል	5.08	5.22	5.36	5.50	5.65	5.81	5.96	6.12	6.29	6.46	6.64
ስንዴ	በሚልየን ኩንታል	3.26	3.44	3.63	3.84	4.05	4.28	4.53	4.78	5.05	5.34	5.64
በቆሎ	በሚልየን ኩንታል	33.85	35.84	37.95	40.18	42.54	45.04	47.69	50.49	53.46	56.60	59.93
ቲማቲም	በሚልየን ኩንታል	0.92	0.98	1.04	1.10	1.17	1.24	1.31	1.39	1.47	1.56	1.66
ሽንኩርት	በሚልየን ኩንታል	8.33	8.57	8.82	9.08	9.35	9.62	9.90	10.19	10.49	10.80	11.12
የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮች (ምርታማነት)												
ጤፍ	ኩንታል በሄክታር	18.49	19.22	19.97	20.76	21.58	22.43	23.32	24.23	25.19	26.18	27.22
	ኩንታል በሄክታር	25.03	25.70	26.40	27.12	27.85	28.61	29.38	30.18	31.00	31.84	32.70
	ኩንታል በሄክታር	29.90	31.42	33.01	34.68	36.44	38.29		40.23	42.27	44.41	46.6 49.02

											6	
	ኩንታል በሄክታር	42.35	44.84	47.48	50.27	53.22	56.35	59.66	63.17	66.89	70.82	74.98
	ኩንታል በሄክታር	197.13	208.99	221.55	234.87	249.00	263.97	279.84	296.67	314.51	333.42	353.47
	ኩንታል በሄክታር	174.94	180.07	185.34	190.78	196.37	202.12	208.05	214.14	220.42	226.88	233.53

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ									
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017	2018	2019	2020	2021	2022
መስኖ												
የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የኮሜርሺያል (የለማ መሬት)												
በቆሎ	በሺህ ሄክታር	140.6	148.9	157.8	167.1	177	187.5	198.6	210.3	222.8	236.0	250
ስንዴ	በሺህ ሄክታር	20	175	280	448	470	493	500	500	500	500	500
ቲማቲም	በሺህ ሄክታር	25.4	25.6	25.8	26.0	26.2	26.4	27.5	28.7	31.0	35.7	45.45
ሽንኩርት	በሺህ ሄክታር	62.2	62.5	62.8	63.2	63.6	64.3	65.5	67.8	72.71	83.6	108.2
የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የኮሜርሺያል (ምርት)												
በቆሎ	በሚልየን ኩንታል	5.96	6.68	7.49	8.40	9.42	10.57	11.85	13.29	14.90	16.71	18.75
ስንዴ	በሚልየን ኩንታል	0.60	0.87	1.26	1.82	2.64	3.83	5.55	8.05	11.66	16.91	24.51
ቲማቲም	በሚልየን ኩንታል	5	5	6	7	8	10	13	18	27	47	88
ሽንኩርት	በሚልየን ኩንታል	10.8	11.7	12.7	13.9	15.4	17.6	21.3	28.1	42.4	73.7	144.4
የአነስተኛ ይዞታ አርሶ አደሮችና የኮሜርሺያል (ምርታማነት)												
በቆሎ	ኩንታል በሄክታር	40.2	42.4	44.8	47.3	50.0	52.8	55.7	58.9	62.2	65.6	69.3
ስንዴ	ኩንታል በሄክታር	28.0	29.7	31.6	33.5	35.6	37.8	40.1	42.6	45.2	48.0	51.0
ቲማቲም	ኩንታል በሄክታር	188.9	201.0	213.8	227.4	241.9	257.3	273.7	291.2	309.7	329.5	350.5
ሽንኩርት	ኩንታል በሄክታር	173.7	178.0	182.4	186.9	191.5	196.3	201.1	206.1	211.2	216.4	221.8

የዘርፍ ቁልፍ ውጤት መስኮችና አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚደረስበት ትንበያ									
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017	2018	2019	2020	2021	2022
ጥራቱ ጤንነቱና ደህንነቱ የተጠበቀ ለገበያ የቀረበ ምርት												
ጤፍ	በሚልየን ኩንታል	15.1	17.4	20.0	22.9	26.3	30.1	34.4	39.4	45.1	51.5	58.9
ገብስ	በሚልየን ኩንታል	2.0	2.1	2.2	2.4	2.6	2.8	3.0	3.2	3.4	3.6	3.8
ስንዴ	በሚልየን ኩንታል	9.2	11.2	13.6	16.6	20.2	24.5	29.7	35.9	43.5	52.6	63.6
በቆሎ	በሚልየን ኩንታል	10.0	13.2	17.2	22.2	28.6	36.7	46.9	59.8	76.0	96.5	122.4
ሰሊጥ	በሚልየን ኩንታል	2.4	2.8	3.1	3.5	3.9	4.4	4.9	5.4	6.0	6.7	7.4
ቲማቲም	በሚልየን ኩንታል	0.3	0.3	0.3	0.4	0.5	0.6	0.7	0.8	0.9	1.0	1.2
ሽንኩርት	በሚልየን ኩንታል	1.3	1.4	1.5	1.7	1.9	2.0	2.2	2.4	2.6	2.9	3.1
አቮካዶ	በሚልየን ኩንታል	0.3	0.4	0.5	0.7	0.9	1.2	1.6	2.1	2.8	3.6	4.8
ሙዝ	በሚልየን ኩንታል	1.8	2.2	2.7	3.4	4.1	5.0	6.1	7.4	9.0	10.9	13.2
ማንጎ	በሚልየን ኩንታል	0.5	0.5	0.6	0.8	0.9	1.1	1.3	1.5	1.7	2.0	2.4

የዘርፍ/ክልል/ቁልፍ ጤና ማዕከላት ኤመልካቾች አመልካቾች	መለኪያ	መነሻ ዓመት	የሚጠበቅበት ትንበያ								
		2012 አፈጻጸም	2013	2014	2015	2016	2017	2018	2019	2020	2021	2022
ከ ድህረ ምርት ብክነት ውጪ የተገኘ ምርት												
ጤፍ	በሚልየን ኩንታል	47.7	50.6	53.7	57.0	60.3	63.9	67.6	71.4	75.4	79.7	84.1
ገብስ	በሚልየን ኩንታል	15.6	16.2	16.7	17.3	17.8	18.4	19.0	19.6	20.2	20.8	21.4
ስንዴ	በሚልየን ኩንታል	44.6	48.1	51.9	55.9	60.1	64.5	69.2	74.1	79.4	84.9	90.8
በቆሎ	በሚልየን ኩንታል	81.0	89.6	98.3	106.9	115.7	124.8	134.0	143.6	153.6	163.9	174.8
ሰሊጥ	በሚልየን ኩንታል	3.9	4.3	4.8	5.3	5.8	6.3	6.9	7.6	8.3	9.0	9.8
ቲማቲም	በሚልየን ኩንታል	1.0	1.1	1.2	1.3	1.4	1.6	1.7	1.9	2.0	2.2	2.4
